


ዳዊት ሰለሞን

ዛዓር

መተላለፉ የቀረችለት፣ ኅጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው።

ምስጋና

ለ፦ ከዘለዓለም በፊት፣ ከአባቱ ብቻ፤ አሁን በዘመን ፍጻሜ፣ ከሴት ከቅድስት ድንግል ማርያም፣ ከእናቱ ብቻ ተወልዶ፤ ጽድቁ የመርገም ጨርቅ የሆነበትን የአዳም ዘር በከበረ ደሙ ፈሳሽነት ከበረዶ ይልቅ ላነጻ፣ ሰው ለሆነ የባህሪ አምላክ መድኀኒዓለም።

እናትም፣ እህትም፣ ከለላም ለሆንሽኝ **ጥላዬ**፤ ለእሳቱ እድሜ ማብረጃ ማለፊያ፣ ግብረገብን ላስታጠቀኝ የስብዕና ማማ **ከፍያለው**፤ ለዚህ ሁሉ መፍለቂያ የትውልድ ጅረት ምንጭ **ሙሉነሽ**።

በ146ኛው እዮቤልዩ በአርባ ሁለተኛው የዘመን ሱባኤ በስድስተኛው ወር ተጻፈ።

zoarethiopia@gmail.com

የሽፋን ንድፍ፦ ሚኪያስ ዮሴፍ

‘’እኔ የምሠራውን ሥርዐት
ለማፍረስ ስለ ሠሩት ጎጢያት ሁሉ፤

እንደ ተለየኋቸው ልጆቻቸው
ይሰሙ ዘንድ በመጽሃፍ ጻፈው”

የአዲሱ ትውልድ፣
ቅዱሱ አብዮት ድምጽ።

"በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?"

ለንደን
ከቀኑ 9:30

፡፡ ዶክተር ዛሪየስ! እንዳትተኩስ

በርናባሶች ነን።

፡፡ Jesus! ምን ትሰራላችሁ እዚህ?

፡፡ ከ ጀነራል ሠሀረ አስቸኳይ ትዕዛዝ

ተሰጥቶን ነው።

፡፡ ኤም.አይ.6ዎች እየተከታተሉኝ እንደሆነ እየታወቀ እንዴት እንደዚህ ይደረጋል? ይህ እብደት ነው! ህቡዕ ድርጅታችንን እና ስንት ነገራችንን መሥዋዕት ያደረግንለትን ዓላማ ገደል መክተት ነው። ትንሽ ፍንጭ ከሰጣችኋቸውና እናንተንም መከታታል ከጀመሩ…

፡፡ በጥንቃቄ ስለሆነ የተከተልንህ ሊያውቁ አይችሉም።

፡፡ ኤፍሮን ይሄ ወኔሽ ሁሌም ያስደምመኛል። ለማንኛውም እዚህ ፓርኪንግ ግራውንድ ውስጥ ካሜራዎች ስላሉ ከእኔ ጋር መታየት የለባችሁም።

፡፡ የካሜራዎቹ security features elementary ስለሆኑ በቀላሉ ሰብረናቸዋል አያሳስብህ። Ml6 ብቻ ሳይሆኑ የሞሳድ እና የሲ.አይ.ኤ አባሎችም እያሳደዱህ እንደሆነ ስለተደረሰበት፤ ለንደንን ለቀህ ወደ ዋናው ማዘዣ መብረር አለብህ አሁኑኑ!

፡፡ አብዳችኋል እንዴ እንኳን ከሀገር መውጣት ቦታ መቀየር እንኳን አዳጋች ነው።

፡፡ እሱን ከደቂቃዎች በኋላ ለራስህ ትመልሳለህ። አስፈላጊዎቹን ሰነዶች ይዘሀል?

፡፡ ሁሉንም በሚገባ አዘጋጅቻለሁ ምን እንደሚከሰት ስለማላውቅ፤ መኪና ውስጥ በሳምሶናይት አድርጌ አስቀምጫቸዋለሁ።

፡፡ ሶዲያር! መኪናው ውስጥ ያለውን ሳምሶናይት ይዘህ ሂድ።

፡፡ አንቺስ?

፡፡ አንድ ላይ መሆን የለብንም፤ ሰነዶቹን ወደ ሀገር ቤት ላካቸው በአስቸኳይ። መሳሪያ ለማለሰቦች

መሸጥ እንዲቆም መንግሥትን ለመጠየቅ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡት ሰልፈኞች፤ የቻሉትንም ያህል ሰው ከመንገድም ለመሰብሰብ መንገዱን ስላራቁት፤ ኖርዝ ባንክ ወደ ሚገኘው ዌስት ሚኒስተር ለመድረስ በዚህ ነው የሚያልፉት። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እዚህ ይደርሳሉ፤ ከእነሱ ጋር ተቀላቅለን እንወጣለን።

።። ጥሩ አሁኑኑ እልከዋለሁ። Best of luck.

ሶዲያር ሰነዶቹን ይዞ ከመሬት ስር መኪና ማቆሚያው በወጣ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የሰልፈኞቹ ድምጽ መሰማት ጀመረ። ዛሪየስ ሳምሶናይቱ ህልውናችን ነው ሲላት፤ አታስብ ሶዲያርን እንደራሴ አምነዋለሁ አለችው። ጥሩ፤ ድምጽ ይሰማሻል? እየመጡ ነው አላት፤ የተወሰኑት ይለፉን መሀላቸው ገብተን እስከ ኦልድ ኩዊን ካፌ አብረናቸው እንሄዳለን።

የእጅ ስልኳን አውጥታ መጀመሪያ ላይ ወዳለው ቁጥር ደወለች ስልኩ እንደተነሣም በርናባስ ዜሮ ይሰማል? ስትል ጠየቀች፤ ቀጥይ በርናባስ አምስት! የሚል ድምጽ ተሰማ፤ ወደ ዌስት ሚኒስተር ፓላስ መገንጠያ መንገድ ዳር ያለው ኦልድ ኩዊን ስትሪት ካፌ ፊት መኪና ይዘጋጅ፤ በሩ ሳይቆለፍ፣ ቁልፉም ውስጥ ይቀመጥ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ስለምንደርስ በፍጥነት! ብላ ትዕዛዝ ሰጠች። አሁኑኑ ይዘጋጃል።

ዛሪየስ የሱፉን ኮት ማውለቅ ጀመረ፤ አፍጥጣ ስታየው አይዞሽ ቅድም ያዩኝ ሰዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት አስቤ ነው ቢላት፣ ለለውጥ ብለህ እንደውም ይበልጥ ትኩረት ትስባለህ። በዚህ ቅዝቃዜ በሱፍ ኮት ብቻ መንቀሳቀስህ ሳያንስ ጭራሽ በሸሚዝ ልትሆን? ይልቅ እንካ ይህን

ደርብ ከውስጥ የለበስኩት ወፍራም ስለሆነ እኔንም አይበርደኝም ትኩረትም አንስብም ብላ የደረበችውን ካፖርት አውልቃ ሰጠችው፤ የወንድ ይመስላል ብሎ ተቀበላት።

ተከተለኝ እንቀላቀላቸው በፍጹም ወደ ኋላ እየዞርክ እንዳታይ፤ ወደ ግራና ቀኝም አንገትህን በተደጋጋሚ እንዳታዞር ትኩረት ከሚስቡ እንቅስቃሴዎች መሀል ዋነኛው እሱ ነው፤ ዐይንህን ብቻ ተጠቀም በተቻለህ መጠን ቀጥ ብለህ ለመራመድ ሞክር። ኤፍሮን! ነርቨስ ሆነሻል ልበል? ለመረጋጋት ሞክሪ ለጀማሪ እንኳን የማይመከር ምክር ነው እየመከርሽኝ ያለሽው።

እጃቸውን እያነሱ መፈክሮችን ከሰልፈኛው ጋር እያስተጋቡ መጓዝ ጀመሩ። መኪናውን እንዳየችው ፈጠን በል ብላ እጁን ስትይዘው፣ ሳታስበው አጠገቧ የነበረች አንዲት ነጭ ሴት አፍንጫዋን በከርሄ መታቻት ተንገዳግዳ ከኋላዋ የነበረው ወጣት ላይ ተለጠፈች። ይህን ሲመለከቱ በስፍራው የነበሩ ሰልፈኞች በመደናበር መጮህ ጀመሩ፤ የሰልፉ አንድ አካል እንጂ ሌላ አልመሰለም፤ አንድ ረጅም ግዙፍ ጥቁር ወጣት የዛሪየስን አንገት አንቆ ጥግ ይዛ ወደ ቆመች ጥቁር ማርቸዲስ ይጎትተው ጀመር።

ኤፍሮን ከአፍንጫዋ የሚፈሰው ደም የለበሰችውን ነጭ ሹራብ እያቀለመው ቢሆንም እሱን ለማስተዋል ጊዜ አልነበራትም፤ እየተንገዳገደች ወደ ዛሪየስ ለመሮጥ ስትሞክር አሁንም ያቺው ሴት አንገቷን ልትመታት እግሯን ስታነሳ ዝቅ ብላ ሸወደቻትና መሬት እረግጦ የነበረውን እግሯን መታችባት ወደ ላይ ተነስታ በጀርባዋ ስትወድቅ የአስፓልቱ ጠርዝ አናቷን ስላገኛት ወዲያው ደም ከጭንቅላቷ መፍሰስ እንደ ጀመረ ጥቂት በኃይል ተንፈራገጠችና ጸጥ አለች።

በሰልፈኞችም መሀል ጩኸት ተጀመረ ተተረማመሱም። ኤፍሮን ሰልፈኞችን እየገፈተረች ወደ ዳር ወጥታ ስትመለከት፤ ዛሪየስን በግድ ጎትቶ መኪና ውስጥ ሊያስገባው ሲታገል ዐይታ ከጀርባዋ ፒስትል መሻርጣ put your hand on the air! ስትል፤ ከኋላዋ ሌላ ቀጠን ያለ ነጭ መጥቶ የቀኝ እግር ሽኗን መታት፤ ሽብረከ ብላ በቀኝ እግሯ ጉልበት አስፋልቱ ላይ ተንበረከከች ከጀርባዋ መጥቶ እጇን ይዞ ፒስትሉን ሊያስለቅቃት ሲታገል አንገቱን በእጆቿ መሀል አስገብታ ቁጢጥ እንደማለት ብላ አንገቱን ወደ ትከሻዋ ዝቅ በማድረግ ተሸክማ በጀርባው ጥላው ሆዱን በኃይል ረገጠችውና ዛሪየስን ሲታገለው የነበረውን ግዙፍ ሰው በፒስትሉ አናቱን ነረተችው። ተዝለፍልፎ ሲወድቅ፤ ተከተለኝ ብላው ወደ መኪናው እየሮጡ ገቡ።

ተሸከርካሪውንም አስነስታ ወደ ኩዊን ኤልዛቤት ሁለተኛ ሴንተር የምታስገባዋን ጠባብ አስፋልት ይዛ ቀጥታ በስቶሪስ ጌት በመውረድ ወደ ዋናው መንገድ በመውጣ ወደ ጆንስ ጎዳና ከነፈች።

።፡ ተጎድተሻል?

።፡ አፍንጫዬን ትንሽ፤ የካፖርቴ ኪስ ውስጥ ናፕኪን አለ ስጠኝ!

።፡ የትአለ ካፖርትሽ?

ያለማቋረጥ ስቃ ለብሰኸዋል እኮ አለችው። በእራሱ እንደማፈር ብሎ ወደ ኪሱ እጆቹን በመስደድ አቀበላት። አይዞህ ለመረጋጋት ሞክር ብላ ትከሻውን ቸብ ቸብ አደረገችው።

ተመልከቻቸው እነዚህን ሕንጻዎች፤ አብዛኛዎቹ የተሰሩት በአሁኑ ትውልድ አይደለም። ያለፉት አባቶቻቸው ናቸው ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ስንቅ አስቀምጠውላቸው ያለፉት። እነዚኛዎቹም ሳይኑቋቸው አክብረው ይዘዋቸው ደግሞ ለሚመጣው ትውልድ ያስተላልፉታል። እዚሁ ከተማ ውስጥ ተወልዶ እንዳደገ አንድ ወጣት ከተማዋ የእኔ እንደሆነች ግን አንድም ቀን ተሰምቶኝ አያውቅም። ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ፤ እነሱ በአባቶቻቸው ስፍራ ያሉ ባለ መብቶች፤ እኔ ባይተዋር የሆንኩ ሲመስለኝ ኖሬአለሁ። ስለ እነዚኛዎቹ ሳይሆን ስለኔዎቹ ቀደምቶች ሳጠና ከርሜአልሁ። ለዚህም አመቺ ትመስለኛለች እቺ ሀገር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ጥንታዊ መዛግብት ተሰርቀው ወደ እዚህ የመጡት ሳይበልጡ የሚቀሩ አይመስለኝም። በእኛ ዕውቀት ይህን ሁሉ ያከናወኑ ይመስለኛል። እንደዚያ ካልሆነ ለምን ለይተው ኢትዮጵያን፣ እውቀቷን ሲያሳድዱ ኖሩ? ይህን ከአንድ ኢትዮጵያዊ ጋር መወያየት ብትጀምሪ ይስቅብሻል። እንደ ሞኝ ይቆጥርሻል። እኛ ያልተገለጸልን ወይም እዲገለጽልን ያልፈለግነው እነሱ በሚገባ የተረዱት እውነት አለ።

የሩቁን ትተሽ የቅርቡን ተመልከቺ፤ አውሮፓውያን መች ነው ወደ ኢትዮጵያ በይፋ መምጣት የጀመሩት? በ15ኛው ክፍለ ዘመን፤ ለንደንን ጨምሮ ደግሞ በዚህ መልኩ መገንባት የጀመሩት ከሮማን ጊዜ ቢባልም ዘመናዊውን ስትመለከቺ 16ኛው ክፍለ ዘመን ሆኖ ታገኚዋለሽ። እሱን እንተወውና፤ በዚህ እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ብዙ እቆጫለሁ። ቀድመን ነቅተን በምን ምክንያት እንዳንቀላፋን ወደ ኋላም እንደ ተመለስን አስባለሁ፤ የትንቢት መፈጸሚያዎች በመሆናችን አዝናለሁ። ሌሎች ካልነበረ ከዜሮ ሀገረ መንግሥት አቋቁመው ሀገር ገንብተው፣ ሕዝብ አስተዳድረው፣

አምርተው፣ መግበው፣ አትርፈው ለሌሎች ሲረዱ፤ እኛ ትላንት ስንረዳቸው በነበርናቸው ሀገራት እጅ መውደቃችን ያስቆጨኛል። ይሄን የሚያይ ወጣት ሀገሩን ቢንቅ አይፈረድበትም። ግን በሥራ እንጂ በጥላቻ አልያም በንቀት ሀገር አትቀየርም።

አብዛኛው የዓለም ወጣት በሚናፍቃት የብዙ ነገሮች መገኛ በሆነችው በእዝች ለንደን ውስጥ የክሪኬት፣ የባስኬት እንዲሁም የእግር ኳስ ጨዋታዎችን ስመለከትና የተለያዩ ነገሮችን ሳደርግ ነው የኖርኩት። በእዚህ ፈንጠዝያ ውስጥ ግን እኔነቴ ይርበኝ ነበር። ታሪኬ፣ ባህሌ፣ ሕዝቦቼ ይናፍቁኝ ነበር። ኢትዮጵያ ታሪክ ብቻ ሆና እንዳትቀር፣ የዘመናዊውን ዓለም ሥርዐት ተጽዕኖ ተቋቁማ፣ ለወጣቶቿ ብሩህ ተስፋን የምትሰጥ፣ ለልባቸው ጮራ የምትፈነጥቅ፤ ሰላምና እድገትን የተላበሰች ሀገር እንድትሆን፤ ህልሜን ተጋርቶ በአንድ ልብ ለክብር፣ ለሥልጣን እና ለዝና ሳይሆን ከልብ በመነጨ በጎ ህሊና፣ በቅንነት የተሻለ ሀገር እንድንገነባ በጋራ አብሮኝ የሚቆም እፈልግ ነበር። የዚህ ድርጅት አባል ከሆንኩ በኋላ የተከፈለው መሰዋዕትነት ተከፍሎ፤ ለኢትዮጵያ ሊወጣ ያለውን ፀሃይ አሻግሬ ስመለከት፤ ያ የብርሃን ጸዳል ልቤን ወተት እንደ ጠገቦች ጊደር ያስቦርቃታል።

አንተ የተማርከበት ዩኒቨርሲቲ የተማሩ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥሩ የሚባል የትምህርት ጊዜ ያሳልፋል? ጠየቀች። ጥሩን define አድርጊልኝ? ጥሩ ልኬቱ በacadamic achievement ነው? በsocial impact ነው? ወይስ በpersonal fulfillment ነው? አየሽ ጥሩ እንደ ሰው ይለያያል አላት። ማሰላሰል ጀመረ።

ለ35 ደቂቃዎች ተጉዘው አንድ ግዙፍ በር ጋር ሲደርሱ መስኮቱን ዝቅ አድርጋ ለካሜራው ፊቷን ስታሳየው በሩ

ተከፍቶ ወደ ውስጥ ገቡ። ዛሪየስ ይሄን ስፍራ ከዚ በፊት አይቶት አያውቅም፤ የሚያያቸው አባላት የታጠቁት መሳሪያ፣ ጊቢ ውስጥ የቆሙት መኪኖች ሞዴላቸው፣ ሰፊው አስፓልት፣ ቤት ውስጥ ያሉት ቴክኖሎጂዎች ሁሉ አዲስ ስለሆኑበት፤ ግር ብሎታል። ዘወር ብሎ እስካሁን ነፍሴንም ሕይወቴንም የሰጠሁለት ድርጅት ሌላ እኔ የማላውቀው ምን አለው? አላት። ሁሉም የተደረገው ለኛው ደህንነት ሲባል ነው ሁሉንም በጊዜው ታየዋለህ ዶክተር! ሥዓቱም አሁን ደርሷል አለችውና እንዲቀመጥ ጋብዛው፤ እንደ ምትመለስ በመንገር ከእንግዳ መቀበያው ወጣ።

ዋሽንግተን

ከቀኑ 9:30

ዳውን ታውን በባሩድ ሽታ ታፍናለች እዚህም እዚያም የሚሰማው የጥይት ድምጽ የሰዎች ጩኸት የመስታወቶች መርገፍና የቁሳቁሶች መሰባበር አከባቢውን የለየለት የጦርነት ቀጠና አስመስሎታል።

ከደቂቃዎች በፊት...

ሰባት የአሜሪካን ልዩ ጥብቅ ወታደራዊ ሚስጥር አዋቂ የሆኑ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰሮች፣ ሦስት ጉምቱ ዶክተሮች፣ ከሦስት የጦር ጄነራሎች ጋር ከአሜሪካን

ኮብልለው ለመውጣት New York Ave NW በሚገኘው Sfoglina Downtown በተሰኘ የጣልያን ሬስቶራንት ውስጥ ተቀጣጥረው ተገናኝተዋል።

ዐሥራ ሦስቱም ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ በሲ.አይ.ኤ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሲሆን በሌሎችም የስለላ ድርጅቶች ዐይን እና ጆሮ የሚጣልባቸው ግለሰቦች ናቸው። ይህም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ወሳኝ ተልዕኮ የሚመራው ደግሞ በጄነራል ሠሀረ ነው።

ሰፊው ጠረጴዛም የከበቡትን ሰዎች ቁጥር ያህል የመመገቢያ ሰሀኖች ባይገኙበትም፤ ሁሉም ግን በጄነራል ሂሶጵ ምርጫ Barbera D'alba የተሰኘ የ1996 የጣልያን ወይን ተቀድቶላቸዋል። እኔ ግን ምን እያሰባችሁ እንደሆነ አልገለጽልህ ብሎኛል። መግቢያ መውጫችን እንዴት እንደሚጠበቅ ከኛው በላይ ማን ይረዳናል? ይህን እያወቅን እንዴት ሁላችንም በአንድ ቦታ እንድንሰበሰብ ይወሰናል ያውም ባልጠፋ ስፍራ መህል ከተማ ላይ በማለት ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ ሁሉንም በጥያቄ ዐይን ተመለከታቸው።

ወንድሞቼ! አሉ ጄነራል ሠሀረ ሀገራችን ከቀን ወደቀን ከድንግዝግዝ ወደ ድቅድቅ ጨለማ፤ ከሀዘን ወደ ለቅሶ፣ ከህመም ወደ መመንመን፣ ከመታሰር ወደ መጎሳቆል፣ ከረሀብ ወደ ጠኔ፣ እልቂት፣ መጨራረስ፣ እርስ በእርስ እልቂት እየገባች፤ መሪ እንደሌላት መርከብ ወዲ ወዲያ እያለች በወጀብ እየተመታች እየሰጠመች ትገኛለች። ሕዝባችንም እንዲሁ። አንገቷን ደፍታ በጠላቶቿ ፊት እንድትንበረከክ ተደርጋለች። ቀና ማለት አለባት። የሚከፈለው ሁሉ ተከፍሎ።

ስልኮቻችሁም ሆኑ ኮምፒውተሮቻችሁ በአጠቃላይ ዲጂታል ዲቫይሶቻችሁ በሙሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ አይደሉም። እኛንም ጨምሮ፤ ስለዚህ በአካል ነው መገናኘት ያለብን። ስውር ስፍራም ጠፍቶ ወይም እዚህ በአንድነት መገኘታችን አደጋ ሳይኖረው ቀርቶም አይደለም። የታቀደበት ነው።

ወንድሞቼ! ይቺ ቀን የአሜሪካን አፈር የምትረግጡባት የመጨረሻዋ ቀን ነች! ሲሉ ሁሉም በግራ መጋባት መተያየት ጀመሩ። አዎ አሁኑኑ ይህቺን ሀገር ለቀን እንወጣለን። አሉ ደግመው። ጄነራል!

አሉ ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ፤ ጄነራሉም ቀጠሉ በተለያየ ምክንያት ቤተሰቦቻችሁን ቀድመን ወደ ኢትዮጵያ እንድንልክ ተደርጓል፤ አንድ አንድ ጠቃሚ ዶክመንቶችም እንደዚያው ገንዘብን ጨምሮ፤ ፕሮፌሰር ሞክሳ ቀድመህ ወደ ሀገር ቤት እንድትልከው ያልኩህን ቺፕ እንዴት አደረከው? ፕሮፌሰር ሞክሳ ቀበል አድርጎ፤ ወንድሜ ምንም አያሳስብህ አሁን በባለ ቤቴት አይከል እጅ ይገኛል። በምንም አይነት ሁኔታ ከእጁ እንዳይወጣ አስጠንቅቄ ነው የላኩላት።

መልካም ብለው ቀጠሉ፤ እናንተንም ቢሆን መንግሥት በጉጉት እየጠበቃችሁ ነው ያለው፤ ቀድሞ በገባለት ፕሮፖዛል መሰረት የሥራ ድርሻቸሁንም ሆነ የምትመደቡበት የሥልጣን እርከን እረቂቅ ተዘጋጅቶ የእናንተን መምጣ በመጠባበቅ ላይ ነው። አሁን ምንም ወደ ኋላ የሚያስብልም ሆነ ጊዜ የሚያስጠይቅ ጉዳይ የለም ሲሉ አቋረጧቸውና ያልተላኩ እኛ ጋር የቀሩ ብዙ ዶክመንቶች ሌሎችም ነገሮች አሉ፤ በዚያ ላይ የዩናይትድ ስቴትስ ሆምላንድ ሴኪውሪቲ አባላት በጥብቅ

እየተከታተሉን ነው በማለት ሲጠይቋቸው፤ አስጨርሰኝ እኛ እዚህ መሰብሰባችን አደጋ እንዳለው እንደምናውቅ እና እንደተዘጋጀንበት በመጀመሪያ ላሳውቃቹ። በመቀጠል የእኛ እዚህ መሰብሰብ ዐይኖችን በሙሉ ወደዚህ ይሰበስባል፤ በዚያም ምክንያት ቤሮዎቻችሁ እና መኖርያ ቤቶቻችሁ ጥበቃቸው ይላላል። አሁን በዚህ ሰዓት በኛ ሰዎች የየአንድ አንዳቹ ቤቶችም ቤሮዎችም እየተፈተሹ ነው። ጠቃሚ የሚመስሉም የማይመስሉም ነገሮችን ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ እየታሸጉ ነው። ስለዚህ የሚያሳስብ ምንም ነገር የለም። በዚህ ላይ በምታውቁአቸው ጥብቅ ሚስጥራት ምክንያት እንዲሁ ሀገር ለቃችሁ እንድትወጡ ሚፈቅዱላቸሁ ይመስላችኋል? በማለት ሲናገሩ ሁሉም በአግራሞት ይመለከቷቸው ነበር።

ይህን ተናግረው እንደጨረሱ የእጅ ስልካቸው ጠራ አነሱና ዝም አሉ፤ ሸማ አንድ ይሰማል? አለ ከመስመሩ ባሻገር ፈጠን ብለው ነጠላ ዜሮ ቀጥል አሉ ተጠናቋል። እደግመዋለው ተልኮ ተጠናቋል አለ። ወደ ቀጣዩ ተልዕኮ በአስቸኳይ ይገባ። ጨርሻለሁ አሉ ጂነራሉ። ወንድሞቼ! ሁሉም ነገር ተጠናቋል። በሰው ድካም ተዘልሎ መቀመጥ አይፈቀድም! ሁላችንም ደክመን፣ ሞተን የምናቆማት ሀገር እንጂ ሌሎች በደከሙበት በድካማቸው ገብተን የምንወርሳት ሀገር አትኖረንም! አሁን የምላችሁን በደንብ ስሙኝ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁነን የወዳጆች መሰባሰብ ብቻ እንደሆነ አስቡና እየተሳሳቅን እንወጣለን። ከጀርባችን በሚገኘው ኮንራድ ሆቴል ውስጥ ባለው መኪና ማቆሚያ በየተራ እየገባችሁ መኪናችሁን እዛው እያቆማቹ እዛው ቁሞ በሚጠብቃቹ ቫን ውስጥ ትገባላችሁ፤ ከዚህ ከወጣን አለቀ ቀሪውን ለእኛ ተውት። ዐይናችሁን ጨፍናቹ ስትከፍቱት እራሳችሁን ሀገር ቤት ታገኙታላችሁ። ግልጽ ነኝ? አሉ። ሁሉም በመስማማት ራሳቸውን ነቀነቁ።

በዚያው ቅስፈት ተኩስ ተከፈተ ጀነራል ሠሀረ እና ጀነራል ሂሶጵ ብድግ ብለው ከጫፍና ጫፍ ጠረጴዛውን ይዘው ሲገለብጡት በመመገቢያው ጠረጴዛ ላይ የነበሩት ብርጭቆዎች ሰሀኖችና መጠጦች በሙሉ ወደ ወለሉ ተዘረሩ፤ ጩኸት ሆነ። ሁሉም በጠረጴዛው ውስጥ እንዲመሸጉ ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ ጀነራል ሠሀረ በግራ በኩል ባለው ግርግዳ ተለጥፈው ከጎን ሽጉጠውት የነበረውን ሁል ጊዜም ይዘውት የሚዞሩትን Beretta 92 የተባለ የጣሊያን ስሪት ፒስትል መዝርጠው በጥይት ፍርክስክሱ በወጣው መስታወት ወደ ውጭ ተኩሱ ወደ ሚመጣበት አቅጣጫ መተኮስ ጀመሩ። ጀነራል ሂሶጵም በቀኝ ያለውን ግርግዳ ተለጥፎ በሌላኛው የሬስቶራንቱ መስታወት በኩል መተኮስ ጀመረ። ጀነራል ሠሀረም ወደ ኋላ ዘወር ብለው ባላቅ በፍጥነት በጀርባ በር ይዘሀቸው ውጣ መዳረሻችን ጋር እንገናኝ አሉ። ጀነራል ባላቅም ዝቅ ብላቹ ተከተሉኝ በማለት የተኩሱን እሩምታ በመሸሽ ቀድሟቸው ወደ ኪችን ገባ ተከትለውት ገቡ በጓሮ በር ለመውጣት፤ ሌላኛው ጀነራል ግን እነ ሠሀረን ለማገዝ እዛው ቀሩ።

ጀነራል ባላቅ በኋለኛው በር ይዞዋቸው እንደወጣ ሁለት የታጠቁ ሰዎች እየተኮሱ ወደ እነሱ ይመጡ ጀመር። ያልጠበቁት በመሆኑ ተተረማመሱ፤ ባላቅም ሽፋን ያዙ ሽፋን ፈልጉ እያለ ትዕዛዝ ሰጠ። የአስፓልቱን ጠርዝ ይዘው ወደ ቆሙት መኪኖች እየሮጡ ሄደው ተመሸጉ፤ ባላቅም አንደኛውን በመኪናው ጎማ ስር በደረቱ ተኝቶ ጉልበቱ ላይ አነጣጥሮ ተኮሰበት። እየጮኸ ሲንበረከክ ደረቱን ደገመው እዚያው በተንበረከከበት በአፍጥሙ ተደፋ። ሁለተኛውም የጓደኛውን መመታት ተመልክቶ በእልህ እየተኮሰ ወደእነሱ መጣ፤ ባላቅ ተነስቶ

ወደ ሌላኛው መኪና ተሻገረና፣ ሲተኩስ የነበረው ሰው ቀለሀው በማለቁ በእልህ ባዶውን ጥይት ቃታ ደጋግሞ በመሳብ ላይ ሳለ፤ ጂነራል ጂነራል ሲለው ፊቱን ሲያዞር ለካ ሲወጡ በተተኮሰ ጥይት ፕሮፌሰ ሞከሳ ደረታቸውን ተመተው ወድቀዋል ሁሉም በድንጋጤ ፈዘዙ፤ ልባቸው አዘነች። በዚህ መሀል የወደቀውን ጓደኛውን ጥይት አንስቶ በድጋሚ ወደ እነሱ መተኮስ ሲጀምር፤ በእልህ ፍንጥር ብሎ በመቆም ግንባሩ ላይ ተኮሰበት።

በሉ እንፍጠን ወንድሞች! ምንም ማድረግ አንችልም አሁን ወንድማችንን ለማዳን እንደምታዩት ሠዓቱ ረፍዷል። ሌሎቻችንም መትረፍችን አንድ ነገር ነው። ሲል ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ ግንባራቸውን አጨማደው አንዳች ለመናገር አፋቸውን ከፈቱና መልሰው ዝም ሲሉ፤ ባላቅ የተናገርኩት እንዳልጣመህ አያለሁ አሁን ለሱ ጊዜው አይደለም፤ ይልቅ ሌሎች መጥተው ሌላ ጥፋት ሳይደርስ መሄድ ይኖርብናል በማለት ከተደረደሩት መኪኖች የ2015 ሞዴል የሆነች የጉዞ ቮልስዋገን አይቶ ወደ መኪናው በመሄድ መስታወቱን በክርኑ ሰበረው፤ እጆቹን አስገብቶ በመሪው ዘንግ ጀርባ እጁን በመክተት የሞተር ማስነሻ ቁልፉን ሸበዎች በጥሶ ሁለቱንም ሲያፋት,ጋቸው ሞተሩ ስለ ተነሣ፣ ፈጠን ብላቹ ግቡና ትከተሉኛላቹ የቀራቹት የፊት ለፊተኛው መኪና ውስጥ እንግባ ፍጠኑ ጊዜ የለንም በማለት ከቮልሷ የተረፉት እንዲከተሉት በመንገር ከፊት ወዳለው መኪና ተጠግቶ በተመሳሳይ መንገድ መስኮቱን በመስበር ወደ ውስጥ ገብቶ ሞተሩን አስነሳውና፤ የኋላውን ኮፈን በመክፈት ወርዶ የፕሮፌሰሩን ትኩስ አስክሬን ኮፈን ውስጥ እንድናስገባው አንዳቹ ውረዱና ታግዙኛላቹ ዶክተር! አንተ ብትሆን የተሻለ ነው ሲል፤ ዶክተር አጵሎስ ኮፈን ውስጥ? በማለት ወረደ፤ አስክሬኑንም በማስገባት ላይ ሳሉ እንደ ገና ከኋላ ተኩስ ተከፈተባቸው። ዶክተሩም ጎንበስ ብሎ ወደ መኪናው ገባ ባላቅም ጎንበስ እንዳለ የአጸፋ ዞሮ ሳያይ እጁን ወደ ኋላ ዘርግቶ እየተኮሰ ኮፈኑን

ለመዝጋት መታ አድርጎት ወደ መኪናው በመግባት ወደ መዳረሻቸው ከነፉ።

⁘⁘⁘

፧ My vsegda prikroem tebya, general

፧ Spasibo za podderzhki!

፧ Ne vopros.

፧ Uvidimsya!

በማለት ምስጋና አቅርበው ሩሲያዊ ወዳጆቻቸውን ተለዩ።

፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧፧

መኪና ማቆሚያው ስፍራ እንደ ደረሱ ጄነራል ሂሶጵ የሚያየውን ማመን አቃተው። ለደቂቃዎች ያህል ፈዞ ቆመ። ድንገትም በመሪር ሀዘን መንሰቅሰቅ ጀመረ። ሁሉም በቆሙበት በሀዘን አንገታቸውን አቀረቀሩ።

እንባ ባፈነው ድምጽ ጓደኛዬ፣ አብሮ አደጌ፣ የልቤ ሰው! ይቅርብኝ እያልከኝ፤ በውጭ ሆኜ የምችለውን ልርዳቹ፤ ምንም ሳልሰስት ባለኝ ሁሉ በእውቀቴም፣ በጉልበቴም ልርዳቹ እያልከኝ፤ ልጆቼ እኔን የሚፈልጉበት ሰዓት ስለሆነ ከአጠገባቸው ልሁን እኮ ብለኸኛል፤ ወንድሜ አሁን የታለ ካሉኝ የት ልበላቸው? አምጣው ሲሉኝ ምን ልስጣቸው? ባለቤትህንስ እንዴት ላርዳት? ሰዎች! ታውቆት ነበረኮ ለዚ ነው ይቅርብኝ ሲለኝ የነበረው። እልፍ ሞት አይቻለሁ። ብዙ ነፍስም በእጇ ጠፍቷል። ግን ይህን ከማይ ብሞት ይሻለኝ ነበር። ይሄን ማየት ያቆሰላል ልብ ያደማል። ወንድሜን ሚስጥረኛዬን አብሮ አደጌን በላሁት። እያለ አስክሬኑ ላይ ተደፍቶ ለረጅም ደቂቃ አለቀሰ። አብረውትም እንባቸውን አፈሰሱ። ጄነራል ሠሀረም መጥተው ይበቃል፤ ይበቃል ተነስ ሚያሳድደን

አንድ ግለሰብ አይደለም! ይህን ያህል ጊዜ ልንገዛላቸው አይገባም። መቀጠል ይኖርብናል ወንድሞች እንቀጥል ብለው ወደ ቫኗ አመሩ።

ቴል-አቪቭ

ከቀኑ 9:27

ፕሮፌሰር! ፕሮፌሰር እያለች ደጋግማ ብትጣራም መልስ ሳትሰጣት ከምታስተምርበት ክፍል ወጥታ፣ በጠባቧ መተላለፊያ ወደ ቢሮዋ በፍጥነት በመራመድ ላይ ሳለች፤ አጠገቧ ደርሳ ፕሮፌሰር ስትላት ድንገት ደንገጥ እንደ ማለት ብላ ቆመች ተማሪዋም "is there everything fine professor? you were watching your wrist watch the entire time. ስትላት ለመረጋጋት እየሞከረች everything is perfectly fine! አለቻትና የሷን መልስ ሳትጠብቅ I'm in a hurry. I will get back to you later! በማለት ሳታስጨርሳት በድጋሚ የእጅ ሰዓቷን እየተመለከተች፤ ቢሮ ገብታ ዶክመንቶቿን ሰብስባ በሳምሶናይት ውስጥ በመጨመር፤ ሳምሶናይቱን ይዛ ቢሮውን እንኳን ሳትቆልፍ፤ በፍጥነት እየተራመደች ቆማ ስትጠብቃት የነበረች የ2024 ሞዴል 3 ቴስላ ውስጥ ገብታ እንደተቀመጠች ወደ ሾፌሩ እየተመለከተች ሁሉንም ዶክሜንቶች ይጥለሁ መሄድ እንችላለን አለችው። መኪናዋ ከ Antin Square በ250 ሜትር

ርቀት ላይ ከሚገኘው ዋናው ጊቢ ወጥተው በ26 ኪሎ ሜትር ርቆ በ Golan street ወደ ሚገኘው Airport city መከነፍ ጀመረች።

የሞሳድ አባላት የሆኑ ሦስት ኤጀንቶች ወደ ፕሮፌሰሯ ማስተማርያ ክፍል ሲሄዱ ተማሪዎቹን ከመማሪያ ክፍል ውጭ በማየታቸው በፍጥነት ወደ ክፍሉ ሲገቡ አጧት፤ ለምን ሰዓት ሳይደርስ እንደወጡ አጠገባቸው ያገኙትን ተማሪ ሲጠይቁት ጨርሰው ስለወጡ ነው ብሎ መለሰላቸው እነሱም በፍጥነት ወደቢሮ ሄደው ሲያንኳኩ ባለመከፈቱ አንደኛው እጀታውን ሳብ ሲያደርገው በሩ ተከፈተ ውስጥ ግን ማንም የለም ቢሮውም ምስቅልቅል ብሎ በማየቱ አንደኛው she is not here. Find her now; we can't lose her ብሎዋቸው ተከታትለው ወጡ። ቴስላዋም Airport city እንደደረሰች ወደ ተዘጋጀው Citation Mustang የግል አውሮፕላን በማምራት ተሳፍረው ያለ አንዳች ኮሽታ ወደ ለንደን ከተማ አመሩ።

ለንደን

ምሽት 1:20

ሶዲያር ወደ ኤፍሮን ክፍል በመሄድ አንድ ጊዜ ብቻ አንኳኩቶ ፍቃድ ሳይጠብቅ በሩን ከፍቶ ገባ ኤፍሮንም ከመታጠቢያ ቤት ወጥታ አንገቷን ዘንበል አድርጋ ጸጉሯን በፎጣ በማድረቅ ላይ ነበረች። እ..እ… ፕሮፌሰሯ

ደርሰዋል ፕሮፌሰር ቤርሳቤህ እዚህ ናቸው አላት የምጡን። ቀጠን ባለ ድምጽ መጣሁ አለችው። ክፍሏን ለቆ ወጣ።

ከደቂቃዎች በኋላም ወደ እንግዳ መቀበያው ብቅ አለች፤ ሁለቱ የግላቸውን ወግ ይዘው በማየቷ፣ በማቋረጧ ይቅርታ ጠይቃ፣ አሁን ወደ ሀገር ቤት የመግቢያው ትክክለኛ ሰዓት ነው። እንደ ደረሰኝ መረጃ ከሆነ ፕሮፌሰር ቤርሳቤህ ያለምንም ችግር ነው እዚህ የደረስሺው፤ ይህም ጊዜ አጠቃቀም ላይ መልካም ልምድ እንዳለሽ ያሳያል። ወጣትነትሽም ሳይጠቅምሽ አልቀረም። ዋሽንግተን የነበረው ህዋሳችን ግን መጠነኛ የሆነ እክል ደርሶበታል። በዚህም ፕሮፌሰር ሞክሳን አጥተናቸዋል። ሁለቱም በሀዘን አንገታቸውን ደፉ። ፕሮፌሰር ቤርሳቤህ ቀና ብላ ቺፑስ? በማለት ጠየቀች፤ ለሱ ጄነራል ሂሶጵ አለ። አሁን እኔ በማወራበት ሰዓት ግን በሩሲያ ኢጋሮቻችን ድጋፍ ሁሉም ወደ እናት ሀገር ኢትዮጵያ በመብረር ላይ ናቸው።

ከነበራችሁበት በቀጥታ ወደ ሀገር ቤት እንዳትበሩ እና ከዚህ እንዲሆን ያደረግነው እናንተን ለማንገላታት ሳይሆን ለደህንነት ትሬስም ላለመደረግ እዚህ ስለ ሚመቸን ነው የራሳችን ሰዎች ስላሉን። አይዞአቹ የሚያሳዝን ቢሆንም የግድ ወደ ፊት መቀጠል ይኖርብናል። ሁላችንም በአንድነት ለቆምንለት ዓላማ መሳካት ሕይወታችንን ድረስ መስጠት እንደ ሚኖርብን ከጅምሩም የአመንበት መሆኑ ይታወስ። በእኛ ጽኑ ተጋድሎ የታፈረች ኢትዮጵያን ለመገንባት ነው ይህ ሁሉ መሥዋዕትነት የሚከፈለው። ይህን ስትናገር ሶዲያር በሩ አጠገብ ቁሞ ዐይን ዐይኗን ይመለከታት ነበር። ዘወር ስትል ዐይን ለዐይን ተጋጠሙ ወዲያው ዐይኗን መለሰች። ተከተሉኝ፤ ወደ ሀገር ቤት እንበራለን።

‘’አንባቢው ያስተውል!

አፉ ከቅቤ ይልቅ ለዘበ፥ በልቡ ግን ሰልፍ ነበረ”

ኢትዮጵያ

አዲስ አበባ፤ ስውር ስፍራ

ኤፍሮን ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ በመግባት ላይ ሳለች፤ ጀነራል ሠሀረን በማየቷ ባለችበት ቀጥ ብላ በመቆም የወታደር ሰላምታ ሰጠቻቸው ከሞቀ ፈገግታ ጋር፤ እሳቸውም ጭንቅላታቸውን በትንሹ ዝቅ አድርገው ሰላምታ ከሰጧት በኋላ፤ ሄዳ ጥምጥም አለችባቸውና ጋሼ የሆነውን ስሰማ ከአቅማቹ በላይ የሆነባቹ መስሎኝ ሰግቼ ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን እርዳታ ባይደርስላቹ የከፋ ሊሆን ይችል ነበር። እንዴት ያለ እረዳት ትንቀሳቀሳላቹ? ያውም እንደዛ ተሰብስባቹ፤ በዚያ ላይ በሀገራቸው ሄዳቹ፤ አፍንጫቸው ስር? ስትራቴጂ ነው። በእርግጥ ሪስክ

ነበረው ግን ኢትዮጵያዊ ነን እኮ ድፍረት እና ኩራታችንን ወንዝና ድንበር አያግደውም ብለው ጉንጯን በሁለት ጣታቸው ይዘው ወዘወዙት። በዚያ መሀል ሶስቱ ጀነራሎች ደረሱ ለነሱም ተመሳሳይ ሰላምታ ሰጠታቸው፤

ወንድሞቼ ኤፍሮን እጅግ ልቤ ሀሴት የሚያደርግባት እንደ ልጄ የማያት ናት። ሥራዋን ጥንቅቅ አድርጋ የምትከውን ስብስብ ያለች አስተዋይና ብልህ ወጣት ነች። ውሳኔ ለመወሰን የማትቸኩል፤ ጊዜ ወስዳ ለወሰነችው ውሳኔ ህይወቷን የምትሰጥ ጽኑ ናት። በሉ እንግባ አሉ ጀነራል ሠሀረ፤ ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ በቅደም ተከተል ገቡ። በአዳራሽ ውስጥም የነበሩት ተሰብሳቢዎች ተነስተው በመቆም፤ በጋለ ፈገግታና ሞቅ ባለ ጭብጨባ ተቀበሏቸው። በየወንበራቸው እንደ ተሰየሙም በእጃቸው የቁጭ በሉ ምልክት ከማመስገን ጋር አሳዩአቸው።

ወንድሞቼና እህቶቼ ለሚቀጥለው እና ትልቁ ተልዕኮአችን የመጀመሪያውን እና ትልቁን ተልዕኮ በድል ተወጥተነዋል። ይሁንና ወንድማችንን ደግሞም አጥተንበታል፤ የታፈረችዋን እና ታላቋን ኢትዮጵያ ከአውሬው እጅ እንዲሁ ፈልቅቀን ማውጣት አንችልም። ብዙ መሥዋዕትነት ይጠይቃል፤ ከዚህም በኋላ ከዚህም የሚበልጥ መሰዋዕትነት ልንከፍል እንችላለን ደግሞም እንከፍላለን ለዚህም ዝግጁ ነን። እያንዳንዳችን ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ በአንድነት የቆምን በሙሉ እያንዳንዷ ቀንና ሰዓት የመጨረሻችን ልትሆን እንደምትችል እያሰብን መኖርን መልመድ አለብን። ይህንም የምናደርገው ፍርሀት ውስጣችን ለማሳደር ሳይሆን፤ የቆምንለትን ዓላማ ታላቅነት ለማስታወስ መሆን አለበት።

ይህም ሲሆን ለምንወዳቸው በሙሉ ያልተገደበና ለነገ ተብሎ የማይሰሰት ፍቅር እንድንሰጣቸው ያደርገናል። ምክንያቱም ስለ አሁን እንጂ ስለ ነገና በኋላ እርግጠኞች ስለማንሆን ማለት ነው። ሳናመሰግነው ቀኑ ማለፍ የሌለበት አንድ ሰው አለ። ምናልባትም ያ ቀን እያየነው የልባችንን ሳንናገርበት ከእጃችን አምልጦንም ይሆናል። እየወደድናቸው ያልነገርናቸው፣ ውለታቸውን በትከሻችን ተሸክመን እየዞርን ያላመሰገንናቸው፤ በልባችን ስለ በደላቸው ይቅር ያልናቸው ነገር ግን የጸጸት ሸክም ያሸከምናቸው የሉም? ይህ ሁሉ የሚመጣው ነገን በባዶ ተስፋ ከማድረግ ነው፤ ነገ ግን ከማናችንም ጋር ሊመጣልን አልያም ሊመጣብን አልተማማለም።

እጃችን ላይ ያለን ዛሬ ነው ያውም አሁን። ወንድሞቼና እህቶቼ፤ በዚህ ሰዓት አጠገባቹ ከተቀመጠው ወንድማቹ ወይም እህታቹ ጋር ደግማቹ ላትተያዩ ትችላላቹ ወይ እናንተ መሰዋዕትነት ከፍላቹ ወይም እነሱ ከፍለው። ፕሮፌሰሩም ሲሰዉ እንደዚያ ነው የሆነው፤ እኔንም ከአሁን ወዲህ ላታዩኝ ትችሉ ይሆናል። በየትኛውም ሰዓትና ቦታ ልሰዋ እችላለሁ ግን ህቡዕ ድርጅታችን ይቀጥላል። ከዓላማችን የሚያሰናክለን አንዳችም ምድራዊ ሀይል አይኖርም ሰማያዊም ቢሆን አይኖርም፤ ምክንያቱም ይህ እንዲሆን የአምላካችንም ፈቃድ ስለሆነ የአባቶቻችን አምላክ ደግሞ አያሳፍረንም።

እስራኤልን ከፈርዖን እጅ ለመንጠቅ ሙሴን የላከ፤ ኢትዮጵያን ከጣልያን ለማስጣል ሚኒሊክን ያስነሳ አባት፤ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማወጅ እኛን አስነስቷል ሲሉ፤ አዳራሹ በፉጨት፤ በጭብጨባ፤ በእልልታ ተናጋ። እስኪበርድ ጠብቀውም፤ ወንድሞቼ በሁሉም መልክ ብቁ ነን በወታደራዊ ሳይንስና አመራር፤ በፖለቲካል ሳይንስ፤ በፋይናንስ፤ በህክምና፤

በጆርናሊዝም፤ በአርትም፤ በምህንድስናው ዘርፍም እንዲሁ።

ይህ ቡድን እንዲሁ በስሜት የተሰበሰበ ሳይሆን፤ ጥልቅ የሀገር ፍቅር ያላቸውና ባንዳነትን አጥብቀው የሚጸየፉ ከዘር ይልቅ ሀገርን የሚያስቀድሙ፤ በዘራቸው የማያፍሩም የማይኮሩም ግን ስለዚህ በማሰብ ጊዜ የማያጠፉ፣ በመተዋወቅ እና በዝምድና የማይቧደኑ፣ በዕውቀትና ችሎታ ብቻ የሚያምኑ፣ አድርባይነትን የሚጸየፉ፣ በአቋራጭ መበልጸግን ፈጽሞ የማያስቡ፣ ሰርቶ እንጂ አጭበርብሮ በመከበር የማያምኑ፣ በጥቅም የማይታለሉ፤ እንቁ የእናት ሀገር ልጆች በጥንቃቄ እና በዕውቀት የተመለመሉበት፤ ሥልጣንን ሳይሆን ለውጥን ፈልገው የተሰበሰቡ ታሪክ ሲዘክራቸው የሚኖር ባለሞያዎች ስብስብ ነው።

እንደገና እልልታ ጭብጨባ ፉጨት። ረገብ ሲልም ቀጠሉ፤ ይህ ማለት ግን እዚህ ውስጥ የተሰበሰብን ሁላችን ከበረዶ የጠራን ከጥጥ ፍልቃቂ የነጻን ነን ማለት አይደለም። ስለዚህ ኮሽ ባለ ቁጥር መደንገጥ መሰዋዕትነት በተከፈለ ቁጥር መሸበር አያስፈልግም። በግለሰብ ላይ የተንጠለጠለ ድርጅት የለንም። ዓላማችን ኃያል ነውና ጽኑአን መሆን ይኖርብናል። ሁላችሁም የሥራ ድርሻቹ አሁን ይታደላቹህል ታዲያ ይህን ሰነድ በካሜራ ማንሳትም ሆነ ከዚህ ዋሻ ይዞ መውጣት አይፈቀድም አደጋ ላይ ይጥለናልና።

ከዚህ ስንወጣ ሁላችንም የየድርሻችን የምንወጣ ግለሰቦች ብቻ እንደሆንን ይቀጥላል። ባለቤቶቻችንም ቢሆኑ ልጆቻችን የልብ ጓደኞቻችንም ቢሆኑ ዘመዶቻችን ስለዚህ ህቡዕ ድርጅት ማወቅ አይገባቸውም። ለራሳቸውም ለራሳችንም ለዓላማችንም ሲባል። ከዚህ ስንወጣ በሕይወት አልያም በሥራ አጋጣሚ የምንገናኝ ሰዎች እስካልሆንን ድረስ አንተዋወቅም፤ እንኳን በሥም

ልንጠራራ ልንገናኝ ቀርቶ በዐይን እንኳ ሰላም መባባል አይኖርብንም። ወታደሮችም፣ ሚኒስትሮችም፣ ባለሀብቶችም፣ ባለስልጣኖችም፣ ተማሪዎችም፣ የመንግሥት ሲቪል ሰርቫንቶችም፣ ሌክቸሮችም፤ ምሁራንም ሁላችንም በሽፋን ቀኑ እስኪደርስ ድምጻችንን አጥፍተን እነሱን መስለን ነው መግባት እና መውጣት የሚኖርብን ግልጽ ነው? አሉ በጭብጨባ መስማማታቸውን ገለጹ። ወንድሞቼ እና እህቶቼ አስቀድሜ እንደ ነገርኳቹ መሰዋዕትነት ሲኖር እየተተካካን መቀጠል ይኖርብናል።

ቆጣ ቆፍጠን መረር ማለት ያስፈልጋል፤ መልፈስፈስ ዋጋው መራራ ነው። ልፍስፍስ ስስ ትውልድ ሲበዛ ሀገር ትፈርሳለች፤ መፍረስ ማለት መበትን ብቻ አይምሰላችሁ በወንበዴ እጅ ስትወድቅ ዝም ብሎ ማየት፤ ፍትህ ሲጠፋ፣ የጎበዝ አለቃ ሲበዛ፣ እኔነት ሲስፋፋ፣ እኔን ካልነኩኝ፣ እኔን ካልዘረፉኝ፣ እኔ ከበላሁ፣ እኔ ሥራ ካለኝ፣ እኔን ካላሰሩኝ፣ እኔ፣ እኔ ብቻ ከሆን ለወንድሜ ደም ካልተፋለምኩ ለእህቴ ካልቆምኩላት ለታናሼ መከታ ካልሆንኩ ለሀገሬ ካልወደኩ እኔ በእኔ ከተሸበብኩ ጎመን በጤና የሚሉትን የልፍስፍስ ሀሞተ ቢስ ራስ ወዳድ አባባል ካነገብኩ የመኖሬ ትርጉም በራሴ ዛቢያ ላይ ብቻ ከተሸከረከረ ያ የበሽታው ዋነኛ ምልክት ነው። እያንዳንዱ የሀገሬ ልጅ ከእኔነት አዙሪት መውጣት መቻል አለበት እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚል ትውልድ መኖር የለበትም።

ይህ ትውልድ የአባቶቹ ባይሆን የሀያቶቹ ልጅ መሆን አለበት የኛ ቀደምቶች ሁለት አይነት እንደሆኑ መዘንጋት የለበትም። አርበኞች ለሀገር ድንበር ለሕዝብ ነጻነት ደማቸውን የሚያፈሱ እንደነበሩ ባንዳዎች ሀገር የሚሸጡ ሆዳቸው አምላካቸው የሆነባቸው እነ ነውር ጌጡ ለመጣ ለሄደ ሰጋጆችም እንደነበሩ አንርሳ፤ አሁንም በሚገርም ሁኔታ ታሪክ እራሱን ደግሞ ያውም በባሰ ሁኔታ ሁለቱም

አይነት ዜጎችን ይዛለች ኢትዮጵያ። በፊተኛው ዘመን
ለምስር ወጥ ብኩርናውን የሸጠ አንድ ዔሳው ነበረ፤
አሁን ግን እልፍ በሥሙ የሚጠሩ የግብር ልጆች አሉት።
ከቤተ መቅደስ እስከ ቤተ መንግሥት ከቢሮ እስከ ሰፈር
ከነጋዴ እስከ ሊስትሮ። እውነትን የያዘ ደግሞ
በየትኛውም የታሪክ አጋጣሚ ተሸንፎ አያውቅም።
በሠዓቱ ይመስላል ግን ጊዜ ፊቷን ታዞራለች።

እኛ ከየትኛው ወገን ታሪክ እንደሚጽፈን የመምረጥ
ሙሉ መብት አለን። መርጠንም ቆመናል። መንገዱ
ለጠፋባቸው ግራ ለተጋቡ እውነቱ የቱ እንደሆነ ማወቅ
ለተሳናቸው የማይጠፉ ግን የሚቀጣጠል ጧፍ ሆነን
ልንመራቸው ወደ ከነዓንም ልናስገባቸው ግዴታ አለብን
በማለት ትንፋሽ ለመውሰድ ረፍት አደረጉ። የቁጭት፣
የእልህ፣ የተስፋ ፊት ታዳሚዎች ላይ ይታይ ነበር።
የጭብጨባም ሆነ የፉጨት ድምጽ አልነበረም።

አሁን ሁላችሁም ከተቀመጣችሁበት ተነሡና
ለወንድማችን የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት እናደርሳለን
አሉ ሁሉም ከተቀመጡበት መነሳት ጀመሩ፣ መነሳት
አልተጠበቀባቸውም ይህን ሁሉ ቁመው ነበርና
የሚናገሩት። ጸሎቱን እንደ ጨረሱም እናመሰግናለን
የአባቶቻችን አምላክ ነፍሱን ከአብርሀም ከይስሀቅ
ከያዕቆብ ጎን ያሳርፍልን። ለዛሬ ይሄው ነው። በጭብጨባ
ስብሰባውን ፈጸሙት።

ረፋድ: 5:28

ቴራስ ከተሳፈረበት ላዳ ወረደና አጠገቡ ወደሚገኘው ህንጻ በጀርባ በር ቤዝመንት አመራ ከጥበቃው ጋር ተጠቃቀሱ ጥበቃውም መግቢያውን በሰንሰለት አጠረው። ቴራስም ወደ ሁለተኛው ቤዝመንት በደረጃው በመውረድ ሲጠብቁት ለነበሩት አምስት ወጣቶች በዐይኑ ሰላምታ ሰጥቶ የያዘውን ከፍተኛ ሚስጥር የሚል ቀይ ረጅም ማህተም የተመታበት ሰነድ አቀበላቸው። በየተራ እስኪመለከቱት በእጅ ስልኩ ውስጥ አንድ ፎቶ በመፈለግ ላይ ነበር። እያያቹ ያላችሁትን ለማመን እንደሚከብዳችሁ አልጠራጠርም በማለት ዐይኑን ከእጅ ስልኩ ላይ አንስቶ ሁሉንም ተመለከታቸው ፊታቸው ላይ ድንጋጤም ግርታም አነበበ። ይበቃቹሀል ምን እየመጣ እንዳለ አውቃችሁ እንድትጠነቀቁና እንድትዘጋጁ ነው ይህን ያሳየኋችሁ ብሎ ሰነዱን ተቀበላቸው።

በእጅ ስልኩ ያዘጋጀውንም ፎቶ በማስፋት አሳይቶ ዛሬ ማታ 4:45 ላይ ቦሌ አየር ማረፊያ ትደርሳለች። ያባል አንተ ትቀበላታለህ ታዲያ ተጠንቀቅ ለረጅም ጊዜ ስትናፍቃት የከረምክ ፍቅረኛህ ናት፤ act like one ጥምጥም ብለህ አንገቷን ረዘም ላለ ጊዜ ሳማት አቅፈህ አንጠልጥላት። ያን አከባቢ ስለምንፈልገው እዚያው skylight ማረፊያ ተይዞላታል። በዛው በረራ 701 የምትመጣ የMI6 ኤጀንት አለች ይህቺ ናት በማለት ከእጅ ስልኩ ሌላ ምስል አሳያቸው። ያባል እንዴ ሀበሻ ናት እኮ አለ ደንገጥ በማለት፤ ቴራስም አልተሳሳትክም እኛን በኛው ነው ሊያጠፉን የተነሡት አለበለዚያ እንደማይችሉን ያውቁታል፤ ለማንኛውም እሷን የምትከታተላት አንተ ነህ ጋይዳድ እንዳለፈው አይነት

ስህተት አሁን ክፍያው ሕይወት ሊሆን ይችላል
ችኩልነትህ ብዙ እንዳይጎዳን አለው።

ሌሎቻችሁ ወንድሞቻችሁን በቅርበት
ተከታተሉዋቸው። አንድ የምስራችም አለኝ።
እንደምታውቁት እናንተ ከተመለመላችሁበት እጅግ ለየት
ባለ እና ረቀቅ ባለ መንገድ የመለመልናቸው፤ እንዲሁም
በአይነቱ ለየት ባለ መልኩ የስለላ፣ ኢንተለጀንስ፣ የተለያዩ
ቋንቋዎች፣ ጥንቃቄ እና ሚስጥረኝነት፣ አስተውሎት፣
የማኒፑሌሽን፣ ኢሚቴሺን፣ የሰርቫይቫል፣ ቴክኖሎጂ እና
ልዩ ልዩ ለስለላ ብቁ የሚያደርጉ አልፎም በዓለም ላይ
አንጋፋ ከሚባሉ የስለላ ድርጅቶች ጋር ቁመት
የሚያለካካን ብሎም አንገት ላንገት የሚያስተናንቀንን
ጥበብ ከተግባር ጋር አጣምረው ሲሰለጥኑ የነበሩት
ከተለያዩ የሀገሪቷ እስትንፋስ ከሆኑ ተቋማት እዚያው
ሆነው እንዲያገለግሉን ጭምር የመለመልናቸው
አባሎቻችን ሁሉም ዛሬ ተመርቀዋል። ሲል የሁሉም ፊት
ላይ የእርካታ ስሜት ይነበብ ነበር። በደሜ ሀገሬ ቀና
ትበል! አለ ቴራስ በነፍሴ ትለምልም! በማለት ተቀበሉት።
በድጋሚ እስከንገናኝ ጥንቃቄ አይለያቹ ከሁለታችሁ ጋር
ቢሮ እንገናኝ ብሎ ተሰናበታቸው።

ምሽት 12:30

ጀነራል ሂሶጵ፣ ከቦሌ ድልድይ ሸቅብ ወደ ቦሌ መድኃኒዓለም በሚወስደው ጎዳና እያሽከረከረ በሀሳብ ግን ከሚነዳው ተሽከርካሪ በብዙ እጥፍ በበለጠ ፍጥነት ይነጉዳል፤ ያወጣል፣ ያወርዳል፣ ያነሳል፣ ይጥላል ወደ IOM የሚያስታጥፈው መገንጠያ ጋር ሲደርስ በመጣበት ፍጥነት መሪውን ወደ ግራ ጠምዝዞ ታጠፈ። ከሱማሊያ ኤምባሲ ከወጣ ተሽከርካሪ ጋር ከአምስት ሴንቲ ሜትሮች በሚያንስ ርቀት ተላለፉ። ክላክስ አድርጎ ይጮህበት ጀመር መሪውን የጨበጠ ሀበሻ። ሂሶጵ ግን ትኩረትም አልሰጠውም ከቱርኩ አታሼ መቀመጫም እንደ ደረሰ ፍጥነቱን አቀዝቅዞ ከአጠገቡ የሚገኝ መኖሪያ በር ፊት ለፊት የሚያሽከረክራትን ጥቁር ሬንጅ ሮቨር አቆማት። ሳይወርድም በተቀመጠበት ብዙ ደቂቃዎች ፊት ለፊቱ ካለው ባለ ሁለት ህንጻ መኖሪያ ላይ ዐይኖቹን ተክሎ በሀሳብ ነጎደ።

በምን ድፍረቴ ነው የምገባው? ዐይናቸውንስ እንዴት አየዋለሁ? እንዴትስ ብዬ አረዳቸኋለሁ? በሚሉ ጥያቄዎች ጭንቅላቱ ተወጥሮ፣ የሚበላ ከዞረው የሰነበተ ከንፈሩም ደርቆ፣ ጉልበቱም እንደመዛል እያለበት ይገኛል። ስለዚህ ሁሉ ግን እሱ ግድ አልሰጠውም። እዚህ አከባቢ ማቆም አትችልም የሚል የአንድ ጎረምሳ ድምጽ አነቃው። ጀነራሉም ያለውን ባይሰማም፣ ሲት ቤልቱን ፈቶ ከመኪናው በመውረድ የጋቢናውን በር ሲዘጋው፤ ጠባቂው ፈንጠር በማለት ወደ ኋላ በመሸሽ የያዘውን AK 47 መሳሪያ አስተካክሎ ምን ልትኾን በማለት

አንባረቀበት። ሂሶጵም ፈገግ ብሎ አይዞህ እዚው ነኝ አለው።

የጊቢው በር ክፍት ስለ ነበር ከዋናው በር አንዲት ቀይ ቀጠን ያለች ቀልጣፋ ህጻን አጎቴ እያለች ስትበር መጥታ ልትለጠፍበት ስትል፤ በሁለት እጆቹ ወገቧን ይዞ ወደ ላይ አንስቷት አሽከረከራትና ወደ ውስጥ ይዟት ገባ። ሳሎን እንደገቡም የህጻኗ ታላቅ ወንድምና እህት በሪሞት እየተጣሉ አገኛቸው፤ ሁለቱም ጆነራል ሂሶጵን ሲያዩት አጎቴ እያሉ ተሸቀዳድመው መጥተው በግራና ቀኝ ወገቡ ላይ ተጠመጠሙበት። አይከልም እንዴ ሂሶጵ መች መጣህ? በማለት ረጅም ሞላ ያለ ሰውነቷን ይዛ ደረጃዎቹን ለመውረድ እግሮቿን ባንቀሳቀሰች ቁጥር እስከ ጪኖቿ የሚገለጥ፤ ባለ ረጅም ቅድ ሰማያዊ ሙሉ ቀሚስ ለብሳ፤ ከደረጃው ሰበር ሰካ እያለች እየወረደች ጠየቀችው፤ መልስ አልመለሰላትም፣ ተሳስመውም ሰላምታ እንደተለዋወጡ ልጆች እስቲ ልቀቁት ይረፍበት ጨዋታው በኋላ ይደርሳል።

ሳትነግረን እንዴት ትመጣለህ ምንም ሳናዘጋጅልህ! ጓደኛህም ስልኩ አይሰራም፤ ልጆቹም ካልደወልሽ እያሉ ያስጨንቁኛል፤ እኔም እንዲሁ ከትላንት ጀምሮ ልቤን ጭንቅ ይለኛል ስትለው፤ ልጆቹ በአንድነት አጎቴ ደውልለት ደውልለት ናፍቆናል እያሉ ሲያስጨንቁት፣ ድንገት አፍኖ የያዘው የሀዘን ስቃይ ፈንቅሎት ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ። ህጻናቱም ደንግጠው ፈጠር ፈጠር ብለው ቆሙ። አጎቴ አታልቅስ ማን መቶክ ነው ንገረኝ ብላ እንባውን ስትጠርግለት፣ አቅፎ ይዞአት እንዳዲስ የመረረ ለቅሶ ማልቀስ ጀመረ።

ይህን ጊዜ አይከል ታውቆኛል! አላምን ብዬ እንጂ የሆነ ነገር እንደተከሰተ ልቤ ነግሮኛል። ሂሶጵ ባሌ ምን ሆነ የልጆቼ አባት ምን ሆነ ብላ የሸሚዙን ኮሌታ በሁለት እጆቿ ጨምድዳ እየነቀነቀችው ማልቀስ ጀመረች።

መናገር አቃተው፤ እየተንሰቀሰቀ አንገቷን ይዞ ትከሻው ላይ አስደግፏት መንሰቅሰቅ ቀጠለ። እጁን አስለቅቃ ዐይኑን እየተመለከተች ሞተ አይደል ስትለው በአዎታ ጭንቅላቱን ነቀነቀላት። ወዲያው ተዝለፍልፋ ወደቀች፤ ህጻናቱም በመደናገጥ እሪታቸውን አቀለጡት። ጠባቂውም ተንደርድሮ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲገባ መሬት ላይ ተዘርራ በማየቱ፤ እጅ ወደ ላይ ብዬሀለሁ ብሎ መሳሪያውን አቀባበለ። የቤት ሰራተኛዋም ደርሳ እመቤቷን ከመሬት በማየቷ፤ የጭንቅ አማላጇን እትዬ ምን ሆኑ ብላ መጮህ ጀመረች። ሂሶጵ ተረጋጉ ሀዘን ላረዳ ነው የመጣሁት የወንድሜን፤ የባሏን ሞት ሰምታ ነው ይልቁን ፎጣና ውሀ አቀብይኝ ፍጠኚ ብሎ ልጆቹን ማረጋጋቱን ተያያዘው። ተሸክሟት ከሶፋ ላይ አስተኙትና በውሃ ነክራ ያመጣችለትን ፎጣ ግንባሯ ላይ እያሻሸው ህጻናቱ መረጋጋት ባለ መቻላቸው መኝታ ቤት ይዛቸው እንድትገባና አብራቸው እንድትሆን አዘዛት።

ከደቂቃዎች በኋላ አይከል በለሆሳጵ ባሌን ማዕረጌን ብላ ብንን አለች፤ ሂሶጵ ወንበር ስቦ ከጎኗ ቁጭ ብሎ ፈዟል። ቀና ብላ ለመቀመጥ ስትነሳ አቅሟ ስለከዳት አቃሰተች። ሂሶጵም ከሀሳቡ በመባነኑ፤ ትንሽ እረፊበት አይዞሽ፤ እንኪ ይህን ጠጪበት በማለት ውሃ ሰጣት። መልስ ሳትመልስለት ባሌን፣ ባሌ የታለ እያለች ለመነሳት ጥረቷን ቀጠለች፤ እሱም ለማረጋጋት እየሞከረ ቀና ብላ እንድትቀመጥ አገዛት። ሂሶጵ ምን እንደሆ ንገረኝ አደጋ ነው? ወይስ ገለውት ነው? መልሳ፣ ደግሞ እሱን ማን ሊገለው ይችላል? እንኳን ጠላት ሊኖረው ይቅርና... አይ አደጋ ነው የሚሆነው፤ ንገረኝ ምን ሆኖ ነው እያለች አጣደፈችው።

ምን እንደ ሚላት ግራ ገባው፤ እንዴት በጥይት ተመታ ልበላት? ተከትሎ የሚመጣውንስ ጥያቄ እንዴት እመልሰዋለሁ? እነማን መቱት? የት መቱት? ምን

ሲያደርግ መቱት? እኚህን ጥያቄዎች ከመለስኩ የድርጅቱን ሚስጢር ማውጣቴ አይደል? የማወቅ መብት ደግሞ አላት። በእነዚህ ሀሳቦች ተወጥሮ ዝም አላት። እየጠበኩህ ነው መልስልኝ አለችው። ከዐይኖቿ የሚወርዱትን ትኩስ እንባዎች እያበሰች። አሁንም ዝም አላት። ጨነቀው፤ አዎ የሆነው ሆኗል፤ የልጆቿን አባት አጥታለች ስለዚህ እውነቱን ማወቅ ይኖርባታል።

ይኸውልሽ አይከል የወንድሜ ገዳይ እኔ ነኝ። ጆሮዋን ተጠራጠረችው፤ አፈጠጠችበት። አዎ ለባለ ቢትሽ ማለፍ ተጠያቂው እኔው ነኝ። ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ታውቂዋለሽ ነጻነት ብሎ ነገር፣ እድገት ብሎ ነገር፣ ሰላም ብሎ ነገር ርቋታል በዓለም ፊት አንገቷን ደፍታለች። ስለዚህ አብዮት ያስፈልጋታል። ስር ነቀል ተሃድሶ ያስፈልጋታል። በዚያም ምክንያት ይህን ማድረግ የሚገባው ብቁም የሆነ ድርጅት መመስረት የግድ የሆነበት ሰዓት ላይ በመደረሱ ይህን ለማድረግ በየዘርፉ ብቁ የሆኑ ባለ ሞያዎች መመልመል ነበረባቸው። በዚህም መሰረት...

ሳታስጨርሰው ባለ ቤቴን መለመላቹት? ይኸውልህ አሁን እኔ እንዲህ ያለ ዝባዝንኬ መስማት አልፈልግም። ጌጤን፣ መመኪያዬን የነጠቀኝ ማን ነው? ሁሉን የማወቅ መብት ስላለሽና ጭንቅላቴም እረፍት ስለነሳኝ እንጂ የምነግርሽ ዝባዝንኬ አይደለም። ይልቁንም የሺዎችን ሕይወት መሰዋእትነት የሚያስከፍል ሚስጥር ነው። ለማንኛውም እሱ ከመጀመሪያው መቀላቀል አልፈለገም ነበር፤ በብዙ ምክንያቶች ዋነኛው ለቤተሰቦቼ ጊዜ መስጠት ይኖርብኛል ነበር ሲላት አምርራ ማልቀስ ጀመረች። እኔ ነኝ ያሳመንኩት ወደ ሀገር ቤት የመመለስ ተልዕኮ ላይ እያለን ነበር በአሜሪካን የደህንነት ሰዎች ደረቱን የተመታው። እኔ ነኝ የወንድሜ ገዳይ።

ድንገት ፍንጥር ብላ በመነሳት፤ ቆይ እኔ እኮ የማይገባኝ ስለ የትኛዋ ኢትዬጵያ ነው የምታወሩት? እኛ የማናውቃት ኢትዮጵያ አለች እንዴ? ስለ ምን ውርደት ስለ ምን መንበርከክ ስለ የትኛው ድህነት ነው የምታወሩት? እንኳን እኛ ጋር አሜሪካን ድህነት የለም እንዴ? አሜሪካን ውስጥ በረንዳ የሚያድር የሚበላ አጥቶ ጾሙን የሚውል የለም እንዴ? የኖርንባት ሀገር ናት አይደል እንዴ አውሮፖ ውስጥ የፖለቲካ አሻጥርስ አይሰራም? እስረኞች የሉም? ይሄ ለሥልጣን ጥማቹ ለደም የማፍሰስ አባዜያቹ የምትሰጡት የዳቦ ስም ነው።

ከትላንት ዛሬ የማይማር ሕዝብ ለናንተ ነፍሱን ይገብራል። ሥልጣን ስትይዙ መልሳቹ ትረግጡታላቹ። መልሶ ነገም ለሌላው ነፍሱን ይገብራል። እንዳናስተውል አዚም ያዞረብን ማን ነው? በናንተ ግትርነት የስንቱ ጎጆ ቀዘቀዘ፤ ስንት ልብ ደማ፤ ስንትስ ህጻን ደጅ ደጁን እያየ በፍቅር እጦት ተሰበረ፤ ይህን ለማሰብ ጊዜ የላችሁም። አሁን ይህ ሁሉ እኔም ቤት ገብቷል። ልጆቼን አባት አልባ፣ እኔን ማዕረግ የለሽ ጋለሞታ አደረገኝ። በያንድ አንዳችን ቤት እስኪገባ አልጠብቅም በእኔ ማብቃት ይኖርበታል። የደም ግብር በዚች ምድር መቆም ይኖርበታል። አሁን እንድትወጣልኝ እፈልጋለው! ይኸውልሽ አይከ... ሂሶጵ እንደተከበርክ ውጣልኝ ብያለው። ቆይኝ አንዴ...ው..ጣ..ልኝ ብላ ቤቱን በጩኸት ሞላችው። እሺ አሁን እወጣለሁ። የቀብሩን ሥነ ሥርዐት ለማስፈጸም የተቋቋመ ኮሚቴ ያነጋግርሻል። አይከል በጣም አዝናለሁ ስለ ሆነው ሁሉ ወቀሳውን እኔ እወስደዋለሁ ብሎዋት ወጣ።

ቦሌ አየር መንገድ

4፡45

ከቴራስ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት የዞዓር ቡድን አባላት ምቹ ብለው በወሰዱት ስፍራ በመሆን በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ያባል ወደ ጉምሩክ በር መውጫ ጠጋ ብሎ ቆመ ብዙም ሳይቆይ በምስሉ ላይ የተመለከታትን እንስት በማየቱ በሩጫ ተጠግቶ አቅፎ አንጠለጠላት እሷም አጸፋውን መለሰችለት። የሻንጣውን ጋሪ እየገፋ አቁሞት ወደ ነበረው ተሽከርካሪ አመሩ። እንዲሁም ይጠብቋት የነበረችው ኤጀንት ወጣች አብረዋት ሦስት ነጮች ነበሩ እየመሯት ቆማ ወደ ነበረችው bmw X5 አምርተው ከኤርፖርት በመውጣት ወደ ስካይ ላይት አቀኑ። ጋይዳድም ከሌሎች ሁለት የዞዓር አባላት ጋር በመሆን ተከተላቸው። ቀሪዎቹ ሁለቱ ያባልን በመከተል ወደዚያው አመሩ።

ያባል፤ ሰዓር በስካይ ላይት ወደ ተያዘላት አንድ መኝታ ኢፓርትመንት ማረፊያ ከአስገባት በኋላ ወደ ኦፕን ኪችኑ በማምራት ቀድሞ ለሷው ተብሎ በምግብ ዘር ከተሞላው ካብኔት አንድ አፕል አንስቶ እየነመጠ ወደ ሶፋው በማምራት ተቀመጠ። ዞር ዞር ብላ የተያዘላትን ማረፊያ ቃኘችና ማውራት ያለብን ነገር አለ? I'm exhausted and need a shower and some rest ብላ አጠገቡ ተቀመጠች። ቀጠል አድርጋም የሚገርምህ በቅርቡ እጇ የገቡ ሰነዶች እንደሚያሳዩት በየግላቸው የተደራጁ ማዕከላዊ መዋቅር የሌላቸው የነጻነት ታጋዮች

በሀገሪቷ ውስጥ ብዙ አሉ። ከሚለዋወጡት መልዕክት፣ ከዓላማና ግባቸው ተነስቼ ረጅም ርቀት ይጓዛሉ ብዬ የጠበኳቸው ቡድኖች፤ ድርጅት እንኳን የመሆን እድል ሳያገኙ በጽናት ሳይሆን በምልመላ እና በመዋቅር ድክመት የውሀ ሽታ ሆነው ቀርተዋል።

አንድን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በተልዕኮው የሚያምኑ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን መሰብሰብና ማሳተፍ ብቻውን በቂ አይደለም። የሚከፈለውን ሁሉ ለመክፈል የተዘጋጁ ከክብር፣ ከዝና፣ ከገንዘብ እና ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ይልቅ መዳረሻቸው ላይ ትኩረት አድርገው የሚጓዙ ሚስጥር ጠባቂ እኔነትን እርግፍ አድርገው የጣሉ የጽኑአን ስብስብ ያስፈልጋል። በዚህ ሂደት ውስጥ ምልመላ ወሳኙን እና ዋናውን ሚና ይጫወታል ይህን ተረድቶ በአግባቡ ያልተገበረ ቡድንም ሆነ ድርጅት ከግቡ የመድረሱ ጉዳይ አጠያያቂ ብቻ ሳይሆን በታሪክ እንዳየነው አሁንም ምስክርም ጭምር እንደሆነው ያለ፤ እጣፈንታ ነው የሚጠብቀው።

ከአንድ በላይ የሆነ የትኛውም ነገር አብሮ ለመዝለቅ የግድ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች አሉ። አተሞችን ተመልከት እንደምታውቀው the basic building blocks of matter እንላቸዋለን። የአንድ ነገር ብዛት እና ክብደቱ ተዛማጅ ጽንሰ ሀሳቦች ቢሆኑም ፍጹም ተመሳሳይ አይደሉም። የእቃው ብዛት በእቃው ውስጥ ያለውን የቁስ መጠን ይወክላል እና ያ ነገር በምድር ላይ ወይም ስበት ዜሮ በሆነበት ከባቢ አየር ውስጥ ተመሳሳይ ነው።

በሌላ በኩል የአንድ ነገር ክብደት በስበት ኃይል በመሳብ የተጨመረ ክብደት ነው። የስበት መጎተት ከስበት ጥንካሬ ያነሰ ከሆነ የቁሱ ክብደት ይበልጣል። ለምሳሌ የጨረቃ ስበት ከምድር ያነሰ ስለሆነ፤ የአንድ የተወሰነ ነገር ክብደት በጨረቃ ላይ ሲሆን በምድር ላይ

ካለው ያነሰ ይመዝናል። በሌላ አነጋገር ክብደት ተለዋዋጭ ነው እና በስበት ኃይል ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

እስኪ አስበው ላንተ ተራ የሆነ ለውይይት እንኳ በቂ አይደለም ብለህ የምታስበው ጉዳይ፤ ሌሎች ሕይወታቸውን ጭምር ሲገብሩበት ታያለህ ለምን? ቅድም እንዳልኩህ ክብደት አንጻራዊ ነው። እምነትም እንደዚያው፤ የታመንክለት ለበለጠብህ ነው፤ ሌላ የሚበልጥብህ ነገር ግን ከዚኛው የሚቃረን ሲመጣስ? እምነት የሁሉም ነገር ጅማሬም ፍጻሜም ነው፤ መርምረህ አሰላስለህ አመዛዝነህ የደረስክበት እምነት አለት ነው። የስሜት እምነት ግን አሸዋ ነው ዝናብም ንፋስም ወደፈለጉት ይወስዱታል። የምልመላም ሂደት ይህን መከተል ይኖርበታል። ብዛት ላይ የሚያተኩር ድርጅት ያለ አግባብ ረዝሞ እንደሚጣመም ዛፍ ያለ ነው ይሰበራል። የዓላማው አንድነት እና ጽናት በሁሉም ልብ ውስጥ ተመሳሳይ ክብደት ሊኖረው ይገባል፤ አይነስ እንጂ መበላለጥ አይኖርበትም ማለት ግን አይደለም። የዓላማው ክብደት ጨረቃ ላይ እንደሚያንሰው ግራቪቲ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በስበት ሕግ የነገሩን ክብደት የሚወስነው ቁሱ ሳይሆን ስበቱ ነውና።

በዚህ መልኩ የተገነባ ድርጅት ጽኑ ይሆናል። በዚህች ዓለም ውስጥ በተፈጥሮ ያሉ ነገሮች በሙሉ ፔሬዲክ ቴብል ላይ ከተደረደሩት ምንም እንኳን አሁን ኩጥራቸው ቢበዛም ከ92ቱ መሠረታዊ ንጥረ ነገሮች አንድ ወይም ከዚያ በላዩን ያቀፉ እንደመሆናቸው አንዱ ለመኖር የሌላኛውንም መኖር የግድ ይፈልገዋል፤ ጥቃቅን የሚመስሉን ነገሮች ናቸው ትልቁን የሚያቆሙት። የኛውም እስከማየው ልባችን ውስጥ ወደ አለትነት ያዘነበለ ይመስላል። ግን የማያቸው አንድ አንድ ነገሮች ደስ አይሉም ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ውሳኔዎችን ስንወስን በተቻለ መጠን በሁኔታዎች ባየስድ ላለመሆን መጣር እና አለመሆናችንንም ማረጋገጥ መልመድ ይኖርብናል። ያን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል? ጠየቀ። የመጀመሪያው ለውሳኔ ይረዱናል ብለን የሰበሰብናቸውን አልያም የተጠቀምናቸውን መረጃዎች፤ ምንጫቸው ከየት እንደሆነ ማወቅ። የመረጃ ምንጮቻችን በምን ኢንቴንሽን ያንን መረጃ እንዳጋሩን እርግጠኛ መሆን ስለሚገባን። ቢቻል መረጃዎቹን ከምንጩ ብናገኛቸው ይመረጣል። ለምሳሌ አንተን የሚጠላህ ሰው ስለ አንተ ጥሩ ሊነግረኝ አይችልም። አንተ ግን መልካም ሰው ልትሆን ትችላለህ። የሚወድህም ሰው ስለ አንተ መጥፎ ሊነግረኝ አይችልም። ምንም ያህል ክፉ ብትሆንም። ያ ሰው ስለጠላህ አልያም ስለ ወደደህ እኔም ተመሳሳዩን ማድረግ አይኖርብኝም። የራሴ መስፈርት ሊኖረኝ ይገባል። ይህ ደግሞ በቅርባችን ሰዎች ሲነገረን ይጠነክራል። ለነሱ ያለን ቦታ፤ ለመረጃው የምንሰጠውን ተአማኒነት ከፍ ያደርገዋል። በዚህ መልኩ በደረሰህ መረጃ ስፍራን፣ ሀገርን፣ ታሪክን፣ ሃይማኖትን፣ ማኅበረሰብን፣ ግለሰብን ጠልተህ ግን በኢጋጣሚም ይሁን ፈልገህ በራስህ መንገድ አጣርተህ፤ ጥላቻህ ከንቱ እንደ ነበር ስትደርስበት በራስህ ያፈርክበት ጊዜ የለም? እጅግ ቡዙ መለሰ። ይሄንን እማ በራሴ የደረስኩበት ነው፣ አይቼዋለሁ፣ እዚያ ነበርኩ ብለህስ ልክ እንዳልነበርክ አረጋግጠህ አታውቅም? በሚገባ ደግሞ መለሰ። ውሳኔ ለመወሰን ማየት ብቻውን በቂ ላይሆን ይችላል። ጨውም ከሩቅ ስኳር ይመስላልና። መቅመስ ሊኖርብህ ይችላል። ስኳሩን ጨው ነው ቢሉህ ምናልባት ስትተወው ሊጠቀሙበት ይሆናል። ወይም በግልባጩ፤ ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል እንደሚባለው። ስለ አንተ ማወቅ ከፈለኩ አንተን ተጠግቼ ያለ ግርታም፣ ብዥታም ማወቅ እችላለሁ። ይሄን አለማድረግ፤ ክርስቶስ

ማነው? ብለህ የጣኦት ካህናትን እንደ መጠየቅ ነው
የሚሆነው። ፍጡር ነዋ ሌላ ምን እንዲሉህ ትጠብቃለህ?
መረጃን ከምንጩ ማለት ይሄ ነው።

ሌላው ውሳኔ ከመወሰንህ አስቀድመህ የተለያዩ እርስ
በእርሳቸው የሚቃረኑ ሀሳቦችን፣ ማስረጃዎችንና
መረጃዎችን መመልከት። ይህም ነገሮችን ከተለያየ
አቅጣጫ እንድታይ በማድረግ በአንድ ወገን ብቻ
ከሚወሰን ውሳኔ ያድንሃል። በውሳኔህም እርግጠኛ
እንድትሆን ያደርግሃል። ይህን ህቡህ ድርጅት ለመቀላቀል
እንዴት ወሰንኩ? አብዮት ፈጽሞ አስፈላጊ እንዳልሆነና
አሁን ያለው ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰላም እና
እድገት ያለበት በመሆኑ፤ ችግር እንኳን ቢኖር ጊዜ
ከሰጠነው፤ ይሄ አስተዳደር ሊፈታው አቅም እንዳለው
የሚያስረዱኝ አያሌ የመረጃ ምንጮች ነበሩ። ስለዚህ ጊዜ
እንስጣቸው እንድትል የሚያደርጉ። በሌላ በኩል ስለ
አይዲአሊዝም አደገኛነት አስረድቶ፤ አብዮት እና ለውጥ
አስፈላጊ ቢሆንም፤ ጉልበት መጠቀም እና ጠመንጃ
ማንሳት ወደ ማያባራ ቀውስና አለመረጋጋት ውስጥ
ሊከት የሚችል መንገድ ስለሆነ በሰላማዊ መንገድ
የፖለቲካ ለውጥ ማምጣቱ እንደሚሻል የሚያስረዱም
አሉ። እኔ እንዚህን መልካም እና አሳማኝ መንገዶች
ረግጬ ለምን ወደ እዚህ መጣሁ? ሁለቱም መንገዶች
ተሞክረው ሊሳኩ እንዳልቻሉና ሊሳኩም እንደማይችሉ፤
በቂ የሆነ ማስረጃ እጄ ላይ ስላለ ነው። አውቆ የተኛን
ለመቀስቀስ መሞከር ትርፉ ድካም ስለሆነ። እነሱ
የሚፈልጉትን ሲስተም ለመገንባት እኔ የምፈልገውን
እየናዱት፤ እረፉ ለሁለታችንም የሚበጅ መንገድ አለ
ስትላቸው፤ ጆሮዋቸውን ደፍነው መንገዳቸውን ከቀጠሉ፤
አፍርሰው፣ ንደው ሳይጨርሱት የሚያስቆማቸው ኃይል
እንደሚያስፈልግ ስለገባኝ፤ መቆምም ስላለባቸው ይሄን
መንገድ መርጥኩ። አደጋዎች አሉት አዎ። እነሱንም
ለመጋፈጥ ወሰንኩ። ታዲያ ይሄን ድርጅት ለምን

መረጥኩ? ቅድም በነገርኩህ መሰረት ሁሉንም ፈትኜ ቀለሉብኝ ይሄንን ያዝኩት ደን።

የመጨረሻው በመንጋ አልያም በቡድን አለማሰብ። ለአንተ ሌሎች እንዲያስቡልህ ጭንቅላትህን አለመስጠት! የራስህ የሆነ አይዲኦሎጂ፣ እምነት፣ ሃይማኖት እና አስተሳሰብ እንዲሁም የኑሮ ዘይቤ ሊኖርህ ይገባል። ይሄ ማለት ዓለም ላይ ያለነው ስምንት ቢሊየኖቻችንም፤ ስምንት ቢሊየን ሃይማኖት እንፍጠር ማለት አይደለም። ሰዎች ስለተጓዙበት ብቻ ዐይናችንን ጨፍነን አንራመድ ማለት እንጂ። ሰከን ብለን ውስጣችንን ማዳመጥን እንልመድ፤ ሌላን ሳይሆን እራሳችንን እንምሰል ማለ እንጂ። አብርሃም ከጣኦት አምላኪዎች መሃል ነው ያውም በአፍላ እድሜው ከመንጋው ተለይቶ፤ በእጅ የሚሰሩት ጣኦታት፤ ጆሮ አላቸው አይሰሙም፤ እግር አላቸው አይራመዱም፤ እጅ አላቸው አይዳስሱም፤ አፍንጫ አላቸው አያሸቱም፤ ዐይን አላቸው አያዩም በማለት ንቆአቻው፤ ፀሀይን እና ጨረቃን ሊያመልክ ዐይኑን ቢያነሳ ይገባሉ ይወጣሉ። እኚህስ ጊዜ አላቸው። የፀሀይ እና የጨረቃ አምላክ እራስህን ግለጽልኝ ብሎ ቢማጸን እግዚአብሔር እራሱን የገለጸለት። መነጠል ያስፈልጋል። ብላ ደገፍ አለች። ያባል መልስ አልሰጣትም ያነሳቻቸው ሀሳቦች ወጥረው ይዘውት ነበር።

ቀጣይ ቀን ረፋድ

6:20

ኤፍሮን ሦስቱ ጀነራሎች ለስብሰባ ወደ ተቀመጡበት ክፍል ለሩጫ ትንሽ በቀረው የፍጥነት እርምጃ እየከነፈች መጥታ ለመግባት ስትሞክር የበሩን ግራና ቀኝ ይዘው ታጥቀው በተጠንቀቅ የቆሙ ባለ ቀይ ቦኔት ኮማንዶዎች ከለከሏት። ስብሰባ ላይ መሆናቸውን እንደምታውቅ እና አስቸኳይ ስለሆነባት እንደመጣች አስረድታ ሳያስገቧት ቢቀሩ ግን ለሚደርሰው ጥፋት ሀላፊነቱን እንደሚወስዱ ስትነግራቸው እያንገራገሩ ፈቀዱላት። ዘላ እንደገባች ምንም ሳትናገር ግርግዳው ላይ የተለጠፈውን ግዙፍ ስክሪን አበራችው። ወይዘሮ አይከል አራት ኪሎ በሚገኘው ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ቅጥር ጊቢ ውስጥ እንዲደረግ በተመቻቸው የባሏ ቀብር ሥነ ሥርዐት ላይ ሀገሪቷ ውስጥ አሉ የተባሉ የመገናኛ ብዙሀንን ሰብስባ በቀጥታ ስርጭት ንግግር እያደረገች ነው። ሦስቱም የሚያዩትን ማመን ተሳናቸው።

… ወገኖቼ እያልኩ ያለሁትን በደንብ እንድትረዱኝ እፈልጋለሁ። ፖለቲከስ እና ፖለቲከኞች አያስፈልጉንም እያልኩ አይደለም። ነገር ግን አብዛኞቹ እኛን የሚፈልጉን ታግለን ደማችንን አፍስሰን ሕይወታችንን ገብረን ወንበር እንድንሰጣቸው ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ይረሱናል፤ ኃይል ከሰጠናቸው ጠመንጃና ሥልጣን ካስረከብናቸው በኋላ በሰጠናቸው ሥልጣን ወገባችንን ይሰብሩበታል አፋችንን ያዘጉበታል። አፈሙዙን አዙረው ደረታችንን ይበሱበታል፤ በሰደፉ ግንባራችንን ይነርቱበታል። እናስተውል ይህ የወንበሩ ጸባይ ነው። በየትኛውም የዓለም ክፍል መጠኑና አይነቱ መንገዱም ይለያያል እንጂ

መንስኤው እና ውጤቱ አንድ ነው የሚከፈለው ሁሉ ተከፍሎ ሥልጣንን መያዝ።

ከዚያም የሚደረገው ሁሉ ተደርጎ፤ በሥልጣን መቆየት ይሄው ነው። ለእኛ ግድ የላቸውም ለምን ታሪክ አያስተምረንም፤ ወገኖቼ እስቲ ቁጭ ብላቹ በሰከነ አዕምሮ ጠይቁ ታግለን፣ ተገለን፣ታስረን፣ ተገርፈንና አንዳንዶቻችንም ከሀገር ጭምር ተሰደን ሥልጣን ያስጨበጥናቸው ዘመዶቻችን፤ አብሮ አደጎቻችን ወይም በሚያራምዱት ዕርዮት ከጎናቸው የነበርናቸው ሰዎች ሥልጣን ከያዙ በኋላ ምን አደረጉልን? እራሳቸውን ጠይቁ። እነሱንም ጠይቋቸው ምን ይመልሱላችኋል? መሰረተ ልማት እያሟላን ነው፤ ከዚህ እስከ እዚህ አስፓልት ዘረጋን፤ ይህን ያህል ሕንጻ እኛ ከመጣን ወዲህ ተገነባ፤ መልካም አስተዳደር እያሰፈንን ነው፤ ነው መልሳቸው ታዲያ ይሄ እኮ መልካም አስተዳደር አይጠይቅም፤ ሰው መኖር ካለበትና ሲኖር የሚመጡ የሰው ልጅ የመኖሩ ሂደት ውጤቶች ናቸው። ደግሞም የሚሰሩት ከሕብረተሰቡ ግብር እና ታክስን ጨምሮ በተለያየ መንገድ በተሰበሰቡ ገንዘቦችና ከራሱ ከሕብረተሰብ በወጡ ባለሞያዎች እንጂ በባለ ሥልጣናቱ አይደለም።

ይህ ሲደረግ ግን ምን ያህል የሕዝብ ገንዘብ ያለ አግባብ እንደ ባከነ አይነግሯቸሁም። ተቃዋሚዎቹን ብትጠይቋቸው ደግሞ ነጻነት የለም፤ እድገት የለም ፍትህ የለም፤ ዜጎቻችን እየተራቡ ነው ይሏችኋል። ሥልጣን ላይ ያሉትም እኮ እንዲ ብለው ነበር እነሱም ሲወጡ ይህን አይመልሱም። ሌላው ደግሞ ይህኑ ጥያቄ ይዞ የወጣቱን ደም እየገበረ ይመጣል። አዙሪቱን ካላስቆምነው እንዲሁ ይቀጥላል። ስለዚህ ምን እናድርግ? በቃ ደምና ነፍስ መገበራችንን እናቁም። የመጣውም የሚመጣውም መጥቶ የሄደውም ለራሳቸው ስለራሳቸው ብቻ እንደሚኖሩ

ካወቅን የደረሰብንን መመለስ ባንችልም ሊደርስብን ያለውን ጥፋት ግን ማስቆም እንችላለን።

ለምን ሁላችን ቤት እስኪገባ እንጠብቃለን? ይኸው በምን አገባኝ ቁጭ ብዬ ዛሬ እኔም ቤት ገባ። ልጆቼን ያለ አባት፤ ያለ መካሪ፤ ያለ አስጠኚ፤ ያለ ትምህርት ቤት ወሳጅ፤ ያለ መከታ አስቀረዋቸው፤ ጎዶሎ ሆኜ አጎደልኳቸው። እኔም ያለጌጥ፤ ያለ መከታ፤ ያለ ባል ብቻዬን ቀረሁ። እዚህ ውስጥ እንዲገባ የገፋፉት እና ህቡዕ ድርጅት አቋቁመን መንግሥትን በኃይል እንገለብጣለን ያሉ ግለሰቦች ግን አሁንም በሕይወት አሉ። ነገም የምስኪኑን ሕይወት እያስገበሩ ይኖራሉ። ዲሞክራሲ በውሸት ተዘርቶ በማስመሰል የሚበቅል አረም ነው። እስራኤልን ተመልከቱ የአህዛብን ሥርዐት አይተው አምላካቸውን አንተ የሾምክልንን አንፈልግም እኛው በምርጫችን ንጉሥ እናነግስለን ብለው ባርያ እስኪሆኑ ነው የተበዘበዙት እሱ የሚቀባላቸው ንጉስ ግን ሲያስከብራቸው እና ወደ ከፍታ ሲመራቸው እናያለን። በቃ ይበቃል እኔ ሁሉንም አጋልጣለሁ። እንዳታስተውሉ አዚም ያዞረባቹ ማን ነው?

ወንድሞቼ ከናንተ ጋር የጀመርነውን እንጨርሳለን እስከዚያው የመፍትሄ ሀሳቡ ላይ እየመከራቹ ጠብቁኝ። ብለው የስብሰባውን አዳራሽ ለቀው ወጡ። ጄነራል ሠሀረ። የእጅ ስለካቸው መጥራት ጀመረ፤ የሊቁ የቢሮ ስልክ ነበር፤ ጎሮሮአቸውን አጽድተው ጥሪውን መለሱ።

።፡ የት ነው ያለኸው?

።፡ ስብሰባ ላይ ነበርኩ!

፡፡ እየተከሰተ ያለውን ነገር አውቀሀል?

፡፡ አዎ!

፡፡ ታድያ ምን እየሰራህ ነው?

፡፡ ሌላ ስብሰብ ልጠራ ነው!

፡፡ ለማንኛውም በፍጥነት ወደዚህ ድረስ።

ለሂሶጵ ደውለው ቺፑ እጅህ ላይ ነው? አሉት አይደለም! ሲል መለሰ፤ ወደ ዋናው ማዘዣ አሁኑኑ መጓዝ ይኖርብሀል። የሎጅስቲክስ ኤር ካርጎ ወደ እዚያው ስለ ሚበር በዛው ትሳፈራለህ የኛው ናቸው። ማንም ሰው እንዳያይህ ተጠንቀቅ። አደጋ ውስጥ ነው የከተትከን፤ ካንተ የማይጠበቅ ስህተት ነው የሰራኸው። እሱን እናወራበታለን አሁን ይደውሉልሀል ጠብቅ ብለውት ስልኩን ዘጉት።

ላንግሊ፣ ቨርጂኒያ

የሲ.አይ.ኤ ዋና ማዘዣ

የዲቨኛን ሃላፊው ዊልያም ባር በብስጭት ጠረቤዛውን ይደበድባል፤ ከዚህ በፊት እንዲህ ከቁጥጥር ውጭ ሲሆን አይተውት ስለማያውቁ ሁሉም አንገታቸውን አቀርቅረው

ቆመዋል። አንድ ይሁን ሁለት እና ሦስትም እንደዚያው ዐሥራ ሦስት ሰው ያውም የሃያ አራት ሰዓት ጥበቃ ያላቸው ጉምቱዎች በሀግሪቱ ዋና ከተማ በዚያ ላይ ዳውን ታውን ጥይት ተታኩሰው አመለጡ! አሁን የት እንዳሉ አይታወቅም! በ..ጣ..ም ጥሩ ቀጣይ ማንን ልጠብቅ? ሁሉንም በየተራ ተመለከታቸው አንዳቸውም አልመለሱለትም። ጂም አልባ አገጩን እያሻሸ ተንሳራደደና ያኑኑ ጥያቄ ደገመላቸው! አሁኑኑ ላለፉት ጊዜያት ከማን ጋር ስልክ እንዳወሩ፣ ያወሩበት መንገድ፣ ድምጻታቸው፣ የስልኩ ሲግናል ከየት ይመጣ እንደነበር፣ የስልክ ቀፎ ወይም ሲም ካርድ እየቀያየሩም ከነበር ፍሪከዌንሲ ትሬሰር ተጠቀሙ፤ በየትኛው ሰዓት በተደጋጋሚ ያወሩ እንደነበር፣ ከእነማን እና የት የት አካባቢዎች ይገኙ እንደነበረ፣ እያንድ አንዱ መውጫ እና መግቢያቸው ያለ አንዳች ስህተት በሰርቬላንስ ሪከርድ በድጋሚ ይፈተሽ! ጨርሻለሁ።

አዲስ አበባ

የናቡከደነጾር ቢሮ

ምን እየተከሰተ እንደሆነ ልታስረዳኝ ትችላለህ? አለ ናቡከደነጾር። ባልተለመደ ሁኔታ በካቢኔ አባላቱ ተሞልቶአል ቢሮው። ጀነራል ሠሀረም እንደውም ብዙ መወያየት ያለብን ነገር ያለ ይመስለኛል። ለመጀመር ያህል ግን እንደሚታወቀው ሚቹ ፕሮፌሰር ምሁራንን ወደ ሀገር ቤት በመመለስ ተልዕኮ ውስጥ ነው ከሲ.ኣይ.ኤ ሰዎች በተተኮሰ ጥይት ሕይወቱ ያለፈው። ለቤተሰቡ

መርዶ ለማርዳት የቅርባቸው የነበረን ሰው ነው የላከነው። በእርግጥ እዛ ምን እንደተከሰተ ለጊዜው ሙሉ መረጃ የለኝም። ናቡከደነጾርም ከተቀመጠበት ተነስቶ እየተንጎራደደ የነገሩን ክብደት የተረዳኸው አልመሰለኝም። መንግሥት ለመገልበጥ ህቡዕ ድርጅት ተደራጅቷል እሱም አባል ነበር ነው ያለችው በአደባባይ። ይህ ሕዝቡ ውስጥ ምንድነው የሚፈጥረው ስሜት? ሌላው፤ ድርጅቱ የት ነው ያለው? አባላቶቹ እነማን ናቸው? ስንትስ ናቸው? መሪያቸውስ ማን ነው? አቅማቸው ምን ያህል ነው? ከኛ ውስጥስ ሰው አላቸው ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ይከተላሉ። ሠሀረ እዚህ አካባቢ የሆነ ሽታ አለ ደስ የማይል ምን እና የማን እንደሆነ መደረስ አለበት ደግሞ ይደረስበታል። አንድ ነገር ግን ልጠይቅህ ሰሞኑን ቢሮህ አትገኝም ለምን?

ጀነራሉም ወደ ሀገር ያስገባናቸው ምሁራን በነበሩበት ሀገር መንግሥታት ጥብቅ ክትትል የሚደረግባቸውና ጥብቅ ሚስጥራትን የሚያውቁ መሆናቸው ይታወቃል። በህጋዊ መንገድ ከሀገር ማስወጣት እንደማይቻልም ተወያይተን የወሰንነው ውሳኔ ነው። በመሆኑም አዲስ አበባ ባሉት ኤምባሲዎቻቸው መሰረት እዚ መሆናቸው ከታወቀ ለመንግሥታችንም ለዲፕሎማሲያችንም መልካም እንደማይሆን ግልጽ በመሆኑ እነሱን ከዓለም አቀፉም ሆነ ከሚዲያው ማኅበረሰብ ለጊዜው መሸሸግ አማራጭ አልተገኘለትም፤ ለዚያም ነው ከስምምነታችን ውጭ ወደ ድብቅ ስፍራ እንዲዘዋወሩ የተደረገው።

ቀጣዩ አቅጣጫ መሆን ያለበት እንዴት ባለ ህጋዊ መሠረት ነው ሹመታቸው የሚጸድቀው? ነው እኚህ ምሁራን ለሀገር ያላቸው ፍቅርና ስሜት ምን ያህል እንደሆነ ይታወቃል፤ ስለዚህ መሾም ያለባቸው ለሀገሪቷ ተሀድሶ ትልቅ አስተዋፅዶ ባላቸው ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ መስሪያ ቤቶች ውስጥ መሆን እንዳለበት ተስማምተላል።

እነሱም የትምህርት ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴርና የመሳሰሉት ናቸው። በትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎችም ውስጥ ፕሬዝዳንት ማድረግ እና የመሳሰሉትን ያካትታል። እኚህን ሰዎች ሀገራችን በደንብ መጠቀም ያስፈልጋታል የሚል ጽኑ እምነት እንዳለኝ ይታወቃል። በመሀል የናቡከደነጾር አማካሪ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ይመስለኛል። ያለው ነባራዊ ሁኔታ ጥርጣሬ ይፈጥራል። ሴትየዋ የተናገረችውን ሁላችንም ሰምተናል። እንዲሁ ዝም ብሎ ሥልጣን መስጠት አደጋ ሊኖረው ይችላል በማለት አስተያየት አቀረበ። ቢሮ ውስጥ የነበሩት ባለ ሥልጣናትም ለሁለት ተከፈሉ ግማሹ ችግር የለውም እውቀታቸው ያስፈልገናል ስለዚህ ልንጠቀማቸው ይገባል ሲሉ፤ ቀሪዎቹ ግን በፍጹም ልናምናቸው አይገባም በሚል።

ጀነራል ሠሀረ ንትርኩን በማቋረጥ ሰዎች አንድ ጊዜ እንደማመጥ። ምሁራኑን በምን ያህል እልህ አስጨራሽ መንገድ እንዳግባባናቸው ይታወቃል። እዚህ እንዲመጡና እንዲያገለግሉን የጠየቅናቸው እኛ እንጂ እነሱ አይደሉም። እዚ የሚመጡትም ኑሮን ለማሸነፍ አልያም የተደላደለ ኑሮ ፈልገው አይደለም። ሁሉም ከሞላበት ከተትረፈረፈበት ምድር ነው የመጡት አሉ። ሌላኛው የካቢኔ አባል ቀበል አድርጎ፤ የፕሮፌሰሩ ባለቤት ስለ ተናገረችው ንግግር እውነትነትም ማረጋገጫ የለንም። ምናልባት ስለደነገጠች አዕምሮዋ ኢሉዥን ውስጥ ከቶዋትም ይሆናል። እንደ እኔ እምነት የነጮቹ ሴራም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እንደሰማነው የተኩስ ልውውጥም ነበረ። ከመሀል ደግሞ ጀነራል ሠሀረ ነበር፤ እሱን አይተው ፊቱን አይለዩትም ማለት ቂልነት ይመስለኛል። ያየው ሰው እርግጠኛ መሆን ቢያቅተው እንኳ መጠርጠር ይጀምራሉ። ለመጠርጠር ደግሞ በቂ ምክንያት ይኖራቸዋል። ምናልባትም ከመጠርጠር አልፈው እርግጠኛ ከሆኑ ደግሞ፤ እንዳናምናቸው እና በሆነ መንገድ እኛ ጋር እንደሆኑ ፍንጭ እንድንሰጣቸው

ለሷ ሂደው የተገደለበት ምክንያት ብለው ቢነግሯት ላታምናቸው የምትችልበት ምክንያት አይኖርም። በዚያ ላይ ዜጋቸው እንደሆነች እንዳይረሳ ብሎ ንግግሩን ጨረሰ። ሁሉም በአንድነት ይሄ ልክ ይመስላል በመባባል ተስማሙ።

ናቡከደነጾር ግን ደስ ያላለው ነገር እንዳለ ከፊቱ ይነበብ ነበር። አሁን ስለ ሴቲቱ ምን እናድርግ? ሰዎች! በማለት በቁጣ አዘል ቃና ጥያቄ አቀረበ፤ በዚህም ጉዳይ ሁለት ዓይነት ሀሳብ ተሰነዘረ፤

እንፍቀድላት እንዲሁም በተለይ የመንግስት ሚዲያዎች ጉዳዩን በደንብ እያራገቡ እሳቱ እንዲቀጣጠል እንዲያደርጉ ይደረግ የሚልና በፍጹም አያያዟ መዘዝ አለው ስለዚህ ልክ እንዳልነበረችና ሀዘኗ የፈጠረባት ስሜት እንደሆነ የተለያዩ የፖለቲካና የስነልቦና ባለሞያዎች ትንተና እንዲሰጡበት ይደረግ የሚል ነበረ። ለኛ ይጠቅማል ተብሎ የተመረጠው መንገድ ግን፤ ትቀጥልበት ከኛም መዎቅራዊ እገዛና ድጋፍ ይደረግበት የሚለው ነበር። በምክንያትነትም የተቀመጠው ሕዝቡን የሚያሳትፍና ለውጥ ይገፍ መጥቻለሁ የሚል አካል እንኳን ቢመጣ፤ ሕዝቡ አንተ መጥተህ ልትረግጠን ደማችንን ስላንተ አናፈስም ብሎ አንቅሮ ይተፋበታል በዚ መንገድ እኛ ጥቅም እናገኛለን።

በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንጂ በኃይል ሥልጣን መያዝ ሕዝብን አስፈጅቶ አንባገነን መንግሥት ከመመስረት በቀር ምንም ፋይዳ እንደሌለውና በኃይል የመጣ መንግሥት በፍጹም ዲሞክራሲያዊ ሊሆን እንደማይችል ለሕዝቡ ማሳመን እንዲቀለን ያደርጋል። በዚህም እዚም እዛም እንደ አረም ማጎበረሰቡን ተደግፈው ብቅ ብቅ የሚሉ ቡድኖችን ከስራቸው ማድረቅ ይቀለናል። የሚል ነበር። የመንግሥት የሆኑ በሙሉ የህትመትም የሬዲዮም

የምስልም ሚዲያዎች በልዩ ትኩረት እንዲሰሩበት ትዕዛዝ እንዲሰጥ ይሄም እንዲፈጸም ተወሰነ።

ምሁራኑም ቢሆኑ ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው እና እንዲሾሙ በሚኒስተር ደረጃም የሚሾሙት ፖርላማው ተሰብስቦ ሹመታቸውን እንዲመክርበትና እንዲጸድቅ ይደረጋል፤ ተቃውሞው እንዳይበዛ ይደረግ የሹመታቸው ጉዳይ በዜና ተቀናብሮ እንጂ በቀጥታ ስርጭት እንዳይተላለፍ በዚያን ሰዓት ሲግናል ይቋረጥ ስለሀገራቱ ብዙም የሚያሳስብ አይሆንም እኔ እወጣዋለሁ በማለት ናቡከደነጾር ትዕዛዝ ሰጠ። አክለውም ወደ ኢትዮጵያ የገባችሁበት ሦስት ሆናቹ ፒስትል ብቻ ይዛቹ ከሲ.አይ.ኤ እና ከMI6 ያውም በሀገራቸው ገብታቹ ያመለጣችሁበት መንገድ ግን ግልጽ አይደለም? አከባቢው ላይ ብዙ ጉዳት ደርሷል እንደ ደረሰን መረጃ ስለዚህ ሁኔታው ቀላል አልነበረም ማለት ነው። እዚህ አከባቢ ግልጽ ያልሆነ ነገር አለ ሠሀረ በማለት ጥያቄ ሰነዘረ በድጋሚ።

ጀነራሉም ነገሩ ቀለል ተደርጎ እንዲታይ በመፈለግ ፈገግ በማለት ያው ቴል አቪቭ የነበረችው ምሁር ያለምንም እንከን እንደመጣች ግልጽ ነው። የለንደኖቹም ቢሆኑ መንገድ ላይ ከገጠማቸው ጥቂት እክል በቀር ኤርፖርት አካባቢ ችግር አልነበረም። የኛም ቢሆን እርግጥ ነው ለሌሎች ይከብድ ይሆናል ግን መረሳት የሌለበት የቱንም ያህል በማንም ቢሰለጥን ተራ ኤጀንት እና ጀነራል ያውም ኢትዮጵያዊ እንዴት እኩል ሊሆኑ ይችላሉ? በማለት አድበስብሰው አለፉት። እናም ትኬቶቹ በሙሉ ቀድመው የተዘጋጁ በመሆኑ እክል አልገጠመንም። በእውነተኛ ስማቸው የተቆረጠ ግን አንድም ትኬት አልነበረም ፓስፖርትም ቪዛም እንዲሁ። እንደዛማ ካልሆነ ኑ ተከተሉኝ እዚህ ነኝ እያሉ መደበቅ አለ እንዴ? አሜሪካን እንደምታስቧት መታለል የማትችል ንስር አይደለችም። ይልቅስ እኛን ማታለል እና ከኛ እይታ

ውጭ መሆን አትችሉም እያሉ ስለ ሚደሰኩሩ ቀድመን ስለ ምንሸነፍላቸው እንጂ አውሮፖም ጭምር እንደ ሚሉት አይደሉም እመኑኝ። አቅማቸውን እየካድኩ አይደለም። ግን ደግሞ እንደ ሚሉት ፍጹማን አይደሉም። አሁን ግልጽ መሰለኝ። አሉ ፈግግ ብለው። ይሄ ግን ከልባቸው ይናገሩ ነበር። ናቡከደነጾርም ለዛሬ ይበቃል ክቡራን ብሎ ስብሰባውን ቋጨት።

ከቢሮውም እንደወጡ የደህንነት እና መረጃ ሚኒስትሩን እንዲከተላቸው በእጃቸው ምልክት ሰጥተዉት ወደ መኪናቸ ገቡ። ተከተለኝ የምንወያየው ነገር አለ ሲሉት፤ ሊቁ ሁሉም ከተበተኑ በኋላ እፈልግሀሉ ብሎኛል። በማለት መለሰ። ዛሬ አኳኋኑ አልጣመኝም የሀገር መሪ ሥነ ምግባር ተላብሶ የሁላችንንም ስሜትና ሀሳብ ሲያደምጥና ሲቀበል ነው የሰነበተው። የሚልህን ሁላ በጥሞና አዳምጠህ ስትጨርስ የተለመደው ቦታ በተለመደው ሰዓት እንገናኝ። ብለው ሞተሩን አስነስተው ጊቢውን ለቀው ወጡ።

:::

አይከል የእጅ ስልኳ እረፍት አጥቷል፤ ድምጹን አጥፍታ ስክሪኑን ወደ ሶፋው ደፍታ አስቀመጠችው። የመስመር ስልኳም እንዲሁ እረፍት ሲያጣ እጇታውን አንስታ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው። የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ካደረገችው ንግግር በኋላ ከጋዜጠኞችና በእጅ ስልኳ ከወዳጆቿም የቀረቡላት ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ግራ እንድትጋባ አድርገዋታል። በስሜታዊነት ያደረገችው ድርጊት መዘዙ ከባድ ሆኖባታል። የእኔ የምትላቸው ሰዎች እንኳ ፊት እንዲያዞሩባት ሆነዋል። የመመገቢያ ጠረጴዛው ጋር ሄዳ አንዱን መቀመጫ ስባ ተቀመጠች። የሆነው ሁሉ ዐይኗ ላይ መሰደር ጀመረ። ሀዘኗን በቅጡ ማዘን አለመቻሏ፣ አይዞሽ ባይ የሀዘኗ ተካፋይ አጠገቧ ማጣትዋ ሲታሰባት ሆዷን ባርባር አላት። መንታ መንታ

እየሆኑ እንባዎቿ በዝምታ በመውረድ ፊቷን በሙቀታቸው ያነዱት ጀመሩ። ሲያዩዋቸው እንባ ይምሰሉ እንጂ ግለታቸው የእንባ አልነበረም። ቢነኳቸው ይፋጃሉ። የዘመናት ህመምና የማይሽር ቁስል ውላጆች ናቸውና። በዝምታ ይፍሰሱ እንጂ እንደ ማዕበል ያገኘውን ሁሉ ጠርጎ እንደ ሚወስድ ያለ የሚናወጽ ስሜትን አዝለዋል።

ቤቱን ቃኘችው እንኳን የቤቱ እራስ የሆነ አባወራ የሞተብት፤ ትኩስ ሀዘን ያለበት ሊመስል ቀርቶ ለዘመናት ሰው ጎብኝቶት እንኳ የሚያውቅ አልመስልሽ አላት። የት አለ ለቀስተኛው? የት አለ ሀዘንተኛው? የት አሉ ጓደኞቼ? የት ናቸው ዘመድ አዝማዶቼ? ጭንቅላቷ ይጮህል አጽናኝ ይጠይቃል። መልስ ግን የሚሰጠው አልተገኘም። ባዶነት ወረራት፤ ብቸኝነት ከበባት፤ የሞት መለአክ ፊቷ የቆ መሰላት፤ ውሰደኝ ምን ቆመህ ታፈጣለህ፣ ምን ትጠብቃለህ በላ ውሰደኝ፤ ፈሪ የማይፈልጉህ ጋር ከምትቀላውጥ ይኸው እኔን አትወስደኝም ስትል ጠየቀችው! መላሽ አልነበረም መልሳ ለራሷ መለሰች አዎ ለሚፈልግህማ አትገኝም፤ ትርቃለህ፤ መኖር ለሚፈልግ፣ ለሚጓጓ፣ ደስታ ለከበበው፤ ሕይወት ትርጉም የሰጠችውን ግን እያሳደድክ ትለቅማለህ። ይህ ሁሉ በውስጧ ይመላለሳል። ሀዘኑን መቋቋም አቃታት አፏን ሀሞት ሀሞት ብሏት አቅለሸለሻት፤ ስትነሳም ብዥ ስላለባት ተንገዳግዳ ጠረጴዛውን በእጆቿ ተደግፋ ትንሽ ከተረጋጋች በኋላ አቅም ስላነሳት ወደ ሶፋው በመሄድ እግሮቿን ዘርግታ ዐይኖቿን ጨፈነች። እትዬ እራት ላቅርብ? ምንም አልመለሰችላትም። ደግማ እትዬ ስትል አላስጨረሰቻትም አልፈልግም! ብላ ጮኸችባት። በርግጋ ወደ ውስጥ ተመለሰች። ልጆቿንም ሳታይ እዚያው ጋደም እንዳለች እንቅልፍ ወሰዳት።

⁘⁘⁘

ጄነራል! ሊቁ ምን እንደሚያስብ እራሱ ግልጽ አይደለም። ሁላችሁም ላይ ጥልቅ ምርመራ እና ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ አዞኛል። በተለይ አንተ ላይ ትኩረት እንዳደርግ ደጋግሞ አስጠንቅቆኛል። ቅድም ሀሳብ ሲቀበለን እና ሲያጨቃጭቀን፤ የጋራ ውሳኔ እንደ ወሰንን እንዲሰማን ሲያደርግም የነበረው ሆን ብሎ ነው። ነገሮች ደስ እያሉኝ አይደለም የሚናገራቸውም ነገሮች ደስ አይሉም። በማለት ስጋቱን ነገራቸው። ያንን አስደንጋጭ ትዕዛዝ ግን ብሎ ንግግሩን በማቋረጥ አካባቢውን ቃኘቶ፤ ኢንጂነሩን እንድገድለው የሰጠኝን ትዕዛዝ መቼም አልረሳውም። አሁንም እንደሱ አይነት ትዕዛዝ ለአምስተኛ ጊዜ ሰጥቶኛል። አዎ ቃል በቃል፤ "ኢንጂነሩን በእጅህ እንድታስወግደው እፈልጋለሁ" ያለኝ የንቀቱ ጥግ ደግሞ፤ ፕሮጀክቱስ? ብለው መጀመሪም እኛው ነን የሰቀልነው እንጂ ከሱ የተሻሉ ብዙ ኢንጂነሮች አሉን። ብዙ መረጃዎች እጁ ላይ አሉ አደባባይ ሊያሰጣቸው እየተዘጋጀ እንደሆነም ታውቃለህ ሳይቀድመን መቅደም ይኖርብናል። ምን ታደርጋለህ መሰለህ ሊገሉት የሚፈልጉ አካላት እንዳሉ እንደ ተደረሰበትና እዛ መሆን ለሕይወቱ አደጋ እንዳለው የሚያስረዳው ሰው ትልካለህ፤ ሥራውን ስለ ሚያውቅ እውነት ነው ብሎ ይቀበላል። ወደ አዲስ አበባም እንዲመጣ ምክር ይሰጠው። እዚ ሲደርስ አንተው ጨርሰው። ታዲያ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አሻሚ እንዲሆን አድርገህ ይሁን ነበር ያለኝ።

በቀጣይም የሀገሪቷ የፖለቲካ ምህዋር መቀየር ስላለበት እና ይህም እንዲሆን ከመንገድ መወገድ ያለባቸው አከቲቪስቶች ስላሉ እነሱን ወንጅለን ለማሰር በሚያመች መልኩ አንድ ካልበቃም ሁለት ታዋቂ አርቲስቶች መወገድ ስለሚኖርባቸው እነ ማን መሆን እንደሚኖርባቸው አጣራ። ብሎ ኢንጂነሩን በገዛ እጁ እንድገድለው አርቲስቱንም እንዲያስወግዱት ትዕዛዝ እንድሰጥ ያስደረገኝ ሳያንስ አሁን ጭራሽ ሀገሪቷን ሶሪያ ከተቻለም ቱትሲ እና ሁቱን በሚያስንቅ መልኩ

ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሀገሪቷ ዳግም የማታንሰራራ ነበረች እየተባለች የምትኖር እንድትሆን የሚያደርጉ ጆሮ ጭር የሚያደርጉ ዲያብሎሳዊ አጀንዳዎችን ለሕዝቡ እንዲበተኑ ነው ትዕዛዝ የሰጠኝ።

አሁን ምን ዓይነት ጨዋታ እንደ ጀመረ ግልጽ ነው። ማጽዳት ነው የተያያዘው። ታማኝ ናቸው ያልኳቸውን ሁሉ ያለ ማንገራገር ይፈጽማሉ፤ ሕይወታቸውንም ቢሆን ይሰዉልኛል የሚላቸውን ብቻ ነው አጠገቡ እንዲኖሩ እየፈለገ ያለው። ስለዚህ በምንም ሁኔታ የጥርጣሬ በር እንዳትከፍትለት የጠየቀህን ሁሉ አድርግለት። ለድርጅታችን ላቅ ያለ ድርሻ ስላለህ ቀኝ እጄ እስኪልህ ታመንለት አሉት ጀነራሉ። የአይከል ጉዳይ ያሳስባል በማለትም አከለበት። እንደ ተመለከትነው ነው የሕዝቡ አቀባባል አስደንግጦኛል በዚሁ ከቀጠለች ለእኛ አደጋ አለው ሕዝቡ ለመሪው ሰግዶ ያለ ማጉረምረም ያለ ተቃውሞ እንዲሁ እንዲኖር የሚያደርግ አደገኛ መንገድ ነው የጀመረችው። ምንም እንኳ ሥርአቱንም የወረፈች ቢሆንም። እንዴት ይህን ልታውቅ ቻለች ግን ጄነራል? በማለት ጥያቄ ሰነዘረ። ሂሶጵ ነው የዘከዘከላት። አብሮ አደጉ ስለ ነበር የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶት ነው የሚሆነው። የሆነው አንዴ ሆኖአል ልናስቆማት የምንችልበት መንገድ አለ? ብለው ጠየቁት። በፍጹም አለ።

መልካም አንተም ማድረግ ያለብህን ሁሉ አድርግ። በአስቸኳይ ምሁራኑ ሥልጣን እንዲይዙ መሆን አለበት ሌሎች አባሎቻችንም ትዕዛዝ ይድረሳቸው። በአስቸኳይ ወደ ቀጣዩ ተልዕኮ መሸጋገር ይኖርብናል። ከዚ በላይ ሥልጣን ላይ መቆየት አይኖርበትም። በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ቀጥተኛ የእሱ ትህዛዝ በሆኑ ሴራዎች ምን ያህል ጥፋት ሀገሪቱ ላይ እንደ ደረሰ እያየን ነው። ጊዜ በሰጠነው ቁጥር ሀገሪቷን ያፈርሳታል። ማብቃት አለበት። ይህን ሬስቶራንት እራሱ ሊያሰልል ይችላል። በተደጋጋሚ

የማስጠነቅቅህ ነገር ይህ ነው። በፍጹም ልቡ እንዲያምንህ አድርገው። ካንተ ሌላ የሚያማክረውና የሚያዘው ሰው እንዳይኖር። ተጠንቀቅ። አሁን ስለመሸ ለዛሬ ይበቃናል። ሹመታቸው እንደ ጸደቀ ሁላችንም የቡድኑ አባላቶች ስብሰባ ይኖረናል። በአካል መገኘት የማይችሉም ስላሉ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ስለምናሳትፋቸው። ኔትዎርካቸው ሴኪውር እንዲደረግ ይሁን።

መስቀል አደባባ

ረፋድ 5:00

በመንግሥት በተጠራ ሕዝባዊ ሰልፍ ምክንያት በሁሉም ክፍለ ከተማ በሚገኙ ወረዳዎች በሙሉ ያሉ ነዋሪዎች ሰልፉ ላይ እንዲገኙ በየወረዳው በሚገኙ የመንግሥት ካድሬዎች በኩል፣ በየቤቱ በመዞር ጥሪ ተደርጓል። የውዴታ ግዴታም እንደሆነ ጭምር ተነግሮአል፤ ነዋሪ ግን እንደተለመደው አድርጎአል። የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞችም እንዲገኙ ተደርጓል። ከንጋት አንስቶ በሚጎርፈው ተሳታፊ መስቀል አደባባይ ታፍናለች በሁሉም አቅጣጫ ጠጠር እንኳ መጣያ እስኪጠፋ ድረስ ከሌላ ስፋራ የመጣ ሕዝብ ፈሶ ይታያል። የተለያዩ የመንግሥት አካላት ረጃጅም ዲስኩሮችን ካደረጉ በኋላ የመድረክ መሪው በመቀጠል ከዚሁ ከመሃል ሀገር በቀጥታ ስርጭት በመላው የሀገሪቷ ክፍል እንዲሁም በተለያየ የዓለም ክፍል ለምትገኙ ኢትዮጵያዊያን ወይዘሮ አይከልን ወደ መድረክ እጋብዝላቹሃለሁ በማለት ሲናገር፤

በአድናቆት ጩኸትና ጭብጨባ መስቀል አደባባይ በአንድ እግሯ ቆመች።

አይከልም ምስጋና አቅርባ ንግግሯን ጀመረች። ወገኖቼ ስለ ሰጣችሁኝ ክብር አመስጋኝ ነኝ። ነገር ግን እኔ በየመድረኩና በየዝግጅቱ እየቀረብኩ የፕሮግራም አድማቂ መሆን አይደለም ፍላጎቴ። ይህም ፕሮግራም የተዘጋጀው ለኔ እንደሆነ እረዳለሁ አመሰግናለሁም። ነገር ግን አላማዬን እና ፍላጎቴን የተረዳችሁኝ አልመሰለኝም። እኔ የየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባልም ደጋፊም አይደለሁም። መሆንም አልፈልግም። እኔ ባሏን በከንቱ የፖለቲካ ቅዠት የተነጠቀች አንዲት የሦስት ልጆች እናት ብቻ ነኝ።ይህን ሁሉ የማደርግበት ምክንያትም አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም የሀገሬ ሕዝብ በተለይ ወጣቱ የጥቂት ግለሰቦችን የማያባራ የደም ጥማትና ለማይሞላ የስግብግብነት ስሜታቸው ማሟያነት ሕይወቱን እንዳይገብር ማንቃትና እንዲያስተውል በማድረግ፤ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የደም ጅረቱን መገደብ ሲሆን፤ ይህን እንዲያደርግ የሚገፋፉትን ግለሰቦችም በስም ዝርዝር ጭምር ማጋለጥ ይሆናል። የራሳችን የምንለው ዓላማ ሊኖረን ይገባል ማንም እንደ ፈለገው ባሻው መንገድ ሊመራን አይገባም። ምክንያታዊ መሆን ይኖርብናል።

ቃልን ብቻ ሰምተን ማመን አይገባንም። እርግጥ ነው ጌታን የምናውቀው በቃል ነው በሀዋርያት በኩል በተከተበልን ቃሉም ነው አምነነው ታምነንለት ያለንን ሁሉ ያለ ማንገራገር እየፈጸምን እየመለከነው የምንኖረው። ነገር ግን እሱ ቃል ብቻ አልነበረም ሥጋም ለብሷል፤ ማንም ለማንም መሆን ከሚችለው ባሻገር አድርጎና ሁኖ አሳይቶናል። ለዚያም ነው ሁለንተናችንን እንድንሰጠው ውስጣችን ያለው መንፈስ ዘውትር የሚቃትተው። ሄዋን የእባብን ቃል ሰምታ ትዕዛዝ ሻረች፤ ባሏም የእሷን ቃል ሰምቶ የሞት ሞትን ሞተ። የማንን

ቃል እንደምንሰማ እናስተውል። ቃል ሲሰሙት ጣፍጭ ነው በተለይ የመጥፊያ፣ መዳኛ እማ መራራ ነው። ለጆሮአችን ሲጣፍጠን ቆም ብለን እንመርምረው ብዙዎቻችን በጣፋጭ ቃል ነውና ሕይወታችን የመረረው። ቃል መጥፊያም መዳኛም ነውና።

ለዚህ አይደል በአንዱ የእግዚአብሄር ቃል እልፍ ክርስትና የሚፈለፈለው! ወገኖቼ ቃልን ብቻ ማመን መሰበሪያችንን ነው የሚያፋጥነው። ወደ መጥፊያችን ጥልቅ ጉድጓድ ጫፍ ነው የሚገፋን። ስለ ቃል፣ ስለተዋበ ንግግር፣ በማር ስለተሸፈነ ፍላጎት ከእኛ ከሴቶች በላይ ማን ምስክር ይኖራል? ስንቶቻችን ነን የልጅነት መልካችን፣ የነመራው ሴትነታችን የሚቀሰም አበባ እንዳየች ትጉህ ንብ እያሯሯጠ በስሜት መአበል እያሸቀዳደመ በአመጣቸው አፈ ቀላጤ ወንዶች የተነደፍነው? ያለጊዜዋ እንደ ተቀጠፈች ጽገሬዳ ጠውልጋ ተሰብራ የቀረችዋን ሴት ቤት ይቁጠራት። እሱ ግን መፈጠሯንም እረስቶ ሌላ ባለጊዜ ሌላ የነመራች ሌላ የደረሰች ጽጌሬዳ ሊቀጥፍ ክንፉን ዘርግቶ በማኩበኩብ ላይ ይሆናል። አሁን ሴት እህቶቼና እናቶቼ የማወራው በደንብ ገብቷችኋል።

ምናልባት ወንዶች ያልገባቹ እንደሆን አንተም አንተኛውም ሁላችሁም ቢያንስ በሕይወታችሁ አንድ ጊዜ እንደዚህ አድርጋቹሀል። ያሰባችሁት ከሷ የፈለጋችሁትን ካገኛችሁ በኋላ ዞር ብላቹ እንደ ማታዩዋት እያወቃቹ፤ የልባችሁን በልባቹ አምቃቹ ልቧን ያራራልኛል ስሜቷን ያግልልኛል የምትሏቸውን ውብ ቃላት በመምረጥ ፍላጎታችሁን አሳክታቹሀል። ከዚያም አይንሽ ላፈር ብላችሁ ተሳልቃቹሀል። አሁን ለመወቃቀስ አይደለም። ነገር ግን ነጥቤ ግልጽ የሆነ ይመስለኛል። ፖለቲከኛቹ የሚፈልጉሽ ለዓላማቸው ማሳኪያነት ብቻ ነው። እናንተንም የሚፈልጓቹ ወንድሞቼ ለጥቅማቸው ብቻ ነው። ዓላማቸውን ካሳኩባችሁ በኋላ እንደ ተመጠጠ

ሸንኮራ ያህል እንኳ ቦታ አይሰጧችሁም። ደግሜ እላችኋለው ታሪክ አያስተምራችሁም? ሁሉንም ስንሾማቸው አጨብጭበን ነው። ግን ስንሰነብት እጃችንን በቆረጠው እንላለን። ደግመን ደግሞ ለመሞት እንነሳለን። ታሪክን ያስተዋለ ከጠቢብ ይበልጣል ይባላልና አስተውለን ጠቢባን እንሁን።

ከዚህ በኋላ አንዳችም ኃይል በቃል ደማችንን አያሙቀው። ስሜታችንን አግሎ የእሳት እራት አያድርገን። እኔ እውነታውን ከማሳወቅ ውጭ በየ ቤታችሁ መጥቼ በር አልቆልፍባችሁም ነገር ግን ዓላማ ይኑረን። ለሕይወታችን ትርጉም እንፈልግላት ለኔስ ሕይወት ትርጉሟ ምን ነበር? ጠየቀች፤ ጠሩ ኑሮ? ገንዘብ ነው? ቤት? መኪና? አልባሳት? ጌጣጌጥ? ይሄማ አሁንም አለ ግን ደስታው የታለ? Money can't buy happiness" ሲባሉ But somehow, it’s much more comfortable to cry in a lamborghini than on a bicycle. ለሚሉት ሰዎች እንደው ሰጥቶ ማሳየት ነው። በእርግጥ ለአጭር ጊዜ ሊሰጥ ይችላል። ግን ደስታ ሁሉ ሰላም ይሰጣል ወይ? ያን ስለ ሚያውቁት ነው ለቅሶን የጨመሩበት። ደስታማ በጎጢአትም ይገኛል። "ለጊዜው በጎጢያት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ" ተብሎ በወንጌል እንደተጻፈ። በጎጢያት የሚገኝ ደስታ አለ። መጠጥ፣ ጭፈራ፣ ዝሙት እኚ ደስታን ይሰጣሉ ጊዜያዊ ናቸው። ለምንድነው ብዙ ጊዜ ብዙ መሰዋትነት ክፍለን የደረስንባቸው ህልሞቻችን ስንይዛቸው ባዶ የሚሆኑብን? ህልሞቻችን ችግር አሉባቸው ማለት ነው? አይደለም። መዳረሻው ላይ ትኩረት ስላደረግን እንጂ። መዳረሻ ከጉዞው ሲጣመር ነው ውበቱ። ደስታን ከየት እየፈለግን እንደሆነ እናስተውል!

በቁስ የሚገኝ ደስታ የሕይወትን ትርጉም ሊሰጥ አይችልም። በሕይወታችን ሁለቱ ታላቅ ቀኖች የተወለድንበት እና ለምን እንደ ተወለድን ያወከበት ቀናት ናቸው ይላል ማርክ ትዌን። የእኔ የሕይወት ትርጉም ቤተ ሰቤ ነው። አዎ ስለዚህ ነው አንዱ ሲጎድል ዓለም የጨለመብኝ። የጎደለብኝ ደግሞ አንድ ብቻ አይደለም። የተሰበረ እኔነቴን የጠገነ፤ የድካም ብርታቴም ጭምር ነው የጎደለብኝ። አሁን ቤቴ የቆመው ያለ መሶሶ ነው። ይህ በቤታቹ እንዲገባ ትፈቅዳላቹ? ለእኔ እንዳልቆም የእግር እሳት እንዳልቀመጥ የመቀመጫ ስር የጃርት እሾህ ሆኖ ሰላምም እረፍትም የነሳኝን፤ የልብም የአካልም ቁስል መጠኑን አሁን ላስረዳችሁ አቅም የለኝም። የህመሙ እንፋሎት ካልነካቹ በትክክለኛው መጠን ሊለበልባቹ አይችልም። ስለዚህ እንደ ጨዋታ ልትቆጥሩት ትችላላቹ። ነገር ግን በጥሞና ካዳመጣችሁኝና ካያችሁኝ ታውቁታላችሁ። ቤታችሁ እስኪገባ አትጠብቁ።

እህቴ ልጆቸሽ ወጥተሽ እስክትገቢ ምን እንደሚሆኑ ታውቂያለሽ። ለዘለዓለም ሲያጡሽስ? ባለ ቤትሽስ ምን ይሆናል? አንተስ ወንድሜ ልጆችህና ሚስትህ አንተን አጥተው ለምን እኔ እየተሰማኝ ያለው ህመም እንዲሰማቸው ትፈቅዳለህ? ይህን አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እናቋርጠው ነው መልዕክቴ። አመሰግናለሁ ብላ ዘለግ ያለ ንግግሯን ስትቋጭ፤ ስፍራው መስቀል አደባባይ ሳይሆን ወረርሽኝ ያጠቃት ትንሽዬ የገጠር አውራጃ ነበር የሚመስለው። ያ ሁሉ ሕዝብ ትንፋሹን ውጦ ዝም ጭጭ ብሎ ነበር፤ አይከል ይሄ ሁላ ግድ አልሰጣትም መድረኩን ለቃ አስቀድማ ወደ ነበረችበት መቀመጫ አመራች።

የፕሮግራሙ መሪም በሁኔታው በመደናገጥ። እስኪ አንድ ጊዜ በጭብጨባ እንሸኛት በማለት የያዘውን ማይክ መታ መታ ማድረግ ጀመረ። መልስ ግን አልነበረም።

ግማሹ አጠገቡ ካለው የሰፈሩ ሰው አልያም ከመስሪያ ቤት ወዳጁ ጋር የአይከልን እውነተኛነት ያደንቃል ልክም እንደሆነች ይመሰክራል። ሌላው ንግግሯ አብዛኛው ቢዋጥላቸውም ሕዝቡን ለማደንዘዝ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ነው ማለት ጀምሮአል። የተቀረው የንግግሯ ልቡን ሰባብሮ ራሱን ቤተሰቡን ሕይወቱን መቃኘት ጀምሯል። ከረጅም አስፈሪ ጸትታ በኋላ አንዲት ወጣት ተነስታ የአይከልን ስም እየጠራች ታጨበጭብ ጀመር። የተቀሩትም ከራሳቸው እና ከወዳጃቸው የጀመሩትን ውይይት ገታ አድርገው ተከተሏት። ያ ሁላ ሕዝብ በአንድ አይነት ዜማ ስሟን እየጠራ ሲያጨበጭብ አንዳች ስሜት የሚፈጥር ድባብ ነበረው። ለደቂቃዎች ቀጠለ። በመጨረሻም የፕሮግራሙ ፍጻሜ ሆነ።

:::::::

እድል እንዲሰጣትና በቀጥታ ስርጭት መልዕክቷን ግልጽ አድርጋ እንድታስተላልፍ በተደጋጋሚ ጥያቄ ብታቀርብም ይሁንታን ተነፈገች። ተስፋ በመቁረጥም ስልኳን አጥፍታ ቤቷን ዘግታ ተቀመጠች።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፓርላማ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዬ ሆን ተብሎ እንዲረዝም እና በሀገሪቱ መገናኛ ብዙሃን ቀጥታም ቢሆን በቴክኒክ ብልሽት በሚል እየተቆራረጠ እንዲተላለፍ እየተደረገ ባለው ጉባኤ በተለያዩ የሀገሪቱ ጉዳዮች የምክር ቤቱን አባላት ሲያወያዩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻም በናቡከደነጾር የቀረቡትን እጩዎች የስም ዝርዝር፤ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ እንዲያብራሩ ለናቡከደነጾር እድል ሰጡ።

በድጋሚ አመሰግናለሁ። የተከበሩ አፈ ጉባኤ። እንደ ሚታወቀው ሀገራችን በሚያስደንቅ እና እጅን ከአፍ ላይ በሚያስጭን ፍጥነት ወደ ለውጥ ጎዳና እየተምዘገዘገች እንደምትገኝ እሙን ነው። በአመራሮቻችን የላቀ ትጋትና ዕውቀት ለሀገርም ባለን ከፍተኛ ፍቅርና ክብር፤ በተለይም ሲያድርብን በከረመ ኢትዮጵያን ታላቅ የማድረግ ቁጭት እየተገፋን እና የሕዝባችንን ድጋፍ በመያዝ በዚች ጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ ሰርተናል። ተቋማትን ከመንግሥት ቀጥተኛ ተጽኖ ለማላቀቅም የተከፈለው ዋጋ ቀላል አይደለም። ያፈጀና ያረጀ ስር ሰዶ የተወሳሰበ ሥርዐትን በአንድ ለሊት ማጽዳት አይታሰብም። በዚህም ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ሥራችንን አጠናቀናል ማለት አይደለም። ነገር ግን ብዙ ርቀት ተጉዘናል። እያንዳንዱ ወንበር ላይ ተገቢው ባለ ሞያ እንዲቀመጥበት እየተደረገ ይገኛል።

በዚህም መልካም አስተዳደርን መፍጠር እንደሚቻል እናምናለን። በመሆኑም ከባድ መሰዋዕትነት በመክፈልም ጭምር ከባህር ማዶ ሳይቀር ሀገራቸውን ይጠቅማሉ፣ ኢትዬጵያን መልሶ ታላቅ በማድረግ ጉዞዋችን ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፤ ብለን ያመንባቸውን ምሁራን ወደ ሀገር ቤት መልሰናቸዋል። አንድ አንዱም በባህር ማዶ የተወለዱ ነገር ግን ምስጋና ለቤተሰቦቻቸው ይሁንና ሀገራቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን እና ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ለሀገራቸውም ጥልቅ ፍቅርና ክብር ያላቸው ናቸው። ይህን ካልኩ ዘንድ የተከበረው ምክር ቤት በጥሞና አድምጦና መርምሮ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ እጩዎቹን ወደ መዘርዘር እገባለሁ።

1ኛ. ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ በንቲ፤ የተወለዱት በምዕራብ ወለጋ ነቀምት በምትባል ከተማ በ1949 ዓ.ም ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪአቸውን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፤ ማስተርስ በኢኮኖሚክስ እንዲሁም ፒ.ኢች.ዲአቸውን በፋይናንስ ሰርተዋል። በዩኒቨርሲቲ አፍ ዋሽንግቶን በኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት ውስጥ ለበርካታ ዓመታት በመምህርነት አገልግለዋል። በተጨማሪም ላለፉት ስድስት ዓመታት ለከተማዋ ከንቲባ የኢኮኖሚ ዘርፍ አማካሪ ሁነው አገልግለዋል። በዚህም መሰረት የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስተር እጩ አድርጌ አቅርቤአቸዋለሁ።

⁜⁜⁜

አሜሪካን ኤምባሲ

አዲስ አበባ

የተልዕኮ ክፍል ምክትል ሀላፊው ከሌሎች አራት የኤምባሲው ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ወደ አምባሳደሩ ቢሮ ገቡ። አምባሳደሩም ግራ በመጋባት ቁጭ ካሉበት በዝምታ ይመለከታቸዋል።

ፓርላማ ውስጥ በታዛቢነት ከተመደቡት አፊሰሮቻቸን በተሰጠን መረጃ መሰረት አንድ ላይ እንድንመለከት ቲቪው ይከፈት ብሎ ሬሞቱን ከጠረጴዛ ላይ አንስቶ ወደ ቻናሉ ኮኔክት በማድረግ ከፈተው። ይህ ጉዳይ ወደ ቨርጂንያም ደርሶአል ሁሉም እየሰሙ ያሉትን ማመን አቅቷቸዋል። ሌሎችም እየመጡ ስለ ነበር ሰፊ ይመስል የነበረው የአምባሳደሩ ቢሮ ለመቆሚያ እንኩዋን እየጠበበ መጣ።

:::::::

ዲግሪዋን በፖለቲካል ሳይንስ፤ ማስተርሷን በኢንተርናሽናል ሪሌሽን እንዲሁም ፒኤችዲዋን በፐብሊክ ፖሊሲ አጠናቅቃለች። በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችም በተለያዩ ኃላፊነቶች አገልግላለች። በዚህም መሰረት የፌዴራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስተር እንድትሆን በእጩነት አቀርባታለሁ።

⁂⁂⁂

⁜⁜⁜

4ኛ. ዶክተር አጽሎስ ለይኩን፤ ክቡራን የዚህ ምክር ቤት አባላት እንደምታውቁት ይህ ግለሰብ የቀድሞውን መንግሥት ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ የመብት ጥሰቶች በብርቱ በማስረጃ እና በመረጃ ሲሞግት የኖረ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ የተወጣ ጉምቱ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነው። የተወለደው በ1976 በውቧ የበረሃ ገነት በድሬዳዋ ከተማ ሲሆን በመጀመሪያ ትምህርቱን ያጠናቀቀው ልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት የደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ፤ ወደ መቐለ ዩኒቨርሲቲ በማምራት የመጀመሪያ ዲግሪውን በሕግ ከሰራ በኋላ በድሬዳዋ መስተዳደር ውስጥ የድርሻውን አገልግሎት እየተወጣ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ማስተርስ አግኝቶአል። ከቀድሞው መንግሥት ጋር በነበረው ቁርሾም ከሚወዳት ሀገሩ ተሰዶ እንደ ብዙሃኑ ጓደኞቹ በባእድ ሀገር ከርሞዋል። አሁን ግን የእናት ሀገሩን ጥሪ ተቀብሎ ሊያገለግላት ከተፍ ብሎአል። እኔም ዛሬ በፍትህ ሚኒስተርነት ሹመት እጩ አድርጌ ሳቀርበው ኩራት ይሰማኛል።

5ኛ. ፕሮፌሰር ዛሪየስ ለገሰ ትውልዱም እድገቱም በዩናይትድ ኪንግደም ዋና ከተማ በሆነችው ለንደን ውስጥ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪውን በዶክተር አፍ ሜድስን ከአከስፈርድ ዩኒቨርሲቲ ያግኘ ሲሆን፤ በሳይካትሪ ስፔሻላይዝድ አድርጎዋል። በርካታ የምርምር ጽሑፎችን ጨምሮ ለበርካታ ዓመታት ብዙ ዶክተሮችን በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ለማዕረግ አብቅቷል እናም ዛሬ የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስተር በማድረግ ለእጩነት አቅርቤዋለሁ

6ኛ. ኢንጂነየር አሜናዳብ መስፍንም እንዲሁ ትውልዱም እድገቱም በባእድ ሀገር ቢሆን ለኢትዮጵያ ያለው ፍቅር እና ቦታ በቃል የሚገለጽ አይደለም። በሚሺገን ስቴት በምትገኘው ዲትሮይት ከተማ ተወልዶ ያደገው ይህ ወጣት ይማር ከነበረበት ዲትሮይት ካንትሪ ደይ የደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ፤ በዘርፉ ከመላው አሜሪካ ቁጥር አንድ ወደ ሆነው ወደ ማሳቹሴትስ የቴክኖሎጂ ተቋም በማምራት በሲቪል ኢንጂነሪንግ ዲግሪውን ከሰር በኋላ በስትራክቸራል ኢንጂነሪንግ ማስተርሱን እንዲሁም ፒ.ኢች.ዲውን አግኝቶአል። በሀገሪቱ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት መስሪያ ቤት ቁልፍ ሚና ሲያበረክት የነበረ ወጣት ነው። እናም ይህን ከግንዛቤ በመክተት እንደ አዲስ ለተዋቀረው ለኢንፎርሜሽን፤ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስተር እጩነት የቀረበውን ይህ ወጣት ምክር ቤቱ በደንብ አጢኖ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ እጠይቃለሁ።

7ኛ. ዶክተር ወልደአብ ወልደማርያም የተወለዱት ዐሥራ ሁለት አውራጃዎች በነበሯት እና የወሎ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ በነበረችው ደሴ በ1948 ሲሆን፤ የመጀመሪያ ዲግሪአቸውን በናቹራል ሪሶርስ ማናጅመንት፣ ማስተርሳቸውን በሩራል ዴቭሎፕመንት ሰርተዋል። የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስተር እንዲሆኑም በእጩነት ቀርበዋል።

8ኛ. ፕሮፌሰር ናኮር ሰገን የተወለደው በ1955 በናዝሬት ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪውንም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መስራት የቻለ ሥራ ፈጣሪ፣ የዩኒቨርሲቲ መምህር እና የነጻነት ታጋይም ጭምር ነው። በተጨማሪም ወደ አሜሪካን በማቅናት ከስቴት ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኒዮርክ በኢኮኖሚክስ ዲግሪ ያለው ሲሆን ፒ.ኤች.ዲውንም በኒውዮርክ ከተማ ከኒው የማህበራዊ ጥናት ትምህርት ቤት በኢኮኖሚክስ አግኝቶአል። ዛሬም በትምህርት ሚኒስተርነት ሀገሩን ያገለግል ዘንድ እጩ አድርጌ አቅርቤዋለሁ። እናም ክቡራት እና ክቡራን አሁን በእጩነት የቀረቡት ውድ እና እንቁ የሀገራችን ልጆች የያዝነውን የእድገት ጎዳና ሊቀላቀሉ በዕውቀት እና ልምዳቸውም ሊያገለግሉ ሊደርስባቸው የሚችልን አደጋ ችላ ብለው ከእራሳቸው ሀገራቸውን አስቀድመው እዚህ ተገኝተዋል። እናም ይህን ተረድተን ከነናቸው ልንቆም ይገባል እላለሁ አመሰግናሁ።

አፈ ጉባኤውም አመስግነው የቀረቡት እጩዎች ላይ ቅሬታ እንዲሁም አስተያየት ከኖራቸው በሚል ለምክር ቤቱ አባላት እድል ሰጡ። ጥቂት እጆች ብቻ ስለነበሩ የመጀመሪያውን እድል ከተቀመጡበት ረድፍ ብቸኛ ለነበሩት ወይዘሮ ሰጡ። እሳቸውም ይህን ሹመት በማሰባቸው ከባድ እና ረጅም የምስጋና ቃላትን በመጠቀም ናቡከደነጾር ከመጣ ጀምሮ ያሉ ለውጦችን መዘርዘር ጀመሩ ረጅም ደቂቃም በዚሁ መንገድ ከወሰዱ በኋላ አፈ ጉባኤው ጣልቃ በመግባት የማጠቃለያ አንድ ደቂቃ ተጨማሪ ፈቀዱላቸው።

ከተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች ከነበሩት ለአንደኛው ነበር በመቀጠል እድሉን የሰጡት። እሳቸውም ቀደም ሲል እድል አግኝተው የነበሩትን የምክር ቤት አባል በመወረፍ ነበር ንግግራቸውን የጀመሩት። ቀጥለውም ሹመቱን እንደሚቃወሙ በመግለጽ ማብራራት ጀመሩ። ክቡራን ይሄ እራስን የመናቅ አባዜ ከመች ጀምሮ እንደተጠናወተን መች እንደ ሚለቀን ማሰብ በጀመርኩ ጊዜ ከአቅሜ በላይ ስለ ሚሆንብኝ ያጥወለውለኛል ያዞረኝማል ጭምር ሲሉ አዳራሹ የሳቅ ድምጽ አስተጋባ።

የሚያስቅ ነገር የተናገርኩ አልመሰለኝም! በዚህ ነቀርሳ ተነድፈናል የኛ የሆነን ሁሉ ከአፈር የመደባለቅ አባዜ እደ ጥበብ በኛ ልጆች ሲሰራ ፋቂ፤ ህክምና ሀገር በቀል ሲሆን ስር ማሽ ቅጠል በጣሽ፤ የምንኖርበትን ልጅ ወልደን ዐይናችንን በዐይን ያየንበት፣ ወልደን ከብደን የኖርንበትን፣ ከረምቱን፣ በጋውን፣ መአልቱን፣ ጽልመቱን፣ ቆፉን፣ ሀሩሩን የተሸሸግንበት፤ ማጣት ማግኘቱን ያሳለፍንበት፤ ተጣልተን የታረቅንበትን ቤት የሰሩልንን ባለሞያዎች የኛው ሲሆኑ ከመጤፍ የማንቆጥራቸው፤ የልፋታቸውን ዋጋ የምንነፍጋቸው አናጢዎች ከነጮቹ ከሆኑ ክቡራን መሀንዲሶች፤ አንድ ታዳጊ ከሀ እስከ ፐ በቃል ከሚያነበንብ እየተኮላተፈ አስር ጊዜ ስቶ በዐሥራ አንደኛው ሙሉውን ABCD ቢጨርስ ያን ጊዜ ተማረ ይባላል። አምስት እና ከዚያ በላይ የሀገር በቀል ቋንቋ አቀላጥፎ ከሚያወራው ይልቅ አንድ የእንግሊዝ ቋንቋ የሚናገረው ነው ምሁር የሚባለው፤ ምሁር ለእናንተ ማን ነው? ለኔ ምሁር የመጣበትን የሚያውቅ በኋላ ታሪኩ የማያፍር ከፉን ለመማሪያ ከትቦ አስቀምጦ ደጉን ይዞ የሚጓዝ የእነሱ ሳይሆን የኔ የሚለው፣ ማንነት፣ ባህል፣ ወግ፣ የኑሮ ዘይቤ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ጥበብ፣ ታሪክ ያለው። ይህን ጠንቅቆ የሚያውቅ እንኳን አንድ እራሱን ቤተ ሰብ እና ቀዬ መምራት የሚችል ሴቷም ባህል፣ እምነት፣ ወጓን በክብሯ ጠባቂ ለቤቷ ማገር፣ ለልጆቿ ኩራት፣ ለባልዋ ፈርጥ ስትሆን ነው። ምሁር

መሆን ፊደል መቁጠር ማለት አይደለም እንደዛ ብለን ሁሉን ዜጋ አስቆጠርነው፤ ሳናጣራ ተቀብለን ሳናበጥር አስፈጭተን ይኸው ማጣፊያው አጠረን። ክቡራን ለራሳችን ክብር መስጠት ካልጀመርን የራስ እየጣሉ የሌላ ከማንገስ አዙሪት ውስጥ ካልወጣን በራሳችን ልብስ ማጌጥ ኋላ ቀርነት ከመሰለን በማንነታችን ካፈርን ከዚህ መቼም አንወጣም መድኃኒቱ በእጃችን ነው ይመራል ተብሎ አይሞትም…

መሀል በመግባት አፈ ጉባኤው እንዲያጠቃልሉት አንድ ደቂቃ እፈቅዳለሁ ሲሉ፤ እሳቸውም ምኑን አጠቃለልኩት በዚሁ ላብቃ አመሰግናለሁ በማለት ማይኩን አጠፉ። እሺ በመቀጠል ወደ ድምጽ አሰጣጥ ሂደት እናመራለን በማለት ምርጫውን አከናወኑ ሁሉም ሙሉ ድምጽ አገኙ፤ ቀርበውም መሃላ ፈጽመው ጉባኤው ተበተነ።

የፓርላማው መውጫ ከፍተኛ ሁከት ማስተናገድ ጀመረ

ከኤም.አይ6፣ ሲ.አይ.ኤ እና ሞሳድ የተውጣጡ ስምንት ኤጀንቶች በሰዓቱ የፓርላማውን ጊቢ ይጠብቁ ከነበሩ የሪፐብሊካን ጋርዶች ጋር እሰጣ ገባ ውስጥ ገብተዋል። የተሰጣቸውን ልዩ የይለፍ ፈቃድ በመጠቀም ተሽከርካሪያቸውን በሚገባ ሳያስፈትሹ የገቡት ኤጀንቶች፤ አምስቱ ከተሽከርካሪያቸው ውስጥ FN P90 ዘመናዊ መሳሪያ በማውጣት በአራቱም አቅጣጫ ለማጥቃት እና ለመከላከል በሚያመች ሁኔታ ጀርባ ለጀርባ በመሆን በተጠንቀቅ ሲቆሙ፤ የተቀሩት ወደ ፓርላማው አዳራሽ መግቢያ በር በማቅናት ላይ ሳሉ ከሪፐብሊካን ጋርዶቹ አዛዥ በተደጋጋሚ የሚሰጣቸውን የቁሙ ትህዛዝ

ባለመቀበላቸው ሁለት ጊዜ ወደ ላይ ተኮሱ። አዳራሽ ውስጥ ያሉት ተሰብሳቢዎች ምን እንደ ተፈጠረ ሳያውቁ ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲታገሱ ተነገራቸው።

ስምንቱንም ኤጀንቶች ባሉበት በሁለት ክበብ እየከበቧቸው ቀለበቱን እያጠበቡ የሚመጡትን ጠባቂዎች ሲያዩ፤ እነሱም ቅርርባቸውን እያሰፉ የከበባውን ስፍራ ለማስፋት እና ከለላ ለማግኘት እንዳነጣጠሩ በክብ ቅርጽ መበተን ጀመሩ። አዛዡም ምን ለማድረግ እንደፈለጉ ስለ ተረዳ የመጀመሪያ ዙር ከባቢዎቹን ፍጥነት እንዲጨምሩና ስፍራውን እንዲያጠቡት ትዕዛዝ ሰጡ።

ስምንት ሆነው በማን አለብኝነት የመጡት ኤጀንቶች ምንም አይነት የጦርነት ስልት ቢጠቀሙ ምንም አይነት አቅም ቢኖራቸው ከዚህ ቀለበት እንደማይወጡ የተረዳው አንደኛው ከመካከላቸው ከነያዘው መሳሪያ እጁን ወደላይ ሰቀለ፤ አንደኛውም ደገመ። ሌሎቹ ግራ በመጋባት ሲተያዩ ከመሀል አንደኛው አዛዡ ላይ ለመተኮስ ፈንጠር ሲል የቡድኑ መሪ አስቁሞ given the hypocritical nature of the decision, we are left with no viable options but to surrender. ሲል ሌላኛውም ቀበል አድርጎ Ya! Guys That Deceitful decision has painted us into a corner. Surrender is now our only recourse ብሎ የያዘውን መሳሪያ መሬት ላይ አስቀመጠው ሌሎቹም እንደዚያው አደረጉ።

እጆቻቸውን በካቴና አስረው ሊደርስ ካለው ጥፋት ስፍራውን ተከላክለው ወደ ብሄራዊ ደህንነት ቤሮ ወሰዷቸው ተሰብሳቢዎችም ምን እንደተፈጠረ ሳይረዱ ውስጥ በጋራ ኢ-መደበኛ የሆነ ውይይት እንዲያደርጉ ተደርጎ ስለ ነበር አሁን እንዲወጡ ተደረገ። አዳዲሶቹ ተሿሚዎችም በከፍተኛ ጥንቃቄ ወደ ተዘጋጀላቸው ጊዚያዊ ስውር ከፍተኛ ጥበቃ ወደ ሚደረግበት እጅግ ሰፊ ቪላ እንዲያቀኑ ተደረገ።

የሪፐብሊካን ጋርድ ኃላፊ፣ የደህንነት ቢሮ ሀላፊው፣ የናቡከደነጾር አማካሪ፣ ጄነራል ሠሀረ እና ሌሎችም እዛው አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበዋል ሁሉም በንዴት በቁጭት ፊታቸው ቀልቷል። ጄነራል ሠሀረም ይህ ጉዳይ ከዚህ አዳራሽ በጭራሽ መውጣት የለበትም፤ ጠባቂዎቹም ቢሆኑ ለራሳቸውም ጭምር ደግመው መናገር የለባቸውም። ይህ የድፍረት ጥግ ነው የንቀት መጨረሻ፤ ማነት ማስኮብለል ያለ ነው ነገር ግን አንድ ሉአላዊ የሆነች ሀገር ውስጥ ፓርላማ ድረስ ታጥቆ ገብቶ ከመንግሥት መፋጠጥ ይህ ተቀባይነት የለውም።

ዛሬ በዚህ ዝም ካልናቸው ነገ ከዚህ በላይ እንደ ማያደርጉ ምን ማረጋገጫ አለን? መቀጣጫ መሆን አለባቸው! ያውም ለሚያስብ አካል ዘግናኝ የሆነ መቀጣጫ። እኛው ነን እዚህ ደረጃ ያደረስናቸው፤ ከኛ በላይ በሀገራችን ነጻነትና ሥልጣን የሰጠናቸው፤ ጓዳችንን ከፍተን ሚስጥራችንን ሁሉ የዘረገፍንላቸው፤ ጥፋቱ የኛው ነው። ሕግ እና ሥርዐት ሊኖር ይገባ ነበር። አሁንም አልረፈደም እስቲ ልብ ብላችሁ አጢኑ ምን ያልሰጠናቸው ሥልጣን አለ? እኛን ወክለው እንደ መንግሥት መግለጫ መስጠት እና በግልጽ ሀገሪቷን ማስተዳደርን ብቻ ነው የነፈግናቸው። እኛን መስለው ሳይሆን እኛን በልጠው እንዲኖሩ አይደል እንዴ ያደረኛቸው? አንድ የውጭ ዜጋ ከእኛ ልጅ ጋር ቢጋጭ

ማንን ነው ጥፋተኛ የምንለው? ፈላጭ ቆራጭ፣ ፖሊሲ አርቃቂ፣ ሸዋሪ እነሱ፤ ይኸው ለዚህ ደረሱ ይበቃል ከዚህ በኋላ ይበቃል። ይህቺ ሀገር በራሷ ልጆች ሕዝቦቿን በመሰለ ሀገር በቀል ብልሀት እና ጥበብ መመራት መጀመር አለባት ምናም ሉአላዊት የማትመስል ሀገር ከሆነች ሰንብታለች።

በእጅ አዙር እጁን የሚጠመዝዟትን በግልጽ እጃቸውን መጠምዘዝ መጀመር አለብን! እኚህ ሀገራት ኢትዮጵያን ከጠቀሟት የጎዷት ይበልጣል። አሁን የገጠሙን ውጥንቅጦች በሙሉ የእነሱ የሴራ ፖለቲካ ውጤቶች አይደሉም? ምን ያህል እንደናቁን የሚገባችሁ የሚጽፉትን ጽሁፍ እና የሚያሳትሟቸውን የምርምር ውጤቶች ስትከታተሉ ነው። እርስ በእርስ እንዳንተማመን፣ በበሬ ወለደ ትርክት ስር የሰደደ ጥላቻን በራሳችን ልጆች አንድ ፍሬ ገና ነፍስ ያላወቁ ልጆቻችንን እየጋቱ ሲያሳድጉ ዝም ብለን ዐየናቸው። ይኸው ዛሬ ፍሬዋን እየለቀምን ነው። ኢትዮጵያ እኮ ስሟ ብቻ ነው የተረፈው ምኗ እሷን ይመስላል? ዜጎች ለድርጅቶቻቸው ከሚሰጡት ስያሜ እንነሳ ትምህርት ቤቱን፣ መዝናኛ ቦታዎችን፣ መመገቢያ ስፍራዎችን፣ ሀገሩን ሁሉ ተመልከቱ አንድ የአውሮፓ ከተማ ውስጥ እንጂ ሀገራቹ ውስጥ ያላቹ አይመስላችሁም።

የራሱ ማንነት፣ ባህል፣ ስነ ልቦና፣ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ሕግ እና ሥርዐት በአጠቃላይ የራሱ የኑሮ ዘይቤ የሌለው ማኅበረሰብ እንደ ማኅበረሰብ መዝለቁ ያጠራጥራል በፍቃዱ ቀኝ እንዲገዛ አድርገነዋል። ወገናችንን ተገዝተን በነበር እሱ ይሻለን ነበር እያለ የሚከራከሩ ወጣቶችን ከማየት ሌላ ምን ኪሳራ አለ? የነጻነት ትርጉም፣ ማንነት፣ ክብርና ኩራት የማይገባው እልፍ ወጣት አፍርተናል። ለማንኛውም ማስወገድ ካለብንም ሁሉን በአንድ ምሽት ጠራርገን እስከ ማባረር የሚደርስ ቆራጥ ውሳኔ መወሰን

አለብን ብለው ዝም አሉ። ሌሎቹ በሳል ሊያስብል ይችላል ያሏቸውን ሀሳቦች በየተራ ሰነዘሩ። ናቡከደነጾርም በጥልቀት ተወያይተን የምንደርስበት ውሳኔ ይኖራል ለአሁኑ ሁሉም ባለበት ይቀጥል በማለት የደህንነት ቢሮ ኃላፊውን አቶ ፊንሐስ አስከትሎ ወጣ። ጀነራል ሠሀረ በዚያች ሰዓት ዐይን ውስጥ ገቡ።

Hyatt Regency

ማለዳ

አኪያ ማልዳ የወጣችውን ፀሐይ ተከትላ በዚሁ ሆቴል ከያዘችው King Bed Garden View Balcony ማረፊያ ለመሞቅ እንዲመቻት Hibiscus Dream Bandeau Ring Cut Out በመባል የሚጠራውን ስስ የበጋ ቀሚስ ለብሳ፤ ቀጭን ሳንድል ተጫምታ ወደ መዋኛ ገንዳው በማምራት በግራ ጥግ ካሉት pool side chairs አንደኛው ላይ ጋደም አለች። የፊት ሰውነቷ በቂ ፀሀይ እንዳገኘ እርግጠኛ ስትሆን ጀርባዋን ለማስመታት ስትገለበጥ ያየችውን ማመን አቃታት፤ የሎቢው ፊት ለፊት ከአንድ ነጭ ሴት አጠገብ የተቀመጠውን ወጣት ረጅም ጊዜ ወስዳ አየችው።

አዎ እራሱ ነው ብላ በደመነፍስ ተነስታ ሄደች፤ ያ የልጅነት መልኩ በወጣት ተቀይሯል ይበልጥ ወንዳወንድ መልከ መልካም ሆኗል። እርሱ እንደሆነ አታሞ የሚመታው ልቧ ነግሯታል፤ ጭንቅላቷ ግን ማረጋገጥ እንዳለባት ይነግራታል። ትኩር ብላ በስስት ስታየው የግራ ጆሮውን ሦስት ጊዜ በከብ ቅርጽ ሲያሽ ስሜቷን

መቆጣጠር አቅቶዋት ፍጥነት ጨመረች፤ አጠገቡ ልትደርስ ስትል እራሷን ቆጠብ አድርጋ ጸጉርዋን በሁለቱም የእጇ አስር ጣቶች እያበጠረች በግራ እና በቀኝ ትከሻዋ ላይ ዘረገፈቻቸው። በቄንጥ እየተራመደች ቴራስ ብላ ልብ በሚያስደነግጥ ሴተኛ በሆነ ቅላጼ ስሙን ጠራችው።

ከገባበት ሀሳብ በመባነን ቀና ብሎ አያት ረጅም ዝምታ ግራ ተጋብቶ ይሆናል በማለት፤ አኪያ ነኝ የልጅነትህ ብላ ፈገግ አለች፤ ሳያስበው ብድግ አለ ግን ባለበት ደንዝዞ ቀረ አብራው የተቀመጠችውን መልከ መልካም ነጭ ወጣት ሰላምታ ሰጥታት ወደ እሱ ዞረችና ቆንጅዬ ናት ብላው፤ ለማንኛውም ስላቋረጥኳቹ ይቅርታ እዚሁ ስለሆንኩ እንገናኛለን ብላው በቄንጥ እየተራመደች ወደ መጣችበት ተመለሰች።

ከዐይኑ እንደተሰወረች ወደ ክፍሏ ለመግባት በፍጥነት መራመድ ጀመረች የእንግዳ መቀቢያው ክፍል እንደደረሰች ከማረፊያው ተቀመጠች፤ ለምን አላቀፍሽውም? በቅጡ እንኳን አላወራሽውም ሌላው ይቅር ሌላ ቀን እንኳን ለመገናኘት ኸረ ለማውራትስ ቢሆን ቁጥርሽን አልሰጠሽው ወይ ቁጥሩን አልተቀበልሽ፤ አድራሻ አልተለዋወጥሽ እያለ ሀሳቧ አጣደፋት። ዘለግ ላለ ጊዜ እንዲህ ስታሰላስል ቆየች፤ እንዴ ሴት እኮ ነኝ ሄጂ ማናገሬ ሳያንስ ደግሞ ብላ ብድግ አለች፤ ዙሪያዋን ከቃኘች በኋላ ትኩረት ያደረገባት እንዳልነበር አረጋግጣ ወደ ማረፊያዋ አቀናች።

ቴራስን አብራው የነበረችው እንግዳ ከዚህ ክስተት በኋላ ቀልቡን መሰብሰብ እንደከበደው በመገንዘብ ቀጠሮአቸውን ወደ ማታ በማዘዋወር ተለየቸው። በተቀመጠበት ደቂቃዎች ነጎዱ። እንዴት አስታወሰችኝ? ይህ ሁላ ጊዜስ እንዲያ ስፈልጋት የት ተደብቃ ነበር?

በአግባቡ እንኳ ሰላም አልተባባልንም አዎ ዐይኗ እንጂ ልቧ እረስቶኛል ስታልፍ በመንገድ ነው እንዲሁ ሰላም ያለችኝ ባይሆን ኖሮ ቁጥር እንኳ እንቀያየር ነበር፤ ቢያንስ አድራሻዋን ታሳውቀኝ ነበር። እዚህ እንደሆነች ነግራኛለች አንተስ ምን አደረግህ እሷው መጥታ እሷው አውርታህ ሁሉ ነገር እሷ እያለ ከራሱ እያወራ ወደ እንግዳ መቀበያው አመራ።

የሚፈልገው ሰው እንዳለ እና መረጃ በመስጠት እንድትተባበረው ባለሞያዋን ጠየቃት ረጋ ባለና ትህትና በተሞላበት መልኩ ይህን ማድረግ እንደማትችል እና ፕሮቶኮሉም እንደማይፈቅድ ነገረችው። እሱም መታወቂያውን አሳይቶ ሊያስገድዳት አሰበና መልሶ ተወው አመስግኖ ወጣ። መኪናውን ወደ አቆመበት በመሄድ ቀጥታ ወደ ቤት አመራ። እንደለመደው ለአመል ያህል ሙዚቃ ከፈተ ግን የሚሰማ ጆሮን አልያዘም።

እየተንጎዳጎደ ሀሳቡን ቀጠለ ሰው እንዴት እንደ ወይን እያደር ይጎመራል? መተንፈስ እስካልችል ለስላሳ ድምጿ በጆሮዬ አልፎ ልቤን ነረተው መናገር ማሰብ እስኪያቅተኝ ውበትዋ በቅጽበት እንደ ቢጋ መብረቅ መላ አካሌን ፈጀው። እየራቀችው ስትመጣ ቅድ ቀሚሷ በንፋሱ እየተገፋ ኩፍ ብሎ ወደ ኋላዋ ሲቀር እያስታወሰ ቀሚሷና ገላዋ እየተጣሉ የነበር መሰለው፤ አንሂድ እዚሁ እንቆይ ሲል ገላዋ አሻፈረኝ ያለ፤ ጸጉሯም እኔን ሲል ነበረ፣ ልቧስ? ልቧ ምን ሲል ነበር? መቆየት ፈልጎ ነበር? ወይስ ከምንም ሳይቆጥረኝ ሄደ? ነው መወሰን አቅቶት ነበር? ልቧ ከቀሚሷም ከገላዋም ኃያል ነው የፈለገውን አድርጎዋል ምንም ይሁን ምን ማግኘት አለብኝ! ተነስቶ ወጣ።

አኪያ ቅንጡ ወደሆነው ክፍሏ ገብታ መጋረጃውን በመሰብሰብ በመስኮት መመልከት ጀመረች ዐይኗ ግን ወደ ውስጥ እንጂ ውጩን አላይ አላት። እንዴት አልተከተለኝም? ጥቂት እንኳ እንጥፍጣፊ ስሜት በልቡ ቀርቶ ቢሆን ቢያንስ ሊያስቆመኝ ይገባ ነበር ፍቅረኛው ልትሆን ትችላለች። እንዲ ስሆን ከዚህ በኋላ ባላገኘውስ? እያለች ተመልሳ ወደ ሎቢው አመራች ሁለቱም የሉም እሱ ተቀምጦ የነበረበትን ወንበር በመሳብ ተቀመጠች መልሳ በሀሳብ ወደኋላ ነጎደች።

ከቴራስ ጋር ወደተዋወቁበት የመጀመሪያይቱ እለት፤ ያን እለት ስትነቃ አኪያ እራሷን ያገኘችው ከነዩኒፎርሟ እጇ ላይ የግልኮስ መርፌ ተወግታ የድንገተኛ ክፍል አልጋ ላይ ተኝታ ነበር እንደ ነቃች አጠግቧ ቁማ የነበረችው ነርስ እንድትረጋጋ አድርጋት የገጠማትን አደጋ አስረዳቻት። ሁኔታውን ለመረዳት አላዳገታትም ነበር ምክንያቱን ስለምታውቀው ከሦስት ቀን በፊት ከእናትዋ ጋር ተጣልታ ስለ ነበር እዕል በአፏ ከዞረ ሶስተኛ ቀኗ ነበረ በዚህም ምክንያት በHypoglycemia እንደተጠቃች ቤተሰቦቿ ተደውሎላቸው እየመጡ እንደሆነ እና የክፍሏ ልጆች እዚህ እንደአመጧት ነበር የነገረቻት የክፍሏ ልጆችም መንቃቷን ሲያዩ እየመጡ አጽናንተዋት ትንሽ ተጫውተው ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ ቴራስ ግን እዛው ቆየ።

ነርሷ ከወደቀችበት ያነሳት ተሸክሞም ቅርብ ስለነበረ ወደእዚህ በጓድኞቹ እጀባ ይዞዋት የመጣው እሱ እንደሆነ ለአኪያ ነግራት ሌላ ታካሚ እንዳለባትና እንዲጫወቱ በመንገር ትታቸው ወጣጭ። ወላጆቿ እስኪመጡ ቀልድ እንዲሁም ጊቢ ውስጥ ተማሪዎችና መምህራን ላይ የሚሰሩትን ተንኮል እየነገራት እያሳቃት ቆይቶ ወላጆቿ ሲመጡ ተሰናብቶአት ወጣ። በማግስቱ ክፍል ስትገባ ሁሉም ተሰብስበው አጠገቧ በመሄድ ደህንነቷን

ሲጠይቋት ቴራስ ግን ከመቀመጫው አልተነሣም ነበር። ረፍት ሰዓት ላይ ብቻውን ዐይታው ሄዳ ለምን ቅድም እንዳልመጣ ስትጠይቀው የመለሰላትን መልስ አስባ ፈገግ አለች።

ከሀሳብ በመንቃት ስታማትር ቴራስ ከእንግዳ መቀበያው ሲወጣ በማየቷ ቆም ብላ እጁን በማውለብለብ ተጣራች አልሰማትም ደገመች የጥሪው ድምጽ ወደመጣበት በመዞር ተመለከተ እሷ እንደሆነች ሲያውቅ ወደእሷ መምጣት ጀመረ። ዐይኖቿን ለማየት አልደፈረም ጭንቅላቷን በቀኝ እጁ ደረቱ ላይ ለጥፎ በግራው ወገቧን አቀፋት እሷም በሁለቱም እጆቿ ወገቡን አቀፈችው ጉንጩን አናቷ ላይ በማድረግ ለሚመለከታቸው ለፍቅር መታሰቢያነት የተቀረጸ ሃውልት እስኪመስሉ ለደቂቃዎች እንዲያው እንዳሉ ቆሙ። ናፍቆቱ ባይወጣላቸውም ተላቀው ቁጭ አሉ። አሁንም ግን ለመተያየት አልደፈሩም።

፡፡ ይሄ ሁሉ ጊዜ የት ነበርሽ?

፡፡ ፓሪስ

፡፡ ሌላውን ተይው የመጨረሻ ቀን ላይ እንዴት አትነግሪኝም ነበር?

፡፡ አልቻልኩም።

፡፡ ማለት?

፡፡ እኔ ለመሄድ ፍላጎቱ ስላልነበረኝ በተደጋጋሚ ከእናቴ ጋር አውርተንበት ተስማምተን ነበር።

፡፡ እና?

፡፡ ቴራስ እባክ ተው

፡፡ ነገ መልሼ እንደማገኝሽ ምንም ማረጋገጫ የለኝም! ስለዚህ ለዘመናት ጎዶሎ ያደረገኝን ይህን ጥያቄ መልሺልኝ!

፡፡ እንገናኛለን እንጂ ለምን አንገናኝም?

፡፡ እሱን አንቺ ነሽ የምታውቂው።

፡፡ ይኸውልህ ቴራስ ልጅ ስለነበርኩ አታለሉኝ ከእናቴ ጋር የነበረንን ጥል የምታውቀው ነው ኤምባሲ ስገባ ለቃለ መጠይቅ ለምርመራ ለያንዳንዱ ቀጠሮ የተለያየ እና የማይገናኝ ምክንያት እየሰጠች ለምጠየቃቸው ጥያቄዎች አሰልጣኜ የሚነግረኝን መልስ ብቻ እንድመልስ አለበለዚያ ለወንድሜ መጥፍ እንደሆነ እዛ እንደሚያስሩትና ንብረቱን ወርሰው ወደዚህ እንደሚመልሱት እየነገረች አስጨረሰችኝ በመጨረሻም አንድ ቀን ለሊት ተነስተው ወደ ኤርፖርት ይዘውኝ ሄዱ፤ ወደ ወንድሜ ላኩኝ። እማዬ ይሄን ሁሉ ያደረገችው አባቴ ላይ እንደምትማግጥበት ስለደረስኩባትና እንድታቆም በተደጋጋሚ ስላስጠነቀኳት ነው ይህን ከማቆም እኔን ከሀገር ማስወጣት ቀለላት።

ታውቃለህ ልቤን እንደጋለ ብረት ነበር የሚያቃጥለኝ ሳያት ትቀፈኛለች ድምጿን ስሰማ ያቅለሸልሸኝ ነበር። ምክንያቱም አባቴ ለቤተ ሰቦቹ ሲል ምን እየሆነ እንደሚኖር ስለማውቅ፤ አባቴ ኑሮ የሞላለት ቁጭ ብሎ መኖር የሚችል ሰው ነበር። ነገር ግን ቤተሰቦቼ አንዳች እንዳይጎልባቸው ለልጅ ልጆቼም የሚተርፍ ንብረት ሊኖረን ይገባል በማለት ለሊት ወጥቶ ማታ ይገባል፤

ውሎውንም ልቡንም ስለማውቅ ሰራተኖችን ሳትሆን እኔ እራሴ ነበርኩ ውሀ አሙቄ እግሩን የማጥበው፤ ፊቱ ላይ የማየው እርካታ እና ድካሙን የሚጋራለት ሰው እንዳለ ሲሰማው የሚያገኘው ረፍት ለእኔ ዓለሜ ነበር።
የሚገርምህ ቤተክርስቲያን ሊያድር ሲወጣ እሷ... ተወው አየህ ብዙ የነገርኩህም የምናገረውም ነበረኝ ግን አሁን ረፍዷል። ደግሞ ቴራስ ሰዉ ሁሉ የሚያወራው ምን አይነት ታማኝ እና ትዳሯን አክቤሪ እንደሆነች ነው በሷ ምክንያት የእውነት ቆራቢ አስቀዳሽ ታማኝ ለሰው ሳይሆን ለህሊናቸው የሚኖሩ ትዳራቸውን አክባሪ የሆኑ ጓደኞቿን ጎረቤቶቻችንን ጭምር ሚስት ለተባሉ ሁሉ ጥላቻዬ ተርፎ ነበር። እናትነት ማለት ምን ማለት ነው? ሚስትነትስ? እኔ ለእማዬ ምንም አይነት ቂምም ጥላቻ አሁን አዲሱ ልቤ ውስጥ የለኝም። እንባ አቅርረው የቦዘዙ ዐይኖቿን ውሀው ላይ እንደተከለች ዝም አለች።

ወንበሩን አስጠግቶ በዝምታ አቀፋት። ያለቀ የመሰላት ለዘመናት ተከማችቶ የነበረ የብቸኝነት፣ የቁጭት፣ የእልህ፣ የናፍቆት ድብልቅልቅ ያለ እንደ ቆይታው ያልበረደ እንባ ጉንጮቿን እየፈጀ ደረቷን አራሰው። ቴራስ አንተስ እስኪ ያለፉትን ጊዜያት እንዴት እንዳሳለፍካቸው አጫውተኝ? እ..እ ያው ከባድ ጊዜያት ነበሩ እንደዚያውም በመሃል እንደ ክረምት ጸሀይ ብቅ የሚሉ መልካም ጊዜያትም ነበሩ። ብሎ ዝም አለ መናገር ባይፈልግ ነው እኔም አሁን መጠየቅ አልነበረብኝም ይሆናል አለች በውስጧ ቀጥላም ለመናገር አፏን ስትከፍት እሱም መናገር ሲጀምር ተገጣጠመ ቅድሚያ አንተ አንቺ ተባብለው ፈጠን ብሎ ለምን ማታ እራት አንበላም አላት እንዳጋጣሚ ዛሬ ቀጠሮ የለኝም ይቻላል በማለት እሺታዋን ገለጸችለት።

⁂⁂⁂

ከመሃል አንደኛው ኮሎኔል ጄነራል አንድ አንዶቹ ሹመቶች ግን ልክ አይመስሉም የማይገባቸውና የማያገባቸው ቦታ የተሾሙ አሉ፤ ከዝግጅት ጉድለት ነው ወይስ ሲል አንድ አንዶችም በመስማማት ጭንቅላታቸውን ወዘወዙ። እሳቸውም ወንድሞቼ ሁሉ ነገር የታቀደበት እና በደንብ የታሰበበት ነው ሊቁም እንደ እናንተ ጥያቄ አንስቶ ነበር እኛ ግን ዓላማችንን እናውቃለን እና አሳማኝ የሚመስል ምክንያት በማቅረብ ነው ያሳመንናቸው። ሥራቸውን ሲጀምሩ ለምን እነዚያ ቦታዎች ላይ እንዳስቀመጥናቸው ይገባቹሃል። ይህን በመናገር ላይ ሳሉ በየግል ስልካቸው ቴሌግራም አካውንት መልዕክት የደረሳቸው አባላት በተመሳሳይ ሰዓት ወደ ስፍራው በመድረሳቸው ወደ ውስጥ ዘለቁ። ሁሉም ወንድማዊ ሰላምታ ተለዋውጠው እስካሁን በአካልም በስምም የማይተዋወቁ ሁሉም እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ ጄነራል ንግግራቸውን በማቆም ትዕዛዝ ሰጡ። አባል መሆናቸውን አይተዋወቁ እንጂ አብዛኛው በአላቸው ዝናና የሥራ ድርሻ በአንድም በሌላ ይተዋወቁ ነበር።

የምክትል ናቡከደነጾር በመሀላቸው መገኘት ግን ሁሉንም አስገርሞአል። ትውውቁን ከአጠናቀቁ በኋላ ጄነራል ሠሀረ ወንድሞች ከአሁን ጀምሮ የማታውቁት አዲስ አባል በአመራር ደረጃ የለም፤ አይጨመርም ማለት ግን አይደለም ሲኖር እናሳውቃቹሀለን እንጂ። የምልመላ ደረጃዎቻችን ምን እንደሚመስሉ የምታውቁት ነው ሁላችሁም ያለፋችሁበት ስለሆነ፤ አያስፈልገንም ማለት አይደለም ግን ተጨማሪ ኃይል ባይኖረን እንኳ ለያዝነው እቅድ አሁን ያለን የሰው ኃይል እና ሪሶርስ በቂ ይመስለኛል ያው ስትራቴጂ እስካልቀየርን ማለቴ ነው። ስለሆነ አሁን የአንድ ሰው የበላይነት እና የዚህ ሁሉ ምሁር አድርባይነት እንዲሁም አንገት መድፋት ማብቂያው ሰዓት መሆን ስላለበት ቀጥታ ወደ ሥራ መግባት ይኖርብናል ሁላችንም ባለንበት የድርሻችንን ባለ

መሰልቸት የምንወጣበትና መሀላችንን በመጠበቅ ሀገራችንን በአፍ ሳይሆን በተግባር ወደ ነበረችበት ከፍታ የምንመልስበት ዘመን ነው። ስብሰባ ስንገባ ሀሳብ ስናንሸራሽር የምንሰጋበት ጊዜ አልፎአል። ምክንያቱም አሁን በአመራር ደረጃ ሁሉም ማለት በሚያስደፈር ሁኔታ የኛ ሆነውዋል ሁለት ዛፍ እየረገጡ የሚጓዙ ቢኖሩም እነሱንም የማጥራት ሥራ እየተሰራ ነው። ማኒፌስቶ ለሁላችሁም ዛሬ ማታ ይደርሳቹሃል። በዛው መሰረት የምንጓዝ ይሆናል ጥሩ ጊዜ ይሁንላችሁ እኔ መሄድ ይኖርብኛል።

:::

አኪያ የወይኑን ብርጭቆ አፍ በቀስታ በመሃል ጣትዋ በክብ ቅርጽ እያሸች ሬስቶራንቱን ቃኘት አድርጋ በጣም አሪፍ ቤት ነው አለችው። ቴራስም ልክ ነሽ ጸጥታ ስፈልግ እዚህ ነው የምመጣው። ከምነግርሽ በላይ ነው ይህን ቤት የምወደው ቦታ አጠቃቀማቸው፣ ቀለም ምርጫቸው፣ ላይት አጠቃቀማቸው ኢንቴርየር ዲዛይኑ ሁሉ ነገር ይስበኛል ጫጫታና ወከባም የለበትም እንደምታዪው። ከሰው ጋር እዚህ ስመጣ ዛሬ የመጀመሪያዬ ነው። ቀደም ሲል አንስታው በቂ መልስ ሳታገኝበት በቀረው ነገር ግን አብዝታ ማወቅ የምትፈልገውን ጥያቄ መጠየቅ ፈልጋለች ግን በቀጥታ መሆን እንደሌለበት ገብቶአታል። ይህን አከባቢ ትወደዋለህ ልበል? ጥዋት ያገኘሁህ አከባቢ ነው አሁነም ይዘኸኝ የመጣኸው ትንሽ ቢርቅም ግን አስፓልት እንኳን አልቀየርንም አለችው።

፧ ልክ ነሽ ለቢሮ እንዲቀርበኝና ስለምወደውም መስቀል ፍላወር አካባቢ ነው የምኖረው።

፧ አንተ ከወደድከው አሪፍ መሆን አለበት! ለኔም እዛው ብትፈልግልኝ ምን ይመስልሃል?

፧ ይቻላል። ምን አይነት እንዲሆን ትፈልጊያለሽ?

፧ ያንተው አይነት። እድሜዬን በሙሉ በምናቤ ከአንት ጋር ስኖር ነው ያሳለፍኩት።

፧ እኔም በሌልሽበት በአንቺ ፍላጎት ቤቴን ስሞላ ነው የኖርኩት።

፧ ይሄን ቤት ለማየት ጓጓሁ ነገ የሆነ ሰዓት ወስደህ ታሳየኛለህ።

ቴራስ ይህን ጊዜ ያላወቀው ስሜት ልቡን ያስጨንቀው ጀመር። ደስታ ከሀዘን ድብልቅልቅ አለበት እየቆየ ትንፋሽ እያጠረው ፊቱን እያላበው መጣ። ስልኩ ጠራ ስክሪኑን ገልብጦ ደዋዩን ተመልከቶ መልሶ በስክሪኑ ደፍቶ አስቀመጠው። አባቴ ምን ሆንክብኝ ፊትህ እኮ ልክ አይደለም ስትለው፤ እራሱን መቆጣጠር ስላቃተው መታጠብ እንደ ሚፈልግ ተናግሮ ወደ ባኞ ቤት አመራ። ፊቱን በውሃ ዳበስ ዳበስ አድርጎ መስታወት ፊት ቆሞ ዐይኑን ሲመለከት ቆየና አንዳች ሀሳብ ስለ መጣለት ወጣ፤ አኪያ በቦታዋ የለችም።

ዐይኑን ማማተር ጀመረ ከአንዲት ወጣት ጋር ቆማ ስትሳሳቅ ተመልከቶ ወደ መቀመጫው አመራ ከጥቂት ቆይታም በኋላ አስታወስካት የሚል የአኪያ ድምጽ ወደ ኋላው እንዲዞር ግድ አለው። ሊያስታውሳት ግን አልቻለም። እንዴት አንድ አለችኝ የምላትን የትምህርት

ቤት ጓደኛዬን ትረሳታለህ? ሕልቃ ናት? አዎ ነኝ፤ ይገርማል በጣም ተለውጠሻል፤ ልክ ነህ ያው ረጅም ጊዜም አይደል፤ ታዲያ አረፍ በያ፤ አይ እናንተ ተጫወቱ እንግዳል አለብኝ ስላገኘኋቹ ደስ ብሎኛል በማለት ተለየቻቸው። are you feeling better? can i help you in any way possible? አለችው፣ አሁን ተሽሎኛል መጀመሪያም ህመም አልነበረም አመሰግናለሁ። ወደ ቤት ሄጀ ማረፍ ሳይኖርብኝ አይቀርም። አሁን? አለችው አዎ አላት።

በብስጭት ብድግ ብላ በመነሳት የእጅ ቦርሳዋን አንስታ ስትንትተው የእጁ ሰንሰለት የወይኑን ብርጭቆ ስለ ጎተተው ወድቆ ሲሰበር ባወጣው ድምጽ የሰዉ ትኩረት ወደ እነሱ ሆነ። ይህን ያወቀው ቴራስ ሳያስበው ብድግ አለ፤ አኪያ ግን ይህን ለማስተዋል ጊዜ አልነበራትም ወደፊት ስትራመድ የቀሚሷን ጫፍ በአንደኛው እግሯ ረግጣው ነበርና በሌላኛው ለመራመድ ስታነሳው አደናቀፋት እጁን ለመያዝ ሲሞክር አስለቅቃው በግራ እጁ ቀሚሷን ከፍ አድርጋ በመያዝ መንገዷን ቀጠለች። ቴራስም ቆም ብሎ አስተናጋጁን አወራውና ተከተላት። ሊደርስባት ግን አልቻለም፤ ኢሊቬተር ውስጥ ቆማ ነበርና እንደ ደረሰ በሩ ሊዘጋ ሲል ሮጠ እየተያዩ በሩ ተዘጋ፤ በሩጫ በደረጃው መውረድ ጀመረ።

አስፓልት ዳር ቆማ ስልክ እያወራች ደረሰባት። አጎንብሶ በእጆቹ የእግሮቹን ጉልበት ተደግፎ ቁና እየተነፈሰ እንደዛ ማለት ፈልጌ አይደለም ብሎ ቀና ብሎ አያት። ልታየው ፍቃደኛ አልሆነችም። የቤት መኪናም መጥታ ከፊታቸው ቆመች። የኋላውን በር ከፍታ ልትገባ ስትል በሩን ዘጋውና በእጁ ሂድ አለው ሹፌሩም ዝናብ መጣል ጀምሮአል አሁን እንኳ መበስበስ ጀምራቹሃል ብትገቡ ይሻላቹሀል እያለ እያጉረመረመ ወደ ፊት መንገዱን ቀጠለ።

ይኸውልሽ አኪያ እኔ በአሁን ሰዓት ልቤ እና ጭልቅላቴ እየተጣሉብኝ ነው እባክሽ ተረጂኝ። ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ሁለቱም ልክ ሆነው አያውቁም! ይህ ለድክመታችን አልያም ለራስ ወዳድነታችን የምንሰጠው የዳቦ ስም ነው አንዱን ምረጥና ና አልያም ቅር። እነዛ ሁለት ሀሳቦች ምን እንደሆኑ ልትነግረኝ አያስፈልግም አውቃቸዋለሁ። አንተን በመውደድ እና ሕይወቴን በመኖር መሀል ስብሰለሰል ኖሬ አንተን የመረጥኩ ሰው ነኝ። ለእኔ የሁለት ሀሳቦችን ግጭት አትንገረኝ የሚያሸንፈው ሁልጊዜም አጥብቀህ ከልብ የምትፈልገው ነው። እሱን እስክትወስን እኔ ጋር አትምጣ። የስካሁኑን ያህል ግን አልጠብቅህም እኔም ይቆርጥልኝና ነገን ትቼ አሁንን እኖራለሁ። ልጅነቴ እንደሆነ በነበረ ትዝታ ውስጥ በመብሰልሰል አልፎአል፤ ወድጀ ተወድጀ ከመኖር በሰው ሀገር ያንተን ትዝታ ታቅፌ በብቸኝነት መኖርን መርጫለሁ። ግን ምንም አይቆጨኝም በምርጫ ስላደርኩት። ይልቁንስ ቁጭት የሚሆነው ከዚህ በኋላ መሆን ያለበትን ሳላደርግ የቀረሁ እንደሆነ ነው።

ብዙ ጊዜ ሕይወት የት ነው ያለው? እያልኩ እጠይቃለሁ ትላንት ዛሬ ወይስ ነገ ትላንት የኖርክበት ቤት የተማርክበት ትምህርት ቤት የተዝናናህበት ስፍራ አሁንም አሉ፤ ያሳለፍካቸው ትዝታዎች ልብህን ትንፋሽ አሳጥረው አሁንን ነገን እንድትረሳ ያደርጉሃል። ትላንትን ብቻ እንድትኖር የግድ ይሉሀል። ምናልባት እነዛ ስፍራዎች ወይም ሰዎች እንኳን ባይኖሩ ትዝታቸው በልብህ አለ። አንተም በደስታ እሺ ትላቸዋለህ፤ ምክንያቱም እዛ አንተነትህ ግማሽ ማንነትህ አለና። ሀዘንም ሆነ ደስታ ያ አንተነትህ ነው። መሻር ብትፈልግ እንኳ ልብህ ላይጨክንም። አሁን ደግሞ አለልህ፤ ስለ አሁን ላንተ አልነግርህም የስሜት ውጣ ውረዱ በራሱ ሕይወት ነው የአሁን ትልቁ ክፋቱ፤ ትላንትን እያስናፈቀ

ዛሬን አስረስቶ ለነገ ማስጨንቁ ነው። ካላወከበት በእነዚህ ሁለት እንቆቅልሾች ወጥሮ ከመቃብር አፋፍ ያደርስሃል። ነገስ? ነገም በባህሪው እንደዚ ነው ገና ሳታየው እንድትፈራው ያደርግሃል በዚህ ጸባዩ ከሁለቱም ይበልጣል መፈራትን ስለ ሚፈልግ ይመስለኛል ቀላሉን ጥበብ ይደብቅብሃል። ያ ጥበብ ዛሬ ላይ ሆነህ ነገን መስራት እንድትችል ያደርግሃል። ስለ ነገ እርግጠኝ የምትሆንበት ብቸኛ መንገድ እሱ ነው። ይህን ሳስብ ሕይወት ግራ ታጋባኛለች። ጎንበስ ያለ ቀና ባለ፣ ቀና ያለ ባጎነበሰ፣ የተቀመጠ በቆመ፣ የቆመ በተቀመጠ፣ የተኛ በነቃ፣ የነቃ በተኛ፣ ምሁር ባለ አዋቂ፣ አላዋቂ በምሁር፣ ሀብታም በደሀ፣ ደሀ በሀብታም፣ አጭር በረጅም፣ ረጅም በአጭር፣ ጥቁር በቀይ፣ ቀይ በጥቁር፣ እየቀና ይኖራል ሁሉም ለየራሱ እውነት አለው። እውነት ግን ቅድም እንዳልኩህ አንድ ናት! ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ልትሆን አትችልም።

ትላንትን ከዛሬ ዛሬን ከነገ ለማሰር ስሞክር ውሉ ይጠፋብኛል እያለች ንግግሯን በእንባ እያጀበች ስሜቷን ስትገልጽ ከላይ የሚወርደው ዝናብ ቀድሞ እንባዋን ያጥብባት ነበር። የለበሰችው የእራት ቀሚስ ረጥቦ ክብደት ጨምሮ አላንቀሳቅስ አላት። ቴራስም እንደዚያው ነገር ግን ከላይ የለበሰው ጃኬት የቆዳ ምርት ስለ ነበር፤ ከውስጥ በለበሰው ሸሚዝ በመሆን ጃኬቱን አውልቆ ደረበላት። ምንም እንኳ ዝናቡ ቢጠርገውም እንባዋን ከማየት አልገደበውምና። አኪያ ግን የደረበላትን ጃኬት መልሳ ደረቱ ላይ ስትለጥፈው ተቀብሎ አርቆ ወረወረው። ተመልከቺ! እኔ ሁሉ የሞላለት ጎዶሎ ሆኜ ነው የኖርኩት። በሰው ተከብቤ ብቸኛ ነኝ፤ እየሳቅኩ ደስተኛ አይደለሁም፤ ሳቄን፣ ደስታዬን፣ ተስፋዬን፣ ፍቅሬን፣ ሕይወቴን ነው ይዘሽ የጠፋሽው። ያንቺ ልጅንነት ብቻ ይመስልሻል በትዝታ ያለፈው? አንቺስ አንደኛውን በባዕድ ሀገር ሆነሽ ነው። እኔ በወገኖቼ፣ በጓደኞቼ፣

በቤተሰቤ ተከብቤ ነው ብቸኛ የነበርኩት። የሚወደድ ብቸኛ የሚፈቀር ባይተዋር የሆንኩት። አንቺ ስትመጪ አፈላልገሽ እንደምታገኚኝ ተስፋ ነበረሽ። ተስፋ ደግሞ የሕይወት መልዕቅ ናት ተብሎአል። እኔስ በሞተ ተስፋ ባዶ ምኞት ታቅፌ፤ ለምትወደኝ በድኔን ሸልሜ፤ በእያንድ አንዱ እርምጃዬ አንቺን ተሸክሜ እየኖርኩ ነው። አሁን በአካል ከነኔ አገኘሁሽ፤ እሺ እኔስ ሊሞላልኝ ሀሴትን ልጨብጥ ሆነ፤ ይህች ምስኪንስ ምን ትሁን? እኔን ብላ በኖረች፣ በታመነች፣ በወደደችኝ ክፍያዋ ክህደት ይሁን? ለመታመኗ ሸልማቷ ይሄ ይሁን? ሁለቱ ገብተውኛል ያልሻቸው እውነትም የተገለጹልሽ ሀሳቦች እኚ ናቸው። ግን አንቺ እንደገመትሺው ስለ እኔ አንቺንና ሌላ ሴት በመውደድ መሃል ያለ ውጥረት አይደለም። ስለ እሷ እንጂ ብሎ ዝም አለ። መጥታ አቀፈችው፤ እንባዋ በእርጥበት ከደረቱ ላይ በተለጠፈው ሸሚዙ ላይ ይወርዳል፤ ግለቱ ልቡን አሞቀበት። ይህን ጊዜ ዝናቡ በብዛቱ አልያም በብርታቱ እንባዋን ሊያሸንፈው አልቻለም።

ጂማ ከተማ

ሂሶጵ በተመቻቸለት መንገድ የፍቅር ከተማ በመባል ወደ ምትጠራው ከአንድ አንዶች አፍም እንደ ሚሰማው የአራዶች መፍለቂያ ከሆነችው ከተማ በመድረሱ እየተደሰተ፤ የታሪክ ቦታዎችንም ለመጎብኘት እድሉ እንደ ሚኖረው እየገመተ ነበር; ፈረንጅን በተለምዶ ከፊት በመጨመር በሚጠራው አራዳ አከባቢ በተዘጋጀለት

ጊዜያዊ ማረፊያ የተሸሸገው። እንዳሰበው ግን ቀላል ሆኖ አላገኘውም፤ እንደልቡ ወጥቶ የመግባትን አጋጣሚ እያገኘ አይደለም። ፎቶው በእያንዳንዱ የደህንነት እንዲሁም የፖሊስ ዋና ዋና አባላት እጅ እንዲገኝ መደረጉ ዋነኛ ምክንያት ነው።

የኛ ሰዎች በየሰዓቱ እየመጡ የሚያስፈልግህን ያሟሉልሃል። አስቀድሞ የሚስጥር ቃል ያልተለዋወጠህ ማንም ቢሆን በር እንዳትከፍትም፤ እራስህንም ለማንም እንዳታጋለጥ ተብሎ የተሰጠውን ጥብቅ ትዕዛዝ በመጣስ፤ ለብቻው ከተሰጠው መኖሪያ ቤት ደጃፍ ቆሞ መርካቶ የሚባለውን ሰፈር በዝና ስለ ሚያውቀው፤ እዛ ከሄድኩ የምፈልጋቸውን እቃዎች አላጣም በሚል እሳቤ፤ ሰው ለመጠየቅ ሲዘጋጅ አንዲት ባጃጅ ስታልፍ በማየቱ፤ በፉጨት አስቁሞ በመግባት መርካቶ እንዲወስደው ከነገረው በኋላ እንደ ተለመዱት የባጃጅ ሹፌሮች ይሄኛውም ወጣት ሆኖ ስላገኘው፤ ማንነቱን ለማወቅ ይረዳኛል ብሎ ያሰባቸውን ጥያቄዎች ይጠይቀው ጀመር።

ወጣቱም በቀልድ እያዋዛ ሳቅን በሚጭሩ ጨዋታዎች ይመልስለት ነበር። ይኸው መርካቶ ደርሰናል ብሎ የያዙትን ጨዋታ አቋርጦ ቆመ። ጀነራል ሂሶጵ ከዚህ ወጣት ጋር መለያየት እንደሌለበት እና በብዙ ሊጠቀም እንደሚችል ወስኖአል። ስለዚም ለከተማዋ አዲስ እንደሆነና መግዛት የሚፈልጋቸው ልብሶች ስላሉ እንዲያጋዛው ጠየቀው እረ ኖርማል ነው፤ ነይ አሪፍ አሪፍ ቤት አሳይሻለው ብሎ ባጃጁን ከአቆመበት ትቶአት ቁልፉን ነቅሎ ወረደ። እንዲሁ ነው ትተሃት የምትሄደው? ሲል ጠየቀው። ነይ አይዞሽ ማንም አይነካትም ብሎ መራመዱን ቀጠለ። ሂሶጵ በሴት አንቀጽ መጠራቱ ባያስደስተውም ከከፋት አልያም የንቀት አለመሆኑ እንዲሁም አንድ አንድ ጊዜ እንደሆነ የሚጠቀመው ስለገባው እንዲያስተካክል ከመንገር ይልቅ

መተውን መረጠ ይልቁንም በተደጋገመ ቁጥር ጆሮው እየለመደው መጣ።

ሁለት ቤት ይዞት ገብቶ ሁለቱም ጋር የሚፈልጋቸውን አልባሳት በማግኘቱ፤ ከሻሮችም ጋር በነበረው መግባባት፣ ለሰዎች በሚያሳየውም ለዛ የተላበሰ መቀላለድ በወጣቱ እየተገረመ መጣ። ለደቂቃዎች አብሮት ሆኖ ለረጅም ጊዜ የሚተዋወቁ ያህል እንዲሰማው አድርጎታል። አንድ ልጅ ጠርቶ ሰላም ሲለው ሰምቶአል ለማስታወስ ሞከረ እናም አንተ ፓፓ ማኪያቶ መጠጣት ፈልጋለሁ አሪፍ ቦታ ውሰደኝ አለው። ያልጠበቀው ስለ ነበር በጣም ሳቀ። ገባውና ስምህ አይደለም እንዴ አለው? እሱማ ያንተም ስም ሊሆን ይችላል ሁሉም ወጣት የሚጠራበት የጋራ ስም ነው። ያው ካንቺ መምጣቱ አስገርሞኝ ነው አለው። እኔ ደግሞ ቅድም አንዱ ሲጠራህ ስለ ሰማሁ ስምህ መስሎኝ ነበር፤ ትክክለኛ ስምህ ማን ነው? ዘሩባቤል! አ ደስ የሚል ስም ነው እኔ ደግሞ ሂሶጵ እባላለሁ። እረ ብራዳ ኢንተርቪው አስመሰልሽው ነይ ለማንኛውም አሪፍ ማኪያቶ ልጋብዝ፤ ሚገርምህ እዛው የተገናኘንበት ቦታ ነው የከተማዋ አሪፍ ባሬስታ ያለው። እሺ እንሂድ!

አራዳ አከባቢ እንደ ደረሱ፤ ደጊቱ ሆቴል ይዞት ገባና አሪፍ ነው ያለውን ማኪያቶ ጋበዘው እሱ ሚሪንዳ አዘዘ። ወይ ለምን ቡና አትጠጣም? ኧይ እኔ ቡና አልጠጣም። ባይሆን አሪፍ ቡና እጋብዝሃለሁ ሌላ ጊዜ። እንዴ የጂማ ልጅ ሆነህ ቡና አትጠጣም? ይገርምሃል እንዲ ስባል አንተ የመጀመሪያዬ አይደለህም። ብዙ ከተለያዩ ከተማዎች በሥራ ወይ የንጉሡን ቤተ መንግሥትና ሌሎችን ስፍራዎች ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች ይሄን ጥያቄ ይጠይቁናል። ጂማ የፍቅር ከተማ ናት የሚባለው

እውነት ነው? ንግግር ያሳንሰዋል ኖረህ እየው። ብሎ መለሰለት።

ከፍተኛው የትምህርት ደረጃህ ምን ያህል ነው? ጠየቀ ሂሶጵ። ይገርማል አንተም ሰዎችን በትምህርት ደረጃቸው ከሚለኩት መሃል ነህ? የትኛውን የትምህርት ደረጃ ልንገርህ? ማለት? በማለት መለሰ ሂሶጵ። ያው ትምህርት ሁለት አይነት እንደሆነ ታውቃለህ ፎርማል እና ኢንፎርማል። applied science, psychology, philosophy… 19ኛውን ክፍለ ዘመን The Nature of Light, Origin of Species, The Laws of Thermodynamics የሚባሉ እንቆቅልሾች ተብዬዎች ሲንጡት ነበር፤ 20ኛውን ደግሞ Quantum Mechanics, Theory of Relativity, The Structure of DNA, Dark Matter and Dark Energy, ተቀበሉት፤ 21ኛው Unifying Physics and Consciousness የተባለ philosophy ተቀበለው የቀጣዩ ዘመን ምን ይመስሃል? ፎርማሉ፣ ዓለም እንድትሆንላት የምትፈልገውን አይነት ሰው እስክትሆን፤ አግላ እንደ ብረት ቀጥቅጣ የፈለገችውን ቅርጽ እንደያዝክላት ስታረጋግጥ ተመርቀሃል ብላ ሰርቲፋይድ ቅጥቅጥ የምታደርግበት ወይም እሷ እንደፈለገችው ሼፕ እንዳደረገችህ መታወቂያ እንዲሆን የምትለጥፍልህ ባጅ አለ። ስለ እያንዳንዱ ቶፒክ እሷ እንደምትፈልገውና በእሷ መንገድ እንደምታስብ እርግጠኛ የምትሆነው ደግሞ ከስድስት ዓመትህ አንስታ ዲግሪ እስክትሰጥህ ድረስ በምታስተምርህ ትምህርቶች ነው፤ ማለትም አውሮፓዊ ታደርግሃለች ማለት ነው። ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስደፈር ሁኔታ ስለ ዓለም ስናወራ ስለ አውሮፓውያን እያወራን እንደሆነ ግልጽ ነው። እነሱም እንደዚያ እንደሚያስቡ ግልጽ እንዲሆንልህ ሱፐር ሂሮ

እያሉ የሚጠሯቸውን ካራክተሮች ማየት በቂ ነው። ይመጣና አሜሪካንን አልያም አንድ የአውሮፓ ከተማን አድኖ፤ ዩ ሴቭ ዘ ዎርልድ ሲሉት ትሰማለህ። እያንዳንዱ የዓለም ማኅበረሰብ በተቻለ መጠን በአውሮፓውያን አስተሳሰብ እንዲጠመቅ ይሆናል። ተጠምቀናልም። ስትጠመቅ ደግሞ አንተነትህን እርግፍ አድርገህ መተው ይኖርብሃል ትተናልም። በዚህች ትንሽ የምትመስል ግን ዓለምን ከመቆጣጠሪያ መንገዶቻቸው ዋነኛው በሆነ መንገድ፤ ማንነት ያሳጡሃል። የነቁ ሀገራት በጥቂቱም ቢሆን ዜጎቻቸውን ያስመልጣሉ። ቢያንስ ካሪኩለሙ ላይ ሀገር በቀል ዕውቀት በመደባለቅ።

እንደኛ ያሉቱ ግን መሰረታቸውም የሀገር ጥላቻ ስለሆነ ባለ ማወቅም ግን አብዛኛውን ሆን ብለው ትውልዱን ገደሉት! ጠያቂ ተመራማሪ ጠፋ። ሁላችንም ልጓም እንደገባለት ፈረስ፤ የእውር ድንብር መፈርጠጥ ከጀመርን ሰነባበትን። እውር እውርን ቢመራው ነውና ሁላችንም ወደ ገደል እየሮጥን ነው። ጥቂት የማይባሉም ተፈጥፍጠው አለቁ። አንድ እንኳ ቆም ብሎ አስተውሎ ቀሪውን የሚያድን ጠፋ። የሚሞክሩ ነበሩ ግን ከራስ ወዳድነት ስሜት ያልተላቀቁ ነበሩ። ከልባቸው የነበሩትን አሳልፈን ሰጠናቸው የበላንበትን ወጪት መስበር ለምደናልና። ጥቂት የማይባሉት ግን ካዱን ወስላታውን ሰው በመከራ ጊዜ መተማመን እንደ ተሰበረ ጥርስ እና እንደሰለለ እግር ነው ተብሎ እንደተጻፈ። በሁሉም አቅጣጫ ዝቅጠት ውስጥ ነን።

ይህንና የመሳሰሉ ውርደቶችን ተሸክሞ ወጣቱ ለምን ይመስልሃል ዝም ብሎ የተቀመጠው? ጥይት ፈርቶ? የምር ለነጻነቱ የሚታገል ቆራጥ ወጣት ጠፍቶ ይመስልሃል? አትሸወድ መከዳት ሰልችቶት ደመከልብ መሆንን ከታላላቆቹ አይቶ፤ ነገም እኔ እንዲሁ ተረስቼ ነው የምቀረው ብሎ እንጂ፤ በእሱ ደም የምትመጣ ነጻነት እንዳለች እርግጠኛ ቢሆን፤ እሱ አካሉን ቆርሶ፣

ወንድሙን ገብሮ፣ ደሙን ያፈሰሰላት ዓላማ፤ ነገ እንደማትረሳ ማረጋገጫ ቢሆረው፤ ታየው ነበር። በአንድ ቀን ሌሊት ዓለምን ጉድ የሚያሰኝ ለአፍሪካ የሚተርፍ ሪቮሉሽን ሲያስነሳ፤ ግን ሁሌ መከዳት ይሰለቻል። ለማንኛውም ይህን ሁሉ ውጥንቅጥ ያስከተለውን ትምህርት ተብዬ ከሆነ የጠየከኝ ዲግሪ አለኝ ግን አልፈልገውም። ይህ ሲስተም ካልተቀየረ ስለ ፎርማል ትምህርት ማሰብ አልፈልግም።

ካምፓስ ክላስ ገብቼ ከተማርኩት ይልቅ በኢንፎርማል ለርኒንግ ያገኘሁት ዕውቀት ግን ሕይወት ሆኖኛል። እንዴት መኖር እንዳለብኝ፣ እንዴት ማሰብ እንዳለብኝ፣ እንዴት ስኬታማ ሕይወት መኖር እንዳለብኝ አሳውቆኛል ስኬታማ ስልህ በገንዘብ ብቻ አይደለም። ለእኔ ትልቁ ስኬት ለምን ወደ እዚህ ዓለም እንደመጣህ ከማወቅ ይጀምራል። ዓላማ! ዓላማ የሚመራው ሕይወት መኖር እያንዳንዱን ቀንህን እንድትኖረው ያደርግሃል። ጥዋት ስትነቃ ደግሞ ነጋ ብለህ አትጨነቅም። የሕይወትህ አንዱ አካል ካላደረከው ሰላም ስለሚነሳህ፤ ተገደህ የኑሮ ዘይቤህን ትቀይራለህ። ጠዋት በለሊት ዓላማህ ይቀሰቅስሃል። ስንፍናን ያስወግድልሃል፤ ሕይወት እንድትጣፍጥህ ያደርጋታል። ዓላማህን ካገኘህ ሰላምህ አብሮ ይመጣል። ይህን የትኛው ካሪኩለም ያስተምርሃል? ፎርማል ለርኒንግ ዶሜን ኖውሌጅ ይሰጥሃል እውነት ነው። የምትፈልገው ፊልድ ካለ። ግን ሕይወት አይሰጥህም። በኢንፎርማል እኔ ሕይወት አግኝቻለሁ ነው እያልኩህ ያለሁት። እኔ ሀገሬን ያወኳት ትምህርት ቤት ተምሬ አይደለም። ሀይማኖቴን ያወኩትም እንደዚያው። አለሙን ሁሉ አትርፈህ ዘለዓለምህን ብታጣ ምን ይጠቅምሃል? ሕይወት ደግሞ የሚጀምረው ከሃይማኖት ነው። ከየት እንደ መጣህ፤ ወደ የት እንደምትሄድ የምታውቀው በዚህ ነው።

የዓላማህ ስር እዚህ ይገኛል፤ ስኬት ደግሞ የምትወለደው በዓላማ ተጸንሳ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ፤ የሕይወት ውሃ ከሆድህ እንዲፈልቅ ያደርጋል፤ የዓላማህን ስር ያጠጣልሃል። ግንዱ ፋፍቶ በጊዜው ጽንሱ ስኬትህን ያዋልድህል። ውልደት ደግሞ ምጥ አለው። ምጡ ግን ለሕይወት ነው። ኢትዮጵያም እዚህ ደረጃ ላይ ያለች ይመስለኛል። ስኬቷን ልትወልድ እያማጠች፤ በእግዚአብሔር ታምና ስለ ኖረች የሕይወት ውሃ ከሆዷ ሲውጣ ኖሮዋል። እንኳን እኛን የጎረቤቶቻችንን ኑሮ ሲያቀና ከርሞአል። ውሃውን በጥበብ ከመሰልነውም እንደዚያው።

ስለዚህ ስኬቷን ልትወልድ ነው። የእሷ ስኬት ደግሞ ጠቢባን ልጆችን ማፍራት ነው፤ የሚከበሩ፣ ግርማቸው ከሩቅ የሚያስፈራ፣ ንኡድ ክቡር የሆኑ፣ ጥበባቸው ለዓለም የሚተርፍ፣ ጻድቅ እና ቅዱስ ሕዝብ ልትወልድ ምጥ ላይ ነች ሀገሬ። በዚሁ አንጻር ሾተላዮች እያስቸገሯት ነው። ምጡን ለማጨናገፍ የሚፈልጉ፤ ምን እንደምትወልድ የገባቸው ጠላቶቿ፤ የዕውቀት ማነስ ያለባቸውን ልጆቿን ከጎን አስልፈው፤ እናት በልጆቿ ስለማትጨክን በልጆቿ እያስወጓት ይገኛሉ። ነፋስ የሚያስፈራው ለእንክርዳድ እና ለገለባ ነው፤ እንደ ወንፊትም ስለሚያገለግል። ይህ ሁሉ መሆኑ ግድ ነው፤ ጽንሱም መወለዱ አይቀርም። እኔ አሁን ያለኝ ዕውቀት ከ90% በላይ የሚሆነውን ትምህርት ቤት አይደለም ያገኘሁት። እመነኝ እዚያ ያገኘኋቸውን አብዛኛዎቹን እዚያው ጥያቸዋለሁ። ዐየህ ሠራተኞች እንጂ አሳቢዎች እንድንሆን አይፈለግም። ህልምህን እንድትረሳ ደሞዝ ይሰጡሃል ስትነቃ ጡረታ ላይ ከነድህነትህ ትደርሳለህ። ጊዜ ተሸክርክሮ ጉልበትህን ይሰብረዋል። ልሩጥ ብትል እግርህ ይከዳሃል። ልሥራ ስትል ጉልበትህ ካንተ ይርቃል። አምራች ሳይሆን ተጠቃሚ ትሆናለል! ከዚህ በላይ እስር አለ? የእራሴ የምትለው ሀሳብ፣ አቋም እና ማንነት ከማጣት በላይ ግዞት አለ? አብዛኛው ሰው

አጥሩን ነው የሚፈራው። መፈራት ያለበት ግን የሀሳብ እስር ነው! ሰው ካላሰበ ንፋስ ያነሳው እቃዬ ገላ ይሆናል! መነሻውም መድረሻውም የእሱ አይሆኑም።

አንድ ዓመት ስንት ቀናት እንዳሉት ብጠይቅህ? 365 ትለኛለህ፤ በምን ዐወቅህ? ብልህ ምንአልባት ሀገረኛ አድርገህ፤ አቡሻአርን ትጠቅስልኝ ይሆናል። እኔ ግን 364 እንደሆነ አስረግጬ አስረዳሀለሁ። የፊደል ገበታችንስ ከ'ሀ' ነው ከ'አ' መጀመር ያለበት? ከገበታውስ ላይ መውጣት ያለባቸው ፊደላት እንዳሉስ ታውቃለህ? ኢትዮጵያውያንስ የሴም ልጆች ነን ወይስ የካም? የካም ትለኛለህ አይደል? ካምን እኮ አባቱ እረግሞታል። ታዲያ እንዴት ነው እኛ የተቀደሰ ሕዝብ የምንሆነው? እኛ የካም ሳንሆን የብሩኩ ሴም ልጆች ነን እልሀለሁ። በዕጣ የደረሰውንም እርስት ማየት ትችላለህ፤ ብዙ ቦታዎችን እየጠቀለለ ይመጣና ወደ አፍራም ግራ ያደርሳታል፤ ወደ ግዮን ፈሳሽ ካደረሳት በኋላ ወደ ሰሜን ቀኝ ወደ ኤደን ገነት አድርሶ ወደ ምስራቅ እስኪደርስ ይወስደዋል፤ ከኤዶም ምድር ሁሉ ያለውን ምስራቅ ይሰጠዋል። ራፋ ወደ ሚባል የምስራቅ ተራራ እስኪደርስ፤ መጥቶ በግዮን ኤደን ገነት ድረስ ይገባል።

እዚህ ጋር ነው ብዙዎቻቹ የምትሸወዱት የካምም ዕጣ ወደ ግዮን ማዶ ስለሆነ። ግን በግዮን ማዶ በስተቀኝ ነው ወደ ሰሜንም ይደርሳል። በሰሜን በኩል ነው የሴም እርስት ኤዶም ድረስ እንደሆነች አባቱ ኖኅ ሲያውቅ ለአምላኩ ምስጋና አቅርቦአል። ሴምን አብልጦ መርቆታልና፤ ካም ልጆቹን ይዞ ወደ ዕጣው ሲሄድ ልጁ ከነዓን፣ እስከ ግብፅ ያለችውን የሊባኖስ ባህር ወደዳት እዚህ ካልሆንኩ ብሎ ሲያስቸግር ይህ አከባቢ የኛ አይደለም እንዳታስረግመን እያሉ ሲነዘንዙት እንቢ በማለቱ ጥለውት ሄዱ። ሴም ዕጣው ግዮንን ወስዶ በኤዶም ገነት፣ የኤርትራ ባሕርን ይዞ በተራሮቹ በኩል

እስከ ሕንድ፣ ሊባኖስ፣ የአሱርን ተራሮች ይዞ እስከ ኤላም ሀገር ነው። ይህቺም ምድር ለዘለዓለም ሊይዟት ለሴም እና ለልጆቹ ተሰጠች።

አሁን ጆሮህን አሲዞ የሚያስሮጥህን እውነት ከመንገሬ በፊት ጥያቄ ልጠይቅህ፤ ክርስቶስ እውነተኛ ስሙ ማን ነው? በስንት ዓመቱስ ተጠመቀ? ስንትስ ዓመት ነው በዚህች ምድር የተመላለሰው? የተጠመቀው በዮርዳኖስ ሳይሆን በግዮን ወንዝ እንደሆነ ብነግርህ ምን ትላለህ? ታሪኮቻችን ሆን ተብለው አልተበረዙም ተመርዘዋል እንጂ። እውነት ብለህ የያዝከው አብዛኛው የተመረዘ ነው። እውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች ስፍራውን እስኪረከቡ እንደተመረዙ የቆያሉ። እነሱ ስፍራውን ሲቆጣጠሩት ለመርዙ መድኃኒት ይዘው ብቅ ይላሉ። እውነት ኢትዮጵያ ማን ናት? ግዛቷስ እስከ ምን ነው? ''Until the lion learns how to write, every story will glorify the hunter'' ይላሉ እራሳቸው። ባለመድኃኒት በሕዝቡም በመኳንንቱም ዘንድ የተከበረ ነበረ። ጥበብን ለክፉ በሚጠቀሙ ጥበብ በተገለጸችላቸው እራስ ወዳዶች ምክንያት፤ ደህናዎቹ ለድህነት የተገለጡት ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ ሆነው አብረው ተወቀጡ እነዚኛው በዝተው መልካሞቹ መነመኑ፤ አዲሱንም ሲያሜ ፈርተው እራሳቸውን ሸሸጉ። የያዙትንም ሊያሸጋግሩ የሚገባው ተቀባይ በማጣት ጥበባቸውን ወስነው አስቀሩት። አየህ አሉባልታስ እንዴት መጥፎ እንደሆነ?

ዕውቀትን ከማን እንደምትቀበል አስተውል! ሁሉ ነገር ከምንጩ ሲሆን መልካም ነው። እኔ ከዝንዠሮም አልመጣሁም! ዓለምም በቢግባንግ ቲዮሪ አልተፈጠረችም! ሰዶማዊነት አጸያፊ እንስሳዊ ተግባር እንጂ መብት አይደለም! ዝሙት የዘመናዊነት መገለጫ ሊሆን አይችልም! ታሪክን ማወቅና በጽድቅ እግዚአብሔርን ማምለክ እንዲሁም አለመቃም፣

አለማጨስ፣ እርቃን አለመሄድ፣ ሴት ጸጉሯን መሸፈኗና፣ ቀሚስ መልበሷ፣ አለመኳኳሏ ኋላ ቀርነት አይደለም! ይህንና የመሳሰሉትን ማድረግ ደግሞ አራዳ አያስብልም! ብዙ Misconceptions አሉ ለምሳሌ የሰው ልጅ እርሻ ከመጀመሩ በፊት አድኖ ነበር የሚበላው ይልሀል። የመጀመሪያው የሰው ልጅ አራሽ እንጂ አዳኝ አልነበረም! ያ ማለት ግን አደን አልነበረም ማለት አይደለም። ለምሳሌ የይስሐቅ የበኩር ልጅ ዔሳው አደን የሚያውቅ የበረሃ ሰው ነበር።

ስለ Stone Age ደግሞም ጽሕፈት የተጀመረው በቻይናዎች ነው። የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ቋንቋ አልነበራቸውም። ልብስ አይለብሱም ነበር። ማነው ይህን ትምህርት ያስተማረን? የሚገርመው አማኝ የተባለውም ሕዝብ ይሄን ያምናል ክርስቲያኑም ሙስሊሙም። ቅድም እንዳልኩህ፤ big bang theory ይሉሀል። የሚገርመው ደግሞ ተሸውደዋል እንደ እዚኛው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ theory የላቸውም። ምክንያቱም የራሳቸው science ምንም ከምንም አይፈጠርም ስለሚል ይህ ፉርሽ ይሆናል። ይህን ሁሉ ለማጥራት የዘፍጥረትን የመጀመሪያዎቹን ምዕራፍ ማንበብ በቂ ይሆናል።

ሁሉም ሚዛኑን ማስተካከል መጀመር አለበት። አራዳነትን ከፋራነት፣ ማወቅን ከአለማወቅ፣ የምንመዝንበትን ሚዛን ማስተካከል አለብን። ክፍል ውስጥ አንደኛ ሲወጣ የኖረ ልጅ በሕይወቱ ፈል አድርጎ ልታገኘው ትችላለህ። እንደዚያውም ደግሞ ከተማሪዎች መጨረሻ ደረጃን አስጠብቆ የኖረ ተማሪ ትዳር መስርቶ፣ ልጆች ወልዶ፣ ንብረት አፍርቶ፣ የመረጠውን የሕይወት መንገድ እየተጓዘ ስኬታማ ሆኖ ልታየው ትችላለህ። በሌላ በኩል ሚሊየኖችን አፍስሶ አንድ ድርጅት ያቋቋመና የከሰረ ሰው ልታውቅ ትችላለህ፤ ሌላው ደግሞ ያንኑ

በጥቂት ገንዘብ ምናልባትም ተበድሮ ጀምሮት ትርፋማ ይሆናል።

ለምን ይመስልሃል? ኣይኪው እና ኢሞሺናል ኢንተለጀንስ ሰውን ከሰው ይለየዋል። መማርህ ኣይኪውህን ሊያሳድግ ይችላል፤ ሕይወት ግን ኢሞሺናል ኢንተለጀንስ ይፈልጋል። በኑሮህ የሚያጋጥሙህ ክስተቶች በሙሉ በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ውሳኔ ከወሰንክ በኋላ ትጸጸታለህ፤ ክፉ ከተናገርክ ኣልያም ስህተት ከሰራህም እንደዛው የስሜት ልህቀት ሲኖርህ ግን እራስህን ስለምትቆጣጠርና ያለብሽጉታ ኣጥርተህ ስለምታስብ እኚን የመሳሰሉ ስህተቶችን ለመሥራት ለራስህ እድል ኣትሰጠውም። ከሌሎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖርህ እና ውሳኔዎችህ በሎጂክ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑም ያደርግሃል። ዝምታ ሰፈነ… እንዲህ ኣይነት ልጅ ትሆናለህ ብዬ ኣልጠበኩም ነበር። እውነት ብለሀል በትምህርት ደረጃ ሰው መገመት ከስህተት ይጥላል። ለማንኛውም ተነስ ወደ ቤት ኣድርሰኝ መተጣጠብ ይኖርብኛል። ልብስም ቀያይሬ መልሰን እንገናኛለን ብሎት እሱ ወደ መታጠቢያ ቤት ኣመራ።

ዘሩባቤል የባጃጁን ሞተር ኣንስነስቶ ለመሄድ ተመቻችቶ ቆመ። ሂሶጵ ከሆቴሉ ከመውጣቱ፤ ጥግ ይዘው ቆመው የነበሩ ሁለት ሲቪሎች ቀረቡት፤ እንደኛው መታወቂያ ኣውጥቶ በማሳይት ራቅ ብላ ወደ ቆመችው ፓትሮል በመጠቆም እንዲሄድ በእጅ ምልክት ሰጠው። ዘሩባቤል ምክንያቱ ግልጽ ባይሆንለትም፤ ምን እየተከሰተ እንዳለ ግን መገመት ኣልከበደውም። ማርሽ ኣስገባና ነዳጅ በቀኝ እጁ እየሰጠ በሱ ቀኝ በኩል ስለ ነበሩና የኋላ በር ስላልነበረው፤ በግራ እጁ የግባ ምልክት ኣሳይቶት መንቀሳቀስ ጀመረ። ሂሶጵም በሩጫ ኣምልጦኣቸው ባጃጁ ውስጥ ገባ። ዘሩባቤልም ወደ ግራ በመታጠፍ በኣራቱ ኣንበሳዎች ኣደባባይ ኣድርጎ ወደ መርካቶ የሚወስደውን ኣስፓልት ይዞ፤ ዳገቷን መውጣት

ጀመረ። የደህንነት አባላቱም በያዙት ፓትሮል ደረሱበት። ከጎን ገጭቶ ሊጥላቸው መሪውን ሲጠመዝዝ፤ ቁልቁለቱን መውረድ ጀምሮ ነበርና ፍሬኑን እንቅ አደረገው። እነሱ ወደ ኋላቸው በመቅረታቸው በግራቸው የነበረ የነዳጅ ማደያን ኮንክሪት ገጭቶ ቆመ። ዘሩባቤልም ፍጥነት ጨምሮ መንዳት ጀመረ ማን ነህ ቆይ? ለምንድነው የፈለጉህ? ምን አይነት ጉድ ውስጥ ነው የገባሁት በማርያም እያለ ጠየቀው። አሁን እሱ ምንም አይጠቅምህም ብቻ እናምልጣቸው ፍጠን። እናምልጣቸው? እኔንም አካተትከኝ ጎበዝ ሲለው በድጋሚ ደርሰውባቸው ነበር ይኸውልህ እኔም የማይሆን ነገር ነው የጀመርኩት። ሳይህ ስላሳዘንከኝ ነው እንጂ እንዲት ነው በባጃጅ ፓትሮል የሚመለጠው? አሁን እማ አንዴ ጀምረነዋል።

ፓትሮሉ ይደርስባቸዋል ግን መንገድ ሊዘጋባቸው ወይም ሊገጫቸው አልቻለም። ወደ ምሳ ሰዓት መቃረቢያም ስለ ነበር፤ መንገዱ በታክሲ እንዲሁም በባጃጆች ተሞልቶ ስለ ነበር፤ ለፍጥነትም እንደፈለጉ ለመሆንም አልተመቻቸውም። ነገር ግን ለዘሩባቤል አመቺ ነበር። በተለምዶ ዳሎል ተብሎ የሚጠራው አከባቢ ሲደርሱ ግን ለደህንነት አባላቱ ይበልጥ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ፤ ተሰልፈው ቆመው ለነበሩት ባጃጅ ሾፌሮሽ ምልክት ስለ ሰጣቸው፤ ሁሉም ከቆሙበት በመነሳት ይከተሉት ጀመር እስካሁን የመጡት ቀጥታ መንገድ ነበር አሁን ንግድ ባንክ አደባባይ ጋር ሲደርሱ ወደ አውቶብስ ተራ ከመታጠፋቸው በፊት፤ ሾፌሮቹ የነዘሩባቤል ባጃጅ የቱ እንደሆነ ለመለየት አዳጋች በሚያደርግ መልኩ መጠላለፍ ጀመሩ። ይህንም እያደረጉ ወጋገን አደባባይ እንደደረሱ፤ ለሦስት በመከፈል ተበተኑ። የተወሰኑት ወደ አውቶቢስ ተራው ወረዱ፤ እነዘሩባቤል ያሉበት ቡድን ወደ ሸዋበር ታጠፉ፤ የተቀሩት ወደ ፈቲ መስጂድ ታጠፉ። የፓትሮሉም ሹፌር የትኞቹን

እንደሚከተል ግራ ስለገባው አደባባዩ ውስጥ ቆመ አባላቱም በሶስቱም አቅጣጫ ያማትሩ ነበር። ዘሩባቤልም አንገቱን አውጥቶ ወደ ኋላው ሲመለከት ሂሶጵ አንገቱን ጎትቶ በማስገባት ግራ ስላጋባቹኅቸው እዛው ቆመው እያማተሩ ነው የሚሆነው ካዩህ አበቃልን! አለው። አብረውት የነበሩት ጓድኞቹም ተበታተኑ። አንደኛው የደህንነት አባል ግን አንገቱን ባወጣበት ቅጽበት አይቶት ነበርና፤ ምንም እንኳን እሱ መሆኑን መለየት ባይችልም ሌሎቹ ይህን ሲያደርጉ ባለማየቱ በእጁ ወደ ሽዋበር ጠቆመ ክላክስ ያደረገ እጅግ በሚያስፈራ ፍጥንት ይከተሏቸው ጀመሩ። ዘሩባቤልም ወደ ውሃልማት ለመሄድ አስቦ በፎቶ ፓርክ ወደ አዌቱ መናፈሻ አቀና። ተከተሉት ወደ ዋናው አስፓልት መውጫ ሲደርስ ግን ነዳጅ ቀድቶ የሚወጣ ተሳቢ መንገዱን ዘግቶት ነበር። ደረሱባቸው፤ ጄነራል ሂሶጵ ወዲያው ከባጃጁ በመውጣት በተሳቢው ጎማ ስር ተንሸራቶ በማለፍ እግሩ ወደመራው ስፍራ ሮጠ። ዘሩባቤልም መሮጥ ጀመረ። ነገር ግን ደረሱበት፤ አንደኛው ተንደርድሮ እግሩን ጠለፈው። በአፍጥሙ አስፓልቱ ላይ ወደቀ እጅግ መቱት ይዘውም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት።

ጄነራል ኑ ይግቡ ብሎ አንድ ጥቁር ቀለም የተቀባች ቶዮታ የያዘ ሰው ጋበዘው። ዘወር ሲል ያውቀዋል ያ ትላንት ማታ ከቤት እንዳይወጣ አስጠንቅቆት የነበረው መቶ አለቃ ነበር። ገባ ልክ አልሰሩም ጄነራል፤ ብቻ ብሎ ወደ ማረፊያው ይወስደው ጀመር ሂሶጵም ምንም አልተነፈሰም። እንደ ደረሱ ግን ዘሩባቤልን ይዘውታል አይደል በማለት ጥየቀ፤ አዎ በማለት መለሰ። ምንም እንኳ ባያውቀውም እሱ ነው ብሎ በመገመት። ወጣቶች ስለሆኑ ልባቸው የሚላቸውን ነው የሚከተሉት እርሶን በመርዳቱ ጥፋት ባይሰራም ያደረገው ተግባር ብዙ ቅጣቶች እንዲደርስበት ያደርገዋል። ለማንኛውም የሚፈልጉት እቃ ካለ ያሰናዱና እንውጣ። ስፍራ መቀየር ግዴታ ነው። እሱም ዱላው ሲበዛበት መናገሩ አይቀርም።

ባይናገር እንኳ እዚህ መሆኖ ጥሩ አይመጣም። እሺ ያው የምፈልጋቸው እቃዎች ሁሉ አንድ ቦርሳ ውስጥ ነው ያሉት ብሎ ወደ መኝታ ክፍል በመግባት ይዞ መጣ። ጠዋት ከዘሩባቤል ጋር የገዟቸው አልባሳት እዚያው ባጃጅ ውስጥ ጥሎአቸው ወርዶአል። አሁን ከአሉበት አራዳ አካባቢ ወደ ቆጪ አምሩ።

ዘሩባቤል የደረሰበትን ዱላ መቋቋም ባለመቻሉና አንደኛው ልቡን ስለረገጠው ትንፋሹ ተቋርጦ ድንገተኛ ክፍል ገብቶአል። ለሰዓታትም በተደረገለት የህክምና ርብርብ ሊነቃ ችሎአል። ሰዓቱም ወደ እኩለ ለሊት እየተጠጋ ነው። እህቱ እና እናቱ ለረጅም ሰዓታት ማልቀስ ስላላቆሙ፤ ማንም እንዳይገባ የሚለውን ትህዛዝ ሽራ ዶክተሯ እንዲገቡ ብትፈቅድም፤ እንዲጠብቁ ከታዘዙት ፖሊሶች መሃል አንደኛው አልፈቀደም። ጓደኞቹ ግን ይህን ሲሰሙ መረበሽ በመጀመራቸው አንዳቸው ብቻ እንዲገቡ ተፈቀደ፤ እህቱ ገባች የምታየውን ማመን ስላልቻለች አብዝታ አለቀሰች። ጥዋት ያየችው ወንድሟ አልመስል አላት ግሉኮስ ተሰክቶለት ፊቱ በሙሉ አብጦ ስታየው አንጀቷ አልችል አላት። ያያታል አያወራትም፤ ዶክተሯ በቃ አሁን እራስሽን አረጋጊና ለእናትሽ ሁሉ ሰላም እንድሆነ ንገሪያቸው። አይዞሽ የኔ ቆንጆ ጠንክር በይ ብላ ይዛት ልትወጣ ስትል ዞራ ምትወደውን ጥብስ እሰራልሃለው እሺ ትበላላህ አይደል ብላ እያለቀሰች እጁን አንስታ ጉንጯ ላይ ስታስደግፈው፤ በሁለቱም ዐይኖቹ አነባ። ይህን ስታይ ዶክተሯ ስሜቷን መቆጣጠር አቅቶአት ወጥታ ለፖሊሶቹ አብሮት የሚሆን ሰው ያስፈልገዋል አለበልዚያ ለሚሆንው ሁሉ አላፊነት ትውስዳላችሁ አለቻቸው፤ ተስማሙ። አብራው እንድትሆንና እየመጣች እንደምታያቸው በመንገር ተለየቻቸው።

ስትወጣ ሁሉም ሲመለከቷት አይዞአቹ ደህና ነው ወደ ቤት መሄድ ትችላላችሁ፤ እንደምታዩት ነው እዚህ ብትሆኑም መግባት አትችሉም። አውቃለሁ ለልባቹ እዚህ መሆን ይሻላቹሀል ግን ለሱ ምንም አትጠቅሙትም። ፖሊሶቹ እንኳን እዳያችሁት እየተቀያየሩ ነው፤ እናንተም ሂዱና አረፍ በሉ። ጠዋት ከፈለጋችሁ መጥታቹ ታዩታላቹሁ። እናቱን እዚህ ብርድ አታስመቷቸው ስትል አይ ልጄ እዛ ልጄ ሞት አፋፍ ተኝቶ ብርድ እኔን ምን ያደርገኛል ብለሽ? እንዲያው ቢቻል ብትቀይሪኝ ብሄድስ እንዴት ይተኛልኛል? አይዞት እማማ፤ እዚህ እኛ አለን እሱ ምንም አይሆንም። ይልቅ የእርሶን እንዲ መሆን ሲሰማ እሱ እየተጨነቀ ነው። እሱም ማረፍ ስላለበት እሺ ይበሉኝና ይሂዱ እባኮትን እናቴ፤ በብዙ ልመና የሰፈር በጓደኞቻቸውም ጉትጎታ የሱም ጓደኞች ተጨምረው፤ ዘሩባቤልን ለእህቱ ጥለው ሄዱ።

ከተወሰኑ ቀናትም በኋላ ዘሩባቤል ሙሉ በሙሉ አገገመ። ነገር ግን ከሆስፒታል ወደ ቤት ሳይሆን ወደ ምርመራ ክፍል ነበር ያመራው። በዚያም ሆስፒታል ሳለ ክፍል ውስጥ የሚያገኙትን ሰው እያስወጡ ለሚጠይቁት ጥያቄ ሲሰጣቸው የነበረውን መልስ ስለ ሰጣቸው፤ ወደ ማረፊያ ክፍል አስገቡት። በዚህ መሃል ጄነራል ሂሶጵ በጥፋተኝነት ስሜት ከመብሰልሰል ባሻገር የሚችለውን ሁሉ ከማድረግ አልቦዘነም ነበር። ነገር ግን ምንም ያህል ዘሩባቤልን ከእስር ማስፈታት ለቡድናቸው ቀላሉ ነገር ቢሆንም እሱን ከእስር ማስፈታት ትዕዛዙ ከላይ መምጣት ነበረበት። ይህን ደግሞ አደጋው ከፍተኛ ነበር። በዚህ ሁኔታ ቀናት ከተቆጠሩ በኋላ ሂሶጵ እራሱን እየቀያየረ በመውጣት የቤተ ሰቦቹን ቤት አፈላልጎ አገኘ። ማን እንደሆነ ግን አልነገራቸውም። በተለዋወጡትም ንግግር መሃል የቀን እቁብ እንዳለበትና ለባለ ቤቱም የቀን ገቢ ማስገባት እንደ ነበረበት ግን ለአሁን እሳቸው እየሸፈኑለት እንደሆነ ሲሰማ አዘነ። ባጃጅ ምን ያህል

እንደሚሸጥ ጠየቃቸው? ለምን እንደፈለገ አንደኛው ወንድሙ ጠየቀው? የሚገዛለት ሰው ቢኖር... ሁሉም በአንድነት ሳቁበት። ግራ በመጋባት ለምን እንደሳቁ ጠየቃቸው እናቱም ልጇ ይኸውልህ ባላስለመንኩት ሰው የለም። አሻፈረኝ ብሎኝ እንጂ እኔ ለእሱ አንሼ መሰለህ? እራሴ ነኝ የምገዛው ብሎኝ እንጂ። እኔ ሙች ለባጃጅ አንሼ አሉት። መልካም እናቴ ብሎ የፈላለትን ቡና ጠጥቶ ተሰናብቶአቸው ወጣ።

ከዚህ በላይ ልጁ ባልሰራው ወንጀል መቀጣት አይኖርበትም። አሁኑኑ መፈታት አለበት። እያለ ከራሱ ጋር እያወራ ስልክ ለመደወል ከኪሱ አወጣ። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያውቃቸው ሁለት ሰዎች ናቸው አንደኛው ጄነራል ሠሀረ ናቸው። ምንም አማራጭ የለኝም እያለ ቁጥር መምታት ሲጀምር ዘሩባቤልን አየው። ደነገጠ አንደበቱ ተሳሰረበትና የሚናገረውን አጣ። እንደፈራው ግን አልሆነም። አንቺ ጉደኛ እኔን እዛ ሸቤ አስወርውረሽ እዚ ፊፊ ትያለሽ አ? አለው። ሂሶጵ ተንደርድሮ ሄዶ አቀፈው። ጀርባውን መታ መታ አድርጎ ፓፓ አረጋጊው ብሎ እጁን ከአንገቱ ላይ አስለቀቀው። ና ቤት እንግባ ብሎ ይዞት ገባ። ሂሶጵ ከአይምሮው በላይ ሆኖበታል። ዘሩባቤል ግን ከጓደኞቹ ጋር ምንም እንዳልተፈጠር፤ እንዴት እንደተገናኙ፣ እንዲት ሲያመልጡ እንደነበረና እንዴት እንደተያዙ እየተሳሳቁ ያወራሉ። አብዛኛው ቋንቋቸው ግን አይገባውም ነበር። አማርኛ እያወሩ አለመግባባት ዘሩባቤል እንደሚለው ፋራ ሆንኩ ወይስ አረጀሁ? ለካስ እንደማይገባኝ እርግጠኛ ስለነበረ ነው እኔን እንዲ ያላወራኝ ብሎ በራሱ ሃሳብ ፈገግ አለ።

ዘሩባቤል እና ጓደኞቹ ኳስ ለማየት ሲወጡ እሱንም ይዘውት ወጡ። ሂሶጵ ግን ሚሰራው ሥራ እንዳለና ቤት መግባት እንዳለበት ነገረው። አንደኛው ጓደኛቸው እንዲሸኘው ተነጋግረው እነሱ በሌላ መንገድ ታጠፉ። ሂሶጵም ቤት ከገባ በኋላ ቨርቹአል ሚቲንግ ከእነ ጄነራል ሠሀረ ጋር ተቀመጠ። በዚኛውም ኮንፈረንስ ዝግጅቶች ሁሉ እንዳለቁና ወደ ተግባር ለመግባት መወሰኑን ተረዳል። በዚህም መሰረት የሂሶጵ ወደ ባህርዳር መሄድ የግድ እንደሆነና ዛሬ ማታ ወደ አዲስ አበባ መመለስ እንደሚኖርበት፤ ለዚያውም እንዲረዳ የዛሬውን የኬላ ጥበቃ ስምሪት የሚወስዱት አባሎች ስለሆኑ፤ ያለ ስጋት መምጣት እንደሚችልና በአየር መንገድ አደጋ እንዳለው ተነግሮት፤ ሙሉ ፍቃደኛነቱን አስታውቆ ኮንፈረንሱ እንዳበቃ፤ የተላከለትን ዳጎስ ያለ ዶኩመንት አዘውትሮ በሚጠቀማት የአፕል ምርት በሆነች አይፓድ 12 ማገላበጡን ቀጠለ።

ይህን ሲያደርግ ቆየና አመሻሽ ላይ ለዘሩባቤል ደወለለት። ቤት እንዲመጣ ቢነግረውም 1፡45 የሚጀምረውን ኳስ ማየት እንደሚፈልግና እንዳማይችል ስላሳወቀው፤ ሰው እንዲልክለትና እራሱ ያለበት እንደሚመጣ ነግሮ ስልኩን ዘጋው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የተላከው ልጅ በመድረሱ፤ ዘሩባቤል ወደ ሚገኝበት ስፍራ አቀኑ። በመንገድ ጓደኛውንም ዘሩባቤልን እንደጠየቀው ተመሳሳይ ጥያቄዎች ያቀርብለት ጀመር። ሂሶጵ የተረዳው አንድ ነገር ቢኖር ተመሳሳይ የሆነ ግንዛቤና ባህሪ እንዳላቸው ነው። ይህኛው ትንሽ ግልፍተኛነት ይታይበታል እንጂ። ደርሰው እንደገቡ ጄነራል ሂሶጵ አዳራሹ በወጣቶች ተሞልቶ በማየቱ ተደነቀ። ከተወጠረው አቡጀዲ ላይ እየነጠረ ከሚመለሰው ብርሃን በስተቀር አዳራሹ ሙሉ ጨለማ ነበር። ከብርሃን የመጣበት የዐይኑ ብሌን ጨለማውን እስኪዋሀደው ጠብቆ፤ የሚመራውን ወጣት እየተከተለ

ወደ ተዘጋጀለት ከጣውላ ወደ ተሰራ አግዳሚ መቀመጫ አመራ። ፈቀቅ ብለውለት ተቀመጠ።

አዳራሹን የሞላውን ድምጽ እንደ ዐይኑ ጆሮው አለምድ ስላለው ምቾት ነፍጎት ነበር። ሀሳቡን የሚወስድ አንድ ክስተት ተከሰተ ያ በወጣቶች ተሞልቶ የነበረው አዳራሽ በፉጨትና በጩኸት ተናጋ ደንገጥ ብሎ ሲመለከታቸው ሁሉም ዐይናቸው አቡጀዲው ላይ ነበር። ለካንስ የኢትዮጵያ ሯጮች ውድድር ላይ ነበሩ። የመጨረሻው ዙር ደውል በመደወሉ ሁሉም ከተቀመጡበት ጭምር በመነሳት፤ በከፍተኛ ሞራል ሆነው ይጮሀሉ። ሦስት ኢትዮጵያዊያን እንስት አትሌቶች ተከታትለው ከፊት ይመራሉ፤ ጩኸቱ በረታ ሂሶጵም ሳይስበው ብድግ ብሎ ማጨብጨብ ጀመረ። ወደ መጨረሻ ያልተጠበቀ ክስተት ተፈጸመ። ከኋላ የነበሩት የኬንያና የኡጋንዳ አትሌቶች ፍጥነት በመጨመር ቀድሞአቸው ገቡ። ኢትዮጵያዊቷ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቀቀች።

የወጣቶቹ ስሜት ወዲያው መቀያየር ጀመረ። የያዙትን እቃ መወርወር የጀመሩም ነበሩ። አንደኛው የሂሶጵን ትኩረት ሳበው፤ በእልህ ያለቅስ ነበር ተገረመ። ታዲያ ባከናአል እያልን የምንቆጭበት ትውልድ የትኛው ነው? እርግጠኛ ነኝ ሌላ ከተማም ሄጀ ይህን ሪሰርች ብሰራ የማገኛቸው ወጣቶች እንደዚ እንደሚሆኑ። እስካሁን በዚህች ከተማ ያየኋቸው ወጣቶች በጣት የሚቆጠሩም ቢሆኑ፤ እኛ ያላስተማርናቸውን የሀገር ፍቅር በሚያስቀና መልኩ ተላብሰውታል። ስለ ሀገራቸው እራሳቸው ተመራምረው አውቀዋል። ጀነራል ኖውሌጃቸውም ቢሆን የሚያኮራ ነው። እኛ የራሳችንን ድክመት በእነሱ ለማሳበብ እንሞክራለን እንጂ ብዕሩም፣ ሚዲያውም፣ ተደማጭነቱም እኛው ጋር ስላለ ሀይ ባይም ስለ ሌለን እንጂማ እነሱ ይኸው እንዲህ ሆነው አሉ። ተስፋቸውን ያጨለምን እኛ፤ በማያውቁት መንገድ የመራናቸው እኛ፤

አልፎ ተርፎ ወቃሽ ሆነን አረፍነው። የተበላሸ ነገር እንኳ ቢኖር ቀርበን፤ አቅርበናቸው የልባቸውን መስማት ነበረብን፤ ያን ያደረግነው መች ነው? ወደድንም ጠላን ኢትዮጵያ የእነሱ ናት።

ድንገት ትከሻውን ወዝውዞ አነቃው የት ሄድክ? እ አለሁ አንድ ሀሳብ ቢጤ ገብቶኝ ነው አለ ሂሶጵ፤ ዘሩባቤል ካላስቸገርኩህ አንድ ጊዜ ውጭ ላውራህ አስቸኳይ ነው!

።፡ አሁንም አስመልጠኝ አይሆንም መቼስ ነው ወይስ ሙሉ ብርጌድ መጡብሽ?

።፡ እንደዚያ አይደለም።

።፡ ስቀልድህ ነው። ና እሺ ግን አፍጥነው ኳስ ሊጀምር ነው።

።፡ አያቆይም።

አጠገቡ የሚገኝ ካፍቴሪያ ገብተው እንደተቀመጡ፤ የማን ደጋፊ ነህ አለው ሂሶጵ፤ ምን ጥርጥር አለው የታወቀ እኮነው ብሎ ከውስጥ የለበሰውን ጀርሲ አሳየው። ዛሬ ከማንቸስተር እና ከአርሰናል ማን የሚያሸንፍ ይመስልሃል ብሎ ጠየቀው በተራው፤ አይ እኔ እንኳን ስለኳስ ብዙ እውቀቱ የለኝም። ከሜሲ እና ከሮናልዶ ማንን ታደንቃለህ ብሎ ጠየቀው ሂሶጵ መልሶ፤ ዘሩባቤልም ፈገግ ብሎ ይህቺ ቶፒክ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሰው ኳስ አዋቂ ነው እንዲባል የሚያነሳት ናት። ሁለት ቀን ኳስ ያየውም እኩል ሊከራከርባት ይፈልጋር። ድሮ በጭፍን ነበር አሁን አሁን የልጁን ማንነት ለማወቅ

ከፈለክ ይህን ቶፒክ ማንሳት በቂ ነው። የአንዱ አድናቂ፤ አንዱን ለማበሳጨትም ይሁን ላለመሸነፍ ሲያበሻቅጠው ትሰማለህ። ሁለቱ እኮ ፍጹም የተለያየ ስታይል እና ብቃት ያላቸው ተጫዋቾች ናቸው አንዱን በሆነ ነገሩ ብታደንቀው አንዱን ደግሞ በሌላ። ሁለቱም የእግር ኳስ ፈርጦች ናቸው። ሁለቱንም በአንድ ዘመን ማየታችን እድለኞች ነን ብዬ አምናለህ አስበኸዋል ኳስ ያለ ሁለቱ?

ሂሶጵ መስማት ፈልጎአል ሰዓት ግን የለም። የጓጓለትን ታሪካዊውን በእንቁላል የተሰራ የተባለውን የንጉሥ አባ ጂፋር ቤተ መንግስት እና እንደዛ የሚወራለትን ጂማ ዩኒቨርሲቲም እንኳን ተደብቆም ለመጎብኘት አልተሳካለትም። መልካም ስልክህን ስጠኝ! አለው፤ ውስጡ ያለውን ፋይል አይተህ ልትገርፈኝ ነው አ? ብሎ እየሳቀ ከፍቶ ሰጠው። እንዳታቋርጠኝ ይኸውልህ ዘፋባቤል፤ ቤተ ሰቦችህ ሁሉን አጫውተውኛል እምነትህንም አከብራለሁ። ግን ሰው የሚልህንም መስማት አለብህ። ሰርተህ መኖር እንደምትችል ሁሉም አቅምህን ያውቃል። ለራስህም ያረጋገጥክ ይመስለኛል። አሁን እኔ ልረዳህ ሳይሆን ከምችለው ጥቂት ላደርግልህ ነው፤ ፍቅረኛ እንዳለህና አብራችሁ መኖር እንድትጀምሩም እንደምትፈልግ አውቃለሁ። የምታሽከረክረው ባጃጅም የሰው እንደሆነም ጭምር። ሁላችንም የሆነ ቦታ ላይ የሆነን ሰው እርዳታ ፈልገናል አንተ ወጣት ነህ። አዲስ ሕይወት መጀመር ይኖርብሃል። እዚህ ከተማ ቆንጆ የሚባል ቪላ ቤት ጥሩ ሰፊር ምን ያህል እንደሚሸጥም አውቃለሁ። እናም አክቲቭ ለመደረግ ያንተን ፊርማ እና መታወቂያ ብቻ የሚፈልግ በሥምህ የተከፈት የአቢሲንያ ባንክ ቡክ አስወጥቼልሃለሁ። ፎቶህን እህትህ ናት የሰጠችን እናም በውስጡ ይህን ለማድረግ እና ለተለያዩ ሌላ ወጪዎች የሚሆን ገንዘብ አስቀምጬልሃለሁ። አልጠቀመውም ብትል ገንዘቡ ማንም ሳይጠቀምበት ይከስራል። መልሼ

ልላክልህ ብትል እንዴት አድርገህ? ያለህ አማራጭ መጠቀም ብቻ ነው። ይህን ነገር ካንተ ወገን ማንም የሚያውቅ የለም። እህትህም ብትሆን። እኔ አሁን ሁለት ሰዓት ወደ አዲስ አበባ እመለሳለሁ። በሌላ አዙሪት እንገናኛለን። አሁን ግን እዚህ ላይ እናበቃለን። መቼም ቢሆን አልረሳህም። ከኋላ ጭንቅላቱን በቀኝ እጁ ይዞ ግንባሩን ከግንባሩ አጋጨና መልስ ሳይጠብቅ ተነስቶ ሲራመድ። ዘሩባቤልም ተነሣና እንባ ያቀረረ ዐይኑን እየጠራረገ አቀፈው። በዚህ ተሰነባበቱ።

ጀነራል ሂሶጵ ያለበት ፒካፕ ውስጥ ሹፌሩን ጨምሮ ሦስት ተጨማሪ የደህንነት አባላት አሉ። አበልቲ የምትባል አነስተኛ አንድን ከተማ ከአንድ ከተማ በሚያገናኝ አውራ ጎዳናን ተከትሎ፤ ከጎዳናው ጫፍ እና ጫፍ ከሚመሰረቱ አነስተኛ መንደሮች ወደ አንደኛው እንደ ደረሱ፤ ብዙ መኪናዎች ቆመው በማየቱ፤ ምን ተከስቶ ነው? በማለት ጠየቀ ሾፌሩም ያው በተለምዶ ቃጥራ በመባል ነው የሚጠራው፤ የምሽት ጉዞ ከአዲስ አበባ ተነስተው ወደ ተለያዩ የሀገሪቷ ከተሞች፤ የተለያዩ መገልገያዎችን የሚያጓጉዙ የጭነት መኪናዎች ወደ መዳረሻ ያቸው ንጋት ላይ ደርሰው የማራገፍ ልማድ ስላላቸው፤ እንዲሁም ነጋዴዎች ማታ ተጉዘው በጠዋት አዲስ አበባ ደርሰው የሚፈልጉትን እቃ ገዝተው በዚያው እለት በማታ ጉዞ ወደ የመጡበት የመመለስ ልማድ ስላላቸው፣ የተወሰኑ ነጋዴዎች እንዲሁም አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች ነቃ ለማለት እየቃሙ ነው የሚጓዙት። መስመራቸው ደግሞ የጂማ የሆኑቱ እዚህ ሲደርሱ ሺሻ ለመጠቀም ይቆማሉ። ቀሪዋንም መንገድ በንቃት ይጓዟታል ብሎ አስረዳው። አቁምልኝ ማየት እፈልጋለሁ በማለት አስቁሞ ወረደ።

ስፍራው እንኳን የለሊቱ እኩሌታ የተጋመሰበት ይቅርና ከጨለም እንኳ ገና ግማሽ ሰዓት ያስቆጠረ አልመስልህ አለው። ተዟዙሮ ተመለከተ፤ ከየበሮቹ በረንዳ ላይ በከሰል ማንደጃ ያለን እሳት ፍም እንዲሆን የምታራግብ ሴት፣ ብርጭቆ የምታጥብ፣ ከተጠቃሚዎች ገንዘብ የምትቀበል ብዙ አስተዋለ። አንደኛዋ ትኩረቱን ያዘችበት፤ ገና አንድ ፍሬ ልጅ ናት እድሜዋ እንኳን ዐሥራ ሁለት መሙላቱን እጠራጠራለሁ እንዴት በዚህ ሰዓት አለመተኛቷ ሳያንስ ብርድ ላይ ቁጭ ብላ ምድጃ እንድታራግብ ትታዘዛለች? ብሎ ሲጠጋት ምድጃውን እንደ ያዘች ወደ ውስጥ ገባች። ተከትሎአት ገባ፤ ቤቱ በጭስ ታፍኖአል። የጭሱ ሽታ ግን አስደሰተው። ግባ አለችው ጥግ ይዛ በመርፌ ፎይል እየበሳች ያለች እንስት፤ በሁለቱም በኩል ተደርድረው የተቀመጡት ተጠቃሚዎችም በጪስ የተሸፈነውን ፊታቸውን ባያሳዩትም እንደ እንግዳት ተቀበሉት። ተሸጋሸገው አስቀመጡት ወዲያው ወደ ጫወታቸው ተመለሱ። ከጎኑ የተቀመጠው ያዝ ብሎ እጇታውን አቀበለው፤ ይቅርብኝ ሲለው፤ አምጥታ ሌላ የሺሻ እቃ ከፊቱ አስቀመጠችለትና በምን ይሁንልህ? አለችው፤ ምኑ? አላት። ስለ ተረዳችው የሺሻውን እቃ እያነሳች ሰው እየጠበክ ነው? የሚል ጥያቄ አቅርባለት ሄደች።

ሂሶጵ መቀመጥ ፈልጎአል ግን ሁኔታው ግራ ስላጋባው ወጥቶ መኪና ውስጥ ገባ። ሹፌሮችና ነጋዴዎች ናቸው አላልከኝም ነበር እንዴ? አዎ! ታዲያ የጓደኛሞች ስብስብ እንጂ በመሃላቸው ሌላ የሌለ ነው የሚመስሉት፤ ሁሉም በአንድነት ነው የሚያወሩት የሚሳሳቁት። ልክ ነው ቀን በቀን ስለ ሚገናኙና እዚህ መስመር ላይ አብዛኞቹ ብዙ ዓመት ስለ ሠሩ ይተዋወቃሉ፤ ባይተዋወቁ እንኳ ወዲያው ይላመዳሉ በማለት መለሰለት መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ያለ ምንም እንከን ጊቤ ደረሱ ለፍተሻ የቆሙ መኪኖችን ተመለከተ፤ ከባድ የጥይት እሩምታ ተከፈተ ሁለቱ በፍጥነት በመውረድ ጭንቅላታቸውን ቀብረው ድምጹ ወደ መጣበት አቅጣጫ ሮጡ። ከደቂቃዎች በኋላ ተመልሰው መጡና ሹፌሩን እንሂድ አሉት። ጀነራል ሂሶጵም ምን ተከስቶ እንደ ነበር ጠየቃቸው እነሱም የቡና ኮንትሮባንድ የጫነ ተሽከርካሪ ኬላ ጥሶ ነው አሁን በቁጥጥር ስር አውለውታል የኛም መንገድ ከዚህ በኋላ ሰላም ነው በማለት መለሰ።

:::

ናቡከደነጾር ለሁሉም የሚኒስተር ቢሮዎች እንዲሁም ሲቪል ሰርቪስ አመራሮች ይድረስ ሲል፤ በአማካሪው በኩል የተጻፈ ጥብቅ መመሪያ እንዲላክ አድርጓል። ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ሠራተኛ፤ ከሃይማኖት ነክ ጉዳዮች እራሱን እንዲያገል! የሚል በውስጡም የተለያዩ አዳዲስ ሕግጋትን የያዘ ሲሆን፤ ይህን በማያደርጉ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወሰድ ይገልጻል።

ይህ በሆነ በሶስተኛው ቀን የኢትዮጵያን አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስን ለሁለት የከፈለ፤ ሌላ ሲኖዶስ እንደ ተቋቋመ በዜና ታወጀ። አስቀድሞ በታቀደው መልኩ የብዙዎች ድምጽ ታፈነ፤ እንደተጠበቀው ግን አልነበረም። ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር በነቂስ መቃወምና ከነባሩ ሲኖዶስ ጎን መቆሙን ማሳየት ጀመረ። ይህም በጉልበት ፍላጎቴን አስፈጽማለሁ ብሎ ከተነሣው ቡድን ጋር ግጭት እንዲፈጠር መንስሄ ሆነ።

ናቡከደነጾርም በሃገሪቷ የመንግሥት ጣቢያ በመቅረብ፤ በግልጽ ይህ ካልተፈጸም የከፋ እልቂት በሀገሪቷ እንደ ሚከሰትና በመቶ ሺዎች በአንድ ለሊት እንደሚታረዱ ዛተ። ይህን ጊዜ የተለያዩ መሰሪ ንግግሮችንም ይሁን ድርጊቶችን እያዩ በየዋህነት ያልፉ የነበሩ የሀገሪቱ ዜጎች እውነተኛ ማንነቱ ተገለጸላቸው። ጥቂት የማይባሉ አሁንም የእሱ እጅ የለበትም በሚለው እምነታቸው ጸኑ። የቤተ ክርስቲያኗ አለቆች የሆኑ የመንጋው ጠባቂዎችም ይሁኑ ምእመናኑ በአንድ መንፈስ ቆሙ። ከአለቆቹ መሃል በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ይሁዳ የሆኑ ዋነኛ አስፈጻሚዎች ሆነው የተገለጡም ነበሩ፤ የበግ ለምዳቸውን ካወለቁት ጎራ ተካተቱ። የቤተ መንግሥት አካላት በዚህ አላበቁም እንደዛቱት በኃይል ቤተ ክርስቲያንን ለመቆጣጠር ሙከራ ማድረግ ጀመሩ። ሕዝቡ የሃይማኖቱ ዘበኛ ሆኖ ነበርና በተሰማሩበት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር በመገኘት የገቡትን ማስወጣት፤ ሊገቡ ያቀዱትን መንገድ በመዝጋት ተጋድሎውን ጀመረ። ኃይል መጠቀም የጀመረው መንግሥትም ወደ ምእመናን መተኮስ ጀመረ። እነዛንም አማኞች ለሰማዕትነት ማዕረግ ሞሽሯቸው።

ይህ መሆን ሲጀምር ከቀድሞው ይበልጥ ሕዝቡ ተቆጣ። ድምጽም ማፈን አልተቻለም ይህ ከጥቂት አክራሪ ቡድኖች በስተቀር የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በዘር በሃይማኖት ያልተገደበ ስሜት ነበርና። አማኞችም የምዕላ ጸሎ ያዙ።

የፈጀውን ያህል ሕዝብ ይፍጅ ይህን ጉዳይ በድል መወጣት እፈልጋለሁ፤ አሸናፊው እኔ ነኝ በማለት ከፊት ለፊቱ የሚገኘውን ገመድ አልባ የቢሮ ስልክ አንስቶ ወደ መሬት ፈጠፈጠው። ሁሉም የከተማዋ ሰፈሮች በአልሞ ተኳሾች እንዲከበቡ፤ አመቺ አመቺ የሆኑ ሕንጻዎች ተመርጠው እዚያው ላይ መሸገው እንዲዘጋጁ፤ ትዕዛዝ በሚሰጣቸው ጊዜ ያገኙትን ሰው አናት አናቱን እንዲቦተርፉ አሁኑኑ ስምሪት ይጀመር። በመቀጠል

ኮማንዶዎች ወደ ቤተ ክህነት ይላኩ። የመገናኛ ብዙሀናቸው ሲግናል ይቋረጥ! ጳጳሳቱ በሙሉ እንዲታሰሩ። ማን አለቃ እንደሆነ ከዚች ደቂቃ አንስቶ ዓለም ማወቅ አለበት። ይህ ትዕዛዜ ሳይፈጸም አንዳችሁም ወደ እዝች ቢሮ ድርሽ እንዳትሉ ውጡልኝ! ብሎ ሰብስቦአቸው የነበሩትን አመራሮች አዘዛቸው።

ከሰዓታት በኋላ በጻፊው፤ በአዲስ በተቀየረው የቢሮ ስልክ ጥሪ ደረሰው፤ ኢታማዦር ሹሙ በቁጣ ድምጸት የሚታዘዛቸው እንደጠፋና ሁሉም እያመጹ እንደሆነ፤ ይህም የሠራዊቱ እንቢተኝነት እንዳስቆጣቸው ለናቡከደነጾር አስታወቁ። ከዚህም እንዲያው በቁጣ ብዙ ከተናገረ በኋላ ወሳኝ የዕዝ ከፍተኛ አመራሮች አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠሩ በማለት ስልኩን ዘጋው።

ስብሰባው ተጀመረ ናቡከደነጾርም በኃይልና በቁጣ ተናሮ እንደጨረሰ ለተሰብሳቢዎቹ እድል ሰጠ። የሁሉም ሀሳብ ግን አንድ ነበር፤ ሕዝቡ ተቆጥቶአል የእምነቱ ተከታዮች ብቻ ደግሞ አይደሉም፤ በመላው ሀገሪቷ ያለውን ይህን ሁሉ ሕዝብ ደግሞ እንተኩስበት እንኳ ብንል ገድለን አንጨርሰውም። አሁን እንኳ ውጭ ያለው ሕዝብ ለመሞት ተዘጋጅቶ ነው የወጣው። እንዲ ሲሆን ደግሞ ምን እንደሚከሰት የታወቀ ነው፤ በመላው ሀገሪቷ ምን ያህል ሠራዊት እንበትናለን? ፍቃደኛስ የሚሆኑት ምን ያህል ናቸው? ሁኔታዎች በዚሁ ከቀጠሉስ ሠራዊቱ ወደ እኛው አፈሙዙን እንደማያዞር በምን እርግጠኛ እንሆናለን? ይህ ነገር ቢቀርብን ይሻላልና የመሳሰሉ ሀሳቦች ከአመራሮች ተሰነዘሩ። ሰዓታት የፈጀውን ስብሰባ ነገ እንቀጥለዋለን ብሎ በተነው።

ይህ ከሆነ ከሰዓታት በኋላ ናቡከደነጾር የንግሥና ወንበሩን ለቆ፤ እንዲቀመጡበት የጋበዛቸውና አንገቱን ደፍቶ እየታዘዛቸው ያሉት አሜሪካዊ ቤሮ ውስጥ የነበሩትን የኢትዮጵያ ናቡከደነጾርን ጨምሮ ዐሥራ አምስት ጉምቱ ባለ ሥልጣናት እያፈራረቁ ከተመለከቱ በኋላ፤ ባለፉት ሁለት መንግሥታት ፓትርያሪክ ለማሾም አቅደን ያንንም አድርገናል። ዋናው ዓላማችን ቤተ ክርስቲያኗን ማፍረስ እና ሕንጻዎቹ እንዳሉ ወርሶ እኛ ለምንፈልግበት ዓላማ መጠቀም ነበር። በሌሎች ዓለማት ይገኙ እንደ ነበሩት አብያተ ክርስቲያናት፤ ነገር ግን ይህቺኛዋ እንደ ሌሎቹ አይደለችም ውስብስብ ናት። ይህ ፓትሪያርክ የመቀየር እቅዳችን የመጣው ካሳለፍነው ልምድና ይህች ቤተክርስቲያን ላይ በተለያየ መልክና ወቅት ስናደርገው በቆየነው ሦስት እና አራት መዶ አመታትን በፊጀ ምርምር ነው። እንደምታዩት አልተሳካም! ፓትርያርክ በመቀየር የሚመጣ አንዳች ለውጥ እንደሌለ ተረድተናል። ምናልባት የምንፈልገውን ለመሾም ያመቸን ይሆናል ግን ያ ማለት ምንም ማለት ነው። ቤተ ክርስትያኗ የምትመራው በፓትሪያርክ ይሁን እንጂ፤ የምትተዳደረው በማይሻር፣ በማይለወጥ ሕግጋት ነው። ያኚን ሕግጋት ደግሞ የሰሩላቸው የቀድሞዎቹ ናቸው። ይህ እንደሚመጣ በተለያዩ መጻሕፍት ጽፈው አስቀምጠውታል። እኛ በቀላሉ እንዳይገኙ ያደረኛቸውና ያቃጠልናቸው አያሌ መጽሐፍት አሏቸው እንደዛም ሆኖ እጃችን ያልገቡ በርካታ አሉ።

ስለዚህ ቀድሜ እንደ ነገርኳችሁ፤ ዓላማችንን ለማሳካት ማድረግ ያለብን መዋቅሩን መበጣጠስና አዲስ መዋቅር መዘርጋት ነው። ያን ካሳካን በኋላ አዳዲስ ለአዲሱ ማኅበረሰብ የሚጠቅሙ የሚመስሉ ግን ቤተ ክርስትያኗን ከስር ገዝግዘው የሚጥሉ ሥርዓቶችንና ሕግጋትን ማጽደቅ እንጀመራለን። በነባሯ ቤተ ክርስትያን ይህን ለማድረግ የሚያስችል አንዳች መፈናፈኛ የለም! መደረግ ያለባቸውና መደረግ የሌለባቸው ሥርአቶች ሁሉ ተጽፈው

ተቀምጠዋል። አቃጥሎ መጨረስም አይቻልም፤ አድራጊው አካል እንኳን የሚጠብቀው ቅጣት ተጽፈው ተቀምጠዋል። እንዳልኳችሁ ሁሉንም የሕግም ሆነ የሥርዐት መጻህፍቶቻቸውን ዋናውን መጽሐፍ ቅዱስ ጨምሮ ብትሰውሩባቸው፤ አልያም ብታቃጥሏቸው ቃል በቃል ምዕራፍ በምዕራፍ ደግመው የሚጽፉ ሊቃውንት አሏቸው።

መፍትሄው ሁሉን ከምንጩ ማድረቅ ነው! ያንን እያደረግን ሰንብተናል። ጥቂት ነው የሚቀረን ከዓላማችን ለመድረስ፤ ግን ብልሃት ይጠይቃል። አሁን የያዝነው መንገድ ትልቁ ስኬታችን ይሆን ነበር፤ ግን አልተሳካም መሞከር እናቆማለን ማለት አይደለም፤ እውነቱን ስነግራችሁ ቁጭ ብዬ ሳስበው ይህቺን ቤተ ክርስትያን መረከብ የሚሳካልን አይመስለኝም፤ የቻልነውን ያህል ግን እንሞክራለን እንችላለንም። የዛሬ አራት እና አምስት መቶ አመት ላይ ቁጭ ብለው አንድ አንድ መዛግብት ከዛም እንደሚቀድም ይጠቁማሉ ዛሬን ቆልፈውት ነው ያለፉት ነገንም ጨምሮ። ስንዱዋ እመቤት እያሉ ቤተ ክርስትያናቸውን ሲጠሯት አጋነው ወይም ካላቸው ፍቅር የተነሣ ብቻ እንዳይመስላቹ፤ የእውነታቸውን ነው። እነዛን አባት ተብዬዎች ባገኛቸው በቁም አቃጥያቸው የምረካ አይመስለኝም። አሁንም ያሉትን ሳያቸው የሚያቅለሸልሹኝ ለዚያ ነው፤ ሕዝቦቹም ጭምር። ሰዎች! የዚህችን ሀገር ሕዝብም ቢሆን አቅልላቹ እንዳታዩት፤ ገድለን ቀብረነዋል ከእግዲህ ነፍስ አይዘራም ብለን፤ የአሁኑን ጨምሮ ስንት ጊዜ እንደ አምላኩ መቃብር ፈንቅሎ ጉድ ሰርቶናል መሰላችሁ። ኢትዮጵያን ለመረከብ መጀመሪያ ይህች ቤተ ክርስቲያን መጥፋት አለባት! ሀገሪቷ በአንተ የምትመራ እንዳይመስልህ! አሁንም ቢሆን የቤተ ክህነት መንፈስ ከቤተ መንግሥት አልወጣም። የኢትዮጵያን የመንግሥት መዋቅር ውስጡን ስትመለከቱ የምትረዱት እሱን ነው።

የሆነው ሆኖ አሁን በሚዲያ ወጥተህ ሰብስበሃቸው አስታራቂ መምሰል አለብህ፤ ነገር ግን ሹመታቸው መሻር የለበትም በፍጹም! አስታራቂ ካልመሰልክ፤ የተነሣው ማዕበል መንግሥትህን ጠርጎ ይዞት ይሄዳል። እናንተም አግዙት ለዚህ ነው መርጠን የሾምናችሁ። ለእኛም ስንት ለፍተንባት እጃችን የገባችን ሀገር እንዲሁ መልቀቅ ይሆንብናል። ያን ደግሞ በፍጹም አንፈቅድም! ስናደርገው ብንቆይም፤ ከአንተ ጀምሮ የትኛውም ሥልጣን የተባለ ስፍራ ያለ እኛ እውቅና ዝር የሚል ሰው እንዲኖር አንፈቅድም! ይህ በአስቸኳይ መፈጸም ያለበት ጉዳይ ነው! እንደማይዋጥልህ አውቃለሁ፤ ይህንም አጋጣሚ ተጠቅመህ ደማቸውን መጠጣት እንደምትፈልግም ጭምር። ግን በስሜትህ ሳይሆን በጭንቅላትህ እንድታስብ ደጋግሜ ነግሬሃለሁ።

የበቀል ቀን ይመጣል አሁን ያቀን አይደለም፤ እኔን ከአሜሪካ ድረስ ያመጣኝ ይህ ጉዳይ ቀላል እንዳልሆነ መረዳቱ አያዳግታችሁም። ሁላችሁም አረጋጉት ለጥፋት ሌላ ቀጠሮ ቅጠሩ። እናንተ መሥራት ያለባችሁን ሁሉ ሥሩ። በሚዲያ እየወጣችሁ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን ንገሩት። እመኑኝ የፈለገ ክፉ ብትሆኑ ይህን በማድረግ ብቻ አደናብራችሁ ብዙሃኑን ከጎናችሁ ማሰለፍ ትችላላችሁ። በዚህ ጉዳይ አትታሙም ነበር። ምነው ብዙሃኑ ንግግራችሁን ማመን ሲያቅሙ ተስፋ ቆረጣችሁ እንዴ? እንዳትቆርጡ! ከሁሉ በላይ አበክሬ የማሳስባችሁ ወጣቶቹ በምንም ተአምር አንድነት እንዳይኖራቸው አድርጉ! ከገዛ የእናቱ ልጅ ጋር እንኳን አንድ አይነት አቋምና መርህ እስካይኖረው ድረስ ልዩነትን፣ መከፋፈልን፣ ጸብን፣ አለመተማመንን፣ ጥርጣሬንና የመሳሰሉትን ዝሩባቸው! አሁን አዘጋጅ ያልኩህን ጉባኤ ለማታ አድርሰው። ያን ተካፍዬ መመለስ ይኖርብኛል፤

ጥበብ ይሙላባችሁ፤ አለበለዚያ መንግሥትህ ተነጥቃ ለሌላ ትሰጣለች።

ለሊት እንቅልፍ በዐይኑ አልዞር አለች፤ ለነገሩ የዛሬ ይለይ እንጂ ከሚወስዳቸው መድኃኒቶች አንደኛው የእንቅልፍ ከሆነ ሰነባብቷል። አልጋ ላይ ከወጣ ቆይቷል ባለ ቤቱም ብትሆን ደጋግማ ጸጉሩን እየዳበሰች ልታረጋጋው ሞክራለች፤ ቢሆንም እንደተለመደው አመናጭቆዋታል። የሷ እንዲህ መሆን ጥቅም እንደሌለው እየገባት መጥቷል አሁን እሷ ተኝታለች፤ ድንገት ብድግ ብሎ ከአልጋው በመውረድ የራስጌውን የአልጋ መብራት ከግርግዳ አጋጨው። ባለ ቤቱም በሰማችው ድንገተኛ ድምጽ ከእንቅልፏ ነቃች፤ ስትመለከተው የራስጌው መብራት ጌጥ ተሰባብሯል፤ ፈቀቅ አለችና የአልጋውን እራስጌ ተደግፋ ቁጭ አለች። ያገኘውን እቃ መሰባበር ጀመረ፤ እኔ አይደለሁም ይህቺን ቤተ ክርስትያን ተብዬ እንዳልነበረች ካላደረኳት! ካልበተንኳት! ወደ ነፋስ የተበተነ ዱቄት ካላደረኳት እኔን አያድርገኝ! እንደ አዋረደቺኝ ባላዋርዳት እያለ ጸያፍ ቃላትንም እየተጠቀመ ቆይቶ፤ ድንገት ከሚስቱ ጋር ዐይን ለዐይን ተገናኘ፤ እያፈጠጠ ወደ እሷ በመጠጋት፤ እዚህ ክፍል እንዳላይሽ ብዙ ጊዜ ነግሬሻለሁ እንቢ እያልሽ ነው? ማን ስለሆንሽ ነው ትዕዛዝ የማትቀበይው? ካሜራ ከሌለ አጠገቤ ላይሽ አልፈልግም ብዬሻለሁ! ተነሽ ውጪ! ብሎ ጸጉሯን በመጎተት በአይበሉባው መታት። አንተው ነህ እኮ የጠራኸኝ እወጣለሁ እሺ ልቀቀኝ አለችው። እና የጠራሁሽ እንደሆነስ? መልሰሽ አትወጪም ብሎ አንድ ጊዜ ደገማት፤ መልሶ መንጎራደድ ጀመረ። የሚመጡለት ሀሳቦች ሁሉ የጭካኔ ቢሆኑም አንዱም አላረካህ አለው። አሁን እያሰበ ያለው ደግሞ ምናልባትም ለወደፊት የሚተገበር እንጂ አሁን ከማስታረቅ በቀር አማራጭ እንደሌለው ሲታወሰው አንድ ጊዜ ጎሮሮውን

እስኪያመው ጮኸ! አባት ተብዬዎቹን በየተራ አርዳቸኋለሁ! አልወጣለትም ሄዶ አልጋው ላይ ተደፋ።

በንጋታውም እንደታዘዘው ሁሉም ተዘጋጀ፤ ጳጳሳቱም በቆራጥነት እስከ ሞት ድረስ መዘጋጀታቸው ነገሩ እውን እንዲሆን አስገዳጅ ሁኔታ ሆነ። ምንም እንኳ እርቅ የሚል መሰሪ እቅድ ይዘው ቢሆንም የተከሰቱት፤ ጳጳሳቱም በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ በጥበብ አከሸፉት ሊመጣ ካለውም ጥፋት ቤተ ክርስቲያን አመለጠች።

ይህ በእንዲህ እያለ ሁኔታዎች ሌላ መስመር ያዙ። ተኝቶ የነበረ ሕዝብ ከፊሉ መልሶ ወደ እንቅልፉ መሄድን አሻፈረኝ አለ። መደራጀት አንድ መሆን አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ እንደሆነ ተገነዘበ።

ማኔ ቴቄል ፋሬስ

በመላው የሀገሪቷ ክፍለ ሀገራት መደራጀትና አመጽ እንደ ወረርሽኝ ሆኖ ተዛመተ። በተለያየ የሃሳብ ጽንፍም ውስጥ የነበሩም ቢሆኑ፤ አንድ በሚያደርጋቸው የጋራ በሆነ ተዳፍኖ የጠፋ መስሎ በነበረ የሀገር ፍቅር ስሜት ውስጥ ተሰባሰቡ። ይህ ከተደራጁት ወጣቶች በስተቀር፤ ለማኅበረሰቡ ድብቅ ሆነ።

ቴራስ ከተማዋ ውስጥ የሚያየው ሁኔታ እያስደሰተው አይመስልም። ከምን ጊዜውም በበለጠ የደህንነት መስሪያ ቤቱ ጥብቅ የሆኑና ከበድ ያሉ ትዕዛዛትን በመቀበሉ የእነዚህ ለውጦች ዋና አስፈጻሚ ደግሞ እንደተለመደው እራሱ ቴራስ ሆኖ በመመረጡ ስጋቱን ጨምሮበታል። ከሕቡህ ድርጅታቸው ከዞዓር አባላትም ጋር ዛሬ ስብሰባ አለበት። ስለዚህ ወሎ ሰፈር ከሚገኘው የደህንነት መስሪያ ቤት፣ ቢሮውን ቆልፎ ወጣ።

ከስፍራው እንደ ደረሰ ቀድመውት ደርሰው ስለነበር፤ እንደገባ ሁሉም ከተቀመጡበት ተነሡ። ቴራስም በተደጋጋሚ ይህን ተግባር እንዲያቆሙ ቢነግራቸውም፤ ፍቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ቀስ በቀስ እሱም እየለመደው መጣ። ከወገቡ ጎንበስ ብሎ የተዘጋጀለት ወንበር ላይ ተሰየመ። ወንድሞቼ ብዙ የምንወያይባቸው ርዕሶች አሉ። ቀዳሚ ቢሆን የምመኘው ግን ሰሞኑን በሃገራችን እየተስተዋለ ያለውን የወጣቱን እንቢተኝነት

በተመለከተ ነው። እንዲህ መንቃቱ የሚያስደስት ቢሆንም፤ የብዙዎችን ቀልብ መግዛቱ በዚያው ልክ አደጋ ይዞ መምጣቱ አይቀርም።

ይህ ወጣት በአንዳች አጋጣሚ የመጠለፍና በማይገቡ ግለሰቦች አልያም ቡድኖች እጅ ከወደቀ የሚከሰተውን እልቂት እና ኪሳራ ከወዲሁ ግንዛቤ ውስጥ መክተት ተገቢ ነው። አሁን እንኳን ከናቡከደነጾር ቢሮ በወረደ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የኔው የደህንነት ቢሮ የሳይበር ሴኪውሪቲው ክንፍ መልምሎ፤ የኛው አባል የሆነ ግለሰብ መሪ አድርጎ ብቅ እንዲል እንዲያደርግ ተልዕኮ ተሰጥቶኛል። የኛው ስል አንድ አንዶቻችሁ ግር እንዳይላችሁ የመንግሥት የደህንነት ቢሮ በአመራር ደረጃ አባል መሆኔ እንዳይዘነጋችሁ። አሁን የተሰጠኝ ተልዕኮ ቢሳካስ? አይሳካም እንጂ። ይህን ወጣት እየለቀሙ ማሰር ከፍ ሲልም መረሸን ነው ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው። ይህ በመንግሥት እጅ የገቡ እንደሆነ ነው። በሌሎች እጅ ሲወድቁስ በመዋጮ ሥም የወጣቱን ገንዘብ መጋጥ፤ አለፍ ሲልም አዲስ አምባገነን ወደ ሥልጣን ማምጣት? በተቻለን መጠን ሊሆን ያለውን፤ ወደ ፊት በቅርቡ የሚመጣውን ቀን ለበጎ መጠቀም፤ በየሶሺያል ሚዲያው የኛው የዘጓር አባላት አይጥ አድሬስ እየቀየሩ፤ ድምጻቸውን በተወሰነ መልኩ ኢንህንስ እያደረጉ ወጣቱን ማንቃት ይኖርባቸዋል። መደራጀት ካለበትም ደግሞም የግድ ነው! የግድ እኛ ጋር መምጣት አይኖርበትም። ግን በዚህ መልኩ አይደለም። አሁን የምጠራችሁ ልጆች በየግል አካውንቶቻችሁ ዶክመንቶች ይደርሷቹሀል። ይህ ተልዕኮ የእናንተ ኃላፊነት ይሆናል ማለት ነው፤ ብሎ የሀያ አባላትን ሥም ጠራ። ተልዕኮአችሁ ቀላል ቢሆንም በጣም ወሳኝ እና ትልቅ ነው። ልምራችሁ ብሎ የሚመጣ ማንንም ሰው እንዳትቀበሉ! እራሳችሁ ምራን ብላችሁ እስካልመረጣችሁት ድረስ ነው የምትሏቸው። ልዩ ልዩ ዓላማ ይዘው በአፍ ጻድቅ እየመሰሉ፤ ፍላጎታቸውን እስኪያሳኩ እውነተኛ ማንነታቸውን ደብቀው ተወዳጅና

ሩሩህ መስለው የሚቀርቡ፤ የበግ ለምድ የለበሱ ለመንጋው ጥቂት ርህራሄ የሌላቸው፤ ነጣቂ ተኩላዎች እጅ እንዳይወድቁ ማድረግ ይኖርብናል።

ሁለተኛው እና ወሳኙ ደግሞ መጀመሪያ መደራጀትን ከሰፈር ከጎረቤት እንዲጀምሩ ንገሯቸው እንደዚያ ሲሆን ማን ምን እንደሆነ ይታወቃል ካድሬ ይሁን፣ ለሆድ አደር፣ ቆራጥ፣ ልፍስፍስ፣ አብሮ አደግ ስለሚሆኑ ባይሆኑ እንኳን በደንብ ስለሚተዋወቁ ከማን ጋር እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ሙሉ መረጃ ስለሚኖራቸው ለመከዳት አልያም ተላልፎ ለመሰጠት እሩቅ ይሆናሉ። አብዮቱንም በሚገባ ያቀጣጥሉታል እንኳን አሳልፎ ሊሰጣጡ ጓደኛዬ ተነካ ብሎ ለጥል ከሚጋበዝ አካል ጋር ነውና አብረው የቆሙት።

በዚህ መልኩ ከሰፈር ይጀምርና እያደገ ይመጣል፤ ሁሉ ነዋሪ መጀመሪያ ከሰፈር ይጀምር፤ በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ወጣቶች ይህን ያድርጉ። ቀጥሎ ወደ ተጎራባች ሰፈሮች ስለሚተዋወቁ ኳስ አብረው ይጫወታሉ፣ ቤተክርስቲያን አብረው ይሰማሉ፣ ማህበራቸው ያገናኛቸዋል፤ ማህበራዊ መስተጋብራቸው አንድ ነው። እንዲህ እያለ ይጋጠማል መሪ ለመምረጥም ቀላል አይሆንም ግን አይቸገሩም። አስረግጬ የምነግራችሁ ግን ይህ መሆን ያለበት ነው ግ..ዴ..ታ ነው! አለበለዚያ ባይደራጁ ይመረጣል ይበላሉና። ወደሌላው ከመሄዳችን በፊት እዚኛው ላይ ሀሳብ ያለው? ሁሉም እንደተስማሙበት ገለጹ መልካም ወደ ሁለተኛው እናልፋለን ተራው የሰዓር ነው።

እሺ አመሰግናለሁ ያው ለአክሰንቴ ይቅርታ ታደርጉልኛላቹ ምክኛቱም አማርኛ ሶስተኛ ቋንቋዬ ነው። አታስቡ ከአክሰንቴ ውጭ አቀላጥፌ ነው የማወራው። አስቀድሞ ቴራስ እንደነገራችሁ ሰዓር እባላለሁ። የዚህ ትልቅ ድርጅት የዞዓር አባል ሆኜ በመሃላችሁ ስለተገኘሁ ደስተኛ ነኝ፤ እዚህ ውስጥ ካልተሳሳትኩ በአካል የማውቀው ቴራስን እና ከኤርፖርት የተቀበለኝን ያባልን ነው አንድ ሁለት ቀን የተገናኘኋችሁም አላችሁ። ለማንኛውም እኔ የማተኩረው የቲም ግንባታው ላይ ይሆናል እያሳደግነው እንሄዳለንና። ከአሁን ጀምሮ ሁላችንም በቡድን እንከፋፈላለን፤ ተጠሪነታችንም ለዚያ ቡድን ይሆናል እየአንድ አንዱ ቡድን ግልጽ የሆነ ተልዕኮ እና ግብ ይሰጠዋል። በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ተልዕኮውን መጨረስ ይኖርበታል። አሁን ለየቡድኑ መሪ አንመርጥም። አብራቹ የምትመደቡ ከመሃላችሁ እራሳቹ ትመርጣላችሁ። እሱ የሚሆነው ታዲያ በጊዜ ሂደት ነው፤ ስትመርጡም ግልጽ የሆነ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ፣ አባላቱን የሚደግፍ፣ ለሥራ የሚያነቃቃ፣ ውሳኔ ማሳለፍ ላይ ቆራጥ የሆነ፣ የሆነችም እያላችሁ አድምጡኝ፤ ከምንም በላይ ትችት የመቀበል አቅም ያለው መሆን ይጠበቅበታል።

ሌላው ቡድኖቻችን ከፍ ሲልም ድርጅታችን የራሱ የሆነ ባህል ሊኖረው ግድ ነው። የጋራ የሆነ እሴት እና እምነት ሊኖረን ይገባል እምነት ደግሞ ከምንም በላይ። በውይይት ልናምን ይገባል። ምንም አይነት ችግር ይግጠመን የፈጀውን ያህል ጊዜ ፈጅቶ መፈታት አለበት። ባይቻል እንኳ ጉዳዩ ለጠረጴዛ መቅረብ አለበት፤ በልዩነትም ደግሞ ማመን እና አካታች መሆን ይኖርብናል፤ ከኛ የተለየ ሀሳብ፣ አቋም አልያም አመለካከት ያለው ሰው በፍጹም መገፋት አይኖርበትም። ሁላችንም ከትላንት ዛሬ እንደተሻልን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ከዛሬ ደግሞ ነገ ለመሻል የማያቋርጥ ሥልጠና ለመውሰድና እራሳችንን ለማሳደግ መዘጋጀት

አለብን። ተባብረን መሥራት ይኖርብናል። ግጭቶች አይኖሩም ማለት አንችልም ግን እንዳይበዙ እንዳያቃቅሩንም ወዲያው መፍታትን መልመድ አለብን። ሁሉም አባላት ከአንድ ትልዕኮ ወደሌላ ሲሸጋገሩ አዳፕተቢሊቲ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። እኚህ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው። አሁን በዝርዝር እናያቸዋለን በማለት ረዘም ያለጊዜን ወስዳ ፈጸመችው። መጨረሷን የወደዱት አይመስልም ነበር፤ አመስግናም በድጋሚ ተራውን ለቴራስ አስረከበችው።

እንዲህ እንዲህ እያለ የተያዙት አጀንዳዎች በሙሉ ውይይት ተደረገባቸው። ወደተግባር ገብተን ለውጥ ማምጣት የምንጀምርበት ወቅት አሁን ጀምሮአል። ቀጣይ ስንገናኝ በብዙ የምስራች ተከበን እንደሚሆን ተስፋ አለኝ። አሁን በማህላችሁ የሚዞሩትን እጣዎች ታነሳላችሁ ተመሳሳይ ቁጥር ካገኛችሁት ሰው ጋር ቡድን ትመሰርታላችሁ። ይህ ለአጠቃላይ ተልዕኮ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል። ሌላው ምደባ በየፕሮፌሽናቹ ነው የሚሆነው፤ ምክንያቱም እንደሚታወቀው እዚህ ውስጥ ከኮሌጅ ተማሪዎች እስከ ዩኒቨርሲቲ መምህራን፤ በተለያየ የሞያ ዘርፍ ሀገራችሁን እያገለገላችሁ የምትገኙ ግለሰቦች ስላላችሁ። የእጣው ስነ ሥርዐት እንደ ተገባደደ ሁለን ከፈጸሙ በኋላ ቴራስ ከተቀመጠበት ብድግ በማለት በደሜ ሀገሬ ቀና ትበል! አለ በነፍሴ ትለምልም! በማለት ተቀበሉት፤ ማጨብጨብ ቢፈልጉም ይህ የህቡህ ድርጅት ድብቅ ስብሰባ ነውና አልቻሉም።

ቴራስም ስብሰባውን እንደ ጨረሰ ቀጥታ መስቀል ፍላወር ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ አመራ። ቁልፍ ከኪሱ አውጥቶ መግቢያውን ሊከፍተው ሲል እንዳልተቆለፈ በማየቱ ሰንጴር ውስጥ እንዳለች እርግጠኛ በመሆን በሩን ከፍቶ ገባ። ከአፕን ኪችኑ የሚመጣው የወጥ ሽታ ቤቱን አውዶታል። ቴራስ የሚወዳቸው ምግቦች ከሽን ብለው እየተሰሩ መሆኑን አውቆአል፤ የርሀብ ስሜት

ተቀሰቀሰበት፤ ወደ ሰንጴር ተጠጋና ቆመ። እንደቀድሞው ከኋላ መጥቶ አንገቷን የሚስምበትን አቅም አላገኘም፤ ዘወር ብላ መጥተህል እንዴ ብላ በቀኝ እጇ ማማሳያ እንደያዘች፤ አንገቷና ወገቧ ላይ የቋጠረችው ሽርጥ ልብሱን እንዳይነካው እራቅ በማለት ጉንጩን ሳመችው። መልሶ ሊስማት አቃተው፤ ደክሞህል መሰለኝ ሂድ ተጣጠብና ልብስ ቀይረህ ተመለስ እስከዚያ እኔ አዘገጃጅቼ እጨርሳለሁ ስትለው ምንም ሳይናገር በደመ ነፍስ እየተራመደ ወደ መኝታ ቤት አመራ።

ጠንቅቆም ሲመለስ እንዳለችውም የምግብ ጠረጴዛውን በምግብ አስጊጣ ጠበቀችው። ከአይነቱ አነሰ ባርኮም ሊበላ ሲጀምር አልዋጥ አለው። ሰንጴር የድካም ነው ብላ ስላሰበች እንዲህ ጠብ እርግፍ ብዬ የሰራሁትን ምግብ እማ ትበላታለህ ብላ ጠቅልላ አጇን ዘረጋች፤ ይቅርብኝ እንደገባሁ ሽታው የመብላት አምሮቴን ቀስቅሶብኝ ነበር፤ ምን እንደሆነ አላውቅም ስጎርሰው አልወርድ አለኝ። ሰንጴር ሰሀኑን አስቀምጣ አጠገቡ መጥታ ወንበር ስባ በመቀመጥ በግራ እጇ ትከሻዋ ላይ አስደግፋው ጸጉሩን መዳበስ ጀመረች። ስልኩ ጠራ አኪያ ነበረች፤ ቀና ብሎ ዐያት መልሶ ገልብጦ አስቀመጠው። የወርቅ መሶብ ላይ ትቢያ የነሰነሰ ስለመሰለው ብድግ ብሎ ተነሣ፤ ሰንጴር ደንግጣ ዐይን ዐይኑን በዝምታ ተመለከተችው፤ ቴራስ ግን ቃል አልተነፈሰም ሰንጴር ከተቀመጠችበት በመነሳት ምን ሆነሃል ቴራስ የተፈጠረ ችግር አለ? ስትል ጠየቀችው፤ አሁንም በዝምታ ቆሞ የግራ ጆሮውን በክብ ቅርጽ ያሻል አንዳች ለመፍታት የቸገረው ሀሳብ ሲገባው እንዲህ የማድረግ ልማድ እንዳለው ታውቃለች።

ቴራስ ዛሬ እኮ ቢሮ እድገት ያገኘሁበት ደብዳቤ የተቀበልኩበት ቀን ነበር፤ ከማንም ቀድሜ ላንተ ነበር የደወልኩት። ዝግ ነበር ከዚያ ነው ለአባቴ የደወልኩት። ይህን ደስታዬን ይዤ ነበር የመጣሁት ሀሳቤ እራት ውጭ እንድንበላ ነበር፤ እዚሁ እንደሚሻል ስላሰብኩ

ለመሥራት ተነሣሁ፤ አስቤዛ አልቆ ስለነበር ለመግዛት ስወጣ ጓደኛህን አገኘሁት እያወራን አጋዛኝ፤ እሱ ነው እዚህ ድረስ ያስገባልኝ ሲወጣ ምን ብሎኝ እንደወጣ ታውቃለህ? ቢያንስ የቤተ ሰብ ቅልቅል ብላቹ ሳትጋብዙን አብሮ መኖር የለም አስቡበት ብሎኝ ነው የወጣው። ቴራስ ከድካም መጥቼ እንዲህ ደክሜ የሰራውልህን ምግብ እንኳ ባትበላ እባክህ ዛሬ የደስታዬ ቀን ነው አባቢንም ትርሲት ጋር እንደምሆን አስፈቅጄዋለሁ። ፕሊስ ወይ ልጋራህ ወይ ደስታዬን ተጋራኝ።

ይህን ጊዜ ቴራስ ጨነቀው። ይህን ማድረግ አልቸልም ሰንጴር አሁን ልነግረሽ አልቸልም። ደስታሽንም መካፈል እንደዚያው። ሰንጴር፤ ቴራስ ይህ ስለሥራ ብቻ አይመስልም። ከአለፉት ጊዜያት ጀምሮ አስተውዬሃለሁ፤ ለአሁን ትቼህ እሄዳለሁ። ግን ሁሉን ማወቅ እፈልጋለሁ! ብላ ወደ መውጫው በማምራት ነጠላ ጫማውን በማውለቅ ለብሳው የመጣችውን ሂል አጥልቃ መቆለፊያዎቹን ለማጥበቅ ስታጎነብስ የለበሰችው ጥቁር ስኪኒ ሱሪ ውስጥ የወተፈችው ነጭ ትሸርት ወደላይ በመሰብሰቡ ሽንጧ ላይ አዲስ ንቅሳት ተመለከተ፤ ጽሁፍ ነው ጥርት ብሎ ሊታየው ባለመቻሉ ተጠጋት ስሙ ነው። ስትጨርስ ትሸርቷን አስተካክላ ካፖርቷን ከተሰቀለበት በማውረድ ለበሰችና ዙራ ሳታየው ደህና እደር ብላው በሩን ከፍታ ወጣች። ያየውን ማመን አቅቶታል ሊያስቆማት ጎትቶ ሊያስገባት እንዳትሄድ ሊማጸናት ፈልጎአል አቅም ግን አልነበረውም። ሀሳቡ ለሁለት ተከፍሎአልና አሁን ይበልጥ ጨነቀው።

የተነሣበት ወንበር ላይ ሄዶ ተቀመጠ ሰንጴር እና አኪያ እየተፈራረቁ ይከሰቱበት ጀመር። ሀሳቡ ማብቂያ እንደሌለው ስለተረዳ እንዲበተን ከመፈለግ ተነስቶ ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው በማቅናት እመጓ የሚለውን የዶክተር አለማየሁ ዋሴን መጽሐፍ አነሳ እንዲሁ ሲገልጸው ገጽ 161 ላይ አረፈ፤ ...እውነት ነው የጠራንህ በረከትን በእምነት እንድትቀበል ወዲሁም የትውልዱን ሕመም እንድታውቅ ነው። አንተ ደግሞ ሁሉን የማወቅ ጉጉትና ወረት የሚንጠው የዚህ ትውልድ ናሙና ነህና የሚል ጽሁፍ አነበበ ከመጽሐፉ ክፍል ይህን ቦት ደጋግሞ ማንበቡ ትዝ አለው። ቀጠለ ...በአፍላ ትጀምራላችሁ በወረት ትተውታላችሁ። ያወቃችሁትን ትረሳላችሁ፤ ያላወቃችሁትን ለማወቅ ትጥራላችሁ፤ የያዛችሁትን ትረግጣላችሁ፤ የረገጣችሁትን ትይዛላችሁ። ምኞታችሁ ልክ የለውም፤ አምሮታችሁ ብዙ ነው። የአማራችሁን ስታገኙ ወዲያው ይሰለቻችኋል። ተዉ የተባላችሁትን ትሽራላችሁ፤ የተከለከላችሁትን ትደፍራላችሁ፤ የተፈቀደላችሁን ችላ ትሉታላችሁ። ቤተ መቅደስ እንዳትገቡ ብትከለከሉ ወደ ፊት ቤተ መቅደሱን በመስታወት ሠርታችሁ መቅደስ ባትገቡ እንኳን ሁሉን ከውጭ ሆናችሁ ማየት ትፈልጋላችሁ። ሁሉን ማወቅ ትፈልጋላችሁ፤ በአንዱም ግን አትጠቀሙም። ሁሉ አላችሁ፤ ግን ባዷችሁን ናችሁ። ሃይማኖት እንጂ እምነት የላችሁም! ...መድኃኒት ነው ያልከው? መቀመሚያውን ነግሬህ ማርከሻውን ሳልገልጥልህ መጀመሪያን ብቻ ሞጭልፈህ ትተኸኝ ትሄዳለህ። ጥበብን "ሀ ግእዝ" ብዬ ላስተምርህ ብሞክር፤ መንደር ውስጥ በቃረምከው ዕውቀት ተመክተህ በመሰልቸት "ሆ ሳብዕ" ብለህ ቀድመህ ትዘጋዋለህ። የግል ታሪካችሁ ቢታይ ወጥነት የጎደለው ከዚህም ከዚያም የተልከፈከፈ የተማሪ ኮፋዳ ውስጥ ያለ እህል ይመስላል። ተምራችሁ ዕውቀት ስታገኙ፣ ሰርታችሁ ሀብት ስታፈሩ፣ ከላይ የሆናችሁበትን ሀገር ለቃችሁ ሰፋ ወዳለው እንሂድ ብላችሁ እንደገና

ከታች ትጀምራላችሁ። ትቀጥላላችሁ በመጨረሻ ከጀመራችሁበት ትገኛላችሁ። ቸኩላችሁ ትወስናላችሁ ወዲያው ትጸጸታላችሁ። በጽኑ ታማችኋል። ከታሪክ ፍቅርንና ልማትን ሳይሆን ጥላቻንና ጥፋትን ለይታችሁ ትቆፍራላችሁ። ከዚያም ቀጥላችሁ የከበረ ማዕድን እንዳውጣችሁ ሁሉ በኩራት ደረታችሁን ነፍታችሁ ሳታማርጡ ሁሉን በአደባባይ ትዘሩታላችሁ፤ እናም ወደ ኋላ ስለታሪካችሁና ስለ ቅርሳችሁ ባሰባችሁ ቁጥር ፍርሃትና ሃፍረት ይሰማችኋል። ስልሆነም ከኋላ ታሪካችሁና ክብራችሁ እየራቃችሁ መጣችሁ። ቴራስ መጽሐፉን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ እሱም እዚያው እጆቹን አነባብሮ እጆቹ ላይ ተደግፎ ዐይኑን ጨፈነ።

:::

አኪያ ስልኳን አንስታ ደወለች አልተነሣም፤ ሰዓቱን ስትመለከተው ስድስት ሰዓት ይላል። አስቀመጠችውና ልትጨርሰው ከአስር ያልበለጡ ገጾች የቀሯትን መጽሐፍ አንስታ መስኮቱ አጠገብ ካለው ወንበር ተሰየመች። የጽሁፍ መልዕክት ደረሳት፤ እየመጣሁ ነው ምሳ አብረን እንበላለን ተዘጋጅተሽ ጠብቂኝ! ሳታስበው እራሷን ልብስ እየመረጠች አገኘችው። ከቆይታም በኋላ በሩ ተንኳኳ j'arrive አለች ከውስጥ ሆና በሩን ስትከፍተው ቴራስ ሆኖ አገኘችው፤ ፈገግ አለች ከእግሩ ስር አንዲት ትንሽ ውሻ ከተከፈተው በር ወጥታ ገባች፤ አኪያም Entrez dans la cour ብላ በእጇ ወደ ውስጥ አመለከተቻት። ታምራለች አላት፤ merci! የmaltese ዝርያ ነች አለችው። ከጀርባው አድርጎት የነበረውን እጁን ወደ ፊት በማድረግ ይዞት የነበረውን ጽገሬዳ ሰጣት ተቀብላ አሸተተችው፤ አቀፈችው ተያይዘው ወጡ።

ምሳ እየተመገቡ ቴራስ ሀሳብ እንደገባው ያስታውቅ ነበር። እያወራችው በመሀል በሀሳብ ጭልጥ ይልባታል፤ አኪያም ቴራስ ልክ አይደለህም ችግር አለ ብላ ጠየከችው አልሰማትም እጇን ከፊቱ በማውለብለብ ከሀሳቡ መልሳ ደግማ ጠየቀችው። እሱም መልስ ሳይመልስላት ሊያነርሳት እጁን ዘረጋ፤ ለመጉረስ ስትጠጋ ድንገት ሰንጲር አጠገባቸው በመቆም ሰላምታ አቀረበችላቸው፤ ለአኪያ እጇን ዘረጋችላት እሷም ጨበጠቻት ቴራስን ግን ዝም ብላ ዐይን ዐይኑን ትመለከተው ነበር። ተነሣና ወንበር አምጥቶ እንድትቀመጥ ጋበዛት። አልቀመጥም እቸኩላለሁ አለችው፤ መልካም አኪያ ተዋወቂያት ሰንጲር ትባላለች፤ ሰንጲር እሷ ደግሞ አኪያ ትባላለች ሲል አኪያ ከተቀመጠችበት እየተነሣች እጇን ሰጠቻት ሰንጲርም በተራዋ ጨበጠቻት፤ ተጫወቱ ብላ መሄድ ስትጀምር አይሆን ቁጭ በይ የምናወራው አለን ብሎ እንድትቀመጥ ግድ አላት።

ይኸውልሽ አኪያ፣ ሰንጲር ፍቅረኛዬ ናት። ብዙም አብረን አሳልፈናል። ከብዙም ጉዳዮች ተሸሽጌባታለሁ። አግብቻትም ልኖር ከወሰንኩ ቆይቻለሁ። ሰንጲር የማልዋሸሽ ነገር ቢኖር ቤት ውስጥ ያሉት እቃዎች አብዛኛዎቹን በአኪያ ብታያቸው ትወዳቸዋለች ስሜት ነው የገዛኋቸው፤ አኪያ ማለት የልጅነቴ ናት። አንቺን እየወደድኩሽ ከአንቺ ጋር ሆኜ አኪያን አልረሳኋትም፤ ይህን የማወራሽ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆንሽ ስለማውቅ ነው። ያለውን ነገር ሁለታችሁም ማወቅ አለባችሁ። እዚህም መምጣትሽ ለመልካም ነው፤ ሰንጲር አንቺ ያጎደልሽብኝ አንዳች ነገር የለም። ማንም ሰው ለሚወደው ሰው አንቺ ካደረግሽው በላይ ሊያደርግ አይቻለውም። ሁሉንም ቀናት መዘርዘር ይቻላል አስፈላጊ አይደለም እንጂ ስለምታውቂው። ልብ ግን የሚፈልገውን ያውቃል አንቺ በኔ ያረፍሽው ልብሽ ውስጥ እኔ ብቻ ስላለሁ ነው። በዚሁ ስሜትሽ ልመለስ አልመለስ ሳላሳውቅሽ ብለይሽስ? ትጠብቂኛለሽ፤ ያጥበቃሽ እስከመች

ይዘልቃል? ማብቂያው የቱ ጋር ነው? እንዲሁ መጠበቅ?

ዓለማችን ላይ ጉድ ያስባሉን ፍቅሮች ሁሉንም ብትመለከቺያቸው ሳያልቁ ነው ያበቁት። እሱ ነው ፍቅራቸውን ኃያል ያደረገው። ተቃርነሽ አልያም ተቃቅረሽ የምትቋጪው ፍቅር እዛው ያበቃል ሊመለስም አቅም አይኖረውም። ያልተደመደም ያልተቋጨ እንደሆነስ? ልክ እንደ ነጠላው በጥቂቱ ትዝታን ከእድሜሽ ጋር እየመዘዘ እርቃንሽን ያስቀርሻል። ወደ እድሜሽ አመሻሽ ይገፋሻል። ተስፋ ያኖርሻል ግን ተስፋ ከምታደርጊው ነገር ውጭ እንዳትመለከቺ አሳውሮ ነው። እኔ ለዘመናት በዚህ ድንግርግር ውስጥ ኖሬያለሁ። በሕይወቴ አንቺ እስክትመጪ ድረስ። ትዝታን አደብዝዘሽ ዛሬዬን ያደመቅሽው አንቺ ነሽ ሰንጴር። እንደ ሥምሽ። ግን ትዝታ በአመድ የተሸፈነ እሳት ነው፤ ፍቅር የሚሉት ነፋስ ሲደርስበት ዳግም የሚገለጥ። በሥጋዬ ላንቺ ታምኜ ኖሬያለሁ፤ ልቤ ግን ስለ አኪያ ሲቃትት ከርሞአል። አቁም ቴራስ ከዚህ በላይ የመስማት አቅም የለኝም ብላ ሳግ በሚያቆራርጠው ድምጿት አስቆመችው።

እንባ ያፈነውን ድምጿን እየሞረደች ከአሁን በኋላ ማውራት ትርፉ ድካም ነው ሁሉ ነገር አሁን ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ ጊዜ የማላስተውልና ትላንት በተከሰተው ክስተት ብቻ እዚህ የተገኘው ይመስልሀል? ድርጊቱን ተወው ማሰቡንም እንደዚያው። አንድን ድርጊት ስትሰማው ካልቀፈፈህ፣ ካላስደነገጠህ፣ አለማድረግ ሕግ ሆኖ ቢመጣ ከማድረግ አያስቆምህም። የሕግ ገዢዋ ህሊና ነች። ለዛም ነው ልብህን ጠብቅ ተብሎ የተጻፈው። ህሊናህ ካላስቆመህ ሕግ በራሷ ከንቱ ናት! መግደል እንደ ሚያስቀጣ እያወቀ ከገደለ፤ መስረቅ ያሳስራል እያልከው ከሰረቀ፤ ዝሙት ኅጢያት ነው ብትለው የሚተው ይመስልሀል? የገላህን አላውቅም ልብህ ግን ሲዘሙትብኝ

ኑሮዋል። የእኔ የሆነን ነገር ማንንም ሰው የማስነካም ለማንምም ብዬ የምተው ሰው አይደለሁም! እሱን በደምብ ታውቃለህ። ያ እና ይሄ ለየቅል ናቸው። አሁን አንተን ሰው አይደለም የነካብኝ አንተው እራስህ ነህ። እሷን ገድያት እንኳ የኔ ባደርግህ በድን ገላህን እንጂ አንተን አላገኝህም። እስካሁን የሆንኩልህ የኔ ካላደረገህ፤ ከዚህ በኋላ ምንም ባደርግልህ የኔ እንደማላደርግህ ግልጽ ነው። የማደርግልህም አዲስ ነገር የለም፤ ምክንያቱም የሰሰትኩት አንዳች አልነበረምና። ድንጋይን በውሃም ብታጥበው በቅቤ ለሱ ለውጥ የለውም ለተመልካች እንጂ፤ ውስጡ አይዘልቅምና። ሁሉም ነገር ጅማሬ እንዳለው ሁሉ መጨረሻም አለው። መጀመሪያም መጨረሻም የሌለው የድንግል ማርያም ልጅ መድኅኒ ዓለም ብቻ ነው። የእኔና ያንተም መጨረሻው ይህ ከሆነ እንግዲህ ይሁን! ያለቀ ነገር ወደ ኋላ ስለማይጎትት ወደፊት እንሄዳለን። ካንተ ጋር ይሄን ማውራት በመስታወት ስብርባሪ ከተሰራ አሰፓልት ላይ በባዶ እግር እንደ መራመድ ነው! አስታውስክ? ተነስ እቀፈኝ ብላው እንባዋን እየጠረገች ተነሣች፤ መቆም ስላቃታት መልሳ ተቀመጠች። እግሮቼ የኔ አልመስልሽ እስኪሉኝ ይህን ያህል ዘመን ተሸክመውኝ እንዳልኖሩ፤ አሁን በፊትህ ስቆም ለሰከንዶች መጽናት አቃታቸው ተብረከረኩብኝ። ልቤማ እንዴት ሊሆን? ብላ በድጋሚ ለመነሳት ሞከረች፤ አገዛት ዘለግ ላሉ ጊዜያት አቅፋው መንገዷን ቀጠለች።

ቴራስ እና አኪያም ዝም እንደተባባሉ ምግባቸውንም መጨረስ ሳይችሉ ቀሩ። አኪያም ያለቀሰችበት ዐይኗ እንደቀላ ነበር። ከዚህ በኋላ ቢሮ ገብቼ ሥራም አይሰራልኝም፤ እራሴንም ጀምሮኛል። ቤት ገብቼ እረፍት ባደርግበት ይሻላል አላት፤ ጭንቅላቷን ከላይ ወደታች አወዛወዘች። ሂሳብ ከፍለው ወጡ። ከማረፊያዋ አድርሶአት ወደቤቱ ገባ፤ ጋደም አለበት።

ከእንቅልፉ ሲነቃ እየጨላለመ ነበር፤ ወጣና በእግሩ መራመድ ጀመረ በጋዜቦ አደባባይ አድርጎ ወደ ደም'በል ወረደና እጁን ኪሱ ውስጥ ሲከት ስልኩን በማጣቱ ወደ መጣበት ተመለሰ። ሲገባ ብዙ ጊዜ ተድውሎለት እንደነበር አይቶ፤ ደዋዮቹን ሲመለከት ከመሃል የአኪያ የለም መልሶ ሊያስቀምጠው ሲል አንድ ስልክ ቁጥር ዐየ የደህንነት እና መረጃ ሚኒስተሩ የአቶ ፊንሐስ ስልክ ነበር፤ ደወለላቸው።

፡፡ ልጅ ቴራስ የት ነህ?

፡፡ ቤት!

፡፡ በአስቸኳይ ቢሮ እንድትመጣ!

፡፡ መጣለሁ!

ቴራስ ሲደርስ ሁሉም ተሰብስበው አገኛቸው። ሰዎች በዚህ ምሽት የተሰበሰብነው ከጠበቅነውና ይሆናል ብለን ከገመትነው በላይ ወጣቱ እየተደራጀ ነው። በአስቸኳይ ካልገታነው አደጋው የከፋ ነው የሚሆነው፤ ይህን ጉዳይ አሁኑኑ ማስቆም ይኖርብናል! ይህ ደግሞ የኛ ሀላፊነት ነው። በተሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ምን ላይ ደርሳቹሀል ሪፖርት ፈልጋለሁ አለ አቶ ፊንሐስ። ቴራስም ፊቱ እንደተኮሳተረ ከቢሮው ይዞ የመጣቸውን ሰነዶች ክብ ሰርተው ከበውት ወደተቀመጡበት ሰፊ ጠረጴዛ አንድ አንድ እያደረገ በመበተን ዘርዝሮ በማስቀመጥ ቆሞ ያብራራ ጀመር። በስድስት ቡድኖች የደህንነት አባላቶቻችንን በመመደብ ዋና ዋና በተባሉ የከተማዋ ክፍለ ከተሞች በቂ የሚባል ኃይል አሰማርተናል። በሚገባም ሥራቸውን እየሰሩ ይገኛሉ፤ እስካሁን ዋና

የድርጊቱን ጠንሳሾች ማግኘት ባንችልም በቅርቡ መሪ ብለን በምንሰጣቸው በእኛ የተመለመለ ሰው አማካኝነት ሁሉን በቁጥጥር ስር እናውለዋለን። ያም ሰው በሚገባ ተዘጋጅቶ ወደ ማኅበራዊ ሚዲያው ለመውጣት ፈቃድ ብቻ ነው የሚጠብቀው። ለምን አልተፈቀደለትም? ሲል ጠየቀ አቶ ፊንሐስ። ወጣቱ ምን አይነት አጀንዳዎችን ነው የያዘው? እንዴትስ ነው እንዲመለሱለት የሚፈልገው? አጀንዳዎቹንስ በምን መንገድ ነው ተፈጻሚ እንዲሆኑለት የሚፈልገው? የሚለውን እያጣራን እንገኛለን። ያን እንደተገነዘብን በአወራርም፤ በጥያቄም፤ እንዴት መፈጸም እንዳለበትም እቅዶችን እና መፍትሄዎችን ካዘጋጀን በኋላ እነሱን መስሎ በመገለጥ ተአማኒነት አትርፎ እንዲከተሉት እያደረገ ወደ እኛ ይዞአቸው መምጣት እንዲች እስክናደርግ ድረስ ነው። መልካም ታዲያ ይህን ስታደርጉ ጥንቃቄ እንዳይለያቹ! ይህ ከባድ ጊዜ ነው። በማለት ሰነዶቹን እንዲያቀብለው ቀኝ እጁን ዘረጋ። ሰነዶቹን ሲመለከት ቆይቶ የተረሱ ክፍለ ከተማዎች እና ትኩረት የተነፈጋቸው ከተማዎች አሉ በማለት ብዕር ከደረት ኪሱ አውጥቶ ትኩረት የሚፈልጉ ያላቸውን ተጨማሪ ከተማዎች የፊተኛው ገጽ ላይ በመጻፍ የከተማው ነዋሪዎች የትውልድ ሰፈራቸውን በመልቀቅ በተለይ ወጣቱ ቅናሽ ቤት በመፈለግ እየተበተነ መሆኑን ከግምት አስገቡ እንዲሁም ከክፍለ ሀገር የሚመጣውም ሰው በዚያኑ ልክ እንደጨመረ፤ ስለዚህ በድሮው በምናውቃቸው ሰፈሮች ከተወሰንን ውጤታማ አንሆንም። ጅማሮው መልካም ነው። ግን ፍጥነት ይጎለዋል፤ ደህና ሰንብቱ ብሎ አዳራሹን ለቆ ወጣ።

ሁሉም ተከትለውት ወጡ ቴራስ ግን እዚያው እንደተቀመጠ ነበር፤ ያባል እና ጋይዳድም አብረውት ነበሩ። ያባልም፤ ሰሞኑን ልክ አይደለህም የተከሰተ ነገር አለ? በማለት ጠየቀው፤ ከአባቴ ጋር በአኪያ ምክንያት ተጋጭተን ነው ለክፉ የሚሰጥ አይደለም ብሎ

መለሰለት። ያባልም ቀጠል አድርጎ፤ ቴራስ ለዚህ ሰውዬ የምታሳየውን ፊት አልወድልህም፤ ጥላቻህን በውስጥህ ያዘው፤ ጥርሱ ውስጥ እንዳትገባ። እኛ ወደነው ነው? ግን እንድትታዘዝለት ሥልጣኑም ዲሲፒሊንም ያስገድድሀላ። ሲለው ቴራስ ምን መሰለህ ያባል ባህሪውን አልወድለትም። እሱ ዱካ ያጠፋ እየመሰለው ብዙ ታላላቅ ወንጀሎችን በሥልጣኑ ጥላ ስር የሠራ ሰው እንደሆነ ታውቃላችሁ። ያንጊዜ እንኳ በእጁ በገደለው ጉምቱ ምክንያት እና በአስገደሉት በዚያ ደመከልብ አርቲስት ምክንያት ምን ያህል ውድመት እንደደረሰ ታውቃላችሁ። እሱን እና ናቡከደነጾርን ሳያቸው ፊታቸው እና እጃቸው ላይ የሚታየኝ የብዙ ወገኖቼ ደም ነው። ታዲያ ለነዚህ እንዴት ብዬ ጥርሴን ላሳያቸው? ቢሆንም አለ ጋይዳድ፤ ቢሆንም ስሜትህን መቆጣጠር ይኖርብሀል። አንተን እንዲህ ብሎ መምከር በራሱ ከጎሮሮ አይወርድም። አስተዋይ እና ቁጥብ ከስሜት የራቅህ ብልህ እንደሆንክ ነው ሁሉም የሚያውቀው። እዚህ ላይ ግን ስተሃል። አውቃለሁ እዚያው ድፋቸውና ሀገሪቱን ገላግላት! የሚሉ ስሜቶች አያሌ ጊዜ ወደ እኔ መጥተዋል፤ በቅርበት አብሮአቸው እንደሚሠራ ሰውም ከዚህም በኋላ በአገኘኋቸው ቁጥር እንደሚመጣ አውቃለሁ ግን ለሁሉም ጊዜ አለው፤ ሁሉም በእጃችን ይወድቃሉ፤ እስከዚያው ግን አንገት ደፍቶ ሥራን በልብ መሥራት አዋጭ ነው አለ። እሺ ይሄን ያህል የሚታይ ከሆነ አስተካከላለሁ፤ ለምክራችሁም አመሠግናለሁ። ምን ያህል ነገሮች እየከፉ እንደመጡ እያያቹ ነው። አሁን በቶሎ ወጣቶቹን ካላነቃናቸው እመኑኝ ከባድ ይሆናል፤ ስለዚህ ይህን መሪ የተባለውን ወደ ሥራ ከማስገባታችን በፊት የማንቃቱ ሥራ በደንብ መሰራት አለበት! ሶስታችንም ከተገናኘን አይቀር ነገ ማለዳ እንድናደርገው የቀጠርነውን ስብሰባ ለምን አሁን አንጀምረውም? እና ያባል ሰዓር እንዴት እየሆነች ነው? በብዙ ነገሮች እየተወጠርኩ…

ኤርፖርት ከአገኘኋት ቀን አንስቶ
እንዳስገረመችኝ ነው፤ ይገርማቹህል ካልተጠየቀች
አታወራም እንጂ በሚነሱ ርዕሶች ላይ የምትሰነዝራቸው
አስተያየቶች ምን ያህል አስተዋይ እና አንባቢ እንደሆነች
ይመሰክራሉ። መልክ ብቻ አይደለችም። የቴክኖሎጂና
የስለላ እውቀቷ የሚያስደምም ነው። በዚህች አጭር ጊዜ
የማይታመኑ ሥራዎችን እየሰራች ትገኛለች። የብዙ
ባለሥልጣናትን ሰነዶች እጃችን ላይ እንዲገቡ
አድርጋለች። ይገርማቹህል የአብዛኛዎቹን የብሮውሰር
ሂስትሪያቸውን ስትመለከቱና የሚላላኳቸውን የጽሁፍ
መልዕክቶች ስታነቡ ምን ያህል የዘቀጠ ማንነት
እንዳላቸውና ሀገሪቷን በማን እጅ እንደጣልናት ግልጽ
ይሆንላቹህላ። አሁን የምንፈልጋቸው ሰነዶች ሁሉ
በእጃችን ይገኛሉ፤ አንድም የምስራች ልንገራችሁ ሰዓር
የመንግሥት ባለሥልጣናት ብላክ ሜይል የሚደረጉበትን
ፍይሎች መገኛ ሰርቨር ደርሳበታለች። እጅግ ጥብቅ ነው
ብለው ስለሚያስቡ እንደዛም ስለሆነና በሰው እጅም
እንዳይገባ ስለሚፈልጉ ኮፒ እንኳ የላቸውም። ማን ከማን
ጎን እንደሆነና ምን እንደሚሠራ አሁን መረጃ በእጃችን
አለ ከነሚሰሩት ወንጀል ጭምር ግን በቂ ስላልሆነ
እየተሄደበት ነው። መረጃዎቻቸው እንዳይወጡባቸው
ብለው ከፍላጎታቸው ውጭ እንደገረድ የሚታዘዙ
ባለሥልጣናት አሉ። በፍላጎታቸው የሚታዘዙ እንዳሉት
ሁሉ። የሳይበር ቲሙን እየመራቸው ስለሆነ ሙሉ ቡድኑ
አመርቂ የሆነ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። የኛም ህቡህ
ድርጅታችን፤ የዞሳር ሰነዶችም ይሁኑ የምንለዋወጣቸው
መልዕክቶች በሙሉ ከምን ጊዜውም በበለጠ ስውር እና
ኢንክሪፕትድ ሆነዋል አለ ያባል።

በጣም ጥሩ አለና ቴራስ፤ ዲጅታል ዓለሙን በተመለከተ እንከን አልባዎች መሆን ይኖርብና። ትልቁን ሥራ እዚያ ስለሆነ መሥራት የሚኖርብን፤ ከላይ ስጡ የምንባለውን አጀንዳ ለሕዝቡ ስንሰጥ የኛ ልጆች ወዲያው ያን አጀንዳ ከመራገብ የሚገቱና ለኛው የመንግሥት አባላት ሌላ እራስ ምታት የሚሆን አጀንዳ የሚወረውሩ መሆን ይኖርባቸዋል! አንተ ጋርስ ምን አለ ጋይዳድ?

ያው ከኤርፖርት ጀምሬ ክትትል የጀመርኩባት የኤም.አይ.6 ኤጀንት ስሟ ጃስሚን እንደሚባል ማወቅ ተችሎአል፤ ከብዙ የሀገሪቷ ባለሥልጣናት ጋር ግንኙነት አላት፤ በአስተዳደር እና በአመራር ዘርፍ ለከፍተኛ ባለሥልጣናት ሥልጠና ለመስጠት ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ እንደመጣች ነው የተነገራቸው የሚታወቀውም። ይህንም አስመልክቶ በሚኒስተር ደረጃ ያሉ ሁሉም እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የሀገሪቷ ባለሥልጣናት በሙሉ የሥልጠናው አካል እንዲሆኑ በመደረጉ አሁን ሁሉም በእጇ ውስጥ እንዲገቡ ሆነዋል። የእኛ ከሆኑትም መረዳት እንደተቻለው፤ በሥልጠናው ሽፋንነት የምትፈልገውን መረጃ ሁሉ እየሰበሰበች ትገኛለች፤ ማኒፑሌሽን ቴክኒክ በመጠቀም ባለሥልጣናቱንም እነሱ ወደቪሚፈልጉት መስመር እየመሯቸው እንደሆነም ተረድተናል።

በአደረግነውም የቡድን ግምገማ ይህቺን የኤም.አይ.6 አባል ወደ ህቡህ ድርጅታችን ዘዓር ማምጣጥ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ወስነናል። ይህንም ለማድረግ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚመራ ተልዕኮ ጀምረናል። እዛው ባሉ የዘዓር አባላት በሆኑ ሚኒስተሮች በብልሀት ወደእኛ እንድትመጣ የሚያደርግ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፤ ብዙ እርቀትም ተጉዘንበታል አላቸው።

መልካም ጥሩ እየተጓዝን ነው ያለነው። እንደዚህ ከሆነና ሁሉም የዞሳር አባል ትዕዛዝ ሳይጠብቅ እየተናበበ መጓዝና፣ ጊዜው በሚፈልገው ፍጥነት እዲህም ቀደም እያለ መራመድ ከጀመረ ፍጻሜው እየቀረበ ይመጣል። እግዚአብሔር ይርዳን! የጋይዳድን ፊት አይቶ፤ ወዳጅህ ሊረዳህ የሚችለውን ችግር፤ እራስህ ለመወጣት እየሞከርክ ስትንገጋገድ ከርመህ፤ ያ ወዳጅህ ቢሰማ እንዴት አልጠየከኝም? ብሎ ይከፋብሃል። በእግዚአብሔር ደግሞ አይብስም ብለህ ታስባለህ? ከእሱ በላይ ወዳጅ የለንም። የሚሳነውም አንዳች የለምና። በእኔ በኩል ጨርሻለሁ እናንተ ጋር የቀረ ካለ መቀጠል ትችላላችሁ፤ እኛም ጋር ያለው ይሄው ነው! መልካም እንውጣ።

ቴራስ መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ ለአኪያ ደወለላት ሰዓቱ መሄዱን ልብ አላለም ነበር፤ ከረጅም ጥሪ በኋላ አነሳችው። ድምጿ ተኝታ እንደነበር ያስታውቅ ነበር፤ እሷም ያንኑ አረጋገጠችለት። ድምጿ አንዳች ንዝረት ፈጠረበት። ማውራት ቀጠሉ፤ ሰውነቱ እየሞቀ ሲመጣ ይታወቀው ጀመር። ያለማቋረጥም ዘለግ ላለ ጊዜ አወሩ፤ የሚሰማውን ስሜት አውጥቶ ሊነግራት ድፍረት አጣ። ለምን ነገ ከከተማ አንወጣም? የሚቀጥለውም ቀን ሰንበት ስለሆነ ብዙ እረፍት ይኖረናል በማለት ጥያቄ አቀረበላት ቢሮስ አይፈልጉህም? ችግር የለውም i'll take the risk አላት። ደግመውም ብዙ አወሩ በመሀል ረጅም ወሬ አውርቶ ጥያቄ ሲጠይቃት ዝም አለችው፤ ደጋግሞ ስሟን ጠራ መልስ አልነበረም። እንደተኛች አውቆዋልና በሷው ቋንቋ ''bonne nuit fais de beaux rêves'' በማለት መልካም እንቅልፍ ተመኝቶላት ስልኩን ዘጋው።

በማግስቱ ቴራስ አረፋፍዶ ተነሣ። ለጉዞ አስፈላጊ ያላቸውን እቃዎች ለማሰናዳት ጀመረ ነገር ግን እነዛ እቃዎች ምን እንደሆኑ አላወቀም ነበር እንዲሁ ሲንጎራደድ ስልኩ ጠራ አኪያ ነበረች፤

፡፡ ማታ እንቅልፍ ጠለፈኝ እንዳልተቀየምከኝ ተስፋ አደርጋለሁ?

፡፡ ምንም አይደል ሰዓቱም ያስገድድ ነበር!

፡፡ እኔ ጨርሻለሁ በጨረስክ ሰዓት መምጣት ትችላለህ።

፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ እመጣለሁ ቁርስ እያደረግን መኪናዋን እናስፈትሻትና እንወጣለን።

፡፡ je vais vous attendre.

፡፡ je viendrai bientôt ብሎ ስልኩን ዘጋው።

ቴራስ አኪያ ጋር ሲደርስ ታች ከእንግዳ መቀበያው ሆኖ መደወል ከተወ ሰንብቷል። አንኳኳ፣ qui est-ce? አለች እኔ ነኝ ለማለት ፈለገና ወዲያው c'est moi በማለት ምላሽ ሰጣት፤ በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ እንዲገባ እየጋበዘችው፤ ከየት ነው ፍሬንች የለመድከው? ሌላ ቀን እነግርሻለሁ እንውጣ? ይቻላል ሻንጣዬን ታች ልኬዋለሁ ብላ ወደበሩ አመሩ። ከመኪና ማቆሚያው ሲደርሱ፤ የላከችው ልጅ ሻንጣውን ይዞ የቴራስ መኪና ጋር ቆሞ ነበር፤ የኋላውን በር ከፈተለት፣ አስገባውና መች ትመለሻለሽ? ሲል ጠየቃት አልቆይም እስከዚያው ፑፒን ተንከባከባት በማለት ለአገልግሎትህ ብላ ገንዘብ ሰጠችው። ጊቢውን ለቀው በመሿለኪያ ወደ ጎተራ

አቀኑ። ቢረፋፍድም የሆነ ነገር እንቅመስ ብሎ መኪናውን እንዲፈትሹለት እዛው አከባቢ ላሉ ለጋራዥ ሰራተኞች ነዳጅም እንዲሞሉለት ቁልፍ እና ገንዘብ ሰጥቶ ወጣ ። የት ነው ግን የምንሄደው? ናዝሬት እናሳልፋለን ብዬ ነበር ግን ለእኔም ለአንቺም አዲስ የሆነ ቦታ ቢሆን ስለሚሻል ወደ ደብረ ዘይት እንዲሆን አሪፍ ቦታ ቡክ አድርጊያለሁ...።

መንገዳቸውን ጀመሩ የአየር ሁኔታው ነፋሻማ ስለሆነ መስታወቱን ዝቅ እያደረገች እግሮቿን ወንበሩ ላይ በማድረግ የመኪናው በር ላይ በመቀመጥ ጥቂት ትጓዝና ንፋሱ ሲያፍናት በድጋሚ ወደ ውስጥ ትገባለች። አመቺ ቦታ በአገኘች ቁጥር ይህን ተግባር እየደጋገመች ደብረ ዘይት ደረሱ።

አስቀድሞ በተያዘላቸው ሪዞርት ክፍል ገብተዋል ነገር ግን አኪያ በምታየው ሁሉ እየተደነቀች ስለሆነ እዚህ መሆንን አልመረጠችም፤ ቴራስም እንደዚያው። እየተዘዋወሩ ስፍራውን መጎብኘት ጀመሩ፤ በዚሁ መልኩ ምሽት ሆነ።

ቴራስ እንደተለመደው ሸሚዝ በካኪ ለብሶ ጃኬት ደርቦበታል። ወደ አኪያ ክፍል በማምራት በሩን አንኳኳ ጊዜ ሳትወስድ ከፈተችለት፤ ሊወስዳት በር ላይ ሲቆም ሁል ጊዜ የመፈለግ፣ የመወደድ ከሁለቱም በላይ የመከበር ስሜት ስለሚሰማት ይህን ትወደዋለች። ቴራስንም እንድታከብረውና ለሱ ያላት ፍቅር እንዲቀጣጠል በማድረግ ልቧን ያሞቀዋል። ቴራስም በበኩሉ በሩን ከፍታ የወጣችው ልዕልት እንጂ የሚያውቃት አኪያ አልመሰል አለችው። የለበሰችው ቀሚስ ከተጫማችው ሂል ተዳምሮ ቁመት ጨምሮላታል፤ በፊትም ምን ረጅም ብትሆን። የቆዳዋ ቅላት፤ የፊቷ ጥራት ከአፍንጫዋ ሰልካካነት ተጨምሮ አይቶአት አልጠግብ አለ። የግራ እጁን ከንድ ሰጣት በቀኝ እጇ ያዘችው፤ አኪያ እየሆነ

ያለው ማመን እየተሳናት መምጣት ጀምሯል። እየተራመዱበት ያለው በመብራት እና በአበቦች ያሸበረቀው ቀጭን መንገድ፤ ከቴራስ ጋር እዚህ መገኘቷ፤ ሀሳቧ ወደኋላ እና ወደፊት እየመላለሰ ልዩ በሆነ ስሜት ልቧን ይሰቅልባት ይዟል።

አሁን አኪያ ከዚህ ቀደም የማታውቀው ሰላም እየተሰማት ነው። ከንዱን በይበልጥ አቀፈችው ውስጧ የነበረ ጥርጣሬ እንዲሁም ፍርሀት ሲተን ይታወቃታል። የጨበጠችው ከንድ ለእድሜ ልክ ምርኩዟ እንዲሆን ተመኘች። ምንም ምድራዊ ኃይል አያስለቅቀኝም፤ ይህ ለእኔ ብቻ የተገባ የተፈቀደም ነው። ላልለቅህ ቃል እገባለሁ አለች ለእራሷ። በአፍንጫዋ እየገባ ያለው ንጹህና ቀዝቃዛ አየር እና ትንፋሽ የሚሰልብ የመልክአ ምድሩ አቀማመጥ ከስሜቷ ጋር ሆኖ ህልም ውስጥ እንጂ በእውን አልመስልሽ አላት። ቴራስም በበኩሉ ውስጡን እያደመጠ ሰገነት ላይ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ከመቀመጫቸው ደረሱ። ወንበር ስቦ አስቀመጣት፤ ጃኬቱንም አውልቆ ደረበላት እሱም ተቀመጠ። ከዝርዝሩ የየፍላጎታቸውን በመምረጥ አዘዙ፤ ከመጠጥ Sauvignon Blanc ወይን ስላየች የሀገሬ ምርት ነው ትወደዋለህ ብላው እንዲያመጣላቸው ነገረችው።

ከተቀመጡበት ሰገነት ግርጌ ወደ ሀይቁ የሚገባ አነስ ያለ ፈሳሽ ከድንጋይ ሲላተም የሚያወጣው ድምጽ ለጫወታቸው እንደማጀቢያ ሙዚቃ ሆነላቸው፤ ከተመገቡ በኋላ የመጣውን ወይን እየጠጡ ማለቂያ የሌለው በሚመስል ጨዋታ ተጠመዱ።

፧፧ እንከን የለሽ የምትለውን ሕይወት፤ በህልምህ ውስጥ እንድትኖር ቢሰጥህ እና ለዘለዓለም መንቃት ብትነፈግ፤ ዘለዓለም መተኛትን ትመርጣለህ?

፧፧ ለኢይምሮአችን በህልም እና በገሀዱ ዓለም መሀል ያለው ልዩነት መንቃት ነው፤ ህልም የሰብኮንሺየስ ኢይምሮአችን ነጸብራቅ ነው። ህልሙ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር፤ ልብሽ በፍቅር እና በይቅርታ ከተሞላ ህልምሽ ለመንቃት የሚያሳሳ ይሆናል። በክፋት እና ቂም ከሞላሺው እንደዚያው ጽልመት የወረሳቸው ለሊቶች ይኖሩሻል። በዚህም አለ በዚያ አሁን ለእኔ መንቃቱ ይሻለኛል አሁን ከዘመናት ህልሞቼ፤ በአንቺ መኖሬ እንዲያጓጓኝ ሆኖአልና።

፧፧ አንተ የሌለህበት ዓለም ምን ቢንቆጠቆጥ፤ ዐይን የማይገባ ጎዶሎ ነው።

፧፧ አንቺን መጠበቅ እራሱን የቻለ የማይድን ቁስል፤ የማይሽሩት ህመም ነበር። አንዳችን ለሌላችን ስለተሰራን፤ ስንጎድል ሙሉ መሆን ምኞት ብቻ ይሆናል። ፍቅር ምንድነው ብትለኝ ህመም ነው እልሀለሁ፤ ያውም ረፍት አልባ! ህመምና ስቃይ ከሌለው ፍቅር ፍቅር አይደለም። ምን አዋቂ ብትሆን፤ የቱንም ያህል ጥበብ ብትሸከም፤ ፍቅር ሞኝ ያደርግሃል። ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል። ግን ቀናተኛ ነው። ያን ሰው ለእኔ ብቻ ያስብላል። ሁሉን ርግፍ አድርጎ ትቶ አንተን ብቻ እንዲል ትፈልጋለህ። ዓለሙ በአንተ ዙሪያ ብቻ እንዲሽከረከር። ጽኑ ፍቅር እንዲህ ነው። ጊዜን፣ ሀሳብን፣ ሁሉ ነገርን ጥሎ መሰጠትን ይመኛል። መጋራትን አጥብቆ ይጸየፋል። ለዚህም ይመስለኛል እግዚአብሔር እኛን ከወደደበት ጽኑ ፍቅሩ የተነሣ፤ ሁሉን ጥለው በበረሃ እሱን ለተከተሉ፤ በነብዩ እንደተናገረው፤ ''በቤቱ ለዘለዓለም የማይጠፋ ሥምን'' የሚተክልላቸው። እንዲህ አስበው አብዝታ

ለምታፈቅርህ ሴት፤ ስጦታዎችንና አበባ እየገዛህ ባትሰጣት፤ በየጊዜው እየደወልክ ድህንነቷን ባትጠይቃት፤ ጊዜን ብትነፍጋት ምን ሊሰማት ይችላል? ይሄን እኛ እናውቀዋለን። በአንተ ገልብጠህ አስበው፤ አንተ በምትሆንላት መጠን ባትሆንልህ ምን ይሰማሃል? አየህ እግዚአብሔር ያን ሁሉ ፍቅር ሰጥቶን እኛ ለእሱ ምን መለስንለት? ጥቂት ጊዜ አብሮን ሊያሳልፍ ቢወድ እኛ ጊዜአችንን ለሌላ እንሰጣለን። ምን ያህል አሳዘንነው?

ተነስቶ እጁን ዘረጋላት፤ እጁን ያዘችው፤ ቅኝ መዳፏን በግራ መዳፉ ውስጥ አድርጎ ቀኝ እጁን ወገቧ ላይ አደረገው፤ እሷም ግራ እጇን ቀኝ ደረቱ ላይ አስደግፋ፣ በቆሙበት መወዛወዝ ጀመሩ። ለዘለዓለም ላልተውሽ ቃል እገባለሁ። ዐይኗ እንባ አቀረረ፤ በግንባሯ ደረቱን ተደገፈችው። ወደእሱ አጥብቆ አቀረባት፤ ቀና ብላ ዐይኑን ተመለከተችው ጉንጯን ሳማት። እጇን ዘርግታል በብርጭቆው የቀረውን ወይን ቀድታ ጨለጠችው፤ ወደ መጡበት ተመለሱ። ከክፍሏ ደጃፍ እንደ ደረሱ በሩን ከፍታ ሳትሰናበተው ገባች።

ስልኩ በተደጋጋሚ ይጠራል፤ ቴራስ ለብዙ ቀናት የተደራረበ እንቅልፍ ተጭኖት ተኝቷል በሩም በተደጋጋሚ ይንኳኳል፤ አኪያም በኃይል በሩን መደብደብ በመጀመሯ ከእንቅልፉ ነቃ፤ ብሩን ከፈተው። በሰላም ነው? የሌለህ መስሎኝ ነበር ሰዓቱን አይተኸዋል? በግማሽ የነቃው ቴራስ መልስ አልመለሰላትም፤ እንድትገባ ጋብዞአት ወደ ጃር በመሄድ ውሃ ቀድቶ ጠጣ። የእጅ ስልኩ አሁንም መጥራት ጀመረ፤ ያባል ነበር አነሳው። ቴራስ፤ ናቡከደነጾር አሁኑኑ ቢሮዬ እፈልገዋለሁ እያለ ነው፤ በአስቸኳይ እንድትደርስ! አሁን ያለሁት ደብረ ዘይት ነው በአስኳይ ልደርስ አልችልም አለ ቴራስ። እባክህ ይሄን ንቀትህን አቁም! በምትችለው ፍጥነት ለመድረስ ሞክር! ስልኩ ተዘጋ። መመለስ

ይኖርብናል! አስፈላጊ ነው? አለች፤ ግዴታ ነው በማለት መለሰ፤ ወጣች።

አዲስ አበባ እንደገቡ ቀጥታ ወደቤቱ ይዞዋት በመሄድ እንደሚመለስ አሳውቆአት ሲመጣም ቀሪ ንብረቶቿን አብረው ሄደው ወደዚህ ሊያመጡ እንደሚገባ ነግሮአት ወጣ። ቢሮ ገብቶ ያባልን ፈለገው ሊያገኘው አልቻለም። ስልኩ መልሶ ጠራ የናቡከደነጾር ቢሮ ስልክ ቁጥር እንደሆነ ያውቃል።

፡፡ አቤት?

፡፡ ቴራስ አልደረስክም?

፡፡ ደርሻለሁ ቢሮ ነኝ።

፡፡ ምን የሚሉት ቅብጠት ነው በዚህ አጣብቂኝ ሰዓት መንዘላዘል አሁን በአስቸኳይ ወደ እኔ ና!

ስልኩ ተዘጋ ወደ ቤተ መንግሥት አመራ። ሰላምታ አቅርቦ ቢሮ ሲገባ ሰባት ተጨማሪ ሰዎችን ተመለከተ አምስቱን ያውቃቸዋል ሁለቱን ነጮች ሊያውቃቸው አልቻለም። አንደኛው ነጭ በቁጣ ያወራል፤ ...እንዲህ አይነቱ ተግባራችሁ ብዙ ዋጋ ያስከፍላቹሀል ለዲፕሎማሲም ጥሩ አይደለም። ጭራሽ ይባስ ብላቹ በፓርላማ ሹመት ሰጣችኋቸው። ምን እንድንል ነበር የጠበቃችሁት? እናንተ እንደምትሉት ሹመት ያዳብር? የወሰዳችኋቸው ዜጎች ተራ ዜጎች አይደሉም፤ ከፍተኛ የሀገር ሚስጥር አዋቂዎች እንጂ እንዴት እንዲ አይነት ስህተት ትሰራላችሁ? በዚያ ላይ ከአንድ ሀገር ጋር

አይደለም የምትጋጩት፤ ይህ ሁለት ሦስት ጊዜ የሚታሰብበት ጉዳይ አይደለም በአስቸኳይ ውሳኔ ይፈልጋል! ብሎ ቢሮውን ጥሎ ወጣ። ቴራስ እንዲህ አይነት ጉዳይ ሲያጋጥመው የመጀመሪያው አይደለም። እንዴት የአንድ ሀገር መሪ በዚህ መልኩ እንዲያናግሩት ይፈቅዳል? ብሎ ትኩር ብሎ ሲመለከተው ቆየ።

አማካሪውም ከቡራን ወደ ተሰበሰብንበት ጉዳይ እንግባ በማለት ዝምታውን ሰበረው። ያው አሁን ያለንበት ወቅታዊ ሁኔታ ይታወቃል፤ በማያዳግም መልኩ ካልቀለበስነው አደጋው የከፋ ነው፤ አንድ አንዶቻችሁ የነገሩ ክብደት የገባችሁ አልመሰለንም። ከዚህ ጉዳይ በላይ ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር የለም፣ መኖርም አይኖርበትም። ስለዚህ የሁላችሁንም አስተያየት እንዲሁም ምን እየሰራችሁ እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል አስፈላጊም ነው። በመሆኑም ጉዳዩ መነሻው ምንድነው? እና ጠንሳሾቹስ እነማን ናቸው? አሁን ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? እንዴትስ ማስቆም እንችላለን? የሚለው ላይ እንወያያለን፤ መጀምሪያ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት እንጀምራለን።

ናቡከደነጾር መህል በመግባት ማውራት ጀመሩ፤ አሁን የተነሡት ጥያቄዎች በሙሉ ተገቢ ናቸው ግን የዚህ ሁሉ ነገር ጀማሪም ጠንሳሽም ማን እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ለማሳመር ካልሆነ ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ቤተ ክርስቲያን ናት! የሚጀምረውም የሚያበቃውም በቤተ ክህነት ነው። እሷ ናት ያመጸችው። እሷን ልክ በማስገባት ነገሩን መቋጨት ይቻላል። በተከበርኩበት ያስናቀችኝ እሷ ናት። ከአሁን በኋላ እሹሩሩ የለም እሱ ካሜራ ፊት ብቻ ይሆናል። ቤተ ክህነትንም ሆነ ምእመናኑን እንደ ብረት ቀጥቅጩ እንደ ሰም አቅልጩ እገዛቸዋለሁ! በፊቴ አንበርክኬ አሰግዳቸዋለሁ። አሁን ቁም ነገሩ በመላው ሀገሪቷ የተስፋፋውን አመጸኝነት እንዴት እንግታው?

የሚል ነው። የእኛን ድምዳሜ አሳውቀናቹሀል ምን ያህል እየተፈጸመ ነው? እና ምን አይነት ተጨማሪ መንገዶችን እንከተል? የሚለውን ነው ከእናንተ የምንፈልገው፤ አሁን መጀመር ትችላላችሁ።

የደህንነት እና መረጃ ሚኒስተሩ አቶ ፊንሐስ ረዘም ያለ ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ ለቴራስ እድሉን ሰጡት። ቴራስም ከዚህ ቀደም ለአቶ ፊንሐስ ያቀረበለትን ዶክመንት ለተሰብሳቢዎቹ አቀረበ። ምንጩን እናውቀዋለን ተብሎአል እርግጥ ነው ዋነኛ ምክንያት እሱ ቢሆንም፤ እውነቱና እጃችን ላይ ያለው መረጃ ይሄ ብቻ እንዳልሆነ ያሳየናል። ማረጋገጫውም አብዮቱ ውስጥ እየተሳተፉ የሚገኙት አማጽያን የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ አለመሆናቸው ነው። ትልቁ ምክንያት አብዛኛዎቻችን የተቃወምነውን የትጥቅ ማስፈታት ሂደት ያለበቂ ዝግጅት እና ምክንያት በግልፍተኝነት መተግበሩ ነው። በማለት ዶክመንቶቹን እንዲመለከቷቸው ጊዜ ሰጣቸው።

ሁሉም በየተራ ተገቢ ያለውን አስተያየት ሰነዘሩ። ሁሉንም ያስደነገጠው ግን የሪፐብሊካን ጋርድ መሪ ጀነራል መርዕድ ባቀረቡት መፍትሄ ናቡከደነጾር በመስማማቱ ነበር። እንዲህ ነበር ያሉት ጄነራል መርዕድ፤ አሁን የተነሡት አማራጮች በአስቸኳይ ተግባራዊ መሆን አለባቸው! በጥቂት ቀናቶች ለውጥ ካላስገኙ ወደ ሌላኛው አማራጭ እንሄዳለን እሱም ኃይል ተጠቅሞ ጸጭ ረጭ ማድረግ ነው። ታዲያ የምንጠቀመው ኃይል ዱላ እና እስር አይደለም ጥይት እንጂ። አንድ እየሆኑ ያሉትን ወጣቶች በተለያየ ሁኔታ መከፋፈል። ዋናው ሃይማኖትን በመጠቀም ይሁን። ሙስሊሞቹንና አርቶዶክሶቹን ለሁለት ከከፈልናቸው በኋላ፤ እነሱንም ደግሞ በብዙ አጀንዳዎች መከፋፈል። በዚህ ሁኔታ ኃይል ማሳጣት፤ ከተቻለም የሃይማኖት ግጭት በመፍጠር ማጫረስ። በዚህ ሁኔታ ቴራስ አንድ መፍትሄ ማምጣ እንዳለበት ለራሱ ቃል ገባ ካልሆነ እንደተናገረው ወጣቱ ማለቁ

ነው። እሱ ይህን ሲያስብ ያላወቀው ነገር ከተሰብሳቢዎቹ ሰባት ሰዎች አራቱ እንደዚያው እሱ እንደሚያስበው እያሰቡ መሆኑን ነበር። ስብሰባው ተቋጨ።

አዮ ፊንሐስ እና ጀኔራል ሠሀረ ተያይዘው ወጡ። ቴራስ ይሄ መሰሪ ጀኔራሉንም ሊበክላቸው ነው ብሎ ግን ምንም ማድረግ እንደማይችል ሲረዳ ወደ መኪናው አመራ። ከቤተ መንግስቱ ጊቢ እንደወጣ ለያባል ደወለ፤ ያባል በአስቸኳይ የማህበራዊ ሚዲያው ተልዕኮ የተሰጣቸውን ቡድኖች ሰብስበህ ዛሬውኑ ሥራቸውን እንዲጀምሩ አድርግ፤ we are running out of time ፍጥነት ያስፈልጋል።

:::

ጀኔራል ሂሶጵ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ የታሰበው እቅድ እስኪፈጸም ቀጨኔ አከባቢ እራሱን ሸሽጎ ቆየ። ዛሬ ማታ ሁለት ሰዓት ወደ ባህር ዳር እንደሚጓዝና አዲሱን ተልዕኮውን እንደሚጀምር ነገር ግን ጂማ ከተማ ላይ የሰራውን አይነት ስህተት ለመሥራትና በሕይወት ለመኖር ምንም ዋስትና እንደሌለው ከጀኔራል ሠሀረ ቡድን ተነግሮታል። ከአሁን በኋላም መደባበቅ እደማያስፈልገው ጭምር፤ ምክንያቱን ጠየቅ ሂሶጵ እንዲህ የሚል ምላሽ ከስልኩ ባሻገር አገኘ፤ ከጂማ የሚመጣ አንድ ላንድ ክሩዘር አበልቲ የሚባ ስፍራ ተገልብጦ ወደ ገደል በመግባቱ ሾፌሩም ውስጡ የነበሩ ሁለት ተሳፋሪዎችም መሞታቸውንና መኪናው ስለነደደ የሟቾቹን ማንነት መለየት እንዳልተቻለ ስለተደረሰበት፤ የቡድኑ አባላት ስንከታተለው ነበር፤ እኛን ለማምለጥ ሲሞክር ነው የተገለበጠው በውስጡ የነበረው አንደኛው ተሳፋሪ ሂሶጵ ነው ብለው ሪፖርት ስላደረጉ፤ ክትትሉ እንዲቋረጥ ተደርጎአል የሚል ነበር። በተያዘለት ሰዓት ሂሶጵ ወደ ባህር ዳር አቀና።

።።።

ድንገተኛ ክፍል ይዘዋቸው ገቡ፤ ህክምና ሲደረግላቸው ጥቂት ከቆዩ በኋላ፤ ጨረሷቸው።

:::

አሁን ሁሉም ነገር ከቁጥጥራችን ወጥቶአል የልባችን ሥራ በሥጋችን ተሸንፏል። እንዴት ጽድቅ በክፋት ይሸነፋል? ሲል ቴራስ ጠየቀ፤ መልካሙ ሥራችን እንዴት በክፉ ላይ አቅም አጣ? ሁለቱንም የሠራነው እኛው ነን፤ ወጣቱን ለማዳን ከሄድንበት መንገድ ግን ያጠፋንበት በለጠ። እንታገልለታለን ብለን ድርጅት በህቡ ከአቋቋምንለት ወገናችን ይልቅ ከቢሮ ተሰጥቶን የሠራነው ሥራ ፍሬያማ ሆነ። እንዴት መጀመሪያ በየሰፈራችሁ ተደራጁ፤ መሪ ለመምረጥና አጀንዳ ለመቀበል አትቸኩሉ፤ ሁሉን በብልሀት መርምሩ ብለን እዚህም እዚያም ያለመዋቅር የተደራጀውን ወጣት ማንቃት ኢቃተን? አሁን ረፍዶዋል።

ያለፈው ሳምንት የሆነውን አምስታችሁም ታውቁታላችሁ፤ ላንቺ ግልጽ ላድርግልሽ ይኸውልሽ ሰዓር የፖሊስ አመራሮችን ብቻ ሰብስቦ በመላው ከታማዋ የሚገኙ ወጣቶች እንዲታፈሱ ትዕዛዝ ተላልፎ ተፈጻሚ እንዲሆን ለሁሉም ክፍለ ከተማዎች ወረደ። ይህ የሆነው በምሽት ነው። ሁሉም የራሱ ሰፈር ብቻ መስሎት ነበር ግን በዋና ዋና መንገዶች ካልሆነ ኤሌክትሪክ በሁሉም ሰፈር ተቋረጠ። ምን እየሆነ እንደነበር ከስምሪት ሰጪዎቹ በቀር ማንም የሚይውቅ አልነበረም፤ እነሱም ቢሆኑ ስልካቸውን ተቀምተዋል። ስምሪት ተቀባዮችም ትዕዛዙን ከመቀበልና ከመፈጸም ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም። በዚህ ሁኔታ ያገኙትን ወጣት በሙሉ አፍሰው በየጣቢያው አጎሩት። ይህ ሁሉ ሲከናወን ነዋሪው ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም፤ ሁሉም የተገለጠለት ሲነጋ ነው።

አሁን ጣቢያዎች በመሙላታቸው የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ሁለቱ ስታዲየሞች ዋነኛ አማራጭ ሁነዋል። የወጣቶቹ ወላጆች ልጆቻቸውን ፍለጋ ትምህርት ቤት በያለበት እየተንከራተቱ ነው። አፈሳው ግን አልቆመም አሁንም ቀጥሎአል።

ጋይዳድ እየተቻኮለ ሁልጊዜ ስብሰባ ወደሚያደርጉበት መገናኛ አከባቢ ወደሚገኝ G+2 መኖሪያ ቤት የበሩን ቁልፍ ከፍቶ በመግባት ከመሬት ስር ለዚሁ ዓላማ ተብሎ የተሰራ ሰፊ አዳራሽ አመራ። ግርግዳው ላይ የተለጠፈውን ማብሪያና ማጥፊያ ሲያበራው ግርግዳው ወደላይ በመንሸራተት ተከፈት፤ ግርግዳ ይምሰል እንጂ በር ነበር፤ አዳራሹ ባዶ እንደሆነ ተመልከቶ ማብሪያውን ሲያጠፋው ወደታች መውረድ ጀመረ። ወደሌላኛው በር በመሄድ በደረጃው ወደ ላይ ሲወጣ ፈዘዝ ያለ ሙብራት ያለበት ሳሎን ውስጥ ቴራስ ቆሞ ጥያቄ በመጠየቅ ላይ ነበረ። ሰላምታ ሳያቀርብላቸው ገብቶ ሪሞት አንስቶ ቴሌቪዥኑን አበራው። ሁሉም ዜና አቅራቢዋ የምታነበውን ማመን ተሳናቸው። ሰዓር ድምጽ ጨመረች፤ ..."አሁን ደግሞ በደረሰን መረጃ ከ11፤30 የጀመረው የተኩስ ልውውጥ የዶክተርን ጨምሮ የብዙ ባለሥልጣናትን ሕይወት እንደ ቀጠፈ ማወቅ ተችሎዋል" "ተመልካቾቻችን አሁን የደረሰን ሰበር ዜና አለ እንደሚቀጥለው አቀርበዋለሁ፤ ጀነራል ሠሀረ በተከፈተባቸው ተኩስ ሕይወታቸው እንዳለፈ ተገለጸ..." ቴራስ በቃ ብሎ በቁጭት የቴሌቪዥኑን ሶኬት ነቀለው። በሁሉም ፊት ላይ ከባድ ሀዘን አጠላ።

ሰዓር ቀጣይ ላሳያችሁ የነበረው ይሄኛው ፋይል የእሳቸው ነበረ። ብላ በክሊፐር የተያያዘ ፋይል አነሳች፤ ተመልከቷቸው እኚህ በእሳቸው ከሚመሩት የህቡህ ድርጅት አባላት ጋር በስውር ሲለዋወጧቸው የነበሩ መልዕክቶች ናቸው። አሁንም እየተለዋወጡበት ይገኛል። በሌሎች እጅ ከገባ ጉዳቱ የከፋ ነው እና ሳይታሰር ወይም ሳይገደል የሚቀርም አንድስ እንኳን ባለሥልጣን አይኖርምና እነሱ ሳይረዱት ፓዝዌዩን ሎክ አድርጌላቸዋለሁ። በሚያስደንቅ ሁኔታ ሁሉም ባለሥልጣናት የቡድናቸው አባላት ናቸው ማለት ይቻላል። አሁን ገዥ ነኝ የሚለውና እናንተ የምታገለግሉት አካል ቀፎ ነው። ሁሉም በአፉ ነው የፓርቲው አባል ሆኖ የሚሰራው። አንዳች የመጣ ቀን ከስሩ ለመነቀል ሰዓታት አይፈጅም። በመረጃ ነው እያወራኋቹ ያለሁት። የእውነት ከልባቸው አብረውት ያሉት አብረውት ለዓላማ የተሸሙት ብቻ ናቸው። እሱም የሚጠበቅ ነው።

ይሄን ዶክመንት ሁላችሁም ተመልከቱት ጥብቅ መረጃ ነው። ውስጡ የምታዩት ያሁኖቹን ባለሥልጣናት ለመሾም፤ እንዴት ባለ ሁኔታ የቀድሞዎቹን አጣብቂኝ ውስጥ ከተው በውዴታ ግዴታ ሥልጣናቸውን ለነዚህ እንዲያስረክቡ እንዳደረጉና የድርጊቶቹ ፈጻሚዎችም እነማን እንደሆኑ ያስረዳቹሀል። የተሿሚዎቹም የስም ዝርዝር ከነሚሾሙበት ቦታ፤ እንዲያሳኩት የሚፈለገውም ተልዕኮ፤ ከነተሰጣቸው ሥልጠና ጭምር። ተወዳጅ መስሎ መቅረብን፤ መሸቀርቀርን፤ ማተለልና የመሳሰሉትን የማኒፑሌሽን ቴክኒኮችን የስለጠኑበት ሰነድም ሊንክ ተደርጎአል። ይህን የቀድሞዎቹ ደርሰውበታል። ቁማሩን የጠቅላይ እንደተበሉም ከዐወቁ ሰንብተዋል። ስለዚህ አሁን በብልጠት እንደማያገኙት ስለገባቸው በጉልበት ሊያደርጉት ነው። እነዚያ ከእነዚህ በብዙ ይበልጣሉ። እንዳልኳቹ ማስረጃዎች አሉ። እናንተ ደግሞ ሁለቱንም ስለምታውቋቸው መረዳት አያዳግታችሁም። የሆነው

ሆኖ፤ አሁን የማሳያችሁ ሰነዶች መጀመሪያ የገቡት ሚቹ ኢንጂነር እጅ ነበር በምታውቁት መንገድ አስወገዱት። ለተወሰኑ ሰዎች ልኮት ነበር፤ እነማን እንደሆኑ ስላላወቁ እነሱንም ለማስደንገጥ ነበር የገደሉት።

አሁን ደግሞ ይህ መረጃ እነሠሀረ እጅ እንደገባ ደርሰውበታል። ለደህንነት ቢሮ ሠራተኞች ለእናንተ እንኳን አላሳወቋችሁም። የአዛዣችሁም እጅ አለበት። የአቶ ፊንሓስ። አሁን ጂነራሉን ከገደሏቸው እናም ተጨማሪ ሦስት ልጆች በእናንተ ቢሮ አሉ፤ እነማን እንደሆኑ በፎቶ ማወቅ አልቻልኩም ስለሌላቸው፤ በድምጽ ግን አሰማችሁና እነማን እንደሆኑ እራሳችሁ ትለዩአቸዋላችሁ፤ እነሱን ተጠንቀቋቸው። አዛዣችሁን ግን አብዝታችሁ። ሌላው የነሠሀረን ቡድን ከኛ ጋር ማዋሀድ አለብን! ለነገ የምንለው ተግባር መሆን የለበትም። አብረን ብዙ እርቀት መሄድ እንችላለን። ያን እንዴት ማድረግ እንዳለብን ለኔ ተዉት።

የዚህ ሀገር ትላልቅ የተባሉ ባለሥልጣናትም ሆነ ድርጅቶች የሁሉም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እንዲሁም ሰነዶች በእጃችን አሉ። በፈለግን ሰዓት የፈለግነውን መረጃ መሰረዝም መለወጥም እንችላለን። ከነዚህ ባለሥልጣናት እና ድርጅቶች ይልቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ማግኘት የሚከብደው የማኅበረሰቡን መረጃ ነው። ምክኛቱም ከማኅበረሰቡ ስልክም ሆነ ኮምፒውተር ውስጥ መረጃ ለማግኘት መጠቀም የሚኖርብን Phishing attacks አልያም Social engineering ቴክኒኮችን ስለሆነ። ይህ ደግሞ ስለ ግለሰቡ በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል። የባለሥልጣናቱን እና የድርጅቶችን ለማግኘት ግን በSoftware bug በኩል በሚፈጠሩ loopholes በቀላሉ exploit ማድረግ ይቻላል። እንደ ድርጅት የሚጠቀሙባቸው ሶፍትዌሮች ደካማ ስለሆኑ።

አሁን እንዳልኳችሁ ድርጅቶቹን ማዋሀድ ይኖርብናል። የMI6 ኤጀንታችን የጃስሚን ጉዳይ እንዴት እየሄደ ነው ጋይዳድ? በፈገግታ ጠየቀችው ሰዓር፤ ተቻኩሎ የገባበት ትንፋሹ መቀዝቀዙን አይታለችና እንዲሁም ይዞ ከመጣው አስደንጋጭ ዜና መንፈስ እንዲላቀቅ። ችኩል እንደሆነ ሁሉም ያወራሉ እኔም አረጋግጫለሁ ቢሆንም፤ እንደዚያ የሆነው ከየዋህነቱና ከንጹ ልቡ የመነጨ እንደሆነ እረዳለሁ። ልቡ እንደ ቁመቱ ያላጠረ እንደ ቆዳው ያልጠየመ ነው። ይልቁንም እንደ በረዶ የነጻ እንጂ አለች ለራሷ።

ጋይዳድ ሁል ጊዜ ከፊቱ የማይጠፋው ፈገግታው ሰሞኑን ተለይቶታል። በጣም በቅርቡ የምስራች ይኖረናል ጃስሚንን በተመለከተ በማለት ንግግሩን ጀመረ። እንደምታውቁት ዓላማችንን እንድትረዳና የቆመችበት ስፍራ ልክ እንዳልሆነ ለማስረዳት በሥልጠና ሥም ሁልጊዜ አጠገቧ የሚገኙ የዞዓር አባላት ሲጥሩ ከርመዋል። በዲፕሎማሲው አንቱ የተባሉ ስለሆኑም ይህ ይከብዳቸዋል የሚል ጥርጣሬም አልነበረንም። አሁን የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሰዋል በጥቂት ቀናት ውስጥ ዞዓርን ትቀላቀላለች። ማረጋገጥ የምትፈልገው ከትክክለኛው ወገን ጎን መሆኗን ብቻ ነው።

ጋይዳድ ይህን በመናገር ላይ እያለ የእጅ ስልኩ ጠራ፤ ጤና ይስጥልኝ አምባሳደር ፍቅረማርያም አለ። ጋይዳድ ፊቱ እየፈካ ሲመጣ ያስታውቅ ነበር፤ ...ይቻላል አምባሳደር! ...አዎ! ...እጠብቃለሁ! ስልኩን ዘጋው። በዚህ ፍጥነት ይሆናል ብዬ አልጠበኩም እንጂ እንደሚያሳኩት አልተጠራጠርኩም ነበር አለ ጋይዳድ ድምጹን ከፍ አድርጎ። ሁሉም ይመለከቱት ነበር። እንደሰማችሁት አምባሳደር ፍቅረማርያም ነበሩ ደዋዩ፤ ጃስሚን አሁን ልታገኛችሁ ትፈልጋለች ነው ያሉኝ። እዚህ እንደሆንን ጠየቁኝ ሳረጋግጥላቸው አልካታለሁ፤

እንደደረሰች ትደውልልሀለች በሚገባ ተቀብሏት፤ አሁን የእኛ ናት ነበር ያሉኝ። ሰዓር እና ያባል ተቃወሙ። እዚህ መምጣት የለባትም አደጋ ይኖረዋል፤ ከሆነም እኛው ያለችበት ብንሄድ ይሻላል አሉ። ቴራስ አምባሳደር ፍቅረማርያምን በቅርበት አውቃቸዋለሁ፤ እናንተም በሚዲያም ቢሆን ምን አይነት በሳል እንደሆኑ ታውቃላችሁ። ማንነቷን እያወቁ ለስህተት በር የሚከፍቱ ሰው አይደሉም። ያውም መላውን የዞዓር አባል በአንድ ምሽት ስብሰባ ሊያጠፋ እንደሚችል ሳይሰወርባቸው፤ ጃስሚንን ሳይሆን አምባሳደሩን እንመናቸው። ተስማሙ።

ጋይዳድ ጃስሚንን ሞቅ ባለ ፈገግታ ከተቀበላት በኋላ እራሱን በሚገባ አስተዋውቆ፤ የተከተላቸው አለመኖሩን እስኪያረጋግጥ ድረስ በያዘውን ተሽከርካሪ አራት ጊዜ ስፍራውን ታጥፎ ወደ አባላቱ ይዞአት ገባ። እነሱም ከጋይዳድ በተመሳሳይ መንገድ ተቀበሏት። ተራዋ ነውና እራስዋን ወደ ማስተዋወቅ ገባች። ያለችው ግን እነሱ ከሚያውቁት በተቃራኒ ነበር ከጥቂቱ በስተቀር። ሰዓር እንዴት ይህን የሚያህል ከባድ ውሳኔ ልትወስኚ ቻልሽ? የሚል ጥያቄን አቀረበችላት

ጃስሚን መጠየቅ ያለበትን ጥያቄ በተገቢው ሰዓት ነው የጠየቅሺኝ በማለት ጀመረች። መነጽሯን እያወለቀች። ኢትዮጵያ ስመጣ የመጀመሪያዬ አይደለም። በተደጋጋሚ የመምጣት እድሉ ነበረኝ ለዚሁ ዓላማ። ሁሌም በማየው ነገር እቆች ነበር፤ ሁሉን ለማለት በሚቻል መርኩ በግል አውቃቸዋለሁ ባለሥልጣናቱን ማለቴ ነው። አንድ ጊዜ እንደውም ሁለት ሚኒስተሮች ተጣልተውብኛል። ስለእኔ ለማውራት አይደለም እነሱን እንድታውቋቸው እንጂ ሚስቶችም አሏቸው። ለማንኛውም ይህ በጣም ጥቂቱ ነው። ተቃዋሚዎቹን ደግሞ ሳገኛቸው ያላቸው የሀገር ፍቅር ያስቀናኝ ነበር። እንደዛውም ደግሞ የእውነት አምርሮ ሀገሪቷን የሚጠሏትም ብዙ አሉ። ሁለቱ ሥልጣን ይዘው አገኘኋቸው አንደኛው አሁንም ጥላቻው

እንዳለ ነው፤ እንዲያውም በቁጣ ሁሉ መናገር ጀምሮአል። አንደኛው ደግሞ ያ ያስቀና የነበረ ፍቅሩ ተኖ ፍጹሙ ሌላ ሰው ሆኖ አገኘሁት። ብዞዎቹ ለሀገሪቷ እንጂ ለሕዝቡ ፍቅር እንደሌላቸው እየተረዳሁ መጣሁ። ማስረጃዬም የሚጻፈውንም የሚጸድቁትንም ፖሊሲዎች ማየት በቂ ይሆናል።

ሲራብ ሲጠማ ዞር ብሎ የሚያየው የለም፤ እነሱ ጋር አይደርስማ፤ ወጣቱ ትዳርም፤ ቤትም፤ ሥራም የለውም፤ ያላቸውም በሰቀቀን ይኖራሉ። እንዴት አንድ ዜጋ በሀገሩ እየኖረ ቤት እንዲኖረው አይደረግም? እንዴት ሕዝብን ከሀገር ለይተው ማየት እንደቻሉ ግን እስካሁን አልገባኝም። ፍቅራቸው ለሀገራቸው እንጂ ለሕዝባቸው እንዳልሆነ ደግሞ እነሱም አያውቁትም። እኔ ደግሞ በደንብ እያወኩት ስመጣ ሕዝቡ እያሳዘነኝ መጣ። ይህን ስሜት ማስተናገድ ከጀመርኩ ቆየሁ፤ ከማንም ጋር አላወራሁበትም፤ ላወራም አልችልም። የማገኛቸው ባለሥልጣናት ስለ ወንበራቸው እንጂ ስለ ሕዝቡ አይጨነቁም። ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ መፈለግ ጀመርኩ፤ ሥልጠናው ለሽፋን ቢሆንም፤ ዋናው ዓላማ እነሱን መሰለል ቢሆንም፤ እኔ ግን ሥልጠናውን ከልቤ እሰጣቸው ጀመርኩ። ሲለወጡም ዐይ ነበር። እንዳልኳችሁ ግን ከመሀላቸው የእውነት ሀገሪቷንም ሕዝቦቿንም የሚጠሉ ነበሩ። ያለ ሀፍረት ያለዋጋ የሚያውቁትን ሁሉ የሀገሯን ሚስጥር አሳልፈው ይሰጡኛል። አንድ አንዶቹን ሪፖርት ማድረግ እንኳን እስኪከብደኝ ድረስ። ግን እኔ እንኳን ባላደርገው ለሌሎችም ያጋሩታል። እኔ እንኳን ባልችል አጠገቤ የማገኛቸውን ሰዎች የራሳቸው ሀሳብ እንደሆነ እንዲሰማቸው በማድረግ revolution እንዲያስነሱ መገፋፋት ጀመርኩ። ጥንቃቄም አይለየኝም ነበር። በመሀል አምባሳደር ፍቅረማርያምን አገኘኋቸው በመጀመሪያ ሁለታችንም አልተማመንም ነበር። እየቆየ ሲመጣ በደምብ ሀሳብ ለሀሳብ እየተግባባን ጭራሽ እንደ

አባት ይመክሩኝና ስለ ብዙ ነገሮች ያስተምሩኝ ጀመሩ። እኔም ከሌሎቹ ጋር ከሚኖረኝ ጊዜ በይበልጥ ለሳቸው መስጠት ጀመርኩ እሳቸውም ብልህ ስለሆኑ መንግሥትም እንዳይጠረጥራቸው እኔም ሥራዬን እንዳልበድል ሚስጥር የሚመስሉ አለቆቼን የማሳምንበት መረጃ ያቀብሉኝ ጀመር።

በዚህ ሁኔታ ነበር ስለ ዞሳር የነገሩኝ። ሀገሪቷ ውስጥ እንዲህ አይነት ብዙ ድርጅቶች እንዳሉ እናውቃለን። ለኛ ስውርም አይደሉም። እነሱም እኛ እንድናውቃቸው ይፈጋሉ። መጨረሻቸውም ምን እንደሆነ እናውቀዋለን። ስለዚህ ብዙ ትኩረት አንሰጣቸውም። የዞሳር ግን ልቤን ገዝቶታል። ሌላም አንድ እንዳለ አውቃለሁ፤ ጭራውን መያዝ ግን ከብዶኛል። ለማንኛውም እዚህ ልገኝ የቻልኩበት ምክንያት ይህ ነው። አሁን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ዶክመንቶችን ኢጋራችኋለሁ፤ በተለይ ከነማን መጠንቀቅ እንደሚኖርባችሁና እነማንን በምን እንደምትይዙ። እኔ የዞሳር አባል ልሁን እንጂ እንዲህ እኔ በምመርጠው ሰዓት ካልሆነ እናንተ በፈለጋችሁት ሰዓት መገናኘት አንችልም። ስለዚህ መረጃ የምንለዋወጥበት መንገድ እናመቻቻለን። ሰዓር ቀበል አድርጋ እሱ አያሳስብሽ IP address እና Botnets እንዲሁም Encryption ቴክኒክን ከObfuscation እንዲሁም LOL Binaries በመቀላቀል በአይነቱ ለየት ያለ ሲስተም ስለዘረጋን የናንተዎቹም ቢሆኑ ሳይደርሱብን፤ የምንፈልገውን ድርጅትም ሆነ የባለ ሥልጣን አልያም ግለሰብ ዲቫይስ ውስጥ በመግባት የምንፈልገውን መረጃ ማግኘትም እንችላለን suspicious or unknown ሶፍትዌሮችን detect የሚያደርግ security systems ቢኖራቸው እንኳን። እንዲሁም ከምንፈልገው አካል ጋር በነጻነት መረጃ መለዋወጥ እንችላለን። ቢደረስብን እንኳን ትክክለኛውን አድራሻቸንን ማኘት አይችሉም፤ ብዙ የተገናኙ

ኮምፒውተሮችን ከስፍራው ሳንሆን ስለምንቆጣጠራቸው ሲደርሱ ባዶ ቤት እንጂ የሚያገኙት ሰው አይኖርም፤ ዳታውንም ማንበብ አይችሉም ዲከሪፕት ማድረጊያው ቁልፍ ስለማይኖራቸው፤ ለመረዳትም እንዲከብድ አድርገን ስለሆነ ኮድ የምናደርገው አለቻት። ስለዚህ ትክክለኛው ቦታ ነው ማለት ነው ያለሁት አለች ጃስሚንም። ጥሩ በመገናኘታችን ደስታ ተሰምቶኛል የተነገረኝ አይነት ሰዎች ሁናችሁ ተገኝታችኋል ከሞላ ጎደል። ወደ ፊት የሚሆነውን አብረን እናያለን፤ መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ በማለት ተሰናብታ ጋይዳድን አስከትላ ወጣች።

አዲስ አበባ ወረርሺኝ የገባባት ከተማ ከመሰለች ሰንብታለች፤ ወጣት የሚባል በሙሉ በነጻነት መንቀሳቀስ አቁሞአል፤ ዘመድ ያለው እየተደበቀ ሰፈር መቀየር ከጀመረም እንደዚያው። ልጆቻቸው የታሰሩባቸው ወላጆች ሊኖሩ ይችላሉ ብለው የሚያስቡበት ቦታ ሁሉ በመዞር ይፈልጓቸዋል። ጥቂቶቹ እድል ይቀናቸዋል። አብዛኛዎቹ ግን ልጆቻቸው የውሃ ሽታ ሆነውባቸዋል ከከተማ ውጭም ተጭነው የተወሰዱ አያሌ ናቸው። ዋና ዋና አደራጆች ተብለው የታሰቡት ወደ አዋሽ አርባ እንዲሄዱ ተደርገዋ። በዚያ የታጎሩት ወጣቶች በሙቀቱ ሰውነታቸው በላብ እየታጠበ፤ በውሃ ጥም ጎሮሮአቸው እየደረቀ፤ ላንቃቸው እየተሰነጠቀ፤ እየተሰቃዩ ይገኛሉ። በየሰዓቱ ደግሞ በምርመራ ሰበብ በፈላ ዘይት በተቀቀለ ዱላ እርቃን ጀርባቸው ይደበደባል፤ የውስጥ እግሮቻቸው ይገረፋሉ፤ ማታ በጅምላ ከሚተኙበት ክፍል የላሜራው በር ከስር በመዛግ የተፈረፈረ በመሆኑ፤ እባቦች እየገቡ ከፊት የሚያገኙትን ሰው ይነድፉ ነበር። በዚህም ጥቂት የማይባሉ አርፈዋል።

ይህን አለመረጋጋት ማስቆም በፈለጉ ዘመናዊ መሳሪያ በታጠቁ አባላት ዋናው ማዘዣያ ጊቢ ውጥረት ውስጥ ገብቶአል። ለግምገማ በሚል የተሰበሰቡ አንድ ሻለቃ ቀይ ቦኔት ለባሾች በአዛዣቸው ሊውተናንት ኮሎኔል ፊኮል መሪነት ወደ ቤተ መንግሥት ለማምራት ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት አንድ አጭር ማሳሰቢያ ሰጡ። ልጆች ያ የሀያ ስድስት ጄነራሎችን ሕይወት ቀጥፎ፤ ጦሩን ባዶ ያስቀረው የዐሥራ ዘጠኝ ሰማንያ አንድ የግንቦት ስምንቱ መፈንቅለ መንግሥት በምን እንደተጠነሰሰና እንደከሸፈ ታውቃላቅሁ። ጄነራል አበራ፤ ጄነራል ደምሴ ቡልቶ እንዲሁም ጄነራል መርዕድ የሚገኙበት ቡድን በብዙ ቅሬታ እንደነበረበትም፤ ያ መፈንቅለ መንግሥት የከሸፈው ከአስመራው ኃይል ከሜጀር ጄነራል ቁምላቸው ደጀኔ ጋር በተከሰተ ጥቂት መተላለፍ ነው። የተማከርንበት አንድም ሳይሸራረፍ መተግበር ይኖርበታል በማለት ቀጥታ ወደ ቤተ መንግሥት አመሩ።

የአራት ኪሎ ቤተ መንግሥትን በአምስት ሜትር እርቀት በመደርደር ከበቡት። ከካዛንቺስ፣ ከአዋሬ፣ ከእሪ በከንቱ እንዲሁም ከቅድስት ሥላሴ ወደ ቤተ መንግሥት ማንኛውም አካል እንዳይንቀሳቀስ አስፓልቱ ተዘጋ። ቀሪዎቹ ያለምንም ተኩስ ልውውጥ በቁጥር የማይመጣጠኑትን ጠባቂዎችን ጥያቄ ለማቅረብ ነው የመጣነው በማለት ወደ ውስጥ ዘለቁ። ሁሉ ነገር በቁጥጥራቸው ውስጥ እንደሆነ ሲያውቁ ወደ ቀጣይ እቅዳቸው ለማምራታ መንቀሳቀስ ጀመሩ። እንዳሰቡት ግን አልሆነላቸውም። የናቡከደነጾር አማካሪ መጀመሪያ ኔትዎርክ እንዲቋረጥ ነበር ትዕዛዝ ያስጠው። ከጅማሬውም የእቅድ ድክመት የነበረበትና በስሜት ብቻ የተመራው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እዚያው ቤተ መንግሥት ስብሰባ ላይ በነበሩ የሀገሪቷ ዲፕሎማቶች ማግባባት እንዲከሽፍ ሆነ። ከእነዚህም መሀል ዋነኛው አምባሳደር ፍቅረማርያም ነበሩ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለጉዳዩ ገለጻ ተደረገ፤ በመገናኛ ብዙሃንም በብዙ ተተነተነ። እንደዚህ አይነትና የመሳሰሉ በሕዝብ ድምጽ የተመረጠን መንግሥት በኃይል ለመገልበጥ የሚደረጉ ማናቸውም ሙከራዎች በፈጻሚዎቻቸው ላይ የማያዳግም እርምጃ የሚወሰድባቸው እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገለጸ። በሕዝቡ ዘንድ ግን ተቀባይነት አልነበረውም። የሕዝቡም ተቃውሞ የመንግሥትም ሁኔታውን በኃይል እቆጣጠረዋለሁ ማለት ሀገሪቷን ረፍት አሳጣት።

:::

ኤፍሮን የጂነራል ሠሀረን መሰዋት ካረጋገጠች ጀምሮ መስማትም ሆነ ማንኛውንም አይነት ምላሽ መስጠት አቁማለች። ወሳኝ የተባሉ ሁለት የድርጅቱን ስብሰባዎችንም ሳትካፈል ቀርታለች፤ የእጅ ስልኳንም አጥፍታ በሯን ከዘጋች ሰንብታለች። በሯ በተደጋጋሚ ይንኳኳል ምላሽ አትሰጥም። ከምትኖርበት አፓርታማ ኮሪደር ላይ እየተንጎራደደ ያለመሰልቸት ሲያንኳኳ የከረመው ሶዲያር፤ ኤፍሮን እንደምትሰሚኝ አውቃለሁ ካልከፈትሽልኝ ከዚህ አልንቀሳቀስም ብሎ ይህን ተግባሩን ቀጠለ።

ከደቂቃዎች በኋላ ከፈተችለት፤ ጸጉሯ ተንጨባሮዋል፤ አይኖቿ ሰርጉደው፣ ከንፈሯ ከመድረቁ የተነሣ መሰነጣጠቅ ጀምሮአል። ኤፍሮን ያንቺ እንዲህ መሆን ማንን የሚጠቅም ይመስልሻል? ይልቁንም ሁላችንንም እየጎዳን ይገኛል። ለሳቸው የሚጠቅማቸው ነፍሳቸውም ረፍት የምታገኘው የተሰዉለትን ዓላማ ከግብ ስናደርስ ነው። አለበለዚያ አጥንታቸው እየወቀሰን ይኖራል ሠላምም አይኖረንም። ጨከን በይና ጠንከር ብለሽ የጀመርነውን መንገድ በድል እንፈጽመው። ይህቺን ኤፍሮን በጭራሽ አላውቃትም፤ ሁሉን እርግፍ አድርገሽ ከበተንሽው ጸጸቱን አትችይውም ከዚህ ይብስብሻል።

እኔ የማውቀው ብርቱ እንደሆንሽ ነው። ለዚህ ድርጅት ያለሽ የማይወላወል ወሰን አልባ ታማኝነትም ለቆራጥነትሽ ማሳያ ነው። በውስጥሽ ያለው የጦረኝነትና የጀብደኝነት መንፈስ ሁሌም ያስቀናኛል። ጭንቅላትሽ ላንቺ እንደ ጦር መሳሪያም እንደሚያገለግልሽ አውቃለሁ። አንቺ በዘቀጠ ሥርዐት ውስጥ የምታበሪ የለውጥ፣ የተስፋ እና የእንቢተኝነት ምልክት ነሽ፤ የፍትህ አርበኛ። እድል ከአንቺ በተቃራኒ ብትሆን እንኳን ለእውነት የምትፋለሚ፤ ይህን ሁሉ እንዲሆን ገፊ ኃይልሽና በጨለማም ጊዜ የሚመራሽ ብርሃን ደግሞ ለሀገርሽና ለሕዝብሽ ያለሽ ፍቅር እንደሆነም አውቃለሁ። ብሎ ከዐይኖቿ የሚወርዱትን እንባዎች መዳፎቹን ከጉንጮቿ ላይ በማሳረፍ በአውራ ጣቶቹ ይጠርግላት ጀመር።

አልቻልኩ ሶዲያር አልቻልኩም ብላ ተጠመጠመችበት። ጸጸት የእግር እሳት ሆኖ እየለበለበኝ ነው። ለጥቂት ነው ያመለጠኝ ጋሼ፤ ጥቂት ቀደም ብዬ ቢሆን ላተርፈው እችል ነበር። ያ ግጥም ትዝ አለኝ ታውቃለህ፤ ከእንግዲህ አልበላም ከሀገሬ ልጅ ጋራ፤ ቢታተጠብ ቢታጠብ የእጁ ደም አይጠራ! የሚለው። እነዚህ ፈሪዎች አንሰው ሊያሳንሱት፤ እንደ ጀግና እንደ አቅሙ ጥሎ ቢወድቅ አይቆጨኝም። እያለች ማልቀሷን ቀጠለች፤ ሶዲያርም እስኪበቃት በዝምታ አቀፋት እንጂ ለቅሶዋን ሊያስቆማት አልፈለገም።

ስትረጋጋም ወደ መታጠቢያ ቤት ልኮዋት እሱ ቶሎ ሊደርስ የሚችል የሚቀመስ ሊያዘጋጅላት ወደ ኪችን ገባ። ሶዲያር እንዳሰበው ምግብ አዘጋጅቶ እስከሚጨርስ ድረስ ታጥባ አልጨረሰችም ነበር። ያዘጋጀላትን ምግብ ከአንድ ብርጭቆ ወተት ጋር አቅርቦ ጠበቃት። ጨርሳ ወደ ሳሎን ስትመጣ እንድትመገብ ግድ አላት። ከጨረሽ

በኋላ መኝታ ቤት ገብተሽ አረፍ ለማለት ሞክሪ ከዚያ ወደ ውጭም ነፋስ ለመቀበል እንወጣለን።

በማግስቱ ኤፍሮን እና ዶክተር ዛሪየስ ሚስጥራዊ በሆነ የመልዕክት መለዋወጫ መስመራቸው በደረሳቸው መልዕክት መሰረት ወደ ተቀጠሩበት ስፍራ አመሩ። ቸርችል ጎዳና እንደ ደረሱ በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ረጅሙን አስፓልት ይዘው በተሰየሙት አግዳሚ ወንበሮች አንደኛው ላይ ተቀመጡ። ኤፍሮን ይህን ማድረጋችን ግን ተገቢ ነው? ሲል ጠየቀ ዶክተር ዛሪየስ ማን እንደሆነ እንኳን ሳናውቅ እንዲሁ ኑ የተባልንበት ስፍራ መገኘት አግባብነት አለው? እንደምታየው ቀድመን የኛን ሰዎች አስማርተናል፤ መንግሥትም ቢሆን ጥበቃዎችን ቀድሞ ልኮልሃል። የኛ ሰው ካልሆነ ከመንግሥት አካል መስመራችንን ኢንክሪፕት ማድረግ የሚችን እንደሌለም ታውቃለህ።

ይህን እየተነጋገሩ አንዲት ቀጠን ያለች ጠይም ወጣት ከጎናቸው በመቀመጥ፤ በእጇ የያዘችውን ሰነድ ለሁለቱም ሰጠቻቸው። በዚህ መሀል ሲቪል ሆነው አከባቢው ላይ እንዲዘዋወሩ የተደረጉት የሁለቱም ቡድን አባላት ከበባቸውን ማጥበብ ጀመሩ።

ሰነዱን አይተው እንደጨረሱ ስታረጋግጥ እንዳያቹት የህቡህ ድርጅታችሁ መረጃዎች ከነ ቡድን አባላቶቻችሁ ጭምር በእጃችን ይገኛሉ። እውነቱን ለመናገር መረጃዎቻችሁን ማግኘት እንዲሁ ቀላል አልነበረም። ይህን ደግሞ ተመልከቱት ብላ ሌላ ወረቀት ሰጠቻቸው። በዚህ መሃል ኤፍሮን በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ምልክት ሰጠቻቸው። ዶክተር ዛሪየስ የሚያያቸው መረጃዎች አንዲስ ስለሆኑበት፤ እናንተ እነማን ናችሁ አላት። የማወቅ ጉጉት በሚታይበት ገጽታ፤ እጇ ላይ ያለውን የእነሱም ሆነ የመንግሥትን መረጃ እንዲሁ በቀላል ማግኘት እንደማይቻል ያውቃልና። የድርጅታችን ስም

ዞሳር ይባላል። ዓላማችን ከዓላማችሁ አንድ ስለሆነ አባላቶቻችን እነማን እንደሆኑና ስለ ዞሳር ጥቂት ካሳየኋችሁ ይበቃል፤ ይህን የማደርገው እንደምንዋሀድ አንዳች ጥርጥር ስለሌለኝ ነው በማለት ሦስት ወረቀቶች ከያዘችው ብሪፍ ኬዝ ውስጥ አውጥታ ሰጠቻቸው። ይህ ለማመን ይከብዳል አለች ኤፍሮን ወረቀቶቹ ላይ እንዳፈጠጠች። ልክ ነሽ እኔም የእናንተን ድርጅት ፋይሎች ስመለከት እንደዚህ ነበር ያልኩት። ይኸውላችሁ ከዚህ በላይ እዚህ ጋር መሆን አይኖርብንም እዚህ አከባቢ ካሜራ አለን ብለው ነው የሚያስቡት። ግን በአሁን ሰዓት ቀድሞ ሬከርድ የተደረገውን በድጋሚ እንዲያስተላልፍ አድርገነዋል። ቀድሜ እንዳሳወቅኳችሁ፤ የእናንተም ሰዎች ያን ማድረጋቸው ስለማይቀር ክራሽ እንዳያደርግ በሚል ነው ቀድሜ የገለጽኩላችሁ።

መተማመን እንዲኖር እና ልባችሁ እንዲረጋ በማንኛውም ጊዜ ወደ እኛ መምጣትና መረጃ ማግኘት ትችላላችሁ። መልዕክት የተለዋወጥንበትን ፍሪኩዌንሲ ክፍት አደርገዋለሁ። መልካም ጊዜ በማለት ተለየቻቸው። ዶክተር ዛሪየስ ወደ ኤፍሮ እየተመለከተ ምን ታስቢያለሽ? የሚል ጥያቄ አቀረበላት እዚያው እንደተቀመጡ። ሰውዬው እንደሆነ ትላንት ያደረገውን ታውቂያለሽ ትልቅ ዝግጅት አዘጋጅቶ ሁላችንንም ሰብስቦ በቀጥታ ስርጭት፤ ምሳ ግብዣ ተደርጎ፤ ለጦር መኮንኖቹ የማዕረግ ማልበስ ፕሮግራም ከተደረገላቸው በኋላ ተበተንን። ይህን ያደረገው ለሱ ያላቸውን ተአማኝነት ለማጠንከር እንደሆነ ግልጽ ነው። ከባድ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጉዳይ እንደሆነ ይገባኛል፤ እንዲሁ ዝም ብለን የምንወስነው ጉዳይ አይደለም ሌሎቹም ጋር መድረስ ይኖርበታል። እንደ ቀላል አይተን እንዳንተወው ለድርጅታችን የጀርባ አጥንት የሆኑ መረጃዎች ሳይቀሩ አሏቸው፤ በዚያ ላይ ወሳኝ የሆኑ ለድርጅታችን የሚያስፈልጉ አባላትንም ይዘዋል አለች።

ለእነሱ ከምናስፈልጋቸው በላይ ለእኛ ያስፈልጉናል። እነዚህ ሰዎች በተለይ ለቀጣዩ ተልዕኮአችን፤ ምን ያህል ስኪልድ የሆኑ እንደሆኑ ባሳየችን መረጃዎችና እጅግ ጥብቅና ሚስጥራዊ ነው በምንለው ዳታ ቤዛችን ውስጥ መግባታቸው ማረጋገጫ ነው። ወጥመድ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተጠና መንገድ አዘጋጅተን እንቅረባቸውና የመጨረሻውን ውሳኔ እናሳልፋለን። አብረናቸው ባንሰራ እንኳ ዞዓር ያለችውን ቡድን ዝም ብሎ መልቀቅ አደጋው የከፋ ነው በማለት መለሰችለት። አክላም የስብሰባው ሰዓት እየደረሰ ስለሆነ መንቀሳቀስ ይኖርብና ለጠባቂዎችህም እንዲመለሱ ንገራቸው አለችው።

ሚስጥራዊው አዳራሽ ከወትሮው በተለየ በአባላቱ ተሞልቶአል። ድባቡ ግን እንደ በፊቱ አይደለም የሁሉም ገጽታ የሐምሌን ሰማይ መልክ ይዞዋል። ጉባኤው የህሊና ጸሎት በማድረግ ተጀመረ። በመቀጠልም ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ ከእንባቸው እየታገሉ ንግግር ጀመሩ።

የተከበራችሁ እህቶች እና ወንድሞች ዛሬ እዚህ የተሰበሰብንበት ዋና ዓላማ የድርጅታችንን መሰሶ ወደ ሰማይ ቤቱ መጠራቱን ተከትሎ ነፍሱ በሰላም ታርፍ ዘንድ እንዲሁም ሁል ጊዜ ሲዘከር እንደሚኖር ቃል ልንገባ እና የማያዳግም ወደ ኋላ አይደለም ወደ ጎን እንኳ የማናይበትን አዲስ የትግል ምዕራፍ እንድንጀምር ነው። አዎ በሰላማዊ መንገድ ብዙ ተሞክሮአል ግን ያ መንገድ እንዲህ የተበጣጠሰ ማንነት ያላቸው ባለሥልጣናት በበዙበት ሀገር እውን የሚሆን አይደለም። ስለዚህ ከዚህች ቀን አንስቶ ኃይል መጠቀም አማራጭ የሌለው መፍትሄ ስለሆነ ያንኑ ማድረግ እንጀምራለን። አዳራሹ በፉጨት እና በጭብጨባ ተናጋ። በየትኛውም መንገድ ተጉዘን ኢትዮጵያን ወደ ልጆቿ እጅ እንመልሳታለን! በውክልና የምትመራ ሀገር ከእንግዲህ አትኖረንም። ኢትዮጵያ በልጆቿ እንዳትመራ ለምን እንደሚፈልጉና

እንዲህ መከራዋን እንደሚጸና ታውቃላችሁ? የመጀመሪያው ከእኛው ጥፋት ነው፤ ከእግዚአብሔር መንገድ መውጣታችን ቅዱሱን ለቀን እርኩሱን በመፈለጋችን፤ እንደ ሀሳቡ ሳይሆን እንደ ሀሳባችን መኖራችን ነው። ሌላው ግን ኢትዮጵያ ባለችበት ቦታ ሀሰት፤ እርኩሰት፤ ጣኦት እንዲሁም የፍርድ መጓደል ስለማይኖር ነው። ልጆቿ ጻድቃን፤ ጠቢባን እና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ስለሆኑ፤ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ እንዲል፤ ቀንዲል ስለሆኑ ይህን ደግሞ ዓለም ስለማትፈልገው እኚን ሕዝቦች ለማጥፋት ተነሣች። አደረገችውም። አሁን ያለውም ትውልድ እንዲፈጠር ሆነ። እኔ ብቻ የሚል፤ የእኔ ነው ትከክል፤ እኔ ያልኩት ካልሆነ፤ እኔን ብቻ ስሙኝ፤ እኔን አንግሡኝ፤ እኔን ብቻ ውደዱኝ፤ እኔ እኔ የምንል ሆንን። አሁን አዲስ አብዮት ይነሳል። የራሱ ሚዛን የራሱ ዐይን የራሱ እሳቤ እና ርዕዮት ያለው አዲስ አብዮት ምክንያቱም አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁፋዳ የሚያደርግ አላዋቂ ነውና።

በዓለም ላይ የተነሡ የከሸፉም ሆኑ የተሳኩ አብዮቶች መመዘን ያለባቸው በስኬት አልያም በውድቀት ሳይሆን ይዘው በተነሡት ዓላማ እና ዓላማቸውን ለማሳካት በተጓዙበት መንገድ ነው። ሙአመር ጋዳፊን የመሰለ እድሜውን እንደ ሻማ አቅልጦ ለሕዝቡ ያበራን፤ ሕዝቤ ቤት ሳይኖረው እኔ የሞቀ አልጋ ላይ አልገላበጠም ብሎ በረሃ የኖረን፤ አፍሪካን አንድ ካላደረኩ እንቅልፍ አይኖረኝም የሚልን፤ ህልምን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተጋራን፤ የፓን አፍሪካኒዝምን ችቦ ከማንዴላ ተቀብሎ ለማቀጣጠል ቆራጥነት የነበረውን መሪ፤ እንደ ተራ ሰው ትቦ ውስጥ ያስተኛ አብዮት አለ። አሜሪካ ጠላቴ ስላለችው ብቻ የዓለም ጠላት እንደሆነ የምንስለው በምን ምክንያት ነው? ያ ሳያጣራ እንደ መንጋ የሚነዳ ሕዝብ ገና ዋጋውን ከፍሎ አልጨረሰም! ብዙ የረከሱ አብዮቶች ሲሳኩ አይተናልና። ቅዱሱን ከእርኩሱ መለየት ያስፈልጋል። ነጻነት፤ እኩልነት፤ ዲሞክራሲ እና እራስ

ገዝን የመሳሰሉ መርሆች በደንብ መፈተሽ ይኖርባቸዋል። ቃሎቹን ስለ ወደድናቸው አልያም የሥልጣኔ መገለጫ አድርገን ስለቆጠርናቸው አይነኬ አድርገናቸዋል፤ ጣኦት ሆነውብናል። ይቀራሉ አይደለም በደንብ ይፈተሻሉ። ዘመናዊነት ምንድነው? ማን ነው ዘመናዊስ? ኋላ ቀርስ ምንድነው? ከየት እና ከማንስ ነው ኋላ የቀረው? ጥበብስ ስንል ምን ማለታችን ነው? የትኛውንስ ጥበብ የያዘን ነው ጠቢብ የምንለው? ታናሽ ማነው? ታላቅስ? መልካም የቱ ነው? ክፋትስ? የማን ርዕዮት በማን የተፈጠረ በማን ልክ የተሰፋስ ነው እኛ የምንቀበለው? ከአሁን በኋላ የምናስነሳው አብዮት የህዳር አህያ የምንሆንበት፤ ከምዕራባዊያን የቃረምናትን በማር የተለወሰ መርዝ፤ አልያም እኛነታችንን እና የኋላ ታሪካችንን የምንንቅበት ሳይሆን፤ ሁሉን በራሳችን ባህል እና እምነት በሀገር በቀል ዕውቀት እና ጥበብ የምንመራው፤ እኛን ሁኖ እኛን አህሎ ወደ ቀደመ ክብራችን የሚመራን፤ በእድሜ፣ በኮታ፣ በቁመት፣ አልያም በመልክ የማንሿሿምበት ዕውቀት ካለው ማንም ይሁን ማን ከየትኛውም የሀገሪቷ ስፍራ ተነስቶ የትኛውም የሀገሪቷ ስፍራ የሚሾምበት፤ እንኳን ኢትዮጵያ አፍሪካን አንድ የሚያደርግ አፍሪካውያንን ያቀፈ ቅዱስ እና ታላቅ አብዮት ዛሬ ይወለዳል! ይህ የድሮ ሥርዐት ናፋቂ ከአስባለን አዎ ነን! በደምብ ነው እንጂ የምንናፍቀው።

አብዝቶ በታሪክ ተወቃሽ ከሚደረጉት ነገሥታት ግንባር ቀደሙ አጼ ሚኒልክ እንደሆኑ ይታወቃል። ይሄ ውንጀላ ከተራ ልብ ወለድነት እና ጭፍን ጥላቻ እንዲሁም የበታችነት ስሜት ከወለደው ቅዠት የመነጨ እንደሆነ በመረጃ እንመልከት። እምዬ ሚኒልክ እጅግ ቅን እና ሩህሩህ ንጉሥ እንደ ነበሩ ከሚያስረዱ ክስተቶች መሃል ቀጥሎ የማጋራችሁ ክስተት አንዱ ነው። ሚሊልክ በፍርድ ወንበር ተቀምጠው ሳለ አንዲት ሴት ክስ ይዛ ትመጣለች። ይህቺም ሴት የጊዜው ኮማሪት ነበረች።

የተለያዩ ባሕላዊ መጠጦችን በመሸጥ የምትተዳደር። በዚህ ተግባር ተሰማርታ እየኖረች ሳለ፤ አንድ ሰው ሊስተናገድ ቤቷ ይገባል። ሁለት ማርትሬዛ በመክፈል ይተኛታል። ተዋደዱ፣ አብረውም ዘለቁ። የሰጣት ማርትሬዛ ላይ እሷ ጋር የነበረውን ጨምራ ንግድ እንዲነግድ ታደርገዋልውች። ብዙ ንብረትም ያፈራል። በዚህ መሃል ወዳጅ ዘመዶቹ፤ እንደማትሆነው በመንገር፤ ይህቺን ኮማሪት እንዴት ታገባለህ? ፍታት እያሉ ይዘበዝቡት ስለ ጀመሩ። በጀ ብሎ ከቤት እንድትወጣ ግድ ይላታል። በዚህ ምክንያት ነበር ወደ ንጉሠ ነገሥት እምዬ ምኒልክ ያመራቸው።

እሳቸውም ሁኔታውን በመረዳት የዘመኑ ሕግ የሚፈቅደውን ውሳኔ ይወስናሉ። አሻፈረኝ አይሆንም፣ አልስማማም። አባ መላ ይዳኙኝ ታላለች። በዚህ ድርገታ የተቆጡ የንጉሡ ሹማምንት እንዴት ንጉሥ የፈረደውን ፍርድ ትቃወሚያለሽ? ከእሳቸው የበላይ ማን አለና? በማለት እንድትገረፍ በአንድነት ያዛሉ። እምዬ ግን ግርፋቱን በመሻር፤ መፍትሄ ያገኘላት እንደሆነ ትሂድ ትሞክረው ብለው፤ ወደ ፈለገችው ወደ ፊት አውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ይልኳታል።

አባ መላ ጋር እንደደረሰች የገጠማትን ሁሉ አስረዳች። አባ መላ ሃብተ ጊዮርጊስም ተከሳሹን በመጥራት አልተጋባችሁም? ሲሉ ይጠይቃሉ።

፡፡ አዎ አልተጋባንም።

፡፡ እንግዲያውስ ምን ያህል ጊዜ ቆያችሁ?

፡፡ ሁለት ዓመት።

፧ መጀመሪያ ምን ያህል ከፈልካት?

፧ ሁለት ማርትሬዛ።

እንግዲያውስ ሁለት ዓመት የተገለገልክበትን በቀን ሁለት ጠገራ አስልተህ ክፈላት ይሉታል። ሲሰላ ብዙ ስለ ነበር፤ አግብቶአት መኖር ጀመሩ። የእምዬ ምኒልክ እንዴት እናቃለሁ ብሎ ያለ መውበራት የሴቷን ሕይወት እንዳስተካከለው ታያላችሁ? ያሁኖቹስ እንዲህ ያደርጋሉ? ስማችን ተጠራ ብለው አይደል እንዴ ጥፍር የሚያስነቅሉት።

ጣልያኖቹ ከእኛ በላይ እንደሚያከብሯቸው ማወቅ ከፈለጋችሁ፤ መለስ ብላችሁ የምስል ቀረጻዎችን አልያም መዛግብትን ማገላበት በቂ ይሆናል። ለዚህ ክብር እና ፍቅር ያበቃቸው ድርጊት ደግሞ፤ የማረኳቸውን ምርኮኛዎች፤ አብልተው አጠጥተው መሸኘታቸው ብቻ አይደለም። ዘመናዊውን ወታደር፤ በጦር እና በጋሻ ማሸመድመዳቸው ጭምር ነው እንጂ። በሮም አደባባይ ቪቫ ሚኒልክ! የሚል መፈክር እያሰሙ ጣልያናውያን የድጋፍ ሰልፍ ያደረጉበትን ቪዲዮ ማንም ሰው በቀላሉ ሊያገኘው የሚችለው ነው። አሁን ግን እናንተ በባዶ ፎክሩ እነሱ እረስተውታል የሚል ብኩን ትውልድ ፈጥረናል። የወለደችው እናቱን የሚረሳ፤ ዞርም ብሎ የማይረዳ ሰው ሚኒልክን ቢረሳም ቢረግም ምን ይደንቃል? ከዚህ በላይ በበታችነት ስሜት የመጠቃት ማሳያ ይኖር ይሆን? ታሪክ ምን ይጠቅማል የሚል ታሪክ የሌለው ነው!

ጥቂት የማይባልን የማኅበረሰብ ክፍል እንዲህ ባለ ተረት ከልጅነቱ ጀምሮ በከለው አሳደጉት። በወጣቱ አይፈረድም። እኔ የማዝነው ሰርተው መለወጥ፣ ተምረው መቀየር ያቃታቸው፤ እንዝላሎች! በጉልበታቸው ማግኘት

ያቃታቸውን ሀብት እና ንብረት ለማካበት ሲሉ ልቦናቸው እያወቀ፤ ወጣቱን እንዲህ ባለ አለማወቅ ውስጥ እንዲዘፈቅ ባደረጉት ኢሊቶች ነው። እንቅልፍስ ተኝተው ያድራሉ ወይ? በፍጹም! የዚህ ሁሉ ወጣት ደም ምድሪቷን ገሃነም ነው የሚያደርግባቸው። ሱፍ ለብሰው ካሜራ ፊት ሲቆሙ እውነት እንዳይመስላችሁ፤ ጓዳቸው ጉዳቸውን ያውቀዋል። ስንት እንቅልፍ አልባ ለሊቶችን፤ ስንት ረፍት አልባ የመባዘን፣ የመረበሽ፣ የመቅበዝበዝ ዘመናትን እንዳሳለፉ እነሱ ያውቁታል። እውነት ሲሰነብት ታሪክ ይሆናል፤ ታሪክ በዘመናት ሲሸመግል ተረት ይመስላል።

ከዚህ የባቢሎን ሥርዐት የአባቶቻችን እጅጉን ይበልጥብናል። ጁልየስ ቄሳር ጓልን በቁጥጥሩ ሲያስገባ፤ የዛሬዋን ፈረንሳይ ማለት ነው። ጓል ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አንድ ሚሊዮን የኬልቲክ ሕዝቦችን ፈጅቶአል። በሙሉ ቁጥራቸው ሦስት ሚሊዮን ነበሩ። አንድ ሚሊዮን የሚሆኑትን ደግሞ ባርያ አደረጋቸው። ቀሪዎቹን ደግሞ እንኳን ወደ ሮማን ሪፐብሊክ በደህና በጣችሁ ነበር ያላቸው። ገና ኢምፓየር አልሆነችም ነበርና። ወደ ዴይሻ በማቅናት ሙሉ ሕዝቡን ነበር የደመሰሷቸው። ከነ ሙሉ ታሪካቸው። አብዛኞቻችን ዴይሻን የማናውቃት ለዚሁ ነው። ያቺ ስፍራ አሁን ሮሜኒያ በመባል ትጠራለች። በሥማቸው ሰይመዋት እስከ ዛሬም እንዲያው ቀጥላለች። አሜሪካ 50 ሀገራትን ጨፍልቃ አንድ ሀገር ሆናለች ያውም በመሳሪያ። አፍሪካ ከእንግዲህ አንድ እንጂ 54 የምትሆንበት ምክንያት አይኖርም በፍቅር ነው ታዲያ። ሁሉም ውስጡን ከአጠራ ድንጋዩን ልብ አውልቆ አዲሱን ከአጠለቀ፤ ከመንጋ አስተሳሰብ ወጥቶ በአመክኮ ማሰብ ከጀመረ፤ አዲስ ሕዝብ እንወልዳለን በአዲስ ሀገር ላይ። ከበፊቱ የላቀ ፉጨት እና ጭብጨባ።

እኛ የነጻነት አርበኞች ነን! አሁን በወንድማችን መሰዋት እና በሀገሬ ሀዘን ስሜት ሁኜ የቋጠርኳትን ግጥም አቀርብላችኋለሁ።

አራጁ ተረኛ

ሀብታሙ ገበሬ፣ ከሰው የወረደ
ከመውረድም አልፎ፣ ዘቅጦ የተገኘ
ይወጣል ማለደ፣ በሬ አዘጋጅቶ
ሞፈር ቀምበር ይዞ፣ ሲተጋ ይውላል፤
አስቦ አሰላስሎ፣ አውጥቶ አውርዶ
በምሽት ቁጭ ብሎ፣ ለንጋት ያቅዳል
አቅዶም አይተወው፣ ማልዶ ይፈጽማል።
እንኳን የዕለቱን፣ የምታመቱን ወጥኗል
እሱን ይጥቀም እጂ፣ ከሰይጣን ያብራል
ደግሞም ተስማምቶ፣ አብሮ አይቶታል።
ትጉ ነው ሲሰራ፣ አንጀትን ያርሳል፤
ግና ምን ያደርጋል፣ ምንስ ይፈይዳል

የሚዘራው ዘር ሲታጨድ፣ ተፈጥሮን ተጣርሷል

በራስ ወዳድነት፣ የቀድሞውን ትቶ በአዱን ዘርቶታል!

ለሱ ይበጅ እንጂ፣ ለሱ ይድላው እንጂ

ሀገሩን አምሶ፣ ዓለሙን በጥብጧል

ለሱ መወደጃ፣ ለሱ መነገጃ

ለሱ የድሎት በር፣ ለሱ ልብ ማማሻ

ለሱ መናገሻ፣ ለሱ መዳረሻ

የሚዘራው ሁሉ፣ የሚኮተኩተው

የሚያስበው ሁሉ የሚናገረውም፣ እሱ የሚነካው

መርዝ ሆኖበታል፣ ለሀገሩ ሁሉ።

በቃኝ ብሎ በነቂስ ወጣና፣ አመጸ ያገር ሰው

ይህንን ሰማና፣ አስቦ አሰላስሎ

ከልጆቹ መሀል፣ መምረጡን ዘንግቶ

ከባሮቹ አንዱን፣ ወከለው አብልጦ

ሾመው በንብረቱ፣ አንግሶ ቀብቶ።

ይህንም ዐየና፣ መጣ ብሎ የቀን አዲስ፤

ሆ ብሎ እንደወጣ፣ መልካም ብሎ ገባ

ይሄ ያ'ገሬ ሰው፣ እረፍት አገኘና።

አዲሱም ሹመኛ፣ ወይ ፍንክች በማለት

ሿሚውን እመቀመቅ ከቶ፣ ያለ አዛኝ ብቻውን ነገሠ

ከቀድሞው ባሰና፣ ሞፈር ቀንበር ትቶ

ዘሩን አባዛ'ና፣ ሀገሩን ነደለው!

እሱ አልበቃህ ቢለው፣ በሬውን ላሙንም ማረዱን

ጀመረው!

መቷል ያለው፣ ለኛ

ሆኖበት አረፈው፣ አራጁ ተረኛ።

ይህን ጊዜ አዳራሹ በጽኑ ጸጸት እና ትካዜ ተሞላ። መድረኩንም ኤፍሮን በመረከብ ቀሪ የተባሉ አጀንዳዎች ላይ ውይይት እንዲጀመር አደረገች።

በዚህ ሁኔታ ሦስት ያህል ቀናት እንደተቆጠሩ፤ ቀድሞ በመልዕክት በተለዋወጡበት ፍሪኩዌንሲ በተደረገ ግንኙነት ቴራስ፣ ሰዓር፣ ያባል እና ጋይዳድ በመሆን ኤፍሮንን ሶዲያርን እና ዶክተር ዛሪየስን የዞዓርን አባላት አንዲሁም ሚስጥራዊ መስሪያ ቤት አስነበቧቸው። የእነ ኤፍሮንም ቡድን ይጠቅመናል የሚሉትን ሁሉ ማጣራት ከፈጸሙ መኋላ የመዋሀዳቸው ጉዳይ ቁርጥ ሆነ። ሁለት የነበሩት ህቡህ ድርጅቶች የጋራ መጠሪያም ዞዓር ሁኖ እንዲቀጥል ከነ ኤፍሮን በኩል በመጣ ፍቃድ ተወሰነ።

በዚህም መሰረት የዞዓር አባላት ያጸደቁት ቀጣይ ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን እንቅስቃሴ ተጀመረ። በያባል እና ሶዲያር በአንድነት እየተመራ የሚገኘው የማኅበራዊ ሚዲያ ቡድን አመርቂ ውጤት ማምጣት ጀምሮአል። መንግሥት በአፈሳ በየትምህርት ቤቱ እንዲሁም ስታዲየም ያነራቸው ወጣቶች ባልተጠበቀ መልኩ ሕብረት ፈጠሩ። ከተለያዩ የከተማዋ ስፍራዎች ተለቅመው በአንድ እንዲሆኑ መደረጉ፤ የታሰሩበት ዓላማ አንድ መሆኑ እንዲሁም አላቸው ተብሎ የታሰበው ኑሮአቸውም የተገኘው እምነት እና አቋም ይበልጡኑ አንድ አደረጋቸው።

ይህም በመሆኑ አልፎ አልፎ በሚፈቀደው እና ለጥየቃ ለሚመጡ ቤተ ሰቦቻቸው በሚያስተላልፉት ሚስጥራዊ መልዕክት አማካኝነት መንግሥት ያስቆመው የመሰለው መደራጀት በህቡህ ቀጠለ። ጊዜያትም ነጎዱ የነሱ መሰወር እና መገደል የወጣቱን ቅስም ይሰብርልኛል ብለው ያሰቧቸውን ዋና መሪዎች ብለው የጠረጠሯቸውን በመረሸን ቀሪዎቹን ፈቷቸው። እኚህም ቀድመው በመሰረቱት አንድነት ወደ መኖሪያ አከባቢያቸው በተቀላቀሉም ጊዜ መደራጀቱን አፋጠኑት። እልህ እና ቁጭቱ ተጨምሮ እየጎመራ መጣ። ከየሰፈሩም የተወጣጡ ስለነበሩ በየሰፈሩ ለተደራጁ ለከተማዋ ወጣቶች አደረጃጀት የሚሞች ከየሰፈሩ አንድ አንድ መሪ መምረጥና ማዕከላዊ ኮሚቴ መመስረት አልከበዳቸውም ነበር። ይህንም ከማንም ተጽኖ ውጭ በሆነ መልኩ ፈጸሙት። ቀጣይ ብለው ባስቀመጡት እቅድም መሰረት ወደ ትግበራው አመሩ።

ይህም የዞዓርን አባላት ለሁለት የከፈለ ሀሳብ አስነሳ። ሰዓር፣ ጋይዳድ፣ሶዲያር እና ዶክተር ዛሪየስ እንዲሁ ይቀጥሉ እኛ ከዚሁ ሆነን እቅዳቸውን እንዲያሳኩ ብቻ መንገዱን እንጥረግላቸው፤ በእነሱ ላይ የታቀደ እቅድ ሲኖር ቀድመን መረጃው እንዲደርሳቸው እናድርግ ሲሉ።

ቴራስ፣ ኤፍሮን እና ያባል በተቃራኒ ሀሳብ ተሟገቱ። ቴራስም ከእኛ ጋር መሆን አለባቸው፤ ቀድሞ መረጃ እንዲደርሳቸው ማድረጉ ብቻውን አይጠቅማቸውም። ሙች እና እንዴት ምን አይነት ተቃውሞ እንደ ሚያደርጉ በሳል የሆነ ስትራቴጂ የሚነድፍላቸው እና ውጤታማነቱን እየለካ፣ እየገመገም ማሻሻያም ሆነ የዕቅድ ለውጥ የሚያዘጋጅ አካል ያስፈልጋቸዋል። ለሰዓር እና ቡድኗ ምስጋና ይድረሳቸው እና እንደምናየው ከሆነ መሪ ብለው ያስቀመጧቸው ልጆች የዕውቀት ማነስ የለባቸውም። ነገር ግን ልምድ ወሳኝነት አለው። ይህን ነገር በቶሎ መስመር ካላስያዝነው ደጋግሜ እንዳልኩት በማን እጅ ሊወድቁ እንደሚቹ አናውቅም። በማለት ስጋቱን አጋራ። በዚህ መልኩ ለቀናት ሀሳብ ሲያነሱና ሲጥሉ ከቆዩ በኋላ። ዞዓርን እንዲቀላቀሉ ተስማሙ።

ስሜታዊ ከሆነ ውሳኔ እና ከጥርጣሬ ያድናቸው ዘንድ የወጣቶቹን ተወካዮች ምንም እንኳን አደጋ ቢኖረውም ከፍ ያለ ሥልጣን እና ዝና ያላቸው አባላት ተመርጠው እንዲያወያዩአቸው በመወሰኑ፤ አምባሳደር ፍቅረማርያም፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተሩ እና ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ በመሆን እንደተለመደው በሰዓር በኩል በተጠሩ የወጣቶቹን ተወካዮች ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ በድብቅ ስፍራ አወያዩአቸው። እንደታሰበውም ተሳካ።

ቴራስ፣ ሰዓር እና ኤፍሮን በተደጋጋሚ በሥራ ምክንያት በመገናኘታቸው፣ ጸባያቸውም በመግጠሙ ይበልጥ እየተቀራረቡ መጥተዋል። ዛሬም ከወጣቶቹ ጋር የነበረውን ስብሰባ አብረው እየተካፈሉ ይገኛሉ፤ ከቡድኑ አባላት ጋር በመሆን። ከወጣቶቹ ተወካዮች አንደኛው ሀሳቡን ሰንዝሮ በማመስገን አበቃ። ሌላኛው ተነስቶ፤ ይኸውላችሁ እኔ በዚህ ከተማ ተወልጄ ነው ያደኩት የተማርኩትም እንደዚያው፤ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ግን አሁን የተናገረው ወንድሜ እዚሁ እንደተማረው ሳይሆን

ሌላ ከተማ ነው ሄጀ የተማርኩት። እዚያም እንዳየሁት ከሆነ ሥራ ከሚሰራው ወጣት ሰፈር የሚቀመጠው ነው የሚበዛው ሁሉም ማለትም ይቻላል። ይህ የተማረውንም ያልተማረውንም ያካትታል። ልክ እዚህ እንደሚሆነው ማለት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ይሁን እንጂ የትም ብትሄዱ ያው ነው። ለምንድነው ወጣቶች ሰፈር የምንቀመጠው? ሥራ ጠል ስለሆንን? ሰነፎች ስለሆንን ነው? ከአባታችን ወይም ከእናትችን በየቀኑ ገንዘብ መቀበል ደስ ብሎን? ወይስ ቁጭ ብሎ የእናት እንጀራ መብላት ስለሚቀል? ሰፈር ውለህ መጥተህ የምትበላው የእናት እንጀራ እንዴት ለጎሮሮህ የአሳ አጥንት እንደሚሆንብህ የሚያውቅ ያውቀዋል።

ለእናትህ ነጠላ ለአባትህ ካፖርት መግዛት ትፈልጋለህ፤ ግን ያንተን እንኳን እነሱ እንደሚገዙልህ ስታስብ ወሸመጥህ ይቆረጣል። ወጥተህ ተፍ ተፍ ማለት ትፈልጋለህ ግን መንገዱ ሁሉ የተዘጋ ይሆንብሃል። ታናሾቻችንን፣ እህቶቻችንን፤ እናት አባቶቻችንን ማስደሰት መርዳት እንፈልጋለን ግን እኛ እራሳችን ተረጂዎች ሆነን እንገኛለን። ሰዎች እኮነን ንብረት ማፍራት፣ ትዳር መመስረት፣ ልጅ መውለድ እንመኛለን። እየሆነ ያለው ደግሞ ይህ ምኞት ብቻ እንዲሆን ያደርገዋል። ቁጭ ብለህ ፊልም ስታይ፣ ዘፈን ስታዳምጥ፣ ከጓደኛህ ጋር ስትጫወት ይመሻል፤ ወክ ታደርጋለህ ቤትህ ገብተህ ትተኛለህ። ይነጋል ያው ቀን ይደገማል ቅዳሜ እና እሁድ ሲመጣ ከየትም ከየትም ብለህ ትጠጣለህ፤ ያቀን ደስ ይልሃል ምክንያቱም ሁሉን ያስረሳሃል። አሁንም ይመሻል ይነጋል፤ ያ ቅድም ከላይ ያልኩት ሁሉ ሲደጋገም እየሰለቸህ ይመጣል። ለአንድ ቀን ብለህ አዕምሮህንም ከጭንቀት ለመገላገል አዲስ ነገር ትፈልጋለህ፤ መቃም ትጀምራለህ፤ ቀኑ ያጥርልሃል ደስ ትሰኛለህ እየደጋገምከው ትመጣለህ፤ አልበቃ ይልሀል ሲጋራ ትጨምርበታለህ። እንዲህ እያልክ ቀልጠህ

ትቀራለህ፤ የሕይወትህ አንዱ አካል ይሆናል። ሁሉም እንዲህ ያደርጋል ማለት ግን ኣይደለም።

ይህን ሁሉ ቀን በቀን ለማድረግ ገንዘብ ያስፈልጋል፤ ኣይኖርህም ይህን ደግሞ የግድ ማድረግ ይኖርብሃል አማራጭህ ምን ይሆናል? የታወቀ ነው! ኣያችሁ ምን ምንን እየወለደ እንደሚመጣ? ይህን ተከትሎ የሚመጡ ሥሞች ደግሞ ይኖራሉ፤ ድርዬና ሥራ ፈትን የመሰሉ። ከዚያ አንድ ወጣት ማኅበረሰቡን ሀገሩን ቢጠላ ልትፈርዱበት ነው? ኣያደርገውም እንጂ። እራሱን ቢጥልና እራሱን ቢያጠፋስ ምን ልትሉት? ከዚያም ተወቃሾቹ ደግሞ እኛው መሆናችን፤ ወጣቱ ሥራ ኣይወድም! ሥራ ይንቃል! ሀገር ተረካቢ እየጠፋ ነው ይሉናል። ስለየትኛዋ ሀገር ነው የሚያወሩት? እነሱ እንኳን ተረከበዋል እንኳን እኛ! ምን የመሰለች የተፈራች፤ የተከበረች፤ ታላቅ እና ገናና ሀገር ተረክበው ሳይሆን በጉልበት ወስደው እኮነው ኣሁን እንደዚህ ወጣቶቿ ተስፋ የቆረጡባት የሚንቋት እና የሚጠሏት፤ ለውርደት የታጨች ሀገር የወለዱት። ግን ምንም ብንደረግ እማማን አንጠላትም ሥርዐቷን እንጂ። እሱን ደግሞ እናስተካከለዋለን። ማን ነው ማንን የሚወቅሰው? ማን ያጠፋው ከማንስ ይበልጣል?

አንድ ገበሬ በጊዜው አርሶ በጊዜው ዘርቶና አርሞ፤ ያደረሰውን ስንዴ እንክርዳዱን እንዴት ከስንዴው መለየት እንዳለበት ያውቃል። አንድን ከተማ ወስደነው ግን የደረሰን ምርት ስንዴውን ከእንክርዳዱ እንዲለይ ብናደርገው፤ ስንዴው የቱ እንክርዳዱ የቱ እንደሆነ መለየት ስለሚከብደው፤ ምናልባትም እንክርዳዱን ጎተራ ሊያስገባው ይችላል። እኛ ሀገርም እንደዛ ነው የሆነው። የማያውቋትን ያልሠሯትን ሀገር በጉልበት ተረከቡ ባለሀገሮቹን አሸማቅቀውና ገፍተው ገለውም አሸሹ። እንክርዳዱን እየሰጡን ስንዴውን ጣሉት የሚቀበል

ተቀበላቸው። አሁን ደርሰው አዋቂ ልሁን ይላሉ። Stereotyping ለማንም አይጠቅምም፣ እስኪ እንዋቀስ ማን ምን ሰርቶ ነው ማንን የሚሰድበው? አዋቃሽስ ማን ነው? መስፈርቱስ ምንድነው? ምስክር የሚሆንስ ሽማግሌ ሀገሪቷ አላት ወይ? የትልቅነት መስፈርቱ ከጠፋ እኮ ቆየ! እሱንስ ያደረገው ወጣቱ ነው? እስቲ እራሳችሁን ታዘቡ ሁላችንንም ጉድ እንዳስባሉን የጋሞ አባቶች አይነት ሽማግሌዎች አሉን? እስቲ እነ እከሌ ሀገሪቱ ውስጥ እሳት የመሰለ ቁጣ ቢነሳ የማብረድ ተሰሚነት በማኅበረሰቡ ውስጥ አላቸው ብላቹ የምትጠሯቸው ሽማግሌዎች አሉ? አብዮቱ ከመፈንዳቱ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ሰሎሞን ደሬሳ ካሳተመው መድብል ላስታውሳችሁ

“ዋኝበት ሜዳውን ሩጠው ባህሩን፣

ውረድ አቀበቱን ረግጠህ ጭንቅላቱን፤

ወንዝ አትሁን ልቀቅ ጎዳናውን ጥንት የሰከነውን፤

ተሰናበት አባቶችህን፣ እራስህ አባት ልትሆን፤

እንቢ በል አትቀበል ለደግነት ውሰት፣ ለይሉኝታ ርህራሄ፣

ግድ የለም አሉልህ የእልፍ ሺ ዘመን ሙታን ከቻይና፣

ከባቢሎን፣ ከአክሱም ኢትዮጵያውያን፤

ቱልቱላ መለከት ሲያቅራሩ ደግሞ ገለሌ የአረር አዋራ፤

አሻፈረኝ ባዩ ወንዱ እንቢ ባይ ወልዱ፤

ተርብ አውራ የገዳይ ሻንፎ ሀድፍቱ መራራ፤

ነፍሱ በመስመር ታጥራ”

ምን አይነት መልዕክት ሊያስተላልፍ ነው የፈለገው ለወቅቱ ወጣቶች? ሰሎሞንን በደንብ ስታውቁት ለአባቶቹ የነበረውን ንቀት ትረዳላችሁ። የኛ አባቶች ማን እንደ ነበሩ ዐያችሁ? የአባቶቻቸው ጎዳና ሁሉ ለነሱ ሬት ነው! እኛ ደግሞ አባቶቻችንን ሳይሆን አያቶቻችንን ከዚያም የቀደሙትን አጥብቀን እንፈልጋቸዋለን! ወደ ፊት መጓዝ የምንፈልገው፣ ወደ ኋላ ተመልከተን ነው! እሱ ብዙ ቀት ያስጉዘናል!

መጀመሪያ ወደ ራስ መመልከት ይቅደም። ከዚያ ሁሉም ይጠራል። ይህ ሁሉ ዕውቀት ያላቸው በመሰላቸው ግብዞች ምክንያት የመጣ ጣጣ ስለሆነ መስተካከል አለበት። ሥልጣን ላይ ያሉትን መውቀስና መጥላት ብቻ ለውጥ አያመጣም። እነሱም የማኅበረሰቡ ውጤቶች ናቸው፤ የስህተታችን፣ የኅጢያታችንም ቅጣቶች። እኛ ወንበሩን ብናገኝ እንደ እነሱ አለመሆናችንን እራሳችንን እንፈትሸና ወንበሩን ለሚገባው ሰው እንስጥ። ያን ለማድረግ እኛ ቆርጠናል! ታዲያ ይህን ስናደርግ እንደ ከዚህ ቀደሙ ወንበሩን ሰጥተን ወደ ቤት በመግባት ሌላ አንባገነን መፍጠር አይኖርብንም። ስለዚህ ሁሉ በእቅድ መሆን ይኖርበታል እሱንም አዘጋጅተናል። ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ መጥራት አለበት ደግሞም ይጠራል። እኔ ከዚህ ቀደም ሌሎች ታግለው፣ ታስረው፣ ተገርፈው፣ ተርበው፣ ተጠምተው፣ ቆስለው፣ ሞተው ነጻነቴን እንዲሰጡኝ እፈልግ ነበር። እኔ ከእነዚ አንዱ እንዲደርስብኝ አልፈልግም። ታዲያ ሌላው ለብቻው የበላው እዳ አለበት? እሱ ሞቶ እኔ ተኝቼ በወንድሞቼና በእህቶቼ ሞት ብቻ እኔ ሳልሳተፍበት የማገኘው ነጻነት ለጎሮዮዬ ምላጭ ይሁን! እንዲህ አይነት ክፉ ደዌ የሆነ እራስ ወዳድነት ከሚተበትበኝ ሞቴን እመርጣለሁ! ታግዬ የማመጣው ነጻነት እንጂ በሌሎች ሞት የማገኘውን ነጻነት

አልመኝም! ባይሆን ለታናናሾቼ የተሻለን ነገ ለማስረከብ እኔ ዛሬ ደሜን አፈሳለሁ! ሰላም በመሰለ ባርነት ውስጥ ከመቆም፣ ለነጻነት እየታገሉ መውደቅ ክብር አለው! ተሸፍኖ ተሰርቶ ያለቀ፤ እሳት፣ ነበልባል የሆነ ትውልድ እየመጣ ነው! ተዘጋጁ! በማለት አመስግኖ አበቃ። እንዲሁም በየተራ ተነስተው ሀሳብ ሰነዘሩ።

ሁላችንም አንድ አይነት ዓላማ እና ፋላጎት እንዳለን ዐያለሁ በዚህም ደስተኛ ነኝ በማለት ንግግሯን ጀመረች ኤፍሮን፤ ሁላችንም ጋር ያለው የቁጭት ስሜት እኔነትን ሳይሆን እኛነትን እና ሀገርን ያቀፈም ስለሆነ እንደዚሁ። ከእኔነት ስንወጣ ሁኔታዎችን እርቃናቸውን ማየት እንጀምራለን። ያ ደግሞ በጥልቀትና በግልጽ እንድናያቸው፣ እንድናውቃቸው እና እንድንረዳቸው ያደርገናል። እሱም ወደ ትክክለኛው መፍትሄ ይወስደናል። ይኸው እዚህም አድርሶናል ወደ ፊትም ከግባችን እንደ ሚያደርሰን ጥርጥር የለውም። አሁን ወደ ኦፐሬሽን መግባት ይኖርብናል! እስከ አሁን የለውጥ ፍላጎት የሠራነውን አሰርቶናል፤ ከዚህ በኋላ ያለውን መንገድ የሚያስጉዘን ውይይት አልያም ወረቀት ሳይሆን ተግባር ነው። ያ ተግባር ደግሞ ሕይወትን ድረስ ያሳጣል፤ ደም ያፈሳል። ያለ ደም ስርየት እንደሌለ ማወቅ ይኖርብናል። ይህቺ ምድር ከፈሰሰባት የወንድም፣ እህቶቻችን እንዲሁም የአባት እናቶቻችን ንጹህ ደም የምትነጻው በአፍሳሾቹ ደም ነው! ይህ ሲሆን ደግሞ በሂደቱ የኛም ደም ሊፈስ ይችላል፤ ያን በቆራጥነት ለመቀበል መዘጋጀት ያስፈልጋል። በተለይ ከዚህ በኋላ የምንጀምረው ምዕራፍ ለስህተት ቦታ የማይሰጥ ስህተት ከፍያው ሞት የሚሆንበት ነው! ብላ በደሜ ሀገሬ ቀና ትበል! አለች በነፍሴ ትለምልም! በማለት ተቀበሏት በዚሁ ፈጸሙት።

“ጻድቅ በቀልን ባየ ጊዜ ደስ
ይለዋል፤

በኀጢአተኛው ደምም እጁን
ይታጠባል”

የዞዓር አባላት ዛሬ ከሰአት በኋላ የሚፈጸመው የመጀመሪያ ዙር ኦፐሬሽን ያለምንም እንከን እንዲቋጭ ሊከሰት ይችላል ብለው ያሰቡትን ሁሉ እክል ከመንገድ በማስወገድ ተጠምደው ቆይተዋል። ሰዓር እና ኤፍሮን ከፊት ለፊታቸው ያለው ሰፊ ስክሪን ላይ በአራት ማዕዘን ቅርጽ ተከፋፍለው በሚታዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ለኦፐሬተሮቹ ትዕዛዝ እየሰጡ ይገኛል። ያባል እና ጄነራል ባላቅ ደግሞ ከጄነራል ሂሶጵ ጋር በሳተላይት ኮምኒኬሽን መረጃ እየተለዋወጡ ይገኛሉ። ጄነራል ሂሶጵ ኦፐሬሽኑ መጀመሩን አበሰረ። እሱ የሚገኝባት ከተማም ሆነች በአራቱም ጠቅላይ ግዛቶች በእኩል ሰዓት በየከተማው የሚገኙ የጦር ግምጃ ቤቶች በሕዝቡ ቁጥጥር ስር ገቡ። ሕዝቡም የጦር መሳሪያዎችን ታጠቀ። በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተማዎች ግን ታቅዶ የነበረው ኦፐሬሽን ተቋረጠ። ይህም የሆነው በዞዓር አባላት ስያሜ ቴቄል ውስጥ ሚኒስተር ሆኖ ከተሾመው ከጄነራል አሮን በመጣ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሌሎቹ ኦፐሬሽኖች እንዲዘገዩ ተደረገ። ለዚህም እንደ ዋነኛ ምክንያት የተቀመጠው የተራዘመ ጊዜን ከወሰደ ሀገር አቋራጭ መንገዶች ስለሚዘጉ ለሕዝቡ በቂ እህል ላይኖር ይችላል የሚል ሆነ።

ጄነራል ሂሶጵ እየመራው የሚገኘው ተልዕኮ በተገቢው ሁኔታ እየተጓዘ ይገኛል። የአሮጌውን ሥርዐት አመራሮች ከመንገድ እያስወገዱ፤ በቀናነት ሲያገለግሉ የነበሩትን ከወገን እየደባለቁ፤ ከተማዎቹን በሙሉ እየተቆጣጠሩና በየቀበሌው ሕዝቡ እራሱ ይሆኑናል መልካም ሥነ ምግባር እና ዕውቀት አላቸው የሚሏቸውን ግለሰቦች እንዲሾሙ በማድረግ፤ ቀጠናውን ነጻ እና ሰላማዊ እያደረጉ መጡ። ይህ እየተከናወነ ወደላይ መምጣት የሚል ስትራቴጂ ተነድፎ ስለነበር፤ ያኑኑ እየተገበሩ እንቅስቃሴዎቹ ሁሉ በዚሁ ዙሪያ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በቴቄል በኩል ደግሞ የደህንነት መስሪያ ቤት እንዲሁም አመራሮች ለሦስት ቀን ያህል ባደረጉት ስብሰባ ተጨማሪ

ኃይል ገብቶ ነገሩን እንዲቆጣጠረውና ከሹማምንቱ እጅ የወጣውን ሥልጣን መልሶ እንዲያስረክባቸው ተወስኖ እዚያው ባለው ሠራዊት ለመተግበር ተሞከረ ነገር ግን እዚያው አስቀሯቸው። የዞዓር ሠራዊት ወደ ዋና ከተማዋ ጉዞ እንደ ጀመረም ስለታወቀ፤ ቴቄል ተጨማሪ ኃይል ወደ ስፍራው በገፍ መላክ ጀመረ።

የዞዓር ሠራዊት በትጥቅ እና በሰው ኃይል ከሚመጣው ሠራዊት ጋር አይመጣጠንም ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉም የአብዮቱ አካል ነበርና ምንም እንኳ በቁጥር ቢበዙም ለማዕከላዊ ቴቄል ሠራዊት ቀላል አልሆነለትም። በመሆኑም የውጊያ ስልት በመቀየር ወደ ሚገኙበት ከተማ ሕዝብ እንዲሁም ቅርስ ከባድ መሳሪያዎችን መተኮስ በመጀመራቸው፤ የዞዓር አባላት ከተማዎችን እየለቀቁ በመውጣት የውጊያውን ስፍራ ከከተማ አርቀው ወደ ዱርና ተራራማ ስፍራዎች ወሰዱት። በዚህም ምክንያትነት የቴቄል ሠራዊት ከተሞችን ተቆጣጠሯቸው፤ ሕዝቡ ግን እንቢተኝነቱን መግለጹን ባለማቆሙ ኃይል እንዲጠቀሙ ከላይ ትዕዛዝ በመምጣቱ ያንኑ ተግባራዊ ተደረገ። ህጻናትን እና አዛውንትን መድፈር እንዲሁም ወጣቶችን በየቤታቸው ጭምር በመግባት መረሸን ጀመሩ። ይህ ተግባር እዚያው ሠራዊቱ ውስጥ በአሉ አባላትም ጭምር ተቃውሞ ይደርስበት ጀመረ። ተቃውሞው ብቻ ድርጊቱን ሊያስቆመው አልቻለም፤ ይልቁን ተቃዋሚዎቹን መረሸን ተጀመረ።

ይህም የጦርነቱን ዓላማ ጥያቄ ውስጥ ከመክተትም ባሻገር ሠራዊቱ እየከዱ የዞዓር አባላትን እንዲቀላቀሉ አደረገ። በዚህ ተግባር ይበልጥ ቁጭት ውስጥ የገባው ቴቄል፤ ኃይል ጨምሮ በሙሉ አቅሙ ጦርነት ውስጥ ገባ። ሠራዊቶቹ ግን የሚላኩበትን ስፍራ መልከአ ምድር አያውቁምና በከበባ እንዲሁም በሽምቅ ውጊያ እልፍ የሚሆኑ ረገፉ። የዞዓር አባላትም በድንበር ከሚገባላቸው በተጨማሪ ከእነዚህና ከሚማረኩ ሠራዊቶች ትጥቅ እና

ስንቅ ያሚሉ ጀመር። ማኅበረሰቡ ስንቅ ሲያሚላላቸው ለእናንተ እየታገልን የናንተኑ ጓዳ ማሚጠጥ ተገቢ አይደለምና ስንቅ አታቅርቡልን ብለው ነበርና። ይህ ሁሉ ሲሆን በዋና ዋና የሀገሪቱ መገናኛ ብዙሀን እንዳይወራ ታግዶ ነበር፤ ሀገሪቷም ሰላም እንደሆነችና ጥቂት ወጣቶች ስለሆኑ በቁጥጥር ስር እናውላቸዋለን የሚል ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ለማዳፈን ጥረት ተደርጓል። ዜና አልያም ፕሮግራም ከተሰራበትም የዞኗር አባላት እየተደመሰሱ እንደሆነ እንዲዘገብ ጥብቅ መመሪያ ተላልፎ ነበር። በሀገሪቱ ብዙ ደም ፈሰሰ። ምድሪቷም በሰው ደም ታጠበች።

ጄነራል ሂሶጵ በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች እየተዘዋወረ ለወጣቶች ወታደራዊ ሥልጠና የሚሰጥበትን እና የሚደራጁበትን መንገድ ማመቻቸቱን ቀጥሎአል። በአንደኛው ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በመገኘትም በገፍ ዞኗርን እየተቀላቀሉ ለሚገኙት ወጣቶች ወታደራዊ ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል። መሰረታዊ የሆነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማሰራት ነበር ሥልጠናውን የጀመረው። የመጀመሪያውን ደረጃ ሥልጠና ቁፋሮ እና ወታደራዊ ሥነ ሥርዐት፣ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ፣ የጦር መሳሪያ አያያዝ፣ ወታደራዊ ባህል እና ጨዋነት፣ መሰረታዊ የሰርቫይቫል ችሎታ፣ የአካል ብቃት እና መሰረታዊ ወታደር ለመሆን የሚያበቃቸውን እውቀቶች እንዲሁም ችሎታዎች የሚያስጨብጡ ሥልጠናዎችን በመስጠት ከተያዘለት ጊዜ ገደብ አስቀድሞ አጠናቀቀ ይህ ለአብዛኛው ሠልጣኝ ከባድ ስላልነበረ።

በቀጣይም AIT በመባል ወደ ሚታወቀው የሥልጠና ደረጃ አሸጋገራቸው፤ ይኸውም ለወታደሮቹ ከወታደራዊ የሙያ ልዕቀት ጋር የተያያዙ ልዩ ሙያዎችን ማሳወቂያ ልዩ የሥልጠና ፕሮግራም ነው። አንድ እግረኛ ወታደር የላቀ የጦር መሳሪያ አያያዝን፣ ስልቶችን እና የጥበቃ ዘዴዎችን እንዲያውቅ ይረዳዋል። በመቀጠል ወደ ዩኒት

ሥልጠና ወሰዳቸው፤ ወታደሮቹ AIT ካጠናቀቁ በኋላ በተለምዶ ለአንድ የተወሰነ ክፍል ይመደባሉ። ክፍሉ ለተልዕኳቸው ለመዘጋጀት የሥልጠና ልምምዶችን እንዲቀስሙ ይረዳቸዋል። ይህ የመስክ ሥልጠና የእሳት ልምምዶችን፣ የተግባር መሰናክሎችን እና ታክቲካል ሥልጠናዎችን እንዲያካትት አደረገ። በመቀጠል፤ አልሞ መተኮስ እና የላቀ የአመራር ጥበብን ያካተተ ሥልጠናን ሰጣቸው። በመጨረሻም፤ ወታደሮቹ ወደ ጦር ሜዳ ከመሰማራታቸው በፊት ለሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን የስምሪት ሥልጠና ሰጣቸው። እሱም የባህል ሥልጠና፣ የህክምና ስልጠና እና የሰርቫይቫል ሥልጠናን ያካተተ ነበር።

ይህንም ደረጃ እንዳጠናቀቁ ወደ መጨረሻው ሥልጠናቸው ወሰዳቸው። ይህ ኮምባት ሥልጠና ባለፉት መሠረታዊ ሥልጠናዎች ላይ የተመሰረተውን መሰረት በመገንባት ለጦርነት ሥራዎች በሚያስፈልጉ ልዩ ችሎታዎች ላይ ያተኮረ ነበር። እኚህም የላቀ የጦር መሣሪያ አያያዝ፣ የከተማ ውጊያ፣ የትግል ዘዴዎች፣ ከበባ፤ የምሽት ኦፕሬሽን፤ ቅኝት፤ ወታደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የተሻሻሉ አይኢዲ ፈንጂዎች፣ ካለፉት ጠንከር እና ለየት ያሉ ሰርቫይቫል ጥበቦች፣ የመሸሸ፣ የመቋቋም እና የማምለጥ ቴክኒኮችን በሚገባ አሠለጠናቸው። በመቀጠል ሠራዊት ማሠልጠኑ ጊዜ የሚወስድ እና በዚህ መልኩ ማዳረስ እንደማይቻል ስለተረዳ፤ ከዚህ ቀደምም ሥልጠና እየሰጡ የነበሩ ብቁ ወታደሮች እንዳሉም በማወቁ አሠልጣኞችን ማብቃቱ ላይ አተኮረ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ የቴቄል ሠራዊት እነሱ ወደ ሚገኙበት ስፍራ እየተጓዘ እንደሆነ መረጃ ደረሳቸው። በዚህም መሰረት ስብሰባ ተቀመጡ። በምን መልኩ ማስተናገድ እንደሚኖርባቸው ውይይት ጀመሩ። ከተነሡት ስልቶች አብዛኛዎቹ የተስማሙበት በማይጠብቁበት ስፍራ፤ መንገድ ላይ እያሉ በደፈጣ

እንግጠማቸው የሚለው በመሆኑ፤ ይህን በሚገባ ይተገብራሉ ተብለው የታሰቡ ተመርጠው ተላኩ፤ ከዚህ መሃል ጄነራር ሂሶጵ አንደኛው ነበር።

የቡድኑን አባላይ ሰብስቦ፤ ንጉሥ ዳዊት እልፍ ተዋጊዎች እንደነበሩት ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ከነሱ መሃል ሦስት ኃያላን ወታደሮች ነበሩ። እነዚህ ሶስቱ ኃያላን በታሪክ ከምታውቋቸው ተዋጊዎች እጅጉን ይበልጣሉ። የዳዊት ኃያላን ከነበሩት አንደኛው፤ በአሁኑ አጠራር ጄነራል የሆነ ከነዓናዊው ኢያቡስቴ ነበረ፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ ስምንት መቶ ያህል ፍልስጥኤማውያንን በአንድ ጊዜ ገደለ። በአንድ ጦር። ከእርሱም በኋላ የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ ኤልያናንም ለሰልፍ የተሰበሰቡትን ፍልስጥኤማውያንን በተገዳደሩ ጊዜ ከዳዊት ጋር ከሦስቱ ኃያላን አንዱ እርሱ ነበረ፤ እጅግ ኃያል ጦረኛም ነበር። የእስራኤልም ሰዎች በፍርሃት ተመለሱ። እርሱ ግን ተነሥቶ እጁ
እስኪደክምና በፈሰሰበት ደም ብዛት ከሰይፉ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ፍልስጥኤማውያንን መታ፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ታላቅ መድኃኒት አደረገ፤ ሕዝቡም ከእርሱ በኋላ ምርኮ ለመግፈፍ ብቻ ተመለሰ። ይሄን ከእናንተ እጠብቃለሁ ዛሬ። ኣይጥ የገደለ ዝሆን ጀግና ኣይባልም!

በስፍራው እንደ ደረሱ ለደፈጣ አመቺ የሆነን አከባቢ መርጠው አድፍጠው መጠበቅ ጀመሩ። ሂሶጵ ስፍራውን በሚገባ መቃኘት በመፈለጉ እንዲከተሉት አምስት ልጆችን በመጥራት ቀሪዎቹ በአሉበት አድፍጠው እንዲጠብቁ አድርጎ ቅኝቱን ቀጠለ። ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ፤ አንድ ቦታ ቀጥ ያለውን ተራራ እየወጡ፤ በሌላ ቦታ አዳጋች የሆነውን ሸለቆ እየወረዱ። ከቆዩ በኋላ ሂሶጵ እንደደረሱ መልዕክት ስለ ደረሰው በፍጥነት ወደ ስፍራው ተመለሱ።

በዚህ መሃል ጄነራል ሂሶጵ ለመፍጠን ሲሞክር እግሩ በሁለት ድንጋዮች መሃል በመግባቱ ህመም ስለተሰማው ጮኸ። ተረባርበው እግሩን ሊያወጡለት ሲሞክሩ፤ አጥንቶቹ ተላቀው፤ የተሰበረው አጥንቱ ቆዳውን በስቶ እንደወጣ ሲመለከቱ፤ አንደኛው በቆመበት አስመለሰው። ሁለቱ ግን ሁለቱን ድንጋዮች አንከባለው ከተቀበሩበት ለማውጣት መቆፈር ጀመሩ። ቀሪዎቹ ሁለቱ፤ ጨርቅ በመቅደድ ጠመጠሙለት፤ እጆቹንም በመያዝ አነሱት። ከቆፋሪዎቹ አንደኛው ጀርባው ላይ ተሸከመው። መንገዳቸውንም ቀጠሉ። ሂሶጵ ግን እንቅስቃሴ በነበር ቁጥር ህመም ይሰማው ነበር። ቢሆንም እነሱንም ላለመረበሽ በውስጡ ያዘው።

እየቀረቡ ሲመጡም ከባድ የተኩስ ልውውጥ መሰማት በመጀመሩ፤ አመቺ ከፍ ያለ ስፍራ በመምረጥ እሱን እዚያው ትተውት እንዲሄዱ አሳሰባቸው። እንደዚያውም አድርገው፤ ውጊያውን ተቀላቀሉ። ጄነራል ሂሶጵ ከዚያው በመሆን፤ የያዘውን 1 ሜትር ከ27 ሴንቲ ሜትር በመርዘም፣ 6.9 ኪሎ ግራም የሚመዝነውን እንግሊዝ ሰራሽ፤ Accuracy International AWM የረጅም ርቀት ተኳሽ ጠብ'መንጃ ወደ ቴቄል ሠራዊት አቅጣጫ በማዞር አነጣጥሮ ለመተኮስ ተዘጋጀ። ይህ ጠብ'መንጃ 936 ሜትር በሰከንድ እየተወነጨፈ እስከ 1.5 ኪሎ ሜትር እንደ ሚምዘገዘግ ያውቃል።

ከአሁን ጀምሬ አከታትዬ የምተኩሰው ጥይት የወንድሞቼ ግንባር ላይ እንደሚያርፍ አውቃለሁ። ግን ምንም አማራጭ የለኝም። ዐይኖቼ እያነቡ ጣቶቼ ግን ቃታውን ይስቡታል። አንቺ ጠብ'መንጃ አንቺና ጓደኞችሽ ከተመረታችሁ ጀምሮ፤ ከአፍጋኒስታን እስከ ኢራቅ የራሺያንና የዩክሬንን ጨምሮ ብዙ ጦርነትን ዐይታቹኻል፤ አሁን እንደ ለመድሺው የባእድ ያልሆነ፤ ወንድም ወንድሙን ሲገድል በታሪክ የሰማሺውን ቃኤል አቤልን

እንደገደለ፤ አሁን ሂሶጵ ወንድሙን ብቻ ሳይሆን ወንድሞቹን ሲገድል ትታዘቢያለሽ በማለት አፈሙዙን ስሞ አነጣጠረ።

የመጀመሪያውንም ጥይት ሠራዊቱን የጫኑትን ተሽከርካሪዎች ከሚያሽከረክሩት አንደኛው ግንባር ላይ ተኮሰው። ስፍራው ገደላማ በመሆኑና መሪውም የሚቆጣጠረው በማጣቱ ከነጫናቸው ሠራዊት ወደ ጥልቁ ገደል ተፈጠፈጠ። መንደድም ጀመረ። ጄነራል ሂሶጵም ይህን በተደጋጋሚ ማድረግ ጀመረ። ይህን የተመለከቱት ሾፌሮችም እያለቁ መሆኑን ስለተገነዘቡ፤ ወታደሮቹ ወጥተው እንዲታኮሱ በመንገር፤ ተሽከርካሪዎቹን በአሉበት ማቆም ጀመሩ። አስፓልቱም ጠባብ በመሆኑ፤ እንዲሁም በሁለቱም ጎን ከገደሎቹ ባሻገር ባሉ ተራሮች የዞሳር ታጋዮች በመኖራቸው፤ የቴቄል ሠራዊቶች አጣብቂኝ ውስጥ ወደቁ። ውስጥ ያሉትም ከሚተኮስባቸው ጥይት ማምለጥ ባለመቻላቸው፤ ከተሽከርካሪው በግራም በቀኝ ሲወጡም እንደዚያው መትረፍ አልቻሉም። በዚህ መልኩ ለመቁጠር እስኪያዳግት እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሠራዊቶች ረገፉ። የቀሩት ጠብ'መንጃቸውን በሁለት እጆቻቸው ከጸገራቸው በላይ ከፍ በማድረግ እጅ ሰጡ።

ይሄን ጊዜ ጄነራል ሂሶጵ በደስታ ጮኸ። መጀመሪያ ለምን እንደዚህ አደረጋችሁ? ለምን ይህ ሁሉ ጥፋት እስኪደርስ ጠበቃችሁ? እያለ ከዐይኖቹ የሚወርዱትን እንባዎች በመዳፉ ጠረገ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ እጅ የሰጡትን ሠራዊቶች ትጥቅ እያስፈቱ፤ የወደቁትን መሰብሰብ ጀመሩ። ጄነራል ሂሶጵንም ለአራት ሆነው ሁለት ረዣዥም ማዕገር በመቁረጥ አጋድመው በልጥ አስረው እሱ ላይ በማስተኛት አመጡት። የረገፉትን ሠራዊቶች ሰብስበው ለመቅበር ተዘጋጁ።

የተማረኩትን ሠራዊቶች ጀነራል ሂሶጵ ጥያቄ መጠየቅ ጀመረ። እነዚህን ጥያቄውች እንድትመልሱልኝ እፈልጋለሁ። ይሄ ሁላ እየሆነ እያያችሁ ለምን ዝም ትላላችሁ? ይባስ ብላችሁ ሕዝቡን ለመውጋት አፈሙዝ ትደቅኑበታላችሁ። በፊት ረብሽ አልያም አመጽ ተነስቶ፤ እናንተ ስትመጡ ሕዝቡ እጅግ ድስ ይለው በደስታም ይቀበላችሁ፣ ያከብራችሁም፣ ይታዘዝላቹም ነበር። አሁን እናንተንም እንደሌሎቹ ማየት ጀምሮአል። ለምን ይመስላችኋል? ሌላ ከመጠየቄ በፊት እኚን መልሱልኝ አላቸው። ሁሉም ለማለት በሚቻል ሁኔታ ከሦስት ወር ያነሰ ሥልጠና ብቻ ተሰጥቶአቸው ወደ ውጊያ የተላኩ፤ ከገጠሪቷ የሀገሩ ክፍል በአፈሳ የተሰበሰቡ፤ የተለያዩ የመጡበትን አከባቢ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩ ወጣቶች ነበሩ። እድሜአቸው ከዐሥራ ስምንት በታች የሆኑ ለአቅመ አዳም እንኳን ያልደረሱ ይገኙበት ነበር። ጥቂት መግባባት የሚችሉትም ሲያወሩ፤ የት እንደሚሄዱ እና ከማን እንደሚዋጉ ጭምር መረጃው የሌላቸው፤ ሀገር ተወረረች ጠላትን ውጉ ብቻ ተብለው እንደተላኩ ማወቅ ተቻለ። ጀነራል ሂሶጵም ይህን በመረዳት ጥያቄውቹን በማቋረጥ ወደ ቀብር ሥነ ሥርዓቱ እንዲያመሩ አዘዘ። የቀብር ሥነ ሥርዓቱም ላይ አብዛኛው የዞሳር አባላት ከልባቸው በመነጨ ሀዘን አለቀሱላቸው። ቀበሯቸውም። ሂሶጵም ወጣት አይበርክትልሽ ብሎ ይህቺ ሀገር የረገማት ማነው? ብሎ ድምጹን አሰምቶ ጮኸ።

⁘⁘⁘

በሚመስል ክብ መድረክ ከፊት መሆኑ፤ እንዲሁም የመጋረጃዎቹ እና የምንጣፉ ሀምራዊ ቀለም የስብሰባ አዳራሽ ሳይሆን ቅንጡ ሆቴል የገባ እንዲመስለው አድርጎት ነበር። ኤፍሮን ትከሻውን በመንካት ወደ ተዘጋጀለት ወንበር እንዲያመራ በእጁ እየጋበዘችው ወደድኸው አይደል? ይሄን ዲዛይን የነደፈችው እንደምታደንቃት የምታወራላት አርክቴክት ናት፤ አልተከፈላትም ግን አለችው። ለድርጅቷ እሺ ተቀባይነት ይኖረዋል። የግዙፍ ፕሮጀክቶችን ንድፍ ያለ ክፍያ የሚነድፉ እንዳሉ አውቃለሁ። ይሄ ልክ አይመስለኝም፤ በግርማዊነታቸው ጊዜ 8% በመንግስቱ ጊዜ 5% የፕሮጀክቱን ኮስት ይከፈላቸው እንደ ነበረ መረጃው አለኝ አሁን የተቀመጠ standard እንደሌለ አውቃለሁ። ዲዛይን አምስት የተለያዩ ደረጃዎች አሉት ያን ሁሉ አልፈው ዋጋ ሲያወጡ ውድ ነው በሚል ውድቅ ይድረግባቸዋል። በዚህ ትግል ውስጥ እያለፉ ያለ ዋጋ? I think this is purely unethical! መልስ አልሰጠችውም ከደቂቃዎች በኋላ ስብሰባው ተጀመረ።

ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ፣ ዶ/ር አጽሎስ፣ ኢንጂነየር አሚናዳብ፣ ፕሮፌሰር ናኮር፣ ዶክተር ወልደአብ፣ ፕሮፌሰር ቤርሳቤህ፣ ጄነራል አሮን እና ዶክተር ዛሪየስ በየተመደቡበት ሚኒስተር መስሪያ ቤት ውስጥ ሲያከናውኑት የከረሙትን የጥናት ውጤት ለዞዓር የላይኛው ምክር ቤት ማቅረብ ከመጀመራቸው በፊት በየተራ አጀንዳዎቻቸውን ማቅረብ ጀመሩ። የመጀመሪያው እድል ለፕሮፌሰር ቤርሳቤህ ተሰጠ።

ፕሮፌሰር ቤርሳቤህ አባተ በማመስገን ጀመረች። እንደምታውቁት እኔ የተረከብኩት የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስተር፤ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ፖሊሲዎችን ሲያረቅ ከርሞአል። አብዛኛዎቹ መሻር ያለባቸውና የሚሻሩም ይሆናሉ! ይህን ለምን

እንዳልኩ ከማስረጃ ጋር አቀርባለሁ ብላ የከቡን አዳራሽ ግማሽ ሊሸፍን ጥቂት ወደ ቀረው በሷ ጀርባ፣ ለታዳሚዎቹ ግን ከፊት ወደ ሆነው ስክሪን ዞራ በእጇ በያዘችው አጭር ሪሞት ሰነዶችን መግለጥ ጀመረች። ይህ መስሪያ ቤት በድጋሚ በአዋጅ ቁ. 471/2005 ከተደራጀና የከተማ ልማቱን አግልሎ በምትኩ ሌሎች ሥልጣናትና ተግባራት ከተሰጡት በኋላ፤ በ2009 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 641/2009 ሚኒስተሩ፤ የሃይማኖት ጉዳዮችን የማስተናገድ ተጨማሪ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶት፤ በተጨማሪም ሚኒስተር መስሪያ ቤቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባና የጦር መሳሪያ፣ የእሳት አደጋ መሳሪያና ፈንጂዎችን መያዝ ወይም መጠቀምን በሚመለከት፤ በፌዴራል ደረጃ ተገቢውን አፈፃፀም የማረጋገጥ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 691/2010 በድጋሚ ተሰጠው።

ታዲያ እኚህ ሥልጣናት ለግጭት አፈታቱ እና ሰላምን ለማስፈን ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ቢሆኑም፤ ቢሮው ግን በተለያየ ሥም እና ተግባር ሽፋንነት በሚመጡ አካላት የሚዘወር በመሆኑ፤ ለገጠሩ ዜጋ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ አይሎ ታይቶኛል። በተለይ ሃይማኖት እና ባህል መበረዝ ቋሚ ተግባራቸው ሆኖ ያገኘሁበትን በጥልቀት ካልተመረመረ አጨብጭበው እንዲቀበሉት በሚያደርግ መልኩ እየተተገበረ ያለን አዋጅ፤ በነማን እንደሚዘወር እንዲሁም ማን እንዲመሰረት እንዳደረገ ነው በስክሪኑ ላይ የምትመለከቱት። ሚኒስተሩ፤ አርብቶ አደሮች ከተለዋዋጭ የአየር ንብረት ሁኔታዎች ጋር እንዲላመዱ ለመርዳት፤ ዘመናዊ የአርብቶ አደርነት ልምዶችን ሲያበረታታ ቆይቷል። ይህ ለድርቅ መዘጋጀት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ የእንስሳት ዝርያዎች እና የተሻሻለ የከብት እርባታ አያያዝን ይጨምራል። ምን ያህል ነውጥ አመጣ? የሚለውን ለእናንተ እተወዋለሁ። ይህም የእህል፤ የጥራጥሬ እና የእንስሳቱን ተፈጥሮአዊ

DNA በመለወጥ የሚሠራ ሥራ ነው። በዚህ ዙሪያ የምለው ብዙ ቢኖርም ያለ አግባብ ሰዓት ላለመውሰድ እዘለዋለሁ፤ ወድሜ ዶክተር ወልደአብ ይሄድበታል ብዬ ስለማስብ።

በ2018 ኤፕሪል ወር የHuman Rights Watch Africa Division, Executive Director ለዚህ መስሪይ ቤት ሚኒስተር የላኩትን ደብዳቤ ተመልከቱት። በተለምዶ ጂል ኡጋዴን እየተባለ ስለ ሚጠራው ማረሚያ ቤት ነው። የሶማሌ ክልል ልዩ ፖሊስን ጨምሮ ከ80 በላይ ቃለ መጠይቆች ከቀድሞ ታሳሪዎች፣ የፍትህ አካላት፣ የክልል እና የአካባቢ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት እና የጸጥታ አካላትን ጨምሬ ጥናት አድርጊያለሁ። ይህም ጥናት ከ2011-2018 G.C መካከል ያሉትን ክስተቶች ይሸፍናል ይላል። በጥናቱ የተካተቱትን ደግሞ ተመልከቱ። ባደረግነው ጥናት ይላል፤

1ኛ. የመንግሥት የጸጥታ አካላት ከባድ ማሰቃየት እና እንግልት እንደሚፈጽሙ ማረጋገጥ ችለናል።

2ኛ. አብዛኛዎቹ እስረኞች ከባድ የፍትህ ሂደት ስጋቶች አሉባቸው።

3ኛ. የልዩ ኃይል ፖሊስ ከ2013 G.C ጀምሮ ለመዘገብናቸው የአብዛኛዎቹ የሙበት ጥሰቶች ተጠያቂዎች ናቸው።

4ኛ. ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል የጤና እንክብካቤ እጥረት አለ። ምግብንም ጨምሮ። ይልቁንም እኚህን ማግኘት እንደ ቅጣት የተገደበ ነው።

5ኛ. የቤተሰብ አባላት ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው እንዲጠይቃቸው አይፈቀድም።

6ኛ. ከክልላዊ መንግሥቱ የማረሚያ ቤት ጠባቂዎች አገኘሁት ባለው የቪዲዮዎች መረጃ ታራሚዎች ላይ ሲወሰዱ

የነበርቡ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን፤ በተለያዩ የማሰቃያ መንገዶች ታራሚዎች የመብት ጥሰት እንደሚደርስባቸው አረጋግጫለሁ። ከተጠቂዎችም ከምስክርነት ጋር አስገድዶ መድፈር እንደነበረ አረጋግጫለሁ።

7ኛ. አብዛኛዎቹ እስረኞች ፍርድ ቤት የመቅረብ እንኳን እድል እንደ ማይሰጣቸው ተረድቻለሁ ይላል።

ይህ ጥያቄዎችንም ያካተተው ደብዳቤ ተጨማሪ ጥያቄዎችንም አካቶ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንም እንዲደርስ ተደርጓል። በዚሁ ዓመት በተደረገ ሌላ ጥናት ደግሞ፤ ያለፉት የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲዎች ሕዝቡን፤ ማኅበራዊ ሥርዓቶቻቸውን፤ እንዲሁም የሥነ-ምህዳር ክፍልን ችላ በማለት በሸቀጦች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው፤ ከማኅበረሰቦች ጋር ያልተዋሃዱና አሁን ያለውን የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም ማኅበረሰቡ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ችላ ያሉ ስለ ነበሩ ውጤታማ አልነበሩም። የሚል አንድምታ ያለው ጥናት ይፋ ሆኖ ነበር። በስክሪኑ ላይ የማመጣላችሁን ምስሎች ተመልከቷቸው። A picture is worth a thousand words ይባል አይደል? በእነዚህ ምስሎች አበቃለሁ፤ የተቀረውን ከሰነዶቹ ተመልከቷቸው። አመሠግናለሁ።

በመቀጠል የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚንስተር ዶክተር ወልደአብ ወልደማርያም መድረኩን ተረከቡ። አመሰግናለሁ እኔ ደግሞ ዩኒቶችን ከማሳየት ልጀምር፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያረፈችው በ113,625.7692 ሄክታር ላይ እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ ውስጥ

112,930.4039 የሚሆነው ላንድ ኤሪያ ነው፤ 37,332 ይህ ደግሞ በግብርና የተያዘው መሬት ነው፤ 17,360.5 ይህን ያህል ሄክታር ደግሞ ደን ነው። እኚህ ቁጥሮች እጃችን ላይ ያሉ መለኪያዎቻችን ናቸው። ልክ ናቸው? መልሱን ለእናንተው ልተወው። ግብርናንስ ያሻሸላል ተብሎ በ1907 በአፄ ምኒልክ ዘመን የተቋቋመ ድርጅት ሀገሪቷ ውስጥ እያለ እንዴት በዚህ ዘመን መርዳት ቢያቅተን እራሳችንን መመገብ አቃተን? ያለፉት መርዳትም ደረጃ ደርሰው እንደ ነበር ግልጽ ነው። እንዴት በዚህ ዘመን ስንዴ እንለምናለን? ይህ እኮ ውርደት ነው! አንገት ያስደፋል።

የማኅበረሰቡን እድሜ በቁጥሮች ላቅርብላችሁ

14.6 % ከ0-4

20.0 % ከ5-12

11.3 % ከ13-17

14.1 % ከ18-24

15.7 % ከ25-34

10.3 % ከ35-44

6.6 % ከ45-54

4.3 % ከ55-64

3.2 % ደግሞ ከ65 በላይ ነው።

ይሄ የሚያሳየን የታዳጊዎች እና የወጣቱ ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ነው። አማካኝ እድሜ 18.9 ይሆናል። ይሄን ቁጥር ይዘን ነው ለማኝ የሆነው! ያሳፍራል!

ለውጥ ከሕንጻ አይጀምርም! ለውጥ እራስን ከመቻል እንጂ። እናቱ ቤት ቁጭ ብሎ ሕንጻ የሚገነባ የለም እንኳን ባዳ ቤት ተጠግቶ። በምግብ እራሳችንን ሳንችል እድገት ምን የሚሉት አለማወቅ ነው? ድህነት የሚጠፋው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ሲቻል ነው። ይህን ደግሞ አላሳካንም። ይህ የሆነው በዋናነት የሚመሩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ባለመኖራቸው ነው። የሥራ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እጥረት በግብርናው ዘርፍ አጠቃላይ ውድቀት አስከትሏል። የግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪያላይዜሽንም ያመጣው እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ የለም።

አሁን ያደጉ የምንላቸው ሀገራት አባዜ ስላለቀቀን እነሱ እንኳን በፍጹም ሕዝባችን ዘንድ እንዳይደርስ ብለው በፖሊሲ ጭምር የተቃወሙትን Genetically Modified Organisms እኛ በአዋጅ ተቀብለነዋል። እስካሁን ሀያ ስድስት ሀገራት፤ ሀገራቸው እንዳይገባ ከልክለዋል ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ቻይና፣ ራሺያ፣ ህንድ፣ ኦስትሪያ፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ኔዘርላንድስ፣ ላቲቪያ፣ ሊትዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ቡልጋሪያ፣ ፖላንድ፣ ዴንማርክ፣ ማልታ፣ ስሎቬኒያ፣ ጣሊያን እና ክሮኤሺያን ጨምሮ ማለት ነው።

ለምን እነሱ ከለከሉት? እኛስ ልንቀበል ፈቀድን? እኛ የተረዳነው እነሱ ያልተረዱት ስላለ? አይደለም። የእነሱ ባለ ሥልጣናት ሁሉም ባይሆኑም ለሕዝባቸው ደህንነት ስለ ሚጨነቁ ነው። ለመጪውም ለወጣቱም ዜጋ ግድ ስለ ሚላቸው ነው። እኛስ? ወደ ፊለግንበት ሀገር ቪዛ አይከልክሉን፤ ገንዘባችንን ስዊዝ ባንክ አሁን ደግሞ

ማልታ እንድናስቀምጥ ይፍቀዱልን፤ ልጆቻችንን ሀገራቸው ወስደው ያስተምሩልን፤ ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም አይወንጅሉን፤ ስለ ሌላው ምን ገዶን! GMO እንደሚሉት nutritional value ከተፈጥሮው ከተሻለ ለምን ይህ ሁሉ ይከሰታል? ይህን ፕሮጀክት በዋናነት የሚቆጣጠሩት ሁለት ድርጅቶች ናቸው። ትኩረታቸውም ታዳጊ ሀገራት ናቸው። እነሱን መቆጣጠር ስለ ሚፈልጉ። አዳዲስ ፖሊሲዎች ሲረቁ፤ ይህን አልገዛም፤ ይህን አልቀበልም፤ ይህንም አልተገብርም ማለት ለታዳጊ ሀገራት አስጨናቂ ነው፤ ቅጣት አለውና።

ይህን ያለችው ሀገር ብድር ከIMFም ሆነ ከWorld bank አይለቀቅላትም። በተጨማሪም ያለባትን በአፋጣኝ እንድትከፍል ትገደዳለች፤ ንብረቷንም እንድትሸጥ አልያም እንድታጋራ ግድ ስለሚሆን፤ የሚኖራት አማራጭ የተባለችውን መቀበል ይሆናል። ገበሬው ዘሩን ከገዛ በኋላ ለሌላ ገበሬ አሳልፎ መስጠት አልያም ማጋራት አይችልም። በሕግ ያስቀጣል። ናይጄሪያ ውስጥ እየሆነ ያለውን መመልከት በቂ ነው። ሌላኛውም ገበሬ ዘሩን ገዝቶ ነው መጠቀም ያለበት። የፈጠራ ባለቤትነት ያላቸው የGMO ዘሮች ሁሉም በአእምሯዊ ንብረት ደንቦች የተጠበቁ ናቸው፣ ይህም ማለት ገበሬዎች እንደ ማይቆጥቡአቸውና እንደገና ላለመትከል ቃል መግባት አለባቸው። ሞንሳንቶ በመባል የሚታወቀው ኮርፖሬት፤ እነዚህን ደንቦች ጥሰዋል ያላቸውን ወደ 150 የሚጠጉ ገበሬዎችን ክስ መስርቻለሁ ብሏል። ከአንድ የምርት ጊዜ በላይም መጠቀም አያስችልም። ይህን የለመደ መሬት ደግሞ የተፈጥሮን ዘር አይቀበልም። መሬቱም ቢሆን ማዳበሪያን ከለመደ ወደ ኋላ ለመመለስ ይከብዳል። GMO ብዙ ፀረ ተባይ መድኃኒቶችን ይጠቀማሉ ምን ማለቴ እንደሆነ ይታወቃል፤ በውስጣቸው የሚይዙትም ንጥረ ነገር አጠያያቂ ነው።

የእኛ ገበሬዎች እጅስ ቢሆን ያለው ዘር የተፈጥሮ ነው ወይስ በተለያየ መልኩ ሞዲፋይ የተደረገ ነው? አብዛኛዎቹን የእህልም ይሁን የጥራጥሬ አልያም የፍራፍሬ ዘሮች ተመልከቷቸው፤ የምናውቃቸው ያደግንባቸው አይደሉም። ካሮት ጥሬውን የሚኮረሽም የነበረ አሁን ለዐይን የጠላ ሰው ያጋጥማችኋል ለምን? ስትሉት ውሃ ውሃ ይላል ይሆናል መልሱ። ኦርጋኒክ የሆኑትን ዘሮች ሰብስበው አንድ ስፍራ አከማችተዋቸዋል። ስፍራውም Svalbard በመባል ይታወቃል፤ በዓለም ላይ ካሉት ሰሜናዊ አካባቢዎች አንዱ፤ በዋናው ኖርዌይ እና በሰሜን ዋልታ መካከል ያለ የኖርዌይ ደሴት ሲሆን እጅግም ቀዝቃዛ ነው። እኚህን ኦርጋኒክ ዘሮች በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ጥበቃ ነው የሚያኖሯቸው። የኛዎቹ በአብዛኛው አሁን ተበርዘዋል። ጤፍን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል። እንጀራ ጠቃሚ ኑትሪሽን እንደሌለው ሊነግሩን ይፈልጋሉ እንድንጥለው አንስተው ሊደምቁበት፤ ኦልሬዲ ለጤፍ ፓተንት ተቀብለዋል። በምትኩ የአኩሪ አተርን ጠቃሚነት ይነግሩናል ወዳጆቼ አኩሪ አተር ትውልድ ልምሻ የሚያደርግ መርዘኛ ነው።

የዘረ መል ማዳቀል ቴክኒክ በዚህ ብቻ አያበቃም፤ በቅርቡ የተፈጥሮ የሴትን እንቁላል በማቀዝቀዝና በማባዛት፣ ከወንድ ዘር ጋር በመደባለቅ፣ ሰው ሰራሽ ማዕጸን ሰርተው፤ ጽንስ ማሳደግ እንደተቻላቸው የሚገልጽ የጥናት ወረቀት ታትሞ አንብበናል። የተለያዩ እንስሳት ዝርያ በማዳቀል ልዩ ዘር እያዋለዱ እንደሆነ ታውቃላችሁ። ስለዚህ አዲስ አስተሳሰብ እና ፖሊሲ ያስፈልገናል! ብድር የሚያስገኝልን ሳይሆን ወገናችንን የሚጠቅም። ከተረጂነት ጉብጠት ፈውሶ ሙሉ ሰው የሚያደርግ ፖሊሲ እንነድፋለን እያደረግነውም ነው። አመሰግናለሁ።

የፍትህ ሚኒስተር ዶ/ር አቋሎስ ለይኩን ወደ መድረክ ወጣ። ወንድሜ ዶክተር ወልደአብ፤ በምግብ እራሳችንን ሳንችል እድገት ምን የሚሉት አለማወቅ ነው? በማለት የጠየቀውን ጥያቄ ሁላችንም ልንመልሰው የሚገባን ጥያቄ ነው። ሥራን እንዲጸየፍ፤ በአቋራጭ መክበርን እንደ ስልጣኔ እንዲቆጥር፤ እኔ ብቻ እንዲል፤ ስንፍናን፣ ዝንጉነትን እየተጋተ ያለን ማኅበረሰብ ይዘን እንዴት ስለ ከፍታ ማውራት ይቻለናል? የሚል ጥያቄ ደግሞ ተፈጠረብኝ። ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች ስትመለከቱ፤ የዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ምክንያት ምንድነው? ብላችሁ እንድትጠይቁ ትገደዳላችሁ። እኔ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ ያገኘሁት የትምህርት ሥርዐቱን ነው። ፕሮፌሰር ናኮር በሚገባ ይሄድበታል ብዬ አስባለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሲፕሊን የሚባል ነገር ጠፍቷል። ከሊቅ እስከ ደቂቅ ልቦናችን ውስጥ ሕግ እና ሥርዐት ተነቅሎ ወጥቶአል። የሃይማኖቱን ሕግጋት ጠብቆ የሚኖር ሰው ታገኛላችሁ? ምእምን ይቅር የሃይማኖት መሪዎችስ ይህን ያደርጋሉ? አትስረቅ ብሎ የሚያስተምር አይሰርቅም? አታመንዝር የሚል አያመነዝርም? አትግደል የሚል አልገደለም? ሕግ አክብር የሚል ሕግ አልጣሰም? ምንም እንኳ ከሁለቱም ወገን የነጠሩ ቢኖሩም።

ሕገ ወጥነት በራሱ ሕጋዊ ሽፋን እንደሚሰጠው ስንቶቻችን እናውቃለን? የሚወረወርልን narrative ግን እንድንደግፈው ያደርገናል። ሀገሪቷ ውስጥ በሕጋዊ ሺፋን ምን ሲሰራ መሸቶ እንደሚነጋ የምታውቁት ነው። dark web በማን እንደ ተመሰረተ እኔ በሚገባ አውቃለሁ። የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን፣ ድራጎችን፣ ህገ ወጥ የሰው ዝውውር፣ የተለያዩ የሰው የአካል ክፍሎች ልብ እና ኩላሊትን ጨምሮ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮችም፤ በአጠቃላይ ሕገ ወጥ የሆኑ ማናቸውም በግልጽ የሚገኙበትና በቀላሉ መገበያየት የሚቻልበት የኢንተርኔት ክፍል ነው። ማንኛውም ተጠቃሚ ወደ ውስጥ ለመግባት

መጀመሪያ anonymous ip መጠቀም ይኖርበታል። ከብሮውሰሮቹ ዋነኛውም tor በመባል ይጠራል። ይሄ ቴክኖሎጂ በመጀመሪያ በማን እጅ ብቻ ይገኝ ነበር መሰላችሁ፤ በአሜሪካን naval research ቢሮ ለወታደራዊ አገልግሎት ብቻ ጥቅም ላይ ይውል ነበር። ይሄን የቴክኖሎጂ ውጤት በመጠቀም ነው የተለያዩ ወንጀሎች በገሀድ የሚፈጸሙት። እኚህም ግብይቶች የሚከናወኑት በቢትኮይን ነው። ለምን ካላችሁኝ በባሕላዊው ገንዘብ ከተገበያዩ ዱካቸውን አነፍንፈው ይደርሱባቸዋል። ይሄ ሳይመጣም በፊት፤ በዚህ መንገድ ብዙ ወንጀለኞች ዘብጥያ ሲወረወሩ ከርመዋል።

አሜሪካን ቲክ ቶክ የተባለውንስ የማሕበራዊ ትስስር ፕላትፎርም ካልዘጋሁት ሙቼ እገኛለሁ፤ ካልሆነ ለእኔ ስጡኝ የምትለው ለምን ይመስላቹሃል? ፕላትፎርሙ ትርክቷን እርቃኑን እያስቀረው ስለሆነ ነው። የዓለም narrative blueprint በአሜሪካ ነው የተነደፈው፤ ይሄ ደግሞ የኃይሏ ምንጭ ነው! የእሱ ተቃራኒ የሆኑትን narratives ሁሉ እንብርት እንደ ሌለው የተራበ አውሬ ሲዘነጥል የኖረ ነው። አሁንም በተቻለው መጠን በቀንዱም በጥርሱም በጥፍሩም ተቃራኒ ያለውን ሲያጠቃ ይኖራል። ምክንያቱም አሁን ዓለም የምትጓዝበት ትርክት ከተገለበጠ ያኔ ታላቋ ባቢሎን ወደቀች የሚለው ትንቢት ይፈጸማልና፤ ይሄ እንዲሆን ደግሞ አትፈቅድም። ዘመናዊነት የእሷ ብቻ ነው፤ የእሷን ፈለግ ተከትሎ የማይጓዝ ኋላቀር ነው። ይሄ narrative ትላልቅ የተባሉ የዜና ማሰራጫዎችን እንዲሁም የህትመትን ጨምሮ የተለያዩ ሚዲያዎችን የሚጠቀም የቃል፣ የሀሳብ ኒውክለሯ ነው። ማንም እንዲነካባት አትፈቅድም። ታጠፋዋለች! መሸቶ በነጋ ቁጥር አዲስ ሃይማኖት መፈልፈል፤ ሰዶማዊነት፣ ጾታ መቀየር፣ ወንዱ ሴት ሴቷ ወንድ መሆን፤ አንቺ ወይም አንተ ብሎ የገዛ ልጅን መጥራትን በሕግ መከልከል፤ ሁሉን ሽሮ አዲስ የዓለም

ሥርዐት መትከል። እነዚህ በነጻነት እና በመብት ሥም ይከወናሉ። ነጻነት ድንበሯ የት ነው? ለእሷ ሲጠቅማት ሕግ ይከበራል፤ ካልሆነ ይቀየራል። አሜሪካ የማይተማመኑባት ሰላላ እና ወስላታ ናት። dark web, tor, bitcoin አሁን ነጥቦቹ እየተገጣጠሙላችሁ ነው?

ወደ እኛ እንመለስ፤ ሙስና እና ስርቆት ምን ያህል ተስፋፍቶአል የሚል ጥያቄ አሁን እርባና ቢስ ነው። ምክንያቱም አሁን ሥራ ስለሆነ። ሕዝቡም ለምዶታል። ይሄን ድርጊት ለማስቆም በ1900 የፍትህ ሚኒስተር በመሆን የተሾሙት አፈ ንጉሥ ነሲቡ ብዙ ርቀት ተጉዘው ነበር። በወቅቱ አዲስ አበባ ውስጥ ሌብነት በርክቶ ስለ ነበር፤ ክስተቱን ለመቆጣጠር፤ ግርፋት ብቻውን በቂ ሆኖ ስላልተገኘ፤ በተደጋጋሚ ወንጀል ሲሰሩ የተገኙ ግንባራቸውን በጋለ ብረት እንዲተኮሱ ያደርጉ ነበር። የሚያያቸው እንዲጠነቀቅ። በዚህ ግን ሁኔታውን መቆጣጠር አልተቻለም። ይልቁንም ወንጀለኞቹ፤ ግንባራቸው ላይ እንደ ሚኒልክ ሻሽ መጠምጠም ጀመሩ። በዚህ የተቆጡት አፈ ንጉሥ ነሲቡ፤ ብረቱ የ"ፕ"ን ቅርጽ እንዲይዝ እና ከግንባራቸው ግራና ቀኝ ተነስቶ እስከ አፍንጫቸው እንዲወርድ አደረጉ። ፍትህ እንዲኖር ሕግ እና ሥርዐት እንዲከበር ማኅበረሰቡ የሰላም ኑሮ እንዲኖር አፈ ንጉስ ነሲቡ እዚህ ድረስ በመራቅ ተጉዘዋል።

ጠበቃው፣ ዶክተሩ፣ ባለ ሥልጣኑ፣ ነጋዴው፣ የቢሮ ሠራተኛ፣ ፖሊሱ፣ ኢንጂነሩ፣ ዳኛው፣ መምህሩ፣ ተማሪው፣ ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ ሴቷ፣ ወንዱ፣ ህጻናት ይህ ሁሉ በሕግ ይመራል? እንደ ልቡ የሚመላለስ አልበዛም? በሙሉ አቅማችን ታዳጊዎች ላይ ነው ትኩረታችን! ምን ያህል ለሚገባው ምግብ ምን ያህል እንጠየቃለን? የቤት ኪራይ እና ግብር የመሳሰሉት ወጪዎች ስላሉበትና ማትረፍ ስለሚገባው? ማትረፍን

ምን መስፈርት አውጥተንለት? እርግጥ ነው ያን አፎርድ የሚያደርጉ ሌግዠሪ ሕይወት መኖር ለሚፈልጉ በልዩነት የሚሰሩ ቤቶች የተለመዱ ናቸው። አብዛኛውን ነዋሪ በሚያስመርር መልክ ሁሉም እንደዚያ ሆነው ነው? ከታች ጀምሮ እየተያያዘ ነው የሚመጣው ይሄ ጉዳይ። ነጋዴውም አገልግሎት ሰጪውም የማኅበረሰቡ አንድ አካል በመሆናቸው፤ ዋጋ ሲጨምሩ ቁሱን የሚገዙበትን፣ የሚያጓጉዙበትንና የሚያወጧውን ወጪዎች ታሳቢ በማድረግ ትርፉን አስልተው የዋጋ ተመን ያወጣሉ። አይደል እንዴ? ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ በማለት በፈገግታ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስተሩን ጠይቆ ቀጠለ፤ ይህ ተፈጥሮአዊም ተገቢም ነው።

ችግሩ የሚነሳው ያ ዋጋ እውነተኛ ነው ወይ? በፍጹም! የተቀመጠ ሮድ ማፕ የለም፤ ፍላጎት እና አቅርቦት በየጊዜው ጥናት አይከናወንባቸውም፤ ተፈጻሚ የሚሆንም አዋጅ የለም። ስለዚህ ሁሉም እንዳሻው ይራመዳል። ዋነኛው ተወቃሽ መንግሥት ነው። ሀገሪቷን ለደላሎች አሳልፎ ሰጣት፤ ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ ለምግብም፣ ለአልባሳትም፣ ለቁስም፣ ለቤትም የፈለገውን ዋጋ ያወጣል። በአጠቃላይ ምን ያህል የሚፈጅ መኖሪያ ቤት ምን ያህል እየተሸጠ ነው? ገዢና ሻጭ ከተማመነ ምን ችግር አለው የምትል ማደናገሪያ አለች። እንዲህ ሀገር አይመራም!

እግራቸው እስኪንቀጠቀጥ፤ ትከሻቸው እስኪጎብጥ፤ ዐይናቸው እስኪፈዝ፤ አዕምሮአቸው እስኪደነዝዝ የሚሰሩ ይሄን ኑሮ ለመኖር አቅም የሚያንሳቸውንስ ለምን አናስብም? ነዳጅ፣ የቤት ኪራይ፣ የምግብ ውጤቶች፣ አልባሳት ላይ ጥቂት የሚባል ጭማሪ ሲደረግ ምን ያህል ዜጋ ሊጎዳ እንደሚችል ለምን አናስብም? ሆን ብለን ካልሆነ፤ ሠራተኛ ሁሉ በሚሰራው ልክ ነው የሚከፈለው? ዲሞክራቲክ ኮንጎ ውስጥ በሚገኝ አንድ

mining site 3000 የሚሆኑ የአከባቢው ሰዎች ቀን እና ማታ ሳይሉ ይሰራሉ። በዓመት 360 ቶን ኮልተን በመባል የሚጠራ የታንታሉም ጥሬ ግብአት ከምድር ሆድ ያወጣሉ። አርባ ኪሎ የሚመዝን ያልተጣራውን በ700 ዩሮ ይሸጡታል፤ ለደላሎች። እነሱ በ4,200 ዩሮ ይሸጡታል። ከእነዚህ ሠራተኞች በአማካኝ አምስቱ በቀን ይሞታሉ። በቂ ምግብ እና የንጹህ ውሃ አቅርቦት የላቸውም። መብራት የሚባል አይተው አያውቁም።

አንድ ሁላችሁም ያላስተዋላችሁትን ነገር ልንገራችሁ፤ ስለ ፍትህ ሚንስተሩ አሟሟት። ከፍርድ ቤት ተረተው እንደ ወጡ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት መኪናቸውን አቁመው የታክሲ ሰልፍ በተሰለፉበት ያልታወቁ የተባሉ ሰዎች በላንድ ክሩዘር ለመግጨት ሙከራ ያደርጋሉ፤ ሰልፍ ላይ የነበሩ ሰዎችም በድንጋጤ ተበተኑ፤ እሳቸውን አከታትለው ከፖል ጀርባ ቢሸሸጉም ፖሉን በመግጨት ፖሉን እላያቸው ላይ ጥለው ገደሏቸው። እንደ ተራ ዜና ከንፈር አስመጥጦ ተረሳ። ልብ የሚል መርማሪ እስካሁን አልተገኘም። እውነታው ላይ ይደርሱ ነበር።

ኮሚሽነር አበረ አዳሙስ? በልብ ህመም ነው የሞተው ተባለ፤ እውነት የምርመራው ውጤት ልክ ነው? ጋዜጠኞችን ጠርቶ ነበር የሰኔ 16ቱን ጉድ ሊዘከዝከው ታዲያ ለነገ ቀጥሮአቸው ዛሬ በልብ ህመም ሞተ። ቀልድ! የእሱ ሞት ውስጥ የሁለቱም እጅ እንዳለበት ጥቂት የማይባል ሰው ያውቃል።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ፌል አድርጋለች። ይኸውላችሁ አንድ ሀገር እንደ ሀገር እንዲቀጥል፤ ማኅበረሰብም እንደ ማኅበረሰብ እንዲተሳሰር፣ እንዲከባበር፣ ይህም መከበርን፣ መፈራትን፣ መወደድን በሌሎች ዘንድ እንዲያስገኝለት፣ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ እንደተባለ፣ መጀመሪያ ያ ማኅበረሰብ የራሴ የሚለው መሪ እና

መተዳደሪያ ሕግ ያስፈልገዋል። እኚን ሕግጋትም በሙሉ ልቡ ሊያከብራቸው ይገባል። ሕግ ሕግ ነው! ኣታመንዝርን ጥሰህ ኣትግደልን ልታከብር ኣትችልም፤ ጽድቅም ኣይሆንልህም! ይሄ ለዓለምም ሕግ ይሰራል ለመንፈሳዊ ብቻ ኣይደለም።ሕግ እና ሥርዐት የሌለው ሀገርም፣ መንግሥትም፣ ሃይማኖትም፣ ሕዝብም ቀጣይነታቸው ኣጠያያቂ ነውና። ኣይጸኑምም!

እንኳን እኚህ ቤተ ሰብ ያለ ሁለቱ ኣይጸናም ይፈርሳል። ልጅም እንደ ልቤ ካለ፤ እናትም ኣባትም እንደዚያው ከሆኑ ምን ሊከሰት እንደሚችል ይታወቃል። ኣሁን ኢትዮጵያ እንደዚህ ሁናለች። ሁሉም የራሱ ሕግ እና ሥርዐት ኣለው። ሁሉም እንደ ልቡ መሻት ይመላለሳል፤ መታዘዝ ታናሽነት ኣይደለም፤ ሕግ እና ሥርዐትን ኣክብሮ ማስከበር የዕውቀት፣ የጥበብ እንዲሁም የማስተዋል ራስንም የመግዛት፣ የስልጡን ሕዝብም መገለጫዎች ናቸው። ይህ ከእኛ እየጠፋ ነው። ለሃይማኖት ሕግጋት ስንገዛ፤ ሃይማኖታችንን ከኣፍ በዘለለ በልባችን የምንወድ ስንሆን የውጥንቅጡን ስር እናገኘዋለን። ሕጉን የምትሰሙ ብቻ ኣትሁኑ የምታደርጉም እንጂ። ተብሎ እንደተጻፈ።

ንቁ እና ሥነ ምግባር የተላበሰ እንዲሁም ግብረ ገብ ያለው ማኅበረሰብ ለመገንባት፤ ሥልጣንን ኢጋጣሚ እጃቸው ላይ የጣለችላቸው ኣልያም በማጭበርበርና በተለያዩ መንገዶች ያገኙ ያልሆኑ፤ በመስፈርት እና በኣገልግሎት የተፈተኑ፤ ምረጡኝ ብለው ሳይሆን የኣከባቢያቸው ነዋሪዎች በእራሳቸው ፈቃድ እኚህ ይወከሉን ያስተዳድሩን ብሎ የሚመሰከርላቸው፤ እራሳቸውን የገዙ ጭምቶች፣ ጨዋዎች፣ ቤተ ሰባቸውን ቀጥ ኣድርገው የሚያስተዳድሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

ኣባቶቻችን በተለይ የቤተክርስቲያኖቹ ሥልጣን ሲሰጣቸው ኣልፈልግም ይሉ እንደነበር ታውቃላችሁ።

ፓትርያርክ ሁኑ ሲባሉ አይገባኝ አልፈልግም ብለህ የሸሹ እንደነበሩ እናውቃለን። አሁንስ? ንግሥናንስ በቃኝ ብለው ጥለው ገዳም የገቡ ነገሥታት አልነበሩንም? ጳጳስም ንጉሥም የነበሩ አስተዳዳሪዎችስ አልነበሩንም? እነዚህን ብንሾማቸው ገንዘብ ያታልላቸዋል? ፍትህ ያጓድላሉ? ሹመት እንዲህ ነው። ሕዝቡ ነው ምሩን ማለት የሚገባው። እንዲህ ያሉ ግለሰቦች በሚደንቅ ሁኔታ አሁንም አሉ።

እንዲህ የአስተዳደር እና የሕይወት ጥበባቸው ታይቶ ወደ ሥልጣን የሚመጡ ግለሰቦች፤ የአከባቢያቸውን ከፍ ሲልም የሀገርን ገጽታ የሚገነቡ፣ የሕዝቡን ሥነ ልቦናና ፍላጎት ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ ከእኔነት ስሜት ወጥተው ሀገርን የሚያቆሙ መሆናቸው ግልጽ ነው። መስፈርቱ መሆን ያለበት ሥነ ምግባር፣ ግብረ ገብ እና ጥበብ ነው። እራሱን ያልገዛ፣ ቤተ ሰቡን ማስተዳደር ያቃተው ግለሰብ እንዴት ሀገር እና ድርጅት ይሰጠዋል? ምክንያቱም እራስንም ይሁን ሌላን፤ የትም ይሁን የት አመራር አመራር ነው።

የአመራር ጥበብ ከእራስ ይጀምራል። ስሜትን፣ ፍላጎትን ከመቆጣጠር፤ በመጠን መኖርን አስከትሎ፤ ወደ ቤተ ሰብ፣ ጓደኛ፣ እያለ ወደ ሀገር ያድጋል። ስለዚህ በእነዚህ ላይ የተመሰረቱ ጠንከር ያሉ ፖሊሲዎችን ከትምህርት ሚኒስተር ጋር በጋራ በመሆን እያረቀቅን እንገኛለን፤ ከታች ጀምሮ እስከ ላይኛው የትምህርት እርከን የሚዘልቅ ይሆናል። ተፈጻሚነቱም በአስቸኳይ መሆን ስለሚኖርበት፤ በይደር የሚያዝ ጉዳይ ስላልሆነ። ለአሁን አመሰግናለሁ።

ፕሮፌሰር ናኮር ሰገን በቀልድ ጀመረና፤ ቀጥሎ ወንድሜ ዶ/ር አጽሎስ እንደተናገረው አሁን ሀገሪቷ መሰረታዊ የሆነ ለውጥ ያስፈልጋታል አለ። የመንግሥት ብቻ አይደለም የሥርዐትም ጭምር እንጂ። ከልጅነቱ ሥርዐትን ያልተማረ ልጅ ምን እንዲሆን ትጠብቃላችሁ? ወላጅ ከእለት ገቢው ቀንሶ እየተቸገረም ወደ ትምህርት ቤት ልጆቹን የሚልካቸው፤ ሳይንሳዊ የሆነ ዕውቀትን እንዲገበዩ ብቻ አስቦ አይደለም። ወላጅ ልጆቹ በሁሉም ዘርፍ ጠቢባን እንዲሆኑ ይፈልጋል። ለዚያም ነው አንድ አንድ ወላጆች ትምህርት ቤት ሲቀያይሩ የሚስተዋለው። ይህን ሲያደርጉ የዘነጉት ነገር የእነሱም ስፔስፊክ የሆኑ ግዴታዎች እንደሚኖርባቸው ነው።

ከሚማሩት እኩል የሚያዩትም የወላጆች ባህሪ ለማንነታቸው ወሳኝነት አለው። ልጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከመምህራኖቻቸው ጋር ነው። እነሱም የሁሉንም ጸባይ መከታተልና ማወቅ ስለ ሚኖርባቸውም ጭምር ነው፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ መምህራን እንዳይቀያየሩባቸው የሚደረገው። ከዚህ ነው ልጆች እየተቀረጹ ማደግ ያለባቸው። ማንነታቸውንም ፈልገው ማግኘት ያለባቸው። እራስህን ፈልገህ አግኝተሃል? የምትኖሪለት ዓላም ምንድነው የሚል ጥያቄ ብዐቀርብ ምን ያህል ሰው ይመልስልኛል? ወደድንም ጠላን በአንድም ሆነ በሌላ መቀረጻቸው የማይቀር ስለሆነ፤ እንዴት መቀረጽ እንዳለባቸው መወሰን አለበት። ሁሉም ትምህርት ቤት ለእኔ ይበጀኛል ያለውን ካሪኩለም ይዞ ማስተማር አይፈቀድም። ይህ ነውና ዝብርቅርቅ የሆኑ እርስ በእርስ በእሴትም ሆነ በምግባር የማይገናኙ፤ በአንድ ሀገር የሚኖሩ፤ ወጥነት የሌላቸው ዜጎች እንዲኖሩን ያደረገን።

ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ከተሞች፣ በየሰፈሩ ተዘዋወሩ የአንድ አከባቢ ልጆች አንድ አይነት ጸባይ ይዘው ታገኛላችሁ፤ የጨርቆስ ልጅ ሲባል ምን አይነት ልጆች ሊሆኑ እንደሚችሉ ትገምታላችሁ አትሳሳቱምም፤ የቦሌ፣ የፒያሳ፣ የካዛንቺስ፣ የቄራ፣ የመርካቶ፣ የቆጪ፣ የመንቲና ይገርማቹሃል 365 ኪሎ ሜትር ርቀት ቢኖራቸውም የዚህ ሰፈር ነዋሪዎች ከጨርቆስ ነዋሪዎች ጋር አንድ አይነቶች ናቸው። ፈረንጅ አራዳ፣ የሳሪስ፣ ሽዋ በር፣ ለገሃር፣ 07፣ 13፣ ፓፒረስ፣ አቶቴ፣ ኮምቦኒ በእነዚህ አካባቢዎች ያደጉ እና የሚኖሩ ሰዎች የራሳቸው የሆኑ መገለጫዎች አሏቸው። አሁን እሱን ለማጥፋት ለሊት እና ቀን እየተሰራ ነው። እነዚህን አሁን ከሀገሪቱ ከተሞች ጥቂቱን ባሕር ዳር፣ አዳማ፣ ሀዋሳ፣ ከአዲስ አበባ እና ጂማ የጠራሁላችሁ ሰፈሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ነበረች። ሁሉም ይመሳሰላሉ። ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላኛው ከተማ የተንቀሳቀሰ ወጣት፤ ልጅነቱን ሲነግራችሁ አብሮ አደጋችሁን የምታወሩት ነው የሚመስላችሁ። በልዩነታችን ውስጥ ወጥነት ነበረ። ወጥነት ያለው የሚግባባ፣ ሁሉም የራሱንም ሆነ የሌላውን ባሕል፣ እምነት እና ታሪክ በሚገባ አክብሮ የሚይዝበት፤ በሁሉም ዘርፍ ብቁ የሆኑ ዜጎችን እንድናፈራ የሚያግዝ ፖሊሲ ወደ ሥራ ይገባል፤ አሁንም የገቡ ስላሉ ማለት ነው።

እንደ ምታውቁት የትምህርት ተቋሞቻችን አብዛኛው ልጆቻችንን የምናጣባቸው ሆነዋል። ለጆሮ እንግዳ የሆኑ ምግባራት ይከናወኑባቸዋል። ያደረግናቸው ጥናቶችና የወሰድናቸው ሰርቬዎች ውጤታቸው አስደንጋጭ ነው። በዘመናዊነት ሥም ብዙ እንግዳ ነገሮችን ለልጆቻችን አስረክበናል፤ አስከፊው ደግሞ ወላጆች ይህን አለማወቃቸው ነው።

አንደኛውም Dissociative Identity ያላቸው ወጣት ተማሪዎች ቁጥራቸው እየጨመረ መሆኑ ነው። ኮመንሊ multiple personality የምንለው ማለት ነው። እንዲ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች አንደኛው ከአንደኛው ፍጹም የሚቃረን ማንነት ሊኖራቸው ይችላል። የተለያየ ሀሳብ፣ ስሜት፣ ጸባይ እንዲሁም የሰውነት ጥንካሬን ጨምሮ። ቤተ ሰቦቻቸው እንዲሁም የቅርብ ዘመዶቻቸው እና ጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው ማንነት እጅጉን የተራራቀ ነው። የአንድ ተማሪ ወላጅ እና ጓደኛ ጀርባ ለጀርባ አስቀምጣችሁ ቃለ መጠይቅ ብታቀርቡላቸው፤ ስለ ሁለት የተለያየ ሰው እንጂ ስለ አንድ ሰው የሚያወሩ አይመስላችሁም ግን ሁለቱም እየዋሹ አይደለም።

ይሄም ወደ Alter ego ሊያድግ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገለጥ ውስጣቸው የሚኖር ሌላ ማንነት። ታዋቂዋን የአሜሪካን የፖፕ እና አር ኤንድ ቢ አርቲስት ቢዮንሴ ኖውልስን ማየት እንችላለን። ብዙ ጊዜ መድረክ ላይ ስትወጣ ብቻ የምትቆጣጠራት፤ ሳሻ ፊርስ ስትል የሰየመቻት ሌላ ሴት ውስጧ እንዳለች ስትናገር ትሰማለች። አም ሳሻ ፊርስ ስትል የሰየመችውም የሙዚቃ አልበም አላት። ልጆች የሚፈልጉትን የሚያህል intimacy ሲያጡ imaginary friend ይፈጥራሉ።

እኚህን የሚያመጡ የተለያዩ ፋክተሮች ቢኖሩትም፤ በእነዚህ ኬዞች በዋነኛነት በአንደኛው ወገን የሚኖር የአታችመንት እና ኢንትመሲ መላላትና በሌላኛው ወገን የመጥበቁ ጉዳይ ነው። ልጆችን ቀርቦ ስሜታቸውን መጋራት እና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ማበረታታት፤ እንዲሁም ማድረግ የሚፈልጉትን በፊታችን እንዲያደርጉ መፍቀድ፤ ለችግሩ ቁልፍ ከሆኑ መፍትሄዎች ዋነኞቹ ናቸው። የቆሙበትን መንገድ እንድናውቅ

ስለሚረዳን፤ ጠቃሚያቸው ካልሆነም በብልሀት ፈቀቅ እንድናደርጋቸው እድሉን ስለሚሰጠን። ከሥማቸው ውጭ ይገምታሉ እንጂ እውነተኛ የልጆቻቸውን ማንነት የማያውቁ ወላጆችም ያጋጥሟችኋል። ልጆቹም ይሄን ሁሉ ውጭ ጓደኞቻቸው ጋር ስለ ሚያገኙት ቤት ሌላ ሰው ይሆናሉ። እነዚህን የመሳሰሉ ወላጆች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በሚያደርጉት ድርጊት፤ ከPost-Traumatic Stress Disorder ከፍ ብሎ ወደ Complex Post-Traumatic Stress Disorder የተሸጋገረ፤ የማንነት ቀውስንም ጭምር የወለደ በሽታ ለልጆቻቸው እያሸከሙ ኖረዋ።

ልጆችን መቅጣት ተገቢም አስፈላጊም መጽሐፍ ቅዱሳዊም ነው። ከመቅጣቱ ግን ምክር እና ፍቅር ሲቀድም ውጤቱ ያማረ ይሆናል። ልጆቻችንንም ከምግባር ጋር እቅፋችን ይከትልናል። ከጂነቲክስ ይልቅ ካልቸር በማንነታችን ላይ ጽኑ ተጽህኖ አለው። ስለዚህ ልጆችን በምግባር አንጾ ለማሳደግ፤ ብቁ የሆነ ማኅበረሰብ እንደገነባን እርግጠኛ መሆን ይኖርብናል። እንደዚያ ካልሆነ ከትላንት ዛሬ እንደ ከፋ፤ ከዛሬ ነገ የማይከፋበት አንዳች ምክንያት የለም። ከአሁን ወዲህ የኢትዮጵያ ልጆች ሳይንስ ብቻ አይማሩም። ሀገራቸውን በሚገባ እንዲያውቁ እናደርጋቸዋለን። ባሕሎቻቸውን፣ ታሪኮቻቸውን፣ ሃይማኖታቸውን፣ ቋንቋዎቻቸውን ጨምሮ። በሥነ ምግባርም በዕውቀትም በጥበብም ሙሉ ሰው እናደርጋቸዋለን። አመሰግናለሁ። ሞቅ ባለ ጭብጨባ ተቀበሉት።

የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስተሩ ዶክተር ዛሪየስ ለገሰ ወደ መድረክ በመውጣት ንግግሩን እንዲ ሲል ጀመረ፤ እንደ ትምህርት ሚኒስተር እናንተ ይህን በአግባብ ከሰራችሁልን፤ የምንረከበው የታነጸ ወጣት ይሆናል። ማብቃቱ ላይ እናተኩራለን። ለማንኛውም አሁን ባህልም ቢጨመርበት፤ የእኔ ቢሮ በተፈጥሮው የወጣት ነው፤

ለዚያም ነው ከማህላቸው በወጡ፤ ሥነ ልቦናቸውን በሚያውቁ አመራሮች መመራት አለበት የምለው። አሁን ቢሮው እንዴት ቅጥ እንዳጣ የምታዩት ነው። የውስጡን በኦሎምፒክ ውጤቶቻችን ማወቅ ትችላላችሁ። እኔ በሪሰርችም፣ በሥራም ኢጋጣሚ የተለያዩ ሀገራት ወጣቶችን የማግኘት ኢጋጣሚው ነበረኝ፤ የኢትዮጵያ ወጣት ግን ይለያል። ሌሎቹ አንድ የተሰጣቸው መንገድ አለ በዚያ ይጓዛሉ። የኛዎቹ የተዘረጋ መንገድ በሌለበት ለራሳቸው መንገድ የዘረጉ ብልሆች ናቸው። አንድ መንገድ ሰጠናቸው ትምህርት የሚባል ያውም አስፓልት ያልሆነ ኮሮኮንች። እሱ ላልሆነላቸው ወጣቶች ምን አዘጋጀንላቸው? እነሱ ግን ከዓለም እራሳቸውን አዛመዱ።

እንደምታስታውሱት በቅርብ አንድ ስብሰባ ነበረን እንደ ዞኖር፤ ከከተማዋ ወጣቶች ተወካዮች ጋር የሚያነሱት ሀሳብ ይገርማችኋል። ዘለግ ያለ ነበር ቆይታችን የተረዳሁት ነገር፤ እኛ እና እነሱ ተብለን እንደተከፈልን እና መሬት ላይ ያለውን ወጣት፤ ከኛ ጋር የሚያገናኘውን ምንም አይነት መስመር እንዳልዘረጋን ነው። ፈጽሞ አናውቃቸውም፤ ይልቁንም ወንድሞቻችን እና ልጆቻችን እንደሆኑ ዘንግተነዋል። ለወቀሳ ብቻ ፊታችንን እናዞርላቸዋለን እንጂ፤ በእነሱ ምክንያት ወደ እራሳችን አንመለከትም። ስህተትም ካለ የኛው ጥፋት እንደሆነ ማወቁ አይከፋም። በልጅነቱ መንገድን ምራው፣ በአደገም ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም አይደል የተባለው፤ ያላሳየናቸውን መንገድ ከየት ያምጡት? መጀመሪያ ያለውን ጋፕ እናጥብበው ከዚያም የሚሆነውን እናያለን። እንደ ተቋም ያንን እያደረግን እንገኛለን። ከተረከብነው በኋላ ማለቴ ነው። የኢትዮጵያ ወጣት የእግር ኳስ እንደሚወድ ይታወቃል፤ ብዙ ልዩነት ያለባቸውን ወጣቶችም አንድ ሲያደርግ አይተናል። ማየት ብቻ አይደለም መጫወትም ይወዳሉ።

በአሳለፍነው ዓመት ወጣቶቿን ወደ ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ገበያ በመቀላቀል አንደኛዋ አፍሪካዊት ሀገር ሴኔጋል ነበረች። ሁለተኛዋ ኮት ዲቫር፤ ናይጄሪያ፣ ጋናና ካሜሮንን በማስከተል። ታዲያ የኛ ወጣቶች ከሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት በምን አነሱ? በአዕምሮ? በአካል ብቃት? አይምሰላችሁ። በሚገባ ቢሰራባቸውና ቢታገዙ እዚህ የሚቀር ወጣት አታገኙም። በአካል ብቃትም ሆነ በአዕምሮ ቅልጥፍናቸው የላቁ ወጣቶች አሉን። የመጫወቻ ሜዳ ከመሥራት ይልቅ የነበረንም ስለቀማናቸው ነው እንዲህ የሆነው፤ ትኩረት ስለነፈኛቸውም ጭምር። እዚህ ላይ ብዙ ማለት አልፈልግም፤ ዶክመንቶች ላሳያችሁና ላብቃ ሌላ ቀን እንቀጥላለን። ለዞዳር ቁልፍ የሆነ ቺፕ በፕሮፌሰር ሞክሳ ባላቤት እጅ እንደሚገኝ ይታወቃል። አሁን በእጃችን መግባት ያለበት ሰዓት ደርሷል፤ እንደምታውቁት ጄነራል ሂሶጵ ከማህላችን የለም፤ ቢኖርም የተከሰተውን ታውቃላችሁ። እንዴት እና በምን መንገድ ነው አይከልን አግባብተን ያን ወሳኝ ቺፕ በእጃችን የምናስገባው? በዚህ ዙሪያ ሀሳባችሁን እፈልጋለሁ። ቀሪ ወንድሞቼ እንደጨረሱ፤ ሀሳባችሁን አካፍሉኝ አመሰግናለሁ።

ከደቂቃዎች በኋላ ዶክተር ዛሪየስ፤ ኤፍሮን፣ ቴራስ፣ ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ እና ዶ/ር አጵሎስ ወደ እሱ ሲመጡ ተመለከተ። እንዲህም አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ቺፑ እጃችን ሳይገባ የምንራመዳቸው እርምጃዎች ወደ ሞት አፍ እንደሚያቀርቡን እርግጠኞች ሁኑ። ጊዜ ሳናባክን እጃችን ማስገባት ይኖርብናል። ይህን ለማድረግ የሚያስችል መንገድ ማግኘት አለብን ዛሬ! ዶ/ር አጵሎስ ቀበል አድርጎ ለምን አናስገድዳትም? አለ፤ ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ በዚህ ድርጅት ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር አልታገስም! ቫዮለንስ ተገደን የገባንበት ቢሆንም፤ በንጹሀን ዜጎች ላይ እንዲህ ያለ ተግባር በፍጹም ሲከናወን ማየትን አልሻም! አሉ ቆፍጠን በማለት። ኤፍሮን በመሀል ገብታ ይህን ጉዳይ

ለሰዓር እንስጣት እሷ በእጃችን እንደምታስገባው እርግጠኛ ነኝ፤ ይሄ ከፕሮፌሰር ሞክሳ የሞታቸው ዕለት አንስቶ ሲያስጨንቀን የነበረ ጉዳይ ነው። ለሰዓር ምን ያህል ቀላል እንደሚሆን ግን ታዩታላችሁ። ከአቃታት እንደገና እንወያይበታለን በማለት ምላሻቸውን በመጠበቅ በተራ ትመለከታቸው ጀመረች። ከዶ/ር አጽሎስ በቀር ሶስቱም ተስማሙ።

ሰዓር በተሰጣት ተልዕኮ መሰረት፤ ወደ ፕሮፌሰር ሞክሳ ባለ ቤት ወደ አይከል አቅንታለች። ሰዓር፤ አይከል በባለ ቤቷ መሰዋት እንደተጎዳች ብታውቅም፤ ባለፉት ጊዜያት ባደረገቻቸው ፕብሊክ ንግግሮች ቁጭት እና እልፅ እንደገባት ብትረደም፤ ይህን ያህል አልጠበቀችም ነበር። አይከል ዐይኖቿ ጎድጉደው፤ ደም ግባቷ እንዳልነበር ሆኖ አገኘቻት።

፡፡ በፕሮፌሰር ሞክሳ ረፍት የተሰማኝን ሀዘን ልገልጽልሽ እወዳለሁ በመጀመሪያ፤ እየበረታሽ ነው?

፡፡ ምንም አልል!

፡፡ በአካል ባላውቃቸውም የምርምር ውጤቶቻቸውም ሆኑ እቅዶችቸው እንዳከብራቸውና በቅርበት የማውቃቸው ያህል እንዲሰማኝ አድርገውኛል።

፡፡ ለህትመት የበቁ የምርምር ውጤቶች አሉት ልክ ነሽ። እቅዶቹ ስትይ ግን ምን ማለትሽ ነው?

፡፡ ይኸውልሽ እነዚህን ዶክመንቶች ተመልከቻቸው።

፡፡ እንዴት ልታገኛቸው ቻልሽ?

።። ባለ ቤትሽ ላንቺ የላኩልሽ ቺፕ ምስልም ይኸው።

ማነሽ አንቺ? ይቅርታ ከዚህ በላይ ማውራት አልችልም እባክሽ ውጪልኝ! አለቻት አይከል ከተቀመጠችበት በመነሳት። ይኸውልሽ አይከል ቺፑ ሪሞትሊ አክቲቬት የሚደረግ ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር አለው። ያለ ምንም ጥቅም ለተወሰነ ጊዜም ከቆየ self disposal timing አካቶአል ይፈነዳል። ይኸው ማረጋገጫ ይህን ተመልከቺ። ምንም ማየት አልፈልግም እባክሽ ውጪልኝ! ይኸውሽ አይከል እኔ እዚሁ እቆያለሁ፤ አንቺ ያለበት ቦታ ሂደሽ ተመልከቺው ቀዩ ሦስት ጊዜ ከበራ በኋላ ቢጫው አንድ ጊዜ ይበራል፤ አንደኛው ግን ፈጽሞ አይበራም እሱ አረንጓዴው ነው። ያ ማለት እራሱን ሊያጸዳ ማለትም ሊፈነዳ ቀናት ከዚያም ያነሱ ጊዜያት ናቸው የቀሩት ማለት ነው። ይህ ለአንቺም ለልጆችሽም አደጋ አለው። አንቺ ጋር እንደሚገኝ ያወኩት ማታ ነው። እመኚኝ መረጃዎቹን ብቻ ፈልጌ ቢሆን አንቺ ጋር መምጣት ሳይጠበቅብኝ ውስጡ ያሉትን መረጃዎች በሙሉ እወስዳቸኋለሁ።

አሁን እዚህ የተገኘውት ለአንቺ እና ለልጆችሽ ስል ነው። ቺፑን አክቲቬት ካላደረኩት የነገርኩሽ ከመከሰት አይቀርም። የምታወሪው እውነት እንደሆነ በምን አውቃለሁ? አለች፤ ቄል ማወቅ የምትፈልጊውን ሁሉ ጠይቂኝ። አይከል የሰዓርን ዐይን ትኩር ብላ ስትመለከት ቆየችና ወደ ደረጃው በማምራት መኝታ ቤት ገብታ ቺፑን ከላፕ ቶፕ ጋር ይዛው ተመለሰች። ማንነትሽ እኔን አያሳስበኝም፤ ውስጡ ምን እንዳለ ለማወቅ ስሞክር ከርሜአለሁ አልተሳካልኝም እንጂ። ይኸው ክፈቺው ብላ ሰጠቻት። ሰዓር ግን እንደማትችል ነገረቻት። ፋይሉን ኮፒ እንዳላደርገው ፈርተሽ እንደሆነ እረዳለሁ ግን ቺፕ

ማለት ሜሞሪ ካርድ አይደለም የትም ቦታ ስክተሽ አክቲቭ አታደርጊውም። ለዚያም ነው ያቃተሽ። ይሄኛው የራሱ የሆነ ኦፐሬቲንግ ሲስተም አለው። እሱን ለማድረግ ደግሞ ይዘሽ የመጣሽ ላፕ ቶፕ አቅሙ አይፈቅድም።

ስለዚህ የኔን እንድጠቀም ፍቀጂልኝ። አሁን ይገፍው ብወጣ ማን የሚከለክለኝ አለ? አንቺም ሆንሽ ዘበኛሽ ልታስቆሙኝ አቅማችሁ አይፈቅድም፤ ቀድሞውኑም በሩን ሰብረን ገብተን አስገድደን መውሰድ አቅማችን ሳይፈቅድ ቀርቶ አይደለም። የቆምንለት ዓላማም ጭንቅላታችንም ስለ ማይፈቅድ እንጂ። ደግሞም ፕሮፌሰር ሞክሳ ይህ ስለማይገባቸው። በጉልበት የበረታ ፍላጎቱን እንዲያሳካ ከፈቀድን እማ ምኑን ተሻልን? ጉልበት አስፈላጊ የሚሆንበት ቦታ አለ። አሁን በእኔ እንድጠቀም ፍቃደኛ ነሽ? በአዎንታ ጭንቅላቷን ነቀነቀች።

ይኸውልሽ አይከል ባለ ቤትሽ ፕሮፌሰር ሞክሳ የተሰዉለት ቅዱስ ዓላማ ይህ ነው በማለት ስክሪኑን በማዞር በብዙ አራት መአዘን ተከፋፍለው የተቀመጡትን ፋይሎች አሳየቻት። አይከል ጊዜ ወስጄ ማየት ይኖርብኝ ይሆናል አለች። ሰዓርም ግር እንዳለሽ ይገባኛል፤ ይኸውልሽ ይህ የሚታይሽ ካርታ ውስጥ አረንጓዴ የተቀቡት ስፍራዎች፤ ለም መሬቶች ናቸው። በምድር ላይ ያለውን ሕይወት የሚደግፉ ውድ ሀብታት ናቸው። ለእጽዋትም ለዘርም እድገት አስፈላጊ የሆኑትን ማዕድናት እና ኦርጋኒክ ንጥረ ነገሮች የያዙ ስፍራዎች ናቸው። ለምሳሌ Humus,Manure, Manganese, Phosphorus, Nitrogen, Potassium እና የመሳሰሉትን የያዙ ስፍራዎች ናቸው። በቢጫ ቀልመው የምትመለከቺያቸው ደግሞ የከበሩ ማዕድናት የሚገኙባቸው ስፍራዎች ናቸው። ለምሳሌ Sapphire,Emerald, Opal, Diamond እና የመሳሰሉት ናቸው። እንደምትመለከቺው ስፍራዎቹ

Open-pit mines, Underground mines እና Placer mines ተብለው ተከፍለዋል እሱን ጊዜ ካገኘው አስረዳሻለሁ። ይህ የምትመለከቺው በግራጫ የቀለመው ስፍራ ደግሞ የነዳጅ ክምችት የሚገኝበት ስፍራ ነው።

አሁን ያሳየሁሽ ጥቂቱን ነው ባለ ቤትሽ በከንቱ እንዳላለፉ እንድትረጂ ይጠቅምሻል ብዬ ስላሰብኩ ነው። ብዙ ወታደራዊ ሚስጥሮችንም የያዙ ሰነዶች አሉት። እነዚህ ደግሞ ግለሰብ ሳይሆን ሲስተም ሀገሪቷን እንዲመራ የሚያግዙ በተለያዩ ቢሮዎች የሚጸድቁ ፖሊሲዎችን እንዲሁም መተዳደሪያ ደንቦችን የያዙ ስትል የአይከልን የለቅሶ ድምጽ በመስማቷ ዐይኖቿን ከስክሪኑ ነቅላ ወደ አይከል ዞረች። አይከል በዚህ ምድር በሕይወት እያሉም ሊለቀስላቸው የሚገባ እልፍ ሰዎች አሉ። እንደዚያውም ሞታቸው የረፍታቸው ቀን የምትሆንላቸውም አሉ። ባለ ቤትሽም ከነዚህ መሀል ናቸው። እርግጥ ነው ባይለዩን ከዚህም በላይ ለሀገራቸው ያገለግላሉ፤ አለመኖራቸው ግን የሚያስቆጭ አይደለም። የምታይውን ያላየሽውንም ብዙ ሰርተዋልና። ከተቻለሽ ህልማቸው እውን እንዲሆን አግዢን፤ አንቺም ልብሽ ያርፋል፤ ለልጆችሽም የሚታይ ማስታወሻ ታስቀምጪላቸዋለሽ። ሀዘኑ ቢበቃሽ ደስ ይለኛል። በማለት አቀፈቻት። ቺፑን አስቀምጣላት የምትፈልጊው ነገር ካለ በዚሁ መስመር የጽሁፍ መልዕክት ማስቀመጥ ትቺያለሽ በማለት ተሰናብታት ወጣች።

አይከል ለቀናት ረዘም ያለ ጊዜ ወስዳ ስታሰላስል ከቆየች በኋላ፤ ቀደም ሲል በተገናኙበት መስመር ልታገኛት እንደምትፈልግ የጽሁፍ መልዕክት ለሰዓር ላከችላት። ከሰዓርም ቦታ እና ጊዜን የሚገልጽ አጭር የጽሁፍ መልዕክት ስለደረሳት፤ መልበሻ ክፍል ውስጥ በሚገኝ የቁም መስታወት ሁለንተናዋን ስትመለከት ቆይታ፤ ከተማ ውስጥ ጥሩ ወደ ሚባለው ስቲም ባዝ አቀናች።

እንፋሎቱ አይከልን ሸፍኖአታል፣ ሙቀቱ የገላዋን በድንነት ከቅዝቃዜ እና ከከባድ የሀዘኗ ጠርዝ መልሶ የማረጋጋት ኃይል ነበረው። በዚህ የእንፋሎት ክፍል ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሰዓታት አሳልፋለች፣ ጥቅጥቅ ያለው እና እርጥቡ አየር ከዚህ ዓለም ማምለጫ መቅደሷ ነበር። ዛሬ ግን ልዩነት ነበረው። ዛሬ መጽናኛ ብቻ አልነበረም የምትፈልገው፤ ዓላማ ትፈልግ ነበር እንጂ። ለአይከል ባልዋ የአጽናፈ ዓለሟ ማዕከል ነበር። ያለ ጊዜው የመጣው ህልፈቱ ዓለሟን ሰባብሮ በሐዘን ባህር ውስጥ ጥሏታል። ለዓመታት፣ ለራሷ እንደኖረች ተሰምቷታል ምንም እንኳን እውነታ ባይኖረው፣ ከህልፈቱ በኋላ ጭንቅላቷን ከውሃው በላይ በማድረግ ልጆቿን መንከባከብ እንኳ ረስታለች። አሁን ግን በውስጧ ብልጭታ ተቀጣጥሎአል። የባልዋን ትዝታ ሥጋ ለማልበስ ህልሙን በማሟላት ማከበር ፈለገች።

ፕሮፌሰር ሞክሳ ሁሌም ለሀገሩ ከፍተኛ ፍቅር ነበረው። በተለይ ለትውልድ የተሻለ የወደ ፊት እድል የሚሰጥ ዘላቂ ማኅበረሰብ የመፍጠር ህልም ነበረው። ለልጆቹ መልካም እና ሩሩህ ነበር፤ ለትዳሩም ቢሆን ታማኝ። አይከል ህልሙን ከእውነታው የራቀ አድርጋ፤ ትኩረት ነፍጋው ቆይታለች። አሁን ግን የእሱ እይታ ከምትገምተው በላይ አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝባለች። እንፋሎቱ በዙሪያዋ ሲታጠፍ፣ አይከል ሀሳቦቿ እየጠሩ ሲመጡ ተሰማት። ምን ማድረግ እንዳለባት አሁን ግልጽ ሆነላት። ፕሮፌሰር ሞክሳ ያሰበውን ዘላቂ ማኅበረሰብ ለመገንባት ሕይወቷን ለመስጠት ቆረጠች። በእንቅፋቶች እና በመሥዋዕትነት የተሞላ ፈታኝ ጉዞ ሊሆን እንደሚችል አሰበች፤ ግን ለፕሮፌሰር ሞክሳ እና ለመጪው ትውልድ ስትል መጓዝ እንዳለባት ወሰነች። አይከል የመታደስ እና የመነቃቃት ስሜት እየተሰማት ከእንፋሎት ክፍሉ ወጣች። ከፊቷ ያለው መንገድ አስቸጋሪ እንደሚሆን ታውቃለች፣ ግን መንገዱን ለመጋፈጥ ዝግጁ ነበረች። በእያንዳንዱ እርምጃ የባልዋን

ህልም ለመፈጸምና የራሷን የሕይወት ዓላማ ለማግኘት የበለጠ እንደተቃረበች ተሰማት።

ይህን አድርጋ ወደ ተቀጠረችበት ስፍራ ደረሰች። ጀርባው ሲቀር ዙሪያው መስታወት የሆነ ካፍቴሪያ ነበር። ሰዓርን እንዳገኘቻት፤ አጠገቧ የነበረችውን ሰው ማንነት ለማጣራት ሳትሞክር፤ ሁሉን ማወቅ እንደምትፈልግ እና ምንም ሳታስቀር ከመጀመሪያው ጀምራ እንድትነግራት አሳስባ ተቀመጠች። ኤፍሮን ግን ብዙ ጥያቄዎች እንደሚኖሩሽ እረዳለሁ፤ በመጀመሪያ የምንነግርሽ ሁሉ አባሎቻችንን ጨምሮ፤ ዓላማችንንም የሚያጠፋ ሚስጥር ነው። አንቺ ደግሞ ከዚህ በፊት በስሜታዊነት ያደረግሽው ንግግር ብዙ ኪሳራ አድርሶብናል። ስለዚህ እኛም በቅድሚያ ከአንቺ የምንፈልገው ማረጋገጫ አለ አለቻት። አይከል በተራዋ እውነቱን ለመናገር እስከ ዛሬይቱ ቀን ድረስ ባመነታም አሁን ግን የሞክሳን ዓላማ ተሳክቶ ከማየት እንዲሳካም የምችለውን ከማድረግ ውጭ የሚያቆመኝ ዓላማ የለም። የምኖረው ለልጆቼ ነው፤ ተስፋዬ ደግሞ በሞክሳ ዓላማ ነው። ስለዚህ አትስጊ ማረጋገጫ እንዲሆንሽ ደግሞ ይኸው ቺፑን አምጥቼዋልለሁ።

ጥሩ የህቡህ ድርጅታችን ስያሜ ዞዓር ይባላል። የመጀመሪያው ስያሜ በርናባስ ነበር፤ ከነሰዓር ቡድን ጋር ከተዋሃድን ጀምሮ ዞዓር ሆኖአል። አብዮቱ የሥልጣን አልያም የሥም ሳይሆን የቅድስና ነውና። የኛ የሚባል መሪም፣ ንብረትም ስያሜም የለም። የሚሻል ሲመጣ ነባሩ ቦታ ይለቃል። ዞዓር የሎጥ ማምለጫ የመማጸኛ ከተማው ነበረች። ለኛም ለዚህች ሀገር ሕዝቦች አሁን ይህ ያስፈልገናል። በልጅነታችን ስንጣላ መታረቂያ የማርያም ጣት ነበረችን፤ ያቺን ጣት አሁን ቆርጠን ጥለናታል። ልጅ እያለን በጨዋታ መሃል መውጫው ሲጨንቀን፤ የማርያም መንገድ ጠይቀን እንወጣ ነበር። ከዚያ ጊዜ ይልቅ አሁን የማርያም መንገድ የሚሰጠን ከዚህ ሁሉ

ውጥንቅጥ የምንወጣበት፤ አንድ ብቻ እንደው ሰጪው ካልጨከነብን ያስፈልገናል። አጥፍተን አባቶቻችን ሊመቱን ሲሉ መሸሸጊያ መማጸኛ የሆኑ የእናቶቻችን ቀሚሶች ነበሩን። አሁን ሲጨንቀን፣ ሲከፋን፣ ቀኑ ሲጨልምብን፣ አይዞአችሁ ባይ ስናጣ፣ ሸክሙ ሲከብድብን፣ ተስፋ ስንቆርጥ የት ሄደን እንሸሸግ? የት ሄደን እንጠለል? እማን እቅፍ ውስጥ ገብተን እናልቅስ? ፅዮናዊት መማጸኛ የሆነችዋን የአምላክ ቤት እንኳን በሯን ከፍተው ደጇን ዘጉት። ይህን ከምናይ ብለው ልጆቿ እረኛ እንደ ሌለው መንጋ ተበተኑ። ልባቸው እያወቀ ወደ ነጣቂ ተኩላ መጠለያ ፍለጋ ሸሹ። ታዲያ ይህ ሕዝብ ዞሯር አያስፈልገውም?

የጠፋውን የጥበብ መቅረዝ ልንለኩሰው፤ የተቆረጠውን ተስፋ ልንቀጥለው፤ የተቀበረውን እኛነታችንን ቆፍረን በተራራ ልንተክለው፤ ከክብር ማማ ሕዝባችንን ልንሰቅለው፤ በመጀመሪያ ንስሃ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና እያለ ከበረሃ እንደ መጣ የዮሐንስ ድምጽ፤ በተለያየ መልክ እያሰማን እየመጣን ነው። ሰምቶ የሚጠቀም አለ፤ የሚዘባበትም እንደዚያው። ውጤቱ ነው ልዩነቱ። ይህን ዓላማችንን በተለያየ መልክ ተፈጻሚ ስናደርግ ቆይተናል። የመጨረሻዋ ነጋሪት እስከትነሰም እንዲሁ ይቀጥላል። ያን ጊዜ ለንስሃ ስፍራ የለምና!። የሚጠረግ ተጠርጎ ምድሪቷ ትነጻለች! ዞሯር ውስጥ ነጥሮ የሚወጣ አንድ ጀግና አይኖርም! ሕዝብን እንጂ ግለሰብን አናጀግንም! ቅዱስ እና ንጹሕ ሕዝብ፤ ገናና፣ ኃያል እና ከቡር ሕዝብ ይሆንላታል ኢትዮጵያ! ስቃይ፣ መከራ፣ እንባ፣ የፍትህ መጓደል፣ ለቅሶና ዋይታ ከምድሯ ይወገዳል! አዲስ ሥርዐት አዲስ ልቦና ይሆናል። ፍቅር እና ሰላም ይሰፍናል። ስደት ወደ ቅድስት ሀገር ይዞራል! አለቻት። ቀሪውን በሂደት ታውቂዋለሽ።

ለውጥ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው። እንኳን ኢትዮጵያን የመሰለ ሀገር ይቅርና አውሮፓውያኑም እለት እለት በለውጥ ውስጥ ያልፋሉ። እኛ ጋር ሲደርስ ለውጥ ከስር መንቀል የሚሆነው ለምንድነው? አሁን እጃችን ላይ ያሉትን የምርምር እና የጥናት ውጤቶች ለምን ሥልጣን ላይ ላሉት አንሰጣቸውም? ከዚያ እነሱ ለሀገር እንዲበጅ አድርገው ይጠቀሙት። መሻሻል አለባቸው ብለን የምናስባቸውን ፖሊሲዎችም ሆኑ መተዳደሪያ ደንቦች ለውይይት እናቅርባቸው ከነመፍትሄ አማራጫቸው። የተሻለው ተመርጦ ወደ አተገባበር እንዲገባ ሁኔታዎች እንዲመቻቹም ማድረግ። ልክ እየሰራ አይደለም የተባለም አካል ቅድሚያ ይገሰድ ቀጥሎ እንደ ሁኔታው እርምጃ ይወሰድ፤ አመጽ እና ደም መፋሰስ ወንበር ላይ የሚቀመጠውን ሰው ይቀይር ይሆናል፤ ሥርዐትንም ጭምር መፍትሄ ግን ሲሆን አልተገኘም። ጦርነት የሚመሩት መሳሪያ እና የጦር እቃ አምራቾች ናቸው። ሴናተሮች ሲመረጡ fund የሚያደርጓቸውም እነሱ ናቸው።

ይሄ የአደባባይ ሚስጥር ነው። በማለት አይከል ልትቅጥል ስትሞክር ኤፍሮን አቋረጠቻት። እዚህ ላይ ጊዜ አንፍጅ፤ አንድ ማስረጃ ብቻ ይበቃሻል። አንቺው ባልሺው መንገድ እንሂድና፤ እስካሁን አንቺ እንደ ሀሳብ ያነሳሻቸው መፍትሄዎች ያልተሞከሩ ይመስልሻል? እኛስ በአንቺ መንገድ መሄዱ ቀላል ሆኖ ሳለ ለምን የራስችንን ጨምሮ የምንወዳቸውን ሰዎች በሞት የምንነጠቅበትን መንገድ መረጥን? አይከል አሁን ሰዓር የምታሳይሽን ማስረጃዎች በትኩረት ትመልከቻቸው ከዚያ እንቀጥላለን። ሰዓር የያዘችውን ታብሌት ስላይድ እያደረግሽ ተመልከቺ ብላ ሰጠቻት። እየቀየረች ከተመለከትች በኋላ እኔ ይሄን ማመን ይከብደኛል! ከባድ ነው! ብላ መለሰችላት። ዐየሽ አለች ኤፍሮን፤ ዐየሽ ለአንቺ በዐይንሽ በማስረጃ ዐሳይተንሽ ማመን ከበደሽ ሌላውን

ማኅበረሰብ ደግሞ አስቢው፤ በአፍ ብቻ ብትነግሪው ምን እንደሚል። አሁን ያየሽው ተወዳጅ የሚባሉ ባለ ሥልጣናትን ድብቅ መረጃ ነው።

ለነዚህ ነው አሁን ማዕድናት የት እንደ ሚገኙ ካርታ የምንሰጣቸው? ነዳጅ የት እንደሚገኝ እንንገራቸው? ፖሊሲ ያልሸውንስ ባለ ቤትሽ ደጋግሞ ለናቡከደነጾር ሳይቀር በእጁ አልሰጠውም? ጥፋት ከተገኘባቸው ይገሰጹ አልሽ? ደጋግመው ሲያጠፉስ? ያንን ደግሞ ከዕውቀት ማነስ ሳይሆን ሆን ብለው እንደሚያደርጉት እንደዚህ በማስረጃ ስታውቂስ? ቀልድ አይደለም የተያዘው! እነሱም አምርረው የሚጠሏትን ሀገር ነው በድከመታችን እልል ብለን ያስረከብናቸው። እኛ ደግሞ በተቃራኒው አምርረን በደማችን ጭምር የምንወዳትን ሀገር የሚከፈለው መሥዋዕትነት ተከፍሎ በእጃችን እናስገባታለን! ይህ ትግል በግለሰቦች ሞት የሚቋረጥ አይደለም! ለዚያም ነው ሥራ አስፈጻሚ እንጂ መሪ የሌለን። አይኖረንምም። ያ ማለት ሁሉም እንደ ልቡ መሻት ይጓዘል ማለትም አይደለም። የተጻፈ የማይሻር ሕግ እና ደንብ አለን። ኃይል መጠቀም ሲኖርብን ለሕይወታችን እንኳን ሳንሳሳ እንጠቀማለን። እየተጠቀምንም ነው፤ እንደዚያው ይቀጥላል።

ከዚህ ወዲህ ወደ ኋላ ላለማየት ቃል ገብቻለሁ። ነገር ግን I am committed to nonviolence. I will not engage in any form of physical harm or aggression. I believe in the power of peace and the importance of resolving conflicts peacefully. Violence is never the answer! በጭራሽ ነው የምላችሁ ኃይል መልስ ሊሆን አይችልም! ይልቁንም በመንግሥት ባተረፍኩት ተአማኝነት ዞሜርን የምረዳው ብዙ ይኖራል የሚል ተስፋ

አለኝ ስትል፤ ኤፍሮን እሱ አያሳስብሽ ከምታስቢው ቁጥር በላይ አስቀድሜ እንደ ነገርኩሽ የነጋሪቱን ድምጽ የሚጠብቁ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ይዘው የተቀመጡ አባላት አሉን አለቻት። በዚህ መሃል ሰዓር ቺፑን ገልብጣ መጨረሷን ለኤፍሮን አሳወቀቻት። ሰዓር አዲስ የእጅ ስልክ ቀፎ ሠጠቻትና ሲም ካርዱን መቀየር አይኖርብሽም፤ በምን መልኩ ክትትል እንደሚያደርጉብሽ ለማወቅ ይረዳናል። ከዚህ በኋላ ከዘዓር የሚደርሱሽ ማናቸውም መልዕክቶች አንድ ጊዜ ከከፈትሻቸው በኋላ እራሳቸውን ስለሚሰርዙ ደግሞ ለማየት እድል አይኖርሽም። በጥንቃቄ አንብቢያቸው፤ ስክሪን ሹትም ለማድረግ እንዳትሞክሪ ቀድሞ ስለሚጠፉ። ቀጣይ እስክንገናኝ እነዚህን ፋይሎች ተመልከቻቸው ስትጨርሺ አቃጥዪው በማለት ተለዩአት።

አይከል አሁን የምትኖርለት አዲስ ዓላማ አግኝታለች በዚህም የመኖር ጉጉቷ ሲጨምር ይታወቃት ጀመር። ከአትላስ አቅጣጫ ስለ መጣች ወደ ቤት ከመግባትዋ አስቀድማ ቦሌ መድኃኒዓለም ገብታ ጸሎት በማድረስ ዛፎቹ ስር ከሚገኙት ድንጋዮች በአንደኛው ተቀመጠች። የተቀመጠችበትን ዛፍ ተከትሎ ባለው ሌላ መቀመጫ ላይ አንድ መነኩሴ ከአንድ ጎልማሳ ጋር ተቀምጠዋል። የሚያወሩት ይሰማታል፤ ጆሮዋን ጣል አድርጋ ትኩረቷን ሰጠቻቸው። ከመነኩሴው አጠገብ የተቀመጠው ጎልማሳ ንስሃ እየገባ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልወሰደባትም። የዝሙት ኅጢያት እንደሚያስቸግረውና እህቱን አንድ አሸከርካሪ ገጭቶ ለዕልፊት እንደዳረጋት እና ከፍርድ ሂደቱ አስቀድሞ እሱ በስለት አንገቱን ደጋግሞ በመውጋት እንደገደለው፤ ያንም ካደረገ እለት አንስቶ፤ የበቀል ስሜት ከሀዘኔ ያሳርፈኛል ብሎ ያንን ቢያደርግም ህሊናው ግን ረፍት እንደነሳው ሲናገር ሰማች። አማተበችና ለመነሳት ሞከረች ግን መልሳ ተቀመጠች።

ቀጠለ አባ በስሜት የፈጸምኩት ወንጀል ሁለት ነፍስ ያላወቁ ህጻናትን ያለ አባት እንዳስቀረ ያወኩት በቅርብ ነው። በድብቅ የምችለውን እየረዳኋቸው እገኛለሁ እሱ ግን ቁሳዊ ነው። አባታቸውን አይመልስላቸውም። ጸጸቱ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም፤ ማልቀስ ጀመረ። መነኩሴውም ልጇ እንባ የንስሃ እናት ናት። ቤተ ክርስቲያንም እንደ ጴጥሮስ ያለ እንባ ስጠን ብላ ትጸልያለች። በኦሪት አትግደል፤ የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል፤ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና፤ ተብሎአል። ይህ ኦሪት ነውና ተሽሮአል። አትግደል ግን ለዘለዓለም ናት። ጌታም በወንጌል እንዲህ ሲል አጽንቶአታል፤ ለቀደሙት 'አትግደል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ 'የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል'። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም 'ጨርቃም' የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ 'ደንቆሮ' የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።

ሀዋርያው ዮሐንስም በመልዕክቱ፤ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ ብሎአል። ስለዝሙቱም ቢሆን፤ ጠቢቡ ሰሎሞን ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮው የጐደለ እንደሆነ ነግሮናል። ጌታም በወንጌሉ አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል። ብሎ ሕግ ሰርቷል። ስላልቻለ እንጂ ወደእሷ ይገባ ነበርና። ዝሙት አሁን የዚህ ዘመን ልጆች እንዳቀለላችኋት ያለች ታናሽ ኅጢያት አትምሰላችሁ። ሰውነትን ሁሉ የምታሳድፍ የኅጢያት ራስ እንጂ። በእንዲህ ያሉ መተላለፎች ከተሞች በዲን እሳት ጠፍተዋል። ልጇ ጌታ ግን ድካማችንን ያውቃልና ንስሃን ሰርቶልናል። መተላለፍን እንጂ ተላላፊውን አይጠላምና። ወደ አርዮን ሚስት ቤርሳቤህ

ገብቶ ካነወራት በኋላ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፤ መዝሙረኛው ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ብሎአል። አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኀጢአቴም አንጻኝ። ኢሳይያስም ቢሆን በትንቢቱ፤ ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኀጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች። ብሎአል።

የሀዋርያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስም በሰሎሞን ቤተ መቅደስ መመላለሻ እንዲመላለስ ያን ነዳይ ሽባነቱን ከተረተረለት በኋላ ለሕዝቡ፤ እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኀጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። ብሎ አሳስቦአል። ዐየህ የኔ ልጅ በማርያም ስጋ እየበላ፣ እየጠጣ፣ እየተኛ የእሷን ባህሪ ባህሪው አድርጎ፤ በፈጠራት ሰው የተገለጠው የዓለም ፈጣሪ፤ በድክመታችን ሊያግዘን፣ ከኀጢያታችን ሊያጥበን፣ ከበደላችን ሊያነጻን የታመነ ነው። ግን አስቀድሞ የእኛን ፍቃድ ይጠይቃል። የግዳጅ አምላክ ሳይሆን የነጻ ፍቃድ አምላክ ስለሆነ። ልትድን ትወዳለህ? ብሎ ጠይቆ እንጂ በግድ አይፈውስህም! አንተም አሁን ልድን እወዳለሁ ጌታዬ ብለህ ደጁ መጥተሃል። እንኳን ቤቱ ድረስ መጥተህ አይደለም፤ በየደጃችን ቆሞ በራችንን በማንኳኳት የሚኖር ሩህሩህ አባት ነው ያለን!። እኛ ግን የልባችንንም የደጃፋችንንም በር ዘጋንበት። እሱ እንደሆን ማንኳኳቱን አይሰለች። እንደበደላችን አልፈረደብንም እንደ ምሕረቱ ይቅር አለን እንጂ። ሁላችን በድለናል፤ ቁጣውን ቀስቅሰናል፤ ከመንገዱ ፈቀቅ ብለናል። ስለዚህ የአሕዛብ መሳለቂያ አድርጎናል። እንመለስ እሱም ወደ እኛ ይመለሳል። ይህን ሲናገሩ አይከል ተነስታ ቦታ ቀየረች። ከቆይታዎች በኋላ መነኩሴው ተነስተ ወደ መቅደስ ሲገቡ

እሱ በነበረበት ቁጭ ብሎ በማየቷ ተነስታ አጠገቡ ተቀመጠች።

ይቅርታ ጥፋት እንዳጠፋው ይገባኛል አፍሬያለሁም። መስማት የሌለብኝን ነገር ሰምቻለሁ። ግን አንድ ጥያቄ ብጠይቅህ ፍቃደኛ ነህ አለችው። ጎልማሳውም ግራ በመጋባት ዐይን እየተመለከታት ዝም አለ። ቅድም ከአባ ጋር ስታወሩ በቅርበት ስለነበርኩ ስትል፤ በድንጋጤ ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሣ። አይከል አብራው በመነሳት እመነኝ እኔ ካንተ የከፉ ብዙ ጥፋቶችንን አጥፍቻለሁ። ልብህ እና ድፍረትህ ስላስደነቀኝ ነው ጥቂት ላማክርህ የመጣሁት እባክህ ተረዳኝ I didn't mean you any harm አለችው። እንዴት እንዲህ ያለ ስህተት ትሰሪያለሽ? ለሃይማኖቱ አዲስ ነሽ? አላት። i wish i were ብላ አንገቷን አቀረቀረች። መራመድ ጀመረና ተመልሶ ተቀመጠ። የሰማሽውን ለማንም መናገር እንደሌለብሽ ላሳስብሽ እፈልጋለሁ! That's why I came back. Even your face is not forgettable አላት። Don't worry, I won't even think about it again. አለች እንዳቀረቀረች።

አብዛኞቻችን ለእግዚአብሔር የምንገልጠውን እኛነታችንን ደግመን ማሰብ አንፈልግም፤ እንኳን በሰዎች ዘንድ እንዲታወቅብን። በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፣ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ፤ የሚለውን የንጉሥ ዳዊትን ጸሎት ሁል ጊዜ እጸልያለሁ። አይከል ፈገግ አለች። ምነው? ብሎ ጠየቃት። አንድ ወዳጄ ትዝ ብሎኝ ነው። እንደ ሥሙ ሀገሪቷን ሊያነጻ ነው ትግሉን የተቀላቀለው? እራሷን ጠየቀች። ቀጥል አለችው። ቀጠለ፤ ንስሃ እገባለሁ መልሼ እበድላለሁ፤ ነገር ግን በፍጹም ከእግዚአብሔር ቤት አልርቅም። በበደልኩ ቁጥር፤ የበደሉንን በቀን ስንት ጊዜ ይቅር እንበላቸው

ሰባት ጊዜ ነውን? ብለው ሲጠይቁት፤ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ ብሎ ጌታ የመለሰላቸው መልስ፤ በጆሮዬ ስለሚያቃጭል። ቂመኛውን ሰው እንዲህ ብሎ ከአዘዘ፤ እሱ ሩህሩሁ እማ እንዴት አብልጦ ኣይምረን? አብዛኞቻችን ለንስሃ ቀጠሮ እንሰጣለን። ዘለን፣ ተራግጠን፣ ጨፍረን፣ አምንዝረን፣ ገድለን፣ ሰርቀን ሲሰለቸን ነው ወደ እሱ መቅረብ የምንፈልገው።

ንስሃ ስንገባ ዓለም የምታበቃ ይመስለናል። ግን ያን ጊዜ ነው የምትጀምረው። ገና ጎጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። በፊቱ ቆመሽ ጎጢያተኛ ነኝ፣ ደካማ ነኝ፣ ጎስቋላ ነኝ፣ አላዋቂ ነኝ፣ አመንዝራ ነኝ እና የመሳሰሉትን ቃላት በመጠቀም እራስሽን ልትወቅሺ ትቺያለሽ። ሌላ ሰው ግን ከነዚህ ያነሱ ቃላትን ቢጠቀምብሽ ለጸብ ትጋበዣለሽ። ከቃል በዘለለ ልባችን ስለማይሰበር ይመስለኛል። ከልብ በሆነች ቃል ግን የምናያት ዓለም ከነመላዋ ተፈጥራለች። ቃል ኃይል አላት። ትገድላለችም ታድናለችም። ርግማን የለመደ ገላም ሆነ መንፈስ፤ ጨለማ ነው። በጎን የሚናገር፤ መንፈሱም ስጋውም ብሩህ ነው። በልቦናችን የሞላው በአፋችን ይፈሳልና። አስደነገጥኩሽ መሰለኝ ይቅርታ አላት። በደሌን ልታብሰው ነው ጥፋተኛዋ እኔው ሆኜ ሳለሁ ይቅርታ የምትጠይቀኝ? እንደዚያ ኣይደለም እኔ አዲስ ሰው መሆን እፈልጋለሁ፤ ለዚያ ነው፤ ያለፈው ማንነቴን እንደ ድሪቶ አውልቄ ጥዬ በክርስቶስ አዲስ ልሆን እናፍቃለሁ አላት።

አዲስ መሆን እንዴት ይቻላል? ጠየቀች ታሪኮቻችን፣ ድርጊቶቻችን፣ ጎጢያቶቻችን፣ ሀሳቦቻችን፣ ልማዶቻችን ከእኛ ጋር እያሉ እንዴት? ልብስ ቢሆን አውልቀህ አርቀህ ትጥለዋለህ፤ ገላህን ታጥበህ ከእድፍ ታነጻዋለህ፤ መንፈስህን፣ ልብህን፣ አዕምሮህን ምን ታደርገዋለህ?

ገላዬን ስታጠብ ሁል ጊዜ ይህን አስባለሁ፤ ገላዬስ በሳሙና ነጻ፤ ልቤስ? እላለሁ። ምግብ ስበላ አንጀቴስ ሞላ፤ በሰው ተከቦ ሰው የራበው እኔነቴስ? ፍቅር የራበው መንፈሴስ? በምን ይሙላ?

አዲስ ማንነት ዳግም ልደትን ይጠይቃል መለሰ። ይህን እንግዳ የመሰለ ጽንሰ ሐሳብ ጎጥያትህ ተሰረየችልህ ከሚለው ቀጥሎ ማለቴ ነው፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጸው ጌታችን እራሱ ነው። በዚያም ወቅት የነበሩ ሰዎች ይህስ ጭንቅ ያወራል እስከ ማለት ደርሰው ነበር። ዳግም ውልደትን በሥጋ አስበውታልና፤ ሰው ከአረጀ በኋላ እንዴት ከእናቱ ማዕጸን ይወለዳል? ብለውም ጠይቀውት ነበር። ከመንፈስ የሆነው ግን በመንፈስ ጀምሮ በመንፈስ ይቋጫል። ይህ አዲስ ሰውነት የሚገለጸው በሥም ነው፤ የብዙሀን አባት የተባለውን አባት ተመልከቺ፤ አባቱ ያወጣለት መጠሪያ አብራም ነበር፣ አምላኩ ማን አለው? አብርሃም። ሚስቱ ሶራም ሳራ ተባለች፤ የልጅ ልጁን ያዕቆብን ውሰጂ ለውጦ ማን አለው? እስራኤል። ሀዋርያው ጳውሎስ ማን ነበር? ስምኦን። ሳኦልን ደግሞ ጳውሎስ አለው። እንዲህ እያልን ብዙ መጥቀስ እንችላለን።

ቤተ ክርስቲያንም ይህን ሚስጥር ተርጉማ ነው በጥምቀት አዲስ ሥም የምታወጣው። ይህ የሚሆነው ለምን ይመስልሻል? ቀጥል አለችው። ሥም የማንነትን ጨምሮ የባህሪ መገላጫ ስለሆነ። በዚህ መንገድ ካልሆነ እግዚአብሔር ሥም የለውም። 'እግዚ' ማለት ገዥ ማለት ሲሆን 'አብ' ማለት ደግሞ አባት ማለት ነው። 'ብሔር' ማለት ደግሞ ሀገር፣ ግዛት፣ ነገድ እንደ ማለት ነው። ሥሙ ባህሪው ነው። ሥላሴ ስንል ምን እያልን ነው? በግዕዝ ቁጥርን ተሰልሶ ነው። ስለዚህ ሦስት እንደሆኑ እየተናገርን ነው። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ከሆነ፤ መድኃኒተ ዓለም ስንለውስ? አብ ማለት አባት ወልድም

ማለት ልጅ፤ መንፈስ ቅዱስም የቅድስና መንፈስ። ሚካኤል ስንል 'ኤል' አምላክ ማለት ነው። ሚካ ማለት 'ማን እንደ' ማለት ነው ሚካኤል ስንል ማን እንደ አምላክ ማለታችን ነው። ይሄ ምን ያስረዳናል? ሥም ኃይል እንደሆነ፤ ለዚያ ነው ጌታ ሲጠራ አብዛኛውን ጊዜ ሥም ከመቀየር የሚጀምረው። አንድ ማሳያ ልጨምርልሽ በቤተ ክርስቲያን ሃዋርያው ዮሐንስን የሚያህል ባለ ብዙ ሥም የለም። ወልደ ዘብዲዎስ፣ አቡቀለምሲስ በግሪክ ባለ ራእይ ማለት ነው፣ ቦኤር ኔጌስ የነጎድጓድ ልጅ ማለት ነው፣ ታኦ ሎጎስ ይሄም ነባቢ መለኮት እንደ ማለት ነው፣ ቁጽረ ገጽም ሥሙ ነው፤ የጌታውን ህማማት በሙሉ በቅርብ ሆኖ እስከ መስቀል ድረስ አይቶአልና ከዚያ ጀምሮ ፊቱ በሃዘን እንደተኮማተረ ህማሙን እያሰበ በለቅሶ ኖሮዋል፣ ፍቁረ እግዚም ይባላል ጌታ ይወደው ስለ ነበረ፤ በዚህ ምድር ሕይወቱ ሁሉ ጌታን ለመምሰል ይጥር ስለ ነበር ጌታ አብዝቶ ይወደው ነበር። አንድ ቀን ጌታ መታጠቂያውን ፈቶ ባስቀመጠበት አንስቶ በመታጠቁ፣ የዚህች አላፊ ጠፊ የሆነች ዓለም ፍትወት በሙሉ ጠፍቶለት ኑሮው እንደ መላዕክት ሆነ።

በዚህች ዓለም ለዘጠና ዘጠኝ ዓመት ኖሮዋል፤ ሞትን ግን አልቀመሰም። የጌታን ስቅለት ስዕል ለመጀመሪያ ጊዜ የሳለው እሱ ነው! አሁን የምናውቀውን የሆሊውድ አክተር Jim Caviezel ፎቶ አይደለም! የዚህን ግለሰብ ፎቶ በፍጹም ክርስቲያኖች መጠቀም እንደሌለባቸው አብዝቼ እሟገታለሁ! መቆም አለበት! ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ የስዕል አሳሳል ሕግ እና ጥበብ አላት። ቅዱሳን በምን መልክ መሳል እንዳለባቸውም ሆነ ኃጥአን በምን መልኩ እንደሚሳሉ ይታወቃል፤ ማንም ተነስቶ የፈለገውን ስዕል ከልቦናው አመንጭቶ መሳል አይፈቀድለትም! መንፈስ ቅዱስ የመራው ብቻ ሱባኤ ይዞ ይስላል እንጂ! የሊቀ መላዕክቱን የቅዱስ ሚካኤልን ምስል ተመልከቺ፤ በነገርሽ ላይ አብዝቼ ነው የምወደው

ጠባቂዬም እሱ ነው! እንብርቱ እየታየ በቻይናዎች የተሳለ ምስል በምን አግባብ ነው ልንጠቀም የምንችለው? እንኳን በኃያሉ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ቅዱሱ የመላዕክት አለቃ ይቅርና ተራ የተባለ ጎጥ እንኳን እንደዚያ ያለ አለባበስ አይለብስም! እሱ ነጭ ሆኖ የረገጠው ሰይጣን የአፍሪካዊ ቆዳ አለው ለምን? ምን ለማመልከት ተፈልጎ ነው? ቀደምቶቹ የተዋህዶ ምስሎች እንዲህ አይደሉም! ቤተ መቅደስ ንብተሽ ተመልከቺ ሁሉም በሥርዐት እና በአግባቡ የተሳሉ ናቸው! በየዋህነት የምናደርገውን እግዚአብሔር ከበደል አይቆጥርም ነገር ግን መቆም አለበት! የቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ምስል በሙሉ መጠቀም የለብንም!

ዳግም ውልደት በአዲስ ሥያሜ ከጀመረ፤ ልብ እና መንፈስ ደግሞ በቃሉ በመታጠብ ይነጻል። ገላሽን በሳሙና እንደ ታጠብሺው ያለ መታጠብ አይደለም። በእሳት እንጂ። በድለሺኝ ይቅር እንዳልኩሽ ካወቅሽ፤ ልብሽ እረፍት ያገኛል። ቃሉ በልብሽ ሲገባ ክፋት እና ጽልመት ቦታውን እየለቀቁ ይመጣሉ። ብርሃን ከጨለማ ህብረት የለውምና። በልብ መታደስ፤ አዲስ ማንነት ይሰጥሻል። ይህ አይነቱ መታደስ እንደ አዲስ ይወልድሻል፤ መንግሥተ ሰማያትን በምድር እንድትኖሪያት መንገድ ይሆንሻል። ሁሉን አዲስ ሊያደርግ የታመነ ጌታ ከእኛ ጋር አለ። ከጎጢያት በቀር እንደ እኛ በሁሉ ስለተፈተነ፤ በድካማችን ይራራልናል።

ጎጢያት ደሞዟ ሞት ነው። ይሄም ማለት ጎጢያትን ያልሠራ ሞትን አይሞትም ማለት ይሆናል። አባታችን አዳም ከሚስቱ እጸ በለስን በመብላቱ አይደለም ጎጥያት የሠራው። የእግዚአብሔርን ቃል ጥሎ የሰይጣንን ቃል በማመኑ እንጂ። አብርሃምን ስትመለከቺው የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ ጽድቅን በመሥራት በድርጊት ፈጸመው። ይህም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ

ተቆጠረለት። አዳምም ሲይጣንን አምኖ፤ እምነቱን፤ በመብላት ድርጊት ፈጸመው። ይህም ኅጢያት ሆነበት። ደም'ወዙ ሞትንም ተቀበለ። በዚህም ምክንያትነት ሞት ወደ ዓለም ገባ። ይህ ሞት የዘለዓለም ቅጣት ሆነ። ታዲያ ይሄን የዘለዓለም ቅጣት እንዴት እናምልጠው? ጽድቅ እንዳንሰራ ጽድቃችን እንደመርገም ጨርቅ ተቆጠረ።

የጽድቅ ፀሃይ የሆነ መሲዕ ያስፈልገን ነበር። ያለ ደም ስርየት የለም። ስለዚህ ለኅጢያት ስርየት፤ ንጹህ የሆነ እንስሳ ለሊቀ ካህናቱ ያቀርቡ ነበር። እጃቸውንም በግንባሩ በመጫን፤ ኅጢያታቸውን ወደ እንስሳው በማዘዋወር ደሙን ያፈሱታል። ለእነሱ መተላለፍ መሥዋዕት ይሆናል። በዚህ መልኩ ስርየት ይፈጸማል። የሕዝቡን ኅጢያት የሚያስተሰርይ ሊቀ ካህኑም በዐመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል። ነገር ግን ይህ ሥርዐት ዓለሙን ሊያነጻ አቅም አልነበረውም። የዓለሙን ሁሉ ኅጢያት በእራሱ ሊሸከም ወደ ዓለም በፍቃዱ የመጣው መሲዕ፤ በመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ እጅ በመጠመቁ፤ እጁንም በጭንቅላቱ ላይ አድርጎ ስለ አጠመቀው፤ ልክ እንደ መሥዋዕቱ እንስሳ ኅጢያታችንን ተሸከመ። እንደ እንስሶቹ የአንድን ሰው ኅጥያት ያይደለ፤ የዓለሙን ሁሉ እንጂ። በመስቀል ላይ በመታረድ ለኅጢያታችን መሥዋዕት በመሆን እኛን አነጻን። የእግዚአብሔር ሞኝነት ከጠቢባን ጥበብ ትበልጣለችና። ፈጣሪ በፍጡራን እጅ እስኪሞት እንዲህ ያለውን ፍቅር ሰጠን። እንደ ሰቀሉት ሞኖ፣ ተቀብሮስ ቢቀር ይህ ሁሉ ለከንቱ በሆነ። ነገር ግን የተዘራ ስንዴ ተቀብሮ እልፍ ሆኖ እንዲበቅል ያለ፤ ለሕይወት የሆነ ትንሳኤን በገዛ ሥልጣኑ ከሙታን መካከል ተነሣ።

በዚህም መሰረት በጥምቀት ለኅጢያት ሞተን፤ ለጽድቅ እንነሳለን። በሞቱ ከተባበርነው በትንሳሄውም እንድንመስለው እናውቃለን። መሲሁ ከመርገም የምንነጻበትና የዘለዓለም ሕይወት የምናገኝበት፤ እውነተኛ

መንገድ እና ብርሃን ነው። መሲሁ የሌለው ሕይወት የለውም የምንለው እንዲሁ ለሃይማኖት ማድመቂያ አይደለም። ያለ እሱ ደም ከኅጥያት መንጻት የሚቻለው አንድም ፍጡር ስለሌለ ነው። እንዲም ይባላል "አብ ባለሞያ ነው ድግስ ያውቅበታል አንድ በግ ሰውዶ ዓለም ጠግቦበታል" እንደ ኦሪት በእንስሳ ደም እነጻለሁ የሚል፤ የበለጠውን ንቆአልና፤ የአባቱንም ምስክርነት አቃሎአልና፤ ቅጣቱ የከፋ ይሆናል! የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ ሀሳቡና መሻቱ ጋር ሰቀሉት እንደተባለ። ኅጢአትን ንቀሽ ከጽድቅ ትዋደጃለሽ። ከዚህ ወዲህ በክርስቶስ ለሆኑቱ መርገም የለም! ተወግዶአል። ይህ ተግባራዊ የሚሆነው እንደ ሥጋ ምኞት ሳይሆን በመንፈስ ለሚጓዙ ብቻ ነው። አዲስ ሰው የመሆን ሚስጥር ይሄ ነው። በሥጋ ሀሳብ አዲስ መሆን አይቻልም! ለዚያም ነው በየጊዜው ለውጥ እንደሚያስፈልገን ለእራሳችን ደጋግመን እናወራለን። ቃልም እንገባለን፤ ይህን፣ ይህን አቆማለሁ። ይሄን፣ ይሄን ደግሞ እጀምራለሁ እንላለን ከቃል የዘለለ የድርጊት ለውጥ ግን አናመጣም።

አዲስ ማንነት ዳግም ውልደትን የሚጠይቀው ሟቹን ሰውነት ለማትሞተው ነፍስ ለማስገዛት ነው። ፊቆሮስ በመባል የሚጠራው ፈላስፋ በዚህ ጉዳይ አብዝቶ ይብሰለሰል ነበር። ይህን ሀሳብ የሚቀበል በጊዜው በግብጽ ስክንድርያ ይመለክ የነበረን ሴራቪ'ስ የሚባል ጣኦት የሚያመልክ፤ ዮስጣጦስ የተባለ የመጽሐፍት መምህር ነበረ። አንድ ቀን እንደ ልማዳቸው፤ በአደባባይ ቆሞ ስለ ሞት እና ከዚያ በኋላ ስለሚኖረው ሁኔታ ለተሰብሳቢዎቹ፤ ሰው ምዋቲ እንደሆነ ከሞት በኋላ ምንም እንደሌለ ያስተምራል። የሀዋርያው ማርቆስ ደቀ መዝሙር የነበረው ሊሲዳድ፤ የፊቆሮስ ፍልስፍና የሚያተኩረው በአካል ወይም በሥጋ ላይ ብቻ እንደሆነና ይህ ገኦድ እና እውነታን ስለሚፈልግ እንደ አንድ አካላዊ

ሰው ልክ መሆኑን ግን መንፈሳዊነትን የዘነጋ፤ ከነፍስ ያልሆነ ዕውቀት እንደሆነ ገልጾለት ያስረዳዋል።

ነፍስ ስትል ምን ማለትህ ነው? ብሎ ይጠይቀዋል ዮስጣጦስ፤ ሊሲዳስም ነፍስ የሥጋ ወይም የአካል ህልውና መገላጫ እንደሆነች፤ አካል ህያው ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችለውን ኃይል የምትሰጠውም እሷ እንደሆነችና ነፍስ የበላይ የሆነችለት ሰው፤ መልካም ምግባር እንደሚኖረው፤ የሥጋን መሻት ያስቀደመ ግን በዐይኑ ጦር ነፍሱን እንደሚወጋ፤ የሥጋ መሻትም ጸብ፣ ክርክር፣ ክፋት፣ አለመታዘዝ፣ ትዕቢት፣ ዝሙት፣ ቅናት እና የመሳሰሉት እንደሆኑና ሥጋ መዋቲ መሆኗን ነፍስ ግን ወደ ፈጠራት እንደምትሄድ እና ዘላለማዊ መሆኗን አስረግጦ ተከራከሮት ነበር። በመጨረሻም በዳግም ውልደት አዲስ ሰው ሆኖ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እስከ መሆን የደረሰው።

Trauma የተሸከምን አንበዛም? በሕይወታችን ባልተከሰተ የምንለው፣ ልንረሳው የምንፈልገው፣ ብዙ አለን፤ እነዚያ ጉዳዮች በቀጥታም በተዘዋዋሪ አሁን ያለው እኛነታችንን ቀርጸውታል። ፍራቻዎቻችንን፣ ስጋቻችንን፣ ጭንቀቶቻችንን ምን ወለዳቸው? ከየት አመጣናቸው? በጥልቀት ወደ ኋላ ብንመለከት መንስሄዎቹ ጋር እንደርሳለን። ምናልባትም በገሀዱ ዓለም የሌሉ እኛ እራሳችን የፈጠርናቸው ሊሆኑም ይችላሉ። አዲስ አልያም ሰው የተሰበሰበበት ቦታ ስንገኝ ምን ይሰማናል? ዐይኖች ሁሉ እኛን የሚያዩ ይመስለናል። ሁሉም በስፍራው የተገኙ ታዳሚዎችም እኛ እንደምናስበው ነው የሚያስቡት። እራስችን በፈጠርነው ጉዳይ ልንጨነቅ እንደምንችል አንዱ ማሳያ ነው። በእኛው ጥፋትም ተወቃሽ ያደረግናቸው ሰዎች ይኖራሉ፤ መለስ ብለን እራሳችንን ከማየት እንጀምራለን? አዲስ ማንነት ረፍት

ይሆንሻል፤ እራስን ማወቅን፣ በሁኔታዎች ተጽኖ ውስጥ ከመግባት ይልቅ መቆጣጠር ሲታከልበት።

አዲስ አእምሮ ስትዪ አንድ ክስተት አስታወስሺኝ። ቶማስ ሃርቪ የሚባል pathologist ነበረ፤ አልበርት አንስታይን በሞተበት በእነሱ 1955 በሠራው ድርጊት በጣም ዝነኛ ሆኖ የነበረ። ታውቂዋለሽ? አይ! ምን መሰለሽ የሠራው፤ አንስታይን ከሞተ በኋላ ሃርቪ የአስከሬን ምርመራ አኪያሂዶ ከአንስታይን ቤተ ሰብ ፍቃድ ሳይሰጠው፤ በድብቅ ለአሥርት ዓመታት አንጎሉን ይዞ ቆየ። የኛም ነገሥታት ከነበሩት አንዱ ላይ ተሞክሮአል። ብዙ ሰዎች የአንስታይንን ፍላጎት ጥሶአል ይህ ክብረነክ ድርጊት ነው ብለው ወቀሳ ሰንዝረዋል። እሱ ግን ምርምሩን ቀጥሎ ነበር። አንዳንዶች የእሱ ምርምር ጠቃሚ እና ስለ ሰው አእምሮ እንድንረዳ አስተዋጽኦ አድርጓል ብለው ይከራከራሉ። የሆነው ሆኖ ይህ ሰው አክቹአል በሆነ የሰው አእምሮ ጥናት ሲያከናውን ሰንብቷል። አይከል ይቅር እየዘገነነኝ ነው ብላ አስቆመችው።

ይልቁንስ ቅድም ስትናገር አንድ ጥያቄ መጣብኝ። ለምንድነው የምንፈልገው ሁሉ የሚነጠቀን? እንዴት ሰው ስሜት አልባ ሊሆን ይችላል? ሰው ውስጡ በድን፣ ኃይል አልባ ሲሆንስ የሚል አልገባኝም አላት። አቅም አጥተህ ታውቃለህ? ውስጥህ ዝም ብሎብህ ያውቃል በቃ የሀሳብ ጋጋታ አይደለም ላስብ ብለህ ማሰብ ያቅትሀል፤ ልታዝን ትሞክራለህ ወይ ልትደሰት ግን ስሜት አልባ ትሆናለህ፤ ልክ ትኩስ ፈሳሽ ምላስህን ሲለበልብህ ያን እለት ምላስህ ጣእምን መለየት እንደሚያቅተው ማለት ነው። ቅዝቃዜ አለ አይበርድህም፣ ፀሀይ ትግላለች አይሞቅህም፣ ሆድህ ባዶ ነው አይርብህም፣ ማልቀስ ትፈልጋለህ አታዝንም፣ መሳቅ ትፈልጋለህ ቢያንስ በልጆችህ ፊት ግን አትደሰትም፣ ማውራት ትፈልጋለህ

አንደበት አይኖርህም፣ ትተኛለህ አታርፍም፣ ትራመዳለህ አይደክምህም፣ ውስጥህ በድን ይሆናል ነፍስ ስንት ሕይወት እንዳላት ትጠይቃለህ መልስ አይኖርህም ታዲያ ሞት ከዚህ በምንድነው የሚለየው? አፈር ስለሚጫንህ? ስለማትንቀሳቀስ? መኖር እና መሞት ተቃራኒ ከሆኑ እንዴት ሞተህ ትኖራለህ? ነው ወይስ ሞት ማለት መቀበር ነው? ነፍስ ሞትን አታውቀውም በነፍስ ሞት የለባትም ሞት ያለባት ይህች ስጋ ናት ስጋ ደግሞ መገለጫ እንጂ መኖሪያ አይደለችም ለዚያ መገለጫህ አፈር ሲጫነው ከሰው ዐይን ትሰወራለህ ያኔ ሞትክ ይሉሀል ያዝኑልሀል ያለቅሱልሀል አንተ ግን ያው ሳትዳሰስ ሳትጨበጥ ለዘለዓለም ትኖራለህ።

በህልም ሁሉንም ሰው ብትጠይቀው ሲሞት ይነቃል ለምን ይመስልሀል? ከሞት በኋላ ምን እንዳለ አይምሮህ ስለማያውቅ ነው፤ ከዚህ ስቃይ ብገላገል ብዮ የወሰንኩባቸው ቀናት አሉ፤ አንድ አንዶቹ ስለልጆቼ ብዮ ውሳኔዮን የሰረዝኩባቸው፤ እነሱ የመጀመሪያዎቹ ሰሞኖች ናቸው መቋቋም እያቃተኝ ሲመጣ ግን ጫፍ ደርሼ የተመለስኩት በአንድ ሀሳብ ነው በዛኛው ዓለም ምን እንደሚጠብቀኝ እርግጠኛ ባለመሆኔ እስከ ትላንት ማታ እኔ የምትራመድ ልቧ የሚመታ ሲያቅፏት ሙቀት የምትሰጥ የቁም እሬሳ ነበርኩ። አ አምላኬ አለች እና ይህን ለምን እንደማወራልህ አላውቅም ይቅርታ ብላ የጀመረችውን አቋረጠችው። አይዞሽ ምናልባት ከእኔ እና ከአምላኬ በቀር ማንም የማያውቀውን የልቤን ጉዳይ መስማትሽ ይሆናል ነጻነት የሰጠሽ ብሎ ትከሻዋን ሦስት ጊዜ ቸብ ቸብ አደረጋት። ለካ ያ ትምህርት ቤት ስንሄድ እለት እለት የምንሸከመው ከባዱ ቦርሳ የህይወታችን ቀላሉ ሸክም ነበር፤ ተደግፋው እንባዋ ይወርድ ጀመር። ሁል ጊዜ ተደግፈህ የምታለቅስበት ትከሻ አታገኝ ይሆናል ለፀሎት የምትንበረከክበት ስፍራ ግን አያሳጣህ። አባበላት።

የኔ ይመስለኝ ስለ ጀመር አንድ ታሪክ ላውራሕ። ነብዩ ሆሴዕ ጋለሞታ የተባለችን ጎሜር እንዲያገባ ታዘዘ፤ በጣምም ይወዳት ነበር። ይህ ስም ለምን ይምስልሃል የተሰጣት አንድ አንድ ምሁር ነን ባዮች እንደሚሉት እኛም እንደምናስበው የአካል ግልሙትና ያለባት እንዳይመስልህ ጋለሞታ የተባለችው ጣኦት ታመልክ ስለነበር ነው። ሆሴዕ የስሙ ትርጓሜ መድሃኒት ማለት ነው ከቅድሙ ጋር እንዳይምታታብህ። የክርስቶስ ምሳሌ አድርገው፣ እሷን ደግሞ የኛ፣ ኃጢያት መሥራት ግልሙትና እንደሆነ ታውቃለህ። በዚህ ትርጓሜ፤ እኛን ጋለሞታዎችን አገባን ማለት አይድል? ክርስቶስ ገና ሀጥያተኛ ሳለን ወደደን ሊያነጻንም የታመነ አምላክ ነው ካልን፤ በጥምቀት ከሱ ጋር አንድ ከሆንን በኋላ ወደ ኃጢያት ስንመለስ ለሥም ኣጠራሩ ክብር ይግባውና የጋለሞታ ሚስት እያደረግነው ነው። ለመስማት ይዘገንናል አይደል? ድርጊቱ ግን ያስደስተናል። ሆሴዕ ከጎሜር ሦስት ልጆች ወልዶአል የመጀመሪያው ኢይዝራኤል ይባላል በዚህ ቦታ አጠፋቸዋለው ማለት ነው። ሁለተኛዋ ሎሩሃማ ትባላለች ምህረት የሌላት ማለት ነው። ሶስተኛውም ሎኣሚ ይባላል ሕዝቤ ያልሆነ ማለት ነው። ሆሴዕ መድኃኒት ሆኖ ለምን ልጆቹን እንዲህ ሰየመ? ነፍሳችን ወደ መድኃኒቷ ካልተመለሰች እንዲህ መባሏ እሙን እንደሆነ ሲያስረግጥ ነው። ኦሪትን ልሸር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ ብሎአልና ጌታ። እግዚአብሔር በአንድም በሌላ ይናገራል። እውነት ትመራለች ለዚያ ነበር የእግዚአብሄር የሆኑትን እያሳደዱ የሚያርዷቸው። በኃጢያት ምክንያት ቅዱሱን እያረከስኩት ያለሁ ይመስለኛል።

የልጆቼ አባት ሳይሰናበተኝ ለዘለዓለም ከተለየኝ በኋላ የማላውቀው ባዶነት ከብቦኛል። እውነተኛ ፍጻሜዎች ስንብት እንደሌላቸው ተረድቻለሁ። በሥጋ ምድር ላይ እያለ ሰላም የማይባባለው ሰው አሁን ባለ ቤቴን የጻድቅ ስፍራ ሲሰጠው ታዝቤአለሁ። ስንሞት እንጂ በሕይወት

እያለን ዘወር ብሎ ያላየን ስንሞት ገድል ካላጻፍንላቸው ብሎ የአዞ እንባ ማንባትን ምን ይሉታል? በችግሩ፣ በሀዘኑ፣ በደስታው ያልደረስንለትን ሰው ሞተ ተብሎ እንዲህ መሆን ምን ይሉታል? ከሞተ በኋላ ጻድቅ ነው፣ ቅዱስት ነበር ብንለው ለእሱ ምን ይጠቅመዋል? መደጋገፉ ላይ ልከ ብለሻል፤ በቁም ስንጠያየቅ በችግር፣ በሀዘን፣ በደስታም ስንደጋገፍ መልካም ይሆናል። የዘነጋሽው ነገር አሁን የምትያቸው ሁሉ በማህበረሰባችን ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ክንውኖች ናቸው። እየተደረጉም ይኖራሉ። አሁን ቀዝቅዞ ይታያል ለምን? የሚለው ይመስለኛል ተገቢው ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ እራሳችንን ከማየት መጀመር ይኖርብናል፤ እኔ ጋር ሰው ለምንድነው የማይመጣው? ድብቆች አልሆንም ግለኝነትን አብዝተን ብቸኝነትን ወደ ህይወታችን አልጋበዝንም? ችግራችንን ብናወያየው ለሌላ አሳልፎ ይሰጠናል፣ ጓዳችንን ቢያውቅ ይታዘበናል ብለን ከቤታችን ከህይወታችን የኛ የሆኑ ሰዎችን ጭምር አልገፋንም? ለምን ምክንያቱም እኛም እንደዚያው ስለሆንን ሚታመን ጠፋ፣ የልብ ጓደኛ ጠፋ እንላለን፤ እኛስ ታማኝና የልብ ጓደኞች ነን? እርግጥ ነው ታምነንለት የከዳን ይኖራል እነዚህ ሰዎች ልብ ብለን ካየናቸው ከመጀመሪያውም የሚሰጡን ምልክቶች አሉ ያውም ብዙ።

መነጽራችንን ማስተካከል እና እንደ እባብ ልባሞች እንደ እርግብም የዋ መሆን ይኖርብናል። በመንፈስም በሥጋም ጠንካሮች፤ ዓለም የሁለቱም ውህድ ናትና። አንዱን ጥሎ ኑሮ የለም እና በሁለት የተሳሉ ሰይፎች ሆነን በጥበብ መመላለስ ይገባናል። ሌላው ያነሳሽው ጥያቄ እጅግ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነው፤ እንደዋዛ ነው የተመለከትሺው። ሰው በዚህ ምድር እያለ ማመስገን

ተገቢ ሆኖ ሳለ ሰዎች ነንና ትላንት የነበርንበት ስፍራ ዛሬ አልያም ነገ ላንገኝ እንችላለን። ዛሬ መልካም ያልነው ነገ ክፉ ይሆናል፤ ትላንት ክፉ ይነበረ ዛሬ መልካም ይሆናል ስለዚህ ክፉም ለመመለስ ለንስሃ ጊዜ ተሰጥቶት መልካሙም በጀመረው መንገድ እሩጫውን እንዲጨርስ ጽናትን ገንዘብ አድርጎ ሁሉም ፍጻሜው ከታየ በኋላ እንጂ እንዲሁ መፈረጁ ተገቢ ስለማይሆን ነው በተለይ በእኛ ሀገር ፍጻሜው የሚጠበቀው። አይከል እግዚአብሔርን አጥብቄ እየፈለኩት ነው አለች፤ እራስ ወዳድ የሆንኩ ያህል ደግሞ ይሰማኛል ቅድም እንደተባለው ያ ሁሉ ጊዜ ሲያንኳኳ የልቤንም የቤቴንም በር ቆልፌበት በደጅ አሳድሬው አሁን ድንገት ግባ ብለው የሚታዘበኝ መሰለኝ።

፡፡ ምን ያህል ጊዜ ሆነው ባለቤትሽ ካረፈ?

፡፡ ጥቂት ወራት ምነው?

፡፡ አሁን መሄድ እንችላለን?

፡፡ አስፈላጊ ነው?

፡፡ በጣም!

፡፡ ይቻላል

ነፋሱ የአይከልን አሳዛኝ የውስጥ ጩኸት ተሸክሞ ባድማ በሆነው መቃብር ውስጥ ማስተጋባቱን ጀመረ። አይከል ምስሏ እየከሰመ ካለው የፀሃይ ብርሃን ጋር በባለ ቤቷ መቃብር ፊት ቆማለች፤ ለወራት ሀዘኗን ሸፍናለች፣ ልቧ እንደ ከባድ ድንጋይ እየተጫናት ከርሟል። ዛሬ ግን

ከቀዝቃዛው እብነበረድ ምልክት ፊት ስትቆም የስሜቷ ግድብ ተፈረካከሰ። እንባዋ በፊቷ ላይ ያለ ማቋረጥ ፈሰሰ፣ እያንዳንዷም ጠብታ ላጣችው ፍቅር መታሰቢያ ነበረች። እጆቿ እርጥበታማውን ምድር እንደያዙ በጉልበቷ ተንበረከከች። በብዙ አነባች፣ አብዝታ አለቀሰች፤ ሰፊ በሆነው የመቃብር ስፍራ፣ ባሏ ብቻውን ያለ መሰላት። እራሷን በአጽናፈ ሰማይ ውስጥ እንዳለች ትንሽ ቅንጣት ቆጠረች። እንግዳው፣ ደግ ልብ ያለው በመሆን ወደ እርስዋ ቀረበ። የሚያጽናና እጅ እና የዋህ ቃል በዚህ ሰዓት መገኘቱ ለቆሰለው ነፍስዋ ፈውስን መገበው። መጀመሪያ ላይ የእሱን ጣልቃ ገብነት የተቃወመችው አይከል እራሷን በእቅፉ ስር አገኘችው።

በነፋሻማው አየር፣ አግዳሚ ወንበር ላይ አብረው ሲቀመጡ አይከል ልቧ ከዳት፣ ቃሏ የሀዘን ስሜት የነበረበት ቢሆንም፤ በትዕግስት ያዳምጣት ነበር። የእሱ በቦታው መገኘት በስሜቷ ማዕበል ውስጥ የሚያጽናና መልሕቅ ነበር። ፀሀይ ረጅም ጥላዎችን በመቃብሮቹ ላይ እየወረወረች መጥለቅ ስትጀምር፣ አይከል የሰላም ስሜት በእሷ ላይ ሲወርድ ተሰማት። የሀዘኗ ክብደት የቀለለ መሰላት፣ በአዲስ እውነታውን በመቀበል ስሜት ተተካ። ለደግነቱ እንግዳውን ሰው አመሰገነችውና ወደ መኪናዋ አመሩ፣ የታደሰ መንፈስ ባለ ቤት ሆነች። ስትሄድ የጠፋባትን ህመም መቼም እንደማትረሳው ታውቃለች። ነገር ግን ወደ ፊውስ የመጀመሪያ እርምጃዎችን እንደተራመደች እና ከጊዜ በኋላ የምትቀጥልበትን መንገድ መዘርጋት እንደ ጀመረች አውቃለች። እንግዳውም ሰው ምናልባት ሌላ ጊዜ ደግሞ እንጫወታለን፤ መልካም ጊዜ ብሎ ተለያት።

አይከል በእጅ ስልኳ ተልኮ ከእንቅልፏ በቀሰቀሳት መልዕክት ምክንያት ዞዓር ተገኝታ ብዙ ሥራ ስትሰራ ውላለች አሁን በመምሸቱ ወደ ቤት ለመሄድ እየተዘጋጀች ነበር። አሁን ያለችበት ስፍራ፤ የዞዓር አባላት ልዩ ልዩ

ኦፐሬሽን የሚያከናውኑበት ነው። በዋናነት ሱፐር ኮምፒውተሮችን፣ የራሳቸውን ሳተላይት መስመር የሚጠቀሙ መልዕክት መቀባበያ ስልኮች፣ ከሌሎች የቡድኑ አባላት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመጠበቅ የሚረዱ የተለያዩ የመገናኛ መሳሪያዎች እንደ ሬዲዮ እና ኢንክሪፕትድ የተደረጉ የመገናኛ መሳሪያዎች፤ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች እና ጥይቶች፤ ምግብ፣ ውሃ፣ የህክምና አቅርቦቶች እና ሌሎች ለቡድኑ አባላት ህልውና አስፈላጊ የሆኑ ሚስጥራዊነት ያላቸው ሰነዶችን፣ ካርታዎችን እና የስለላ መረጃዎችን የያዘ ነው። ኢይከል በሰፋፊ ስክሪኖች ላይ በቀጥታ እየተመለከተች ያለችው የከተማዋን ዋና ዋና የተባሉ ስፍራዎች እየቀረጹ የሚያስተላልፉት ካሜራዎች የት እና በምን መልክ እንደሚገኙ ማወቅ ፈልጋለች፤ ግን ሁሉም በሥራ ተወጥረው ነበር። ካሜራዎቹ ስፍራ ቀየሩ ኢይከል የምትመለከተውን ማመን አልቻለችም።

ስክሪኖቹን በመመላለስ ተመለከተቻቸው፤ በእኩል ጊዜ ፍንዳታዎች ተስተናገዱ የምትመለከተው የሀገሪቱ ዋና ዋና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ነበር። ግራ በመጋባት ሰዓር እና ኤፍሮንን ተመለከተቻቸው፤ ኤፍሮን ዘወር ብላ ዐየቻትና መልሳ ስክሪኑን መመልከት ጀመረች። ጠጋ ብላ ምን የተከሰት እንደሆነ ጠየቀች፤ ኢይከል ከቁጥጥራችን ውጭ ነው ይሄ፤ ቀስ እያልሽ ትረጂዋለሽ አለቻት ሰዓር። ምንም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ነገር ኢይታየኝም፤ ይህ ልክ ኢይደለም እንዳልሆነም ደግሞ ታውቃላችሁ። ቀድማችሁ ታውቁታላችሁ ለዚያም ነው ስትከታተሉት የነበረው። የእናንተም እጅ ከሌለበት እንዴት አታስቆሙትም? በማለት በቁጣ ጠየቀች፤ ኤፍሮን አሁን የምናስረዳሽ ነገር ኢይኖርም የምንነግርሽ አንድ ነገር እጃችን እንደሌለበት ነው አለቻትና አጠገቧ የነበረውን ኪይቦርድ አንስታ ተቀምጦ ከነበረበት ጠረጴዛ ላይ ደጋግማ አጋጨችው ተሰባበረ። አባላቶቹ ቢደነግጡም ሥራቸውን ቀጠሉ። ይኸውልሽ ኢይከል ያንቺ ቅንነት ልክ እያለፈ ነው። የማይገባሽ ቦታ እንድትገኚ እንዳደረግንሽ እንዲሰማኝ

አታድርጊ ለሀገርሽ ተቆርቋሪ፣ በጎ አሳቢ ቅን እንደሆንሽ ነው የምታስቢው። ሌላው ለሀገሩ ግድ እንደሌለውና ትክክለኛው የለውጥ መንገድ አንቺ ነው ብለሽ የምታስቢው ብቻ ይመስልሻል።

ንግግር እና ድርድር ማንም እንደማይጠላ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ ግን የምትነጋገሪው፣ የምትመካከሪውና የምትደራደሪው ከማን ጋር ነው? ደም አይፍሰስ በሚል ሞኝነት እንዲሁም አለፍ ሲል ፈሪነት በወለደው መደበቂያ ውስጥ እስከመች ትሸሸጋላችሁ አንቺ እና መሰሎችሽ? መሆን ያለበትን ሁሉ ሳናመነታ እንደምናደርግ አስረግጬ ልነግርሽ እፈልጋለሁ። ሁላችንም የሞቀ ኑሮአችንን ትተን በነፍሳችን የምንወራረደው ለአንቺም፣ ለልጆችሽም፣ ለሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ የተሻለች ኢትዮጵያን ልንገነባ እንጂ አንቺ አና መሰለችሽ እንደምትሉት የሥልጣን ጥመኞች ሆነን አይደለም። እሱን እማ ንቀነው እንጂ ምን ያህል ሥልጣን እንደነበረን ለአንቺ አልነግርሽም። ፍላጎታችን ገንዘብም እንዳልሆነ የገዛ ባለ ቤትሽ ምስክር ነው። ያንን ሁሉ ማዕድን ይዞ ለመጪው ትውልድ ብሎ ነው ቆልፎ ያስቀመጠው። ስለዚህ ዓላማችን ግልጽ ካልሆነልሽ እባክሽ ከመንገዳችን ገለል በማለት አግዢን። ስትላት ሰዓር በመሀል ገብታ ይኸውልሽ አይከል አሁን ያየሻቸውን ፍንዳታዎች ያጠመዱትም ሆነ ያፈነዱት እራሳቸው ናቸው ያውም ቀጥታ ከዋናው ሰውዬ በወረደ ትዕዛዝ። እኔ አላምንም አለች አይከል። አዎ ብዙ ነገር አታምኚም ምክንያቱም የቅርብ ሩቅ ስለሆንሽ ለዚህም ነው ሁሉን ነገር የማንነግርሽ። አንቺ ጭንቅላትሽ ውስጥ የምታምኚው የራሴ ያልሺው እውነት አለ፤ የእሱ ተቃራኒ የሆነ ነገር ሲያጋጥምሽ ነገሩን ለመመርመር አልይም ለመረዳት ከመሞከር ይልቅ፤ የእኔ ባልሺው እውነት ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ውድቅ ታደርጊዋለሽ። ያንቺስ

እውነት፤ እውነት መሆኑን ማረጋገጫሽ ምንድነው?
በማስረጃ ከምታዪው በምናብሽ የሳልሺው ለምን በለጠ?

አንደኛው ስክሪን ሰበር ዜና የሚል የዜና መግቢያ በማሳየቱ ሁሉም እሱን መመልከት ጀመሩ። የዜና አቅራቢው የተከሰተውን ክስተት አብራርቶ፤ አሁን የሀገሪቷ መሪ ለሥራ ጉብኝት ከሄዱበት ከቻይና የሚያስተላልፉልን መልዕክት ይኖራል እሱን ተከታትለን እንመለሳለን አለ። ክቡራን የሀገሬ ዜጎች ዛሬ በተፈጸመብን የሀገር ክህደት ወንጀል እጅጉን ደንግጠናል። እኚህን ወንጀለኞች ተከታትለን በቅርብ ቀን ለፍርድ እንደምናቀርባቸው ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ጠላት ሆነው ከኖሩ ሀገራት የተሰጣቸውን ኢትዮጵያን የማፍረስ ተልዕኮ ለመፈጸም ደፋ ቀና ሲሉ የከረሙት እኚህ አሸባሪዎች ዛሬ ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቦቿ ያላቸውን ጥላቻ በይፋ አሳይተውናል። እነዚህን አሸባሪዎች በቁጥጥር ስር ለማዋል በምንሄድባቸው ማናቸውም መንገዶች ሕዝባችን ከጎናችን እንዲቆ በጥብቅ አሳስባለሁ... ኤፍሮን ይሄው ነው አለች፤ ብናስር ብንገድል እንዳትጠይቁን ብሎ ወጣቱ ላይ አዋጅ ለማወጅ ነበር፤ አደረገው። ገና የፍንዳታው ድምጽ ሳይረግብ እንዲህ እርግጠኛ ሆኖ ሲያወራ ዐየሽ? አይከል ንቂ! እንዲህ በግልጽ እያሳየንሽ አሁንም ማንነቱ አልተገለጸልሽም ንቂ! በቀጣይ የምትመለከቺው ግን እውነተኛ የሕዝብ አብዮት ነው። እነ ጄነራል ሂሶጵ ያፈነዱት አይነት ያልሆነ ዋና ከተማ ውስጥ የሚጀመር፤ ሽባ የሚያደርግ ወጣቶች በራሳቸው የሚያቀጣጥሉት አብዮት፤ ለነፍሱ ሳይሳሳ ለሀገሩ የወደፊት እጣ ፈንታ የሚዋደቅ ቆራጥ እና ወኔያም እናቱ የወለደችው ወጣት አሁን መመልከት ትጀምሪያለሽ ብላ ቀድሞ ወደ ነበሩት ካሜራዎች መለሰችው።

ደንገዝ ገዝ ባለው ሰማይ ውስጥ በከተማዋ ሁሉ በእኩል ሰዓት ወጣቶች በየሰፈራቸው ዋና ዋና መንገዶች ላይ በመውጣት ጎማ ደርድረው በማቃጠል፤ በማሕበራዊ ሚዲያዎች በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ ጀመሩ። ለሁለት ሳምንት በተከታታይ በዚህ ድርጊት ቀጠሉበት። መጀመሪያ በታቀደው እቅድ መሰረት ሁሉም አከባቢ እራሱን ከካድሬ ከማጽዳት በመጀመሩ፤ አልታዘዝም ባሉት ላይ ከሰፈር እስከማባረር የሚደርሱ ውሳኔዎች በመወሰናቸው፤ ለማስቆም ኃይል የታከለበት ሙከራም ቢደረግም፤ ተቃውሞውን በቁጥጥር ስር ማዋል ከባድ ሆኖ ተገኘ።

በዚህ መልኩ ተቀጣጥሎ ወደ ተለያዩ ከተማዎችም የተስፋፋው እንቢተኝነት አሁን ወደ ሙሉ ሕዝባዊ እንቢተኝነት ተሸጋግሮ በሙሉ ከተማዋ ምግብ ነክ ምርቶችን ከሚያቀርቡ በስተቀር ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ስፍራዎችና ትራንስፖርትን ጨምሮ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ በየመሃሉ ለተከታታይ ሦስት ቀናት በማቋረጥ ከፍተኛ ተቃውሞ መከናወኑን ቀጠለ። በየጊዜው በየክፍለ ከተማው የሚገኙ የወረዳ ሹመኞች ከንጋት አንስተው ሁሉም በከተማዋ የሚገኙ አገልግሎት በመስጠት ዘርፍ የተሰማሩ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱ ካልሆነ ከባድ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በማስጠንቀቅ እንቅስቃሴዎች ወደ ቀደም መልካቸው እንዲመለሱ ቢጥሩም ምላሽ አላገኙም። በዚህ መልክ በተደጋጋሚ ተቃውሞዎች በርትተው ቀጠሉ።

ቤተ መንግሥት

የዚህ ሕዝባዊ እንቢተኝነት እንዲህ መቀጣጠል ዓለም አቀፍ ትኩረቶችን እየሳበ መጣ። በዚህም መሰረት ዛሬ በአፍሪካ ቀንድ የአሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ የሆነው ዲፕሎማት እዚሁ ይገኛል። ጊቢውን እየነበኘ፤ አሳምረኸዋል! ባለፈው ከመጣሁ በኋላ ብዙ ለውጥ እያየሁ ነው። ሕዝቡ ግን በተቃራኒው አልፈልግህም እያለህ ነው ምን ታስባለህ? በቁጣ ሆኖ መቼም አያሸንፉኝም መቼም! አሸናፊው እኔ ነኝ የምሆነው። በጥላቻ የተዋጡ፣ በበቀል ልባቸው የተሞላ፣ ደም የጠማቸው እጅግ ብዙ ወታደሮች አሠልጥኛለሁ። በማኅበረሰቡ የተጠሉ፣ ዱርዬ፣ ሌባ እና የመሳሰሉትን ሲባሉ የኖሩ ለዚህች ደሃ ሀገር ከፍተኛ ጥላቻ እና ንቀት ያላቸውን ወጣቶች ሰብስቤ አሠልጥኛቸው፤ የሚፈልጉትን ሁሉ የማሟላላቸው ታማኝ የሆኑ ወታደሮች አሉኝ። ልክ ሥልጣን ላይ እንደ ሾምኳቸው አይነቶች። በአንድ ምሽት ጨፍጭፈው ሀገሪቷን ወንድ አልባ አና ሊያደርጉ የታመኑ ወታደሮች አሉኝ; በምንም መልኩ አያሸንፉኝም። ይህን ያደረጉትን ሁሉ በተከበርኩበት ያዋረዱኝን ሁሉ አንድ በአንድ እበቀላቸዋለሁ! አዋርጀ ከአፈር እቀላቅላቸዋለሁ።

ተረጋጋ! አለው እንዲህ በድንፋታ የሚሆን ቢሆን ካንተ በፊት የነበሩትም ያደርጉት ነበር። ኢሊቱ ሲያምጽ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም በንብረቱ፣ በቤተ ሰቡ በማስፈራራት፤ በማሰር አለፍ ሲልም በመግደል ተቃውሞውን ታበርደዋለህ። ሕዝብ እንቢ ካለ በቁጣ፣ በጉልበት አታበርደውም፤ ይበላሃል! አገልጋዮችህም የእነሱ አካል እንደሆኑ አትርሳ። አፈሙዛቸውን

ያዞሩብሃል፤ እንዳለኝ መረጃ ከሆነ አሁንም እንደዚያ ማድረግ የጀመሩ አሉ ምቹ ጊዜን የሚጠብቁ። ከነሙሉ ትጥቃቸው ጫካ የገቡና እየገቡ ካሉት ውጭ ማለት ነው። ነገሮች አንተ በጭፍን እንደ ምትመለከታቸው አይደሉም፤ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። አምጥታችሁ የሾማችኋቸው ምሁራን እንኳን እኛ እጃችንን ባንከት ከባድ ቀውስ የሚያስነሳ ጉዳይ ነበር።

በተደጋጋሚ እንደ ተነገረህ እኛ በስንት መከራ እና ስቃይ እጃችን ያስገባናት ሀገር ከእጃችን እንድትወጣ አንፈቅድም! በምንም ተአምር። መደረግ ያለበትን ሁሉ እናደርጋለን። እስካሁን ትኩረት እንዳልሰጠነው የሆነው፤ በተራዘመ ጦርነት ሕዝቡ እራሳቸው ላይ ያምጽና ያጠፋቸዋል በማለት ነበር። መሬት ላይ ያለው ሌላ ነው ስለዚህ ድርድር መጀመር እንዳለበት ወስነናል። ማን እንደሆኑና ምን እንደ ሚመስሉ ካጣራን በኋላ ለኛ አመቺ ካልሆኑ በአደጋ አስመስለን እስከ መጨረስ እንጓዛለን። መጀመሪያ ተአማኝነትን ማግኘት ይኖርብናል፤ ድራማውን በሚገባ ተውኑት። አሁን የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሰናል። ራሺያንም ቢሆን በዐይነ ቁራኛ ተመልከታት። የኢትዮጵያ ስም ሲነሳ ዐይኑን ጨፍኖ ወደ ጦርነት የሚያቀና ማኅበረሰብ አሁን ልትወረር ነውም፣ ተወረርክም ሲባል ጆሮ ዳባ ልበስ የሚለው ርስትህን አስመልስ ሲባል ፈንጨበት የሚለው ለምን ይመስልሀል? ብዙ የተደከመባቸው አጀንዳዎች ሲሰጡት ምላሽ መስጠት ያቆመው ይባስ ብሎ እኛኑ ያበሸቅበት የጀመረው ለምን ይመስልሀል? ጥንቃቄ ይፈልጋል።

ይሄ ሕዝብ እንኳን ላንተ ለእኛም እስከ ዛሬ ልንፈታው ያልቻልነው እንቆቅልሽ ነው። እንደፍላጎታችን እንደ ድርጊታችን እስካሁን ሀገሪቷ መኖሯ እንደሚያስገርምህ አንተው ነህ የነገርከን። አሁን እጃችን ላይ ያሉት አጀንዳዎች በሙሉ ያለስስት ተግባራዊ ይደረጉ። እስካሁን ከማን ጋር እንደምንደራደር አናውቅም እሱ ሥራችንን

አስቸጋሪ አድርጎታል። ኢትዮጵያን የያዘ፤ የአፍሪካ ቀንድን በቁጥጥሩ ማስገባቱ የቀናት ሥራ ነው የሚሆነው። ሀገሪቷ ውስጥ አሉ የሚባሉ ቆንጆ የሴት አርቲስቶችም ይሁኑ ማናቸውንም ተጠቀሙባቸው፤ ደውለው ጀግና እንደሆኑ እንደሚያደንቋቸው በተደጋጋሚ በመንገር ወዳጅነት ከፈጠሩ በኋላ፤ ቢያገኟቸው ደስ እንደሚላቸውና ኑ የሚባሉበት ድረስ ያለማወላወል እንደሚገኙ ይንገሯቸው። ይሄን በሚገባ አሠልጥናችሁ ወደ ትግበራ ግቡ። ያሉበትን እንዳወቃችሁ እርምጃ እንዳትወስዱ፤ መንገዱ ተአማኝነት አትርፎ ብዙዎችንና ዋና ዋና የሚባሉትን፤ ወሳኝ መረጃን ጨምሮ በእጃችን እስኪገባ ድረስ። ይሄን መንገድ ጋዜጠኞች እና ተጽኖ ፈጣሪዎች እንዲሁም ተቃዋሚዎች ላይ ተጠቀሙት፤ አቅም በፈቀደ መልኩ ሁሉም ብላክ ሜል ይደረጉ። ሕዝቡ ምን ነካቸው እስኪል ድረስና እስኪጠሉ ድረስ የኛን አጀንዳ እንዲያቀነቅኑ ይደረግ። ሰልችቶአቸው ሀገሪቱ ተቆርቋሪ የላትም ማለት ነው? እነሱ እንዲህ ከሆኑማ እኛ ምን እንፈይዳለን ብለው ተስፋ እስኪቆርጡ ድረስ።

ይህም አልበቃ ካለ ሕዝቡ ፖለቲካን እንደ ሞት እስኪፈራ ማሰሩም ግድያውም ይቀጥል። የሐሰት ክስ በማደራጀት ተጽኖ ፈጣሪዎችን ሁሉ እሰሯቸው። ከሁሉም በላይ እነሱ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች በሙሉ ሰብስባችሁ፤ የራሳችሁ ሰዎች እንዲጠይቁ አድርጉ አየሩንም ሙሉት፤ እንወያይ ብለህ እራሳችሁ ተወያይታችሁ እንደተፈታ አጽድቀው። ሕገ መንግሥቱንም ቢሆን እስከ መቀየር ድረስ የሚደርስ ውይይት አዘጋጅ። መልሰህ ሁሉም ሲነሱ የነበሩት ጥያቄዎች ተፈተዋል ብለህ ሕዝቡ የለውጥ ሳይሆን የሥልጣን እንደሆነ ጥያቄያቸው እንዲያስብና እንዲቃወማቸው አድርግ። ጋዜጠኞች፣ መምህራን፣ የጥበብ ሰዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ሁሉ በቴሌቪዥንም ይሁን በሬዲዮ እንዲሁም በሶሻል ሚዲያ በመቅረብ እየታሰሩም ቢሆን ሕዝቡን ማነሳሳት እንዳይጀምሩ

ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርግ! Narrative በእጁ የሆነ፣ ትርክትን የሚቆጣጠር፣ የነበረን የሚሸር እና አዲስ የሚፈበርክ ተገዳዳሪ የሌለው ኃያል ነው የሚሆነው! የሀገሪቱን ዋና ዋና በዓላት ሽረህ እና አደብዝዘህ በአዲስ እና እንግዳ የእኛ በሆኑ በዓላት ቀይራቸው ያልንህንም በሚገባ እየሄድክበት አይደለም። ያን ለማድረግ ቀላሉ እና ውጤታማው መንገደ፤ እኛ የማንፈልጋቸው በዓላት ሲደርሱ በሰላም እንዳይከበሩ ሽብር መንዛት ነው። የእኛ ለሆኑት በዓላት ደግሞ መዋቅራዊ የሆነ ድጋፍ በመስጠት በድምቀትና በሰላም እንዲከበሩ ማድረግ። እያገቱ ገንዘብ እየጠየቁ ሕዝቡ ከቦታ ቦታ እንዳይዘዋወር ማሳቀቅ የሚጀምሩም ቡድኖች አሰማራ። የኢትዮጵያውያንን ልብ ማግኘት ከፈለክ ስለ ባንዲራቸው እና ሃይማኖታቸው አብዝተህ አውራላቸው ብለን ከበፊትም ደጋግመን የነገርንህን አትርሳ። እየተሸነፋችሁም እያሸነፋችሁ እንደሆነ ፕሮፓጋንዳ ማሰራጨት እንዳታቆሙ! ገፍተው ከመጡ ከተማዋንም ሀገሩንም ወደ አመድነት ለውጧቸው! አዲስ አበባም እንዲ ጩኸት የበዛባት ሀገሪቷ አንድ ዋና ከተማ ብቻ ስላላት ነው እሱን አብዙት! ትኩረትም ከኛ እንዲዞር ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር ያለህን ወዳጅነት አጠንክር! ለሁሉም እንደ ልባቸው ዝንባሌ ቃል ግባላቸው! ሌላውን በድጋሚ እሱ ሲመጣ የምታወሩት ይሆናል፤ እንደተለመደው ማድረግ ያለብህን ሁሉ ይነግርሃል።

ሩሲያ ኤምባሲ

ዶክተር ዛሪየስ፣ ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ፣ ቴራስ እና ኤፍሮን ከሩስያ ከመጡ የደህንነት እንዲሁም ወታደራዊ አዛዦች ጋር በመወያየት ላይ ናቸው። ኤጀንት ሜትሮቪች ንግግሩን ጀመረ፤ ጓደኞቼ እንዳሉት ጄነራል ሠሀረን እናንተ ብቻ አይደላችሁም ያጣችሁት እኛም ጭምር እንጂ፤ ዋሽንግተን ላይ ስንረዳቸው እንገናኛለን ብሎኝ ነበር፤ እኔም ደግሜ እንደማገኘው ነበር የተሰማኝ አልሆነም እንጂ። አሁን እንደምናየው አብዮቱ ወደ መጨረሻው እየተንደረደረ ነው። እስካሁን በመልካም ሁኔታ እንደተጓዛችሁ ይታወቃል የትጥቅ ትግሉም ቢሆን እኛ የፈራነው እና የምናውቀው አይነት ተግዳሮት አልደረሰበትም። ኪሳራውም ቢሆን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ይልቁኑ እየተገኘ ያለው ድል የማይታመን አስደማሚም ነው። ይዛችሁ የተነሣችሁት ዓላማ እና ስትራቴጂ ለዚህ ትልቁን አስተዋፅዶ ይወስዳል የሚል ሀሳብ አለኝ። እናንተ ነገሮችን በማመቻቸት እንጂ በአመራር አለመሳተፋችሁ፤ ለሴራም እንዳይመች፤ ትግሉም አመራር እንዳይኖረው ታጋዮቹ እራሳቸው እንዲመሩት ያደረጋችሁበትም መንገድ፤ ለትግሉ ቁልፍ ሚና ተጫውቶአል። እንዳይጠለፍም ረድቶአል። ይህን አብዮት ታላላቅ ሀገራት እንደ ሰጎን እንቁላል እንደሚመለከቱት አይጠፉችሁም። መጪውን መቶም ከዚያም በኋላም የሚኖሩትን ዓመታት የሀገሪቱን ብቻ ሳይሆን የቀጠናውን ፖለቲካ ጭምር የሚወስን አብዮት በመሆኑ ይህን ማድረጋቸውም የሚጠበቅ ነው። እኛ አንድ ሁለት ስጋቶች አሉን። አሁን እየተሄደበት ያለው አኪያሄድ በመጨረሻ ታጋዮቹን ለሥልጣን ሽኩቻ

አይዳርጋቸውም? ሌላው ሕዝቡስ ለሚመጣው ለውጥ ዝግጁ ነው?

ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ በቅድሚያ ሁላችሁም ህመማችንን ስለምትታመሙልን እናመሰግናለን በማለት ጀመሩ። ለመጀመሪያው ጥያቄ እኛም የምንፈልገው እንዲሻኩቱ ነው። ማን በምን አይነት ፍላጎት ትግሉ ውስጥ እንደገባ ግልጽ እየሆነ እንዲሄድ መንገድ ስለሚከፍት፤ በትክክል የወገኑ ፍትህ ማጣት የሀገሩ ችግር አሳስቦት ለወገኑም ለሀገሩም ረፍት ለመስጠት አልሞ በእውነት የቆመ የሥልጣን ርዕስ ልቡን አይስበውም። ማንም መራ ማን አመራሩ ልክ እስከሆነና ወደ ዓላማው የሚያደርሰው እስከሆነ ለሱ ግድ አይለውም። እኔ ካልሆንኩ የሚልም በመሃላቸው አይስተናገድም። ይሆነናል የሚሉትን መርጠውም ሹመዋል። የአንድነት አይሁን እንጂ። በአሁን ሰዓት ያ እንዲሆንም አያስፈልግም። መናበባቸው እንጂ አንድ መሆናቸው ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ ለአጥቂዎችም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ኢትዮጵያዊው ዮቶር ሙሴ ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብሎ በዚያ በረሀ ለእስራኤል ፍርድ እንዲፈርድ ባወቀ ጊዜ አንተም ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፥ የታመኑ፥ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ፤ ከእነርሱም የሺህ አለቆችን፥ የመቶ አለቆችን፥ የአምሳ አለቆችን፥ የአሥርም አለቆችን ሹምላቸው። ብሎ የአስተዳደርን ጥበብ እንደገለጸለት ሀገር በቀል እና ከዓለም ቀዳሚ የሆነን ይህን የአባቶቻቸውን ጥበብ ተጠቅመው ተሿሹመዋል።

አሁን ብዙ መሻሻል አለ ከላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ምሁራን ናቸው፤ ብዙ ሰው እንደሚያስበው እንዲሁ መተኮስ ስለቻሉ የተሰባሰቡ አይደሉም። በትጥቅም አሁን የተሟላ አቋም ላይ ይገኛሉ። ሁለተኛው ስለ ሕዝቡ የተነሣው ጥያቄ ነው ወዳጆቼ አሁን ባለው ሁኔታ ማንም ሥልጣን ላይ ቢወጣ በሁሉም ዘንድ በአንድ ልብ

ተቀባይነት አያገኝም። ያማለት የሚያስማማ ሀሳብ የለም ማለት አይደለም፤ ፍቃደኝነት ነው የሌለው። ይሄ ደግሞ ለዘመናት ስንዘራው የነበረው ዘር አዝመራው ነው። የተዘራ ደግሞ ይበቅላል ያውም በሚገባ የተንከባከብነው። አሁን የማጨጃ ዘመን ነው እያጨድነው ነው። ሁሉን በአንድ የውዴታ ግዴታ በሆነ መአቀፍ መሰብሰብ ግድ ይላል። ካልሆነ ከትላንት ዛሬ እንደከፋው፤ ከዛሬ ነገ ይከፋል። ቆፍጠን ያለ አመራር ቢመርም መዋጥ ካለበት መድኃኒት ከሆነ ውሳኔ ጋር ያስፈልጋል። ልጅን እሹሩሩ በማለት ሥርዐት ማስተማር ይቻል ይሆናል፤ ሥርዐት ያለው ምግባሩ ያማረ እንዲሆን ጠበቅ አድርጎ መያዝ መቅጣትም ተገቢ ይሆናል። በዚሁ መሰረት ሁሉ መልኩን ይይዛል። ከታች እስከ ላይ ከባለ ሥልጣን እንከ ሲቪሉ ማኅበረሰብ። የእኛ ድርጅት አጥብቆ እንደሚያምንበት ሕግ እና ሥርዐት የግድ አስፈላጊና መሰረታዊ ስለሆኑ ሊከበሩ ግድ ይላል። እንዚህ የሌሏት ሀገር ምን እንደምትመስል በአሁኗ ኢትዮጵያ ማየት ይቻላል።

ከመሃላቸው በእድሜ ተለቅ ያሉ የሩሲያ አምባሳዶር እንዲህ በማለት ጥያቄ አቀረቡ ከ1935 እስከ 1939 የመከላከያ ኃላፊ በመሆን ያገለገለው ልጅ ዐብይ አበበ የሊቀ መቋስ አበበ ሰጋድ ልጅ ማለቴ ነው። ለምን ይመስላችኋል ሦስት ጊዜ ሹም ሽረት የተደረገበት? 1939 በአበበ አረጋይ ተተካ በድጋሚ ከሁለት ዓመት በኋላ ተሾመ፤ ለስድስት ዓመት አገልግሎ አሁንም በእራሱ በአበበ አረጋይ ተተካ፤ የፍትህ ሚኒስተር በመሆንም አገልግሎአል። ከዐሥራ ዘጠኝ ዓመታት በኋላ በድጋሚ በ1966 ወደ ሥልጣን መጣ። የሶሻሊስት ፓርቲ መጥቶ እስር ቤት እስኪያስገባው ለ አራት ወር አገልግሎ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስተር አክሊሉ ሃብተ ወልድ መልቀቂያ ሲያስገባ በሳቸው ቦታ ጀነራል ዐብይን እንዲሾሙት፤ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ምክረ ሀሳብ አቅርቦ ነበር። አንድ አንድ ሰዎች ደግሞ ጀነራል ዐብይን

ያስቀመጠው የአከሊሉ ሀብተ ወልድ ተቀናቃኝ የነበረው ልዑል አሥራተ ካሳ እንደነበር ይጠቁማሉ። የሆነው ሆኖ ጄነራል ዐብይ የጠቅላይ ሚኒስተርነቱን ሥልጣን የምቀበለው እጩነቴና የካቢኔዎቹ ሹመት ለፓርላማ አባላት ቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው በማለቱ ግርማዊነታቸውም ይህን ለማድረግ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በምትኩ እንዳልካቸው መኮንንን ጠቅላይ ሚኒስተር አድርገው ሾሙ። ልጅ ዐብይ በዛች ምሽት በኢቃቂ ማዕከላዊ እስር ቤት በደርግ ከተረሸኑት 60 የቀድሞ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት መካከል አንዱ ነበር። ይህ ለምን የሆነ ይመስላችኋል? ሁሉም ዝም አሉ። ሥልጣን ሸኩቻና ሴራ ይበዛበታል፤ ለነባሮችም ያዳግታል ለአዲስ ሰው ይቅርና። ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ ሚዲያ ትልቅ አቅም አለው። ዲጂታል ሚዲያ ላይ ብቻ አታተኩሩ! ኢትዮጵያ ውስጥ 71.4 ሚሊየን ሞባይል ተጠቃሚዎች እና 77.39 ሚሊየን active የሆነ cellular connection አለ። ነገር ግን 103 ሚሊየን የሚሆነው ማሕበረሰብ ኢንተርኔት አይጠቀምም! 24 ሚሊየኑ ብቻ ነው ተጠቃሚው። ከዚህ ውስጥም 7.5 ሚሊየን ነው ከዐሥራ ስምንት ዓመት በላይ ሆኖ የማሕበራዊ ሚዲያን በደንብ የሚጠቀመው። ይሄ ቁጥር ለፌስ ቡክ ነው! ይሄም ማለት 80.6 % offline ነው ማለት ነው። ስለዚህ መሬት ውረዱ! ከተማ ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ 23.4 % ብቻ ነው። 76.4 % የሚሆነው ገጠር ነው ያለው! ይሄን ቁጥር ከያዛችሁት በቅርቡ ታሸንፉላችሁ! አለበለዚያ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው የሚሆንባችሁ! በፕሮፓጋንዳ መበለጥ የለባችሁም አጅንዳ ሰጪ እንጂ ተቀባይ እንዳትሆኑ! አሁን እየሄዳችሁ ያለበት መንገድ አስደሳች ነው። ጆሴፍ ጎቤልስ በመባል የሚጠራው ከ1933 እራሱን እስካጠፋበት 1945 የናዚ ጀርመን ፕሮፓጋንዳ

ሚኒስተር በሞሆን ያገለገለው ሰው የሰራውን ታውቃላችሁ። ጋዜጣውንም፣ ሬዲዮ፣ የፊልም ኢንዱስትሪውን ሳይቀር ተጠቅሞበታል። ንስር እና የእናንተውን ሀገር የላሊበላ ምልክት ስዋስቲካ በማለት ጠንካራ የሆነ ስሜትን በሕዝቡ ውስጥ ማስረጽ ችሎአል። አይሁዳውያንን እና ኮሚኒስቶችን እንደ ስጋት በማስቆጠር ምን እንዳደረገ ታውቃላችሁ። ወጣቶችን በመጠቀም ነው የናዚን አይዲኦሎጂ በማኅበረሰቡ ውስጥ በማስረጽ ለወታደራዊ አገልግሎት በፍቃደኛነት እራሳቸውን እንዲሰጡ ማድረግ የቻለው። ደግሜ የማሳስባችሁ ንግግሬንም የምቋጨው የፕሮፓጋንዳን አቅም አሳንሳችሁ እንዳትመለከቱት! በሚገባ ተጠቀሙበት! በዚህ እንዳትበለጡ!

አሜሪካን ኤምባሲ

የመሰብሰቢያ ክፍል ውስጥ ከአፍሪካ ቀንድ የአሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ ጋር አብሮ ከመጡ መሃል የሲ.አይ.ኤ ዋና ማዘጋጥ፣ የዲቨሸን ሃላፊው ዊልያም ባር እንዲሁም የMI6 እና የሞሳድ አባላት ይገኙበታል። በስፋት MI6 ተብሎ በሚታወቀው የዩናይትድ ኪንግደም SIS አባል የሆነው ስቴፈን አሌ፤ ከእጃችን ስትወጣ ዝም ብለን እንመርከት ነው የምትሉት? ሲል ጠየቀ እየሆነ ያለው ይሄ ነው። መሆን ያለበትን ሁሉ አድርገን፤ ጊዜ ሳናባክን ሁኔታውን በቁጥጥራችን ስር ልናስገባው ይገባል። የእኛዋ ልጅ ጃስሚንም የምታቀርብልን ሪፖርት እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ባለ ሥልጣናት ከአብዮተኞቹ ጋር ናቸው። የጦር መኮንኖችን ጨምሮ።

ሳይረፍድ ሁሉንም አማራጮች ተጠቅመን አስኳሉን ማግኘት ይኖርብናል። ያን ጊዜ እኛ የምንፈልጋቸው ወደፊት እንዲመጡ ሁኔታዎችን እናመቻችላቸዋለን፤ አልታዘዝ የሚሉትን እስከወዲያኛው እናሰናብታቸዋለን። ሥልጣኑን መያዛቸው እሙን ነው። ተበታትነው ደካማ የማይናቡቡ ይመስላሉ ስልዚህ ይሄኛውን አሁን ደብድበን እናዳከመው ቀጣይ ወደእነዚያኛው እናመራለን በሚል ስትራቴጂ ስትመሩ ከሩቅ መጥተው ከነዚኛዎቹ ጋር ተደርበው ያጠቋችኋል። አንድ እንዳልሆኑ የሚያሳዩን ሆን ብለው እየመሰለኝ ነው።

ለማንኛውም፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እጅግ ተወዳጅነትን እና ተአማኝነትን ያተረፉ የሚከበሩ በእኛ ከሚታዘዙት ሁለት መርጠን ትግሉን እንዲቀላቀሉ እናድርግ። ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች እንዲደርሷቸውና ለአባላቶቹ እንዲያጋሩም ይሁን፤ በሚገባ ከኋላው የተሻለ፣ አመኔታ እንዳተረፉ ስናረጋግጥ ለአመራርነት እጩ እንዲያደርጓቸው እነሱ በሚፈጥሩት ኔትዎርክ መሰረት አባላቶቹን በጥቅማጥቅም በመግዛት ወደ አመራርነት ማምጣት። በዚህ መሃል እኛ ካዘጋጀናቸው ኢትዮጵያውያን መሃል የምንፈልገውን ሰው መርጠን፤ ያ በራሳቸው እንዲመርጡት ያደረግነውን ሰው፤ ከእኔ የተሻለ ለሀገሪቷ ይጠቅማል ስለዚህ በገዛ ፈቃዴ ሥልጣኑን ለእሱ እሰጣለሁ ብሎ እንዲያስረክብ ማድረግ እንችላለል። እንዲህ ቀላል ይሆናል ብለህ ታስባለህ? አለው ዊልያም ባር፤ በፍጹም ለዚያም ነው አስቀድሜ መሆን ያለበትን ሁሉ ማድረግ እንደሚገባን የገለጽኩት።

አንደኛው ግሩፕ አንደኛውን ሊያጠፋው ቀን እየቆጠረ እንደሆነ ለሁለቱም ነግሮ ሳይቀድሚችሁ ቅደሚቸው ብለን ነገሩን በአክቲቪስቶችም አግለን እርስ በእርስ እንዲጫረሱ ማድረግ ይቻላል፤ የአሸናፊው ወዳጅ ሆነን እንገለጣለን። አሁን ባለው ሁኔታ ያን ማድረግ ስለሚያስቸግርና አላስፈላጊ ጊዜም ጭምር ስለሚወስድ

ነው የመጀመሪያውን ሀሳብ እንደ አማራጭ ያቀረብኩት። እኛን ለማገልገል ፍቃደኝነታቸውን የገለጹ ነበሩ እርዱን ሥልጣን ከያዝን በኋላ እንረዳችኋለን ያሉን። ግን አቅም የላቸውም የቱንም ያህል ብንረዳቸው መቶ ኪሎ ሜትር የመጓዝ አቅም የላቸውም። አቅሙም ቆራጥነቱም የሕዝቡም ድጋፍ ያለው እነዚያኛዎቹ ጋር ነው። እነሱ ደግሞ ከኛ ጋር ለመሥራት ፍቃደኛ አይደሉም። ያለን አማራጭ እርስ በእርስ እንዳይተማመኑ ማድረግና ሰርጎገቦችን እንዲሁም አሁን እጃችን ላይ ያሉትን ጥቂቶቹን በመጠቀም መከፋፈል፤ በዚያም መሃል ወደ እኛ መጠምዘዝ ነው። ይበልጥ በሃገሪቱ መታመን ስላላቸው በሚል ይህን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ለሞሳድ አባላት ኃላፊነቱ ተሰጣቸው።

ምሽት 2:00

ቴራስ ስለ አኪያ ከአባቱ ጋር ማውራት ከጀመረ አንስቶ በማሃላቸው አለመግባባት ተፈጥሮ ሰንብቶአል። በተለይ ለማግባት እንደወሰነና ሽማግሌ እንዲልኩለት ለአባቱ ከነገራቸው እለት ጀምሮ አባቱ ፍቃደኝ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ቴራስ ከፍቶት ሰንብቶአል። ዛሬ የመጨረሻ ያለውን ሙከራ ለመሞከር በአባቱ ቤት ተገኝቶአል። ጋሼ አለ፤ ጋሼ እባክህ ልትረዳኝ ሞክር አኪያ ለእኔ ኤሴቅ ናት ከብዙ ተጣልቼባታለሁ የልጅነቴ ናት ብዙ አይቼባታለሁ፤ እሷ የሌለችበትም ጉዞ ተጉዣለሁ፤ በድኔ እንጂ እኔ አልነበርኩም። ጉድለቴን የምትሞላው እውነተኛ የግራ ሳትሆን የቀኝ ጎኔ እሷ ናት። አቋረጡት። ባህላችን እንዲህ አይደለም፤ እንደ አባቶቼ ሥርዐት

ከወገኖቼ እንጂ እንዲሁ ካገኘሁት አልድርህም። አንተስ ከተማ አድገህል ሚስት ከዚህ ትሆንልህ ዘንድ አልሻም! ካደግኹበት ከተሞሸርኩበት ከእናት ከአባቴ መኖሪያ ትሁንህ እንጂ፤ አንድ ልጇ ነህ እግዜሩም ሌላ አልሰጠኝ፤ ብዙ ዘርን ዘርቶ ጥቂት ማጨድን ማን ይፈቅዳል? የእሱ ፈቃድ ተከናውኖአል፤ የመቃወም አቅም ያለው የለም። ያቺን የበቀለችውን ፍሬ ግን እልፍ አፍርታ ማየትን እሻለሁ። ለአብርሃም አንዱን ይስሐቅ በያዕቆብ እልፍ እንዳደረገለት፤ ሕዝብም አድርጎ እንደባረከው ያለ ባርኮት በአንተ ይሆንልኛል። ዛሬ በአፍላ ስሜት ስለከነፋችሁ ተዋዳችኋል ማለት አይደለም። ይረግባል መተሳሰብ ነው ዘላቂው። ዛሬ ደግሼ ነገ ፍርድ ቤት ልዞር አልድርህም። እኔው መርጬ በወግ ያደገች የትልቅ ሰው ልጅ እድርሃለሁ። የእድሜ ልክ እንጂ ጽገሬዳን ያልመሰለ፤ ጎምርቶ በመአዛው ልብን አሸፍቶ፤ ሲነጋ የማይጠወልግ ሽልማት እሸልምሀለሁ። መርቄ እሰድሃለሁ። ትዕዛዜን የምትቃወም ከሆነም ያውልህ መንገዱ የወላድ መካን እንዳደረከኝ ቆጥሬ በእርግማን እሸኝሃለሁ።

እናቱ እያለቀሰች በማየቱ፤ የመጨረሻና የማይቀየር አቋማቸው እንደሆነ ተረዳ ሁለቱንም ያውቃቸዋልና። ቴራስ በተሰበረ ስሜት እናቱን አንገቷ ውስጥ ገብቶ ስሞአት የአባቱን ጉልበት በመሳለም ወጣ። እህቱም የሚመጣው እንደተገለጸለት ነብይ፤ ዛሬ ይሄን ቤት የምታይበት የመጨረሻ ቀንህ ነው፤ ግባና ያደከበትን ክፍል ተሰናበተው አለችው፤ ተቃቅፈው አለቀሱ። ጸጉሯን በጣቶቹ ብትንትን አደረጋቸው፤ የእኔና የአንቺ ግን መጨረሻ አይደለም! አደራ ጋሼን በደንብ ተንከባከቢው። በድጋሚ ተቃቅፈው ተላቀሱ። ተሰናበታት።

ቤት እንደገባ አኪያ መጠየቅ አልተጠበቀባትም፤ የዐይኑን ቅላት ተመልክታለችና፤ እሱም በሩን ከፍቶ እንደገባ በቆመበት በዝምታ እየተመለከታት እንባው ይወርድ ጀመር። አኪያ ምን ማድረግ እንዳለባት ማወቅ

ተሳናት፤ ከቆመችበት ወደ ሶፋው በመሄድ ሁለት እጆቿን ጉልበቶቿ ላይ በማሳረፍ በሁለቱም መዳፎቿ ላይ ግንባሯን አስደግፋ መተከዝ ጀመረች። እግሩን በመዘርጋት ሶፋው ላይ ተጋድሞ በእጆቿ መሃል ጭኗ ላይ አንገቱን አስደገፈ።

፡፡ በአንቺ ምክንያት የማላጣው ምንድነው?

፡፡ ስቃዬን አታብሰው!

፡፡ ልጅነቴንም፣ ደስታዬንም፣ ቤተ ሰቤንም እኔንም። ግዙፍ የሚመስል ተራራ በአንቺ ፊት እንደ በረዶ ይቀልጣል።

ቴራስ አኪያን እንደተደገፉት ጸጉሩን እየዳበሰችው፤ ከባድ እንቅልፍ ወደቀበት። በዚህ ሁኔታ ወራትን አሳለፉ፤ እህቱ የወንድሟን ሚስት መጸነስ ከዐወቀችበት እለት ጀምሮ፤ በተደጋጋሚ እየመጣች ትጎበኛቸው ከነበረ ውጭ እናቱም ሆኑ አባቱ ይህን ቢያውቁም፤ ምንም ባለማድረጋቸው ይብሰለሰል ስለነበር፤ የሥራውም ሁኔታ ተጨምሮ ቴራስ ደስታ ርቆት ከረመ። እዲህ መሆኑ ያሳሰባት አኪያ፤ ከቤተ ሰቡ የምታስታርቅበት መፍትሄ በማሰብ ተጠምዳ ዛሬ መንገድ ያገኘች ስለመሰላት የመጣላትን ዘዴ ሳይውል ለመተግበር በማሰብ ወደ ቴራስ አባት የእጅ ስልክ ደወለች።

፡፡ ጋሼ እንዴት ሰነበትክ?

፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን ማን ልበል?

፡፡ አኪያ ነኝ የቴራስ ሚስት

፡፡ ምን?

፡፡ እንዲያው መደወሌ ከድፍረት ዐይታይብኝ ቢጨንቀኝ ነው። ስልኩ ተቋረጠ። መልሳ ደወለች አይነሳም። ደገመች!

፡፡ ምን አድርግ ነው የምትዪኝ?

፡፡ እኔ በጸና ስለታመምኩ የምተርፍም ስላልመሰለኝ፤ ትንፋሼ እያለ በእኔ ምክንያት የተቆራረጡ አባት እና ልጅ ሲታረቁ ዐይቼ ብሞት ብዬ ተመኝቼ ነው። ምን አልባት እድለኛ ከሆንኩ በምርቃትዎም ቢፈቱኝ፤ ጽንሱንም ቢዳብሱት የዘለዓለም እረፍት ይሆነኛል። እባኮትን? አባቴ ለአንዴ ብቻ ይመልከቱኝ ሌላ አልለምኖትም?

የቴራስ እናት ከባለ ቤታቸው እጅ ስልኩን በመንጠቅ...

፡፡ የእኔ ልጅ ሰላም አይደላችሁም? ሲሉ ጠየቁ።

፡፡ አይደለንም! እኔ ጽንሱን እንደተሸከምኩ የሞት አፋፍ ላይ ቆሜያለሁ። የልጆትን ሚስት እና ልጅ ከመቅበርዎ በፊት አንድ ጊዜ በዐይነ ሥጋ ይመልከቱኝ እናቴ።

፡፡ የት ነው ያለሺው?

አኪያ የጓደኞዋን የሕልቃን ሆስፒታል ጠራችላቸው። አሁኑኑ እንደ ሚመጡ ነግረዋት ስልኩ ተዘጋ። እንዲህ በቶሎ ይሳካል ብላ ያልገመተችው አኪያ፤ እየተቻኮለች

መልበስ ጀመረች፤ ድንገተኛ ማስመሰል እንደሚኖርባት ስላሰበች የመኝታ ልብስ ለብሳ እየመጣች እንደሆነ ለሕልቃ በማሳወቅ ወደዚያው አቀናች።

የሆነውን አጫውታት፤ እውነት ለማስመሰል ድንገተኛ ክፍል እንድታስገባትና ግሉኮስ እንድትሰካላት ጠየቀቻት። ሕልቃም የሞያው ሥነ ምግባር እንደማይፈቅድ በማስታወስ ማድረግ እንደማትችል አሳወቀቻት። ብዙ ብትዘበዝባትም፤ ልታስቀይማት እንደማትፈልግና ከዚህ በላይ ባያወሩበት መልካም እንደሚሆን በመንገር፤ ታካሚዎች ስላሉባት አሁን መውጣት እንደሚኖርባትና በኋላ ቤት እደሚገናኙ አሳውቃት፤ ወደ ቤት እንድትሄድ ነገረቻት። እንዲሁ እያሉ አኪያ ስልኳ ጠራ አነሳችው፤ ያለቻቸው ሆስፒታል እንደደረሱ አሳወቋት። ቢያንስ ወጥታ የሆነ ነገር እድትላቸው ሕልቃን ተማጸነቻት። እያቅማማች ሄዳ ስታገኛቸው ሁኔታው እንዳሰበችው አለመሆኑን ስለተረዳች፤ አረፍ ብለው ጥቂት እንዲጠብቁ በመንገር ወደ አኪያ ተመለሰች። አኪያ በፍጹም አደርገዋለሁ ብዬ አስቤው የማላውቀውን ነገር ልታስደርጊኝ ነው፤ ካላደረኩት ያበቃልሻል። እድሜ ልክሽን ተቆራርጠሽ ነው የምትቀሪው! ነይ ተከተዪኝ ብላ ወደ ድንገተኛ ክፍል ይዛት በመግባት አስተኝታ መርፌውን ሳትወጋት በነጭ ፕላስተር ክንዷ ላይ ለጠፈችውና ግሉኮሱን ሰክታ፤ ጠርታ አስገብታቸው ወጣች።

የቴራስ እናት ከገቡበት የድንገተኛ ህሙማን ክፍል የልጃቸውን ሚስት ተኝታ በማግኘታቸው፤ ምንም ሳይናገሩ በቆሙበት እየተወዛወዙ እጆቻቸውን ወደኋላ አጣምረው ማልቀስ ቀጠሉ። በአንዱ ድንጋጤ ላይ ሌላ የተጨመረባቸው አባት፤ ወደ ክፍሉ በመዝለቅ ከአልጋው ጠርዝ ተንጠልጥሎ የነበረውን ግራ እጇን በግራ እጃቸው በመያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በስስት እየተመለከቱ ምን

አጋጥሞአት እንደሆነ ይጠይቋት ጀመር። ቀድማ
የተዘጋጀችበትን በሙሉ ነገረቻቸው።

ሀሳቤስ ከጎጆአችሁ ለአንድም ቀን ርቆ አያውቅም፤
አኮረፍኩት እንጂ ልጄን ፈጽሞ አልተውኩትም።
የምታኮርፊው የምትወጂውን ሰው ነው። አንቺም ይሄን
ኩርፊያችንን ገፍተሽ መምጣትሽ የልብሽን ንጽህና
ያሳያል። በመሃል ገብታ፤ ግትርነት እና ኩራት ብዙ
ያሳጡናል አባባ። ይሄን የሚያስረዳ አንድ ወግ ላጋራዎት፤
በአንድ ከተማ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ፤ ሁለት ወጣቶች
በፍቅር ወደቁ፣ ተጋቡ፤ ደጋሾቹ እራሳቸው ስለ ነበሩ፤
ሲያስተናግዱ ውለው ማታ ወደ አልጋ ሂደው ጫማቸውን
እኩል አወለቁ፤ በዚህ መሃል በሩ እንዳልተዘጋ አስተዋለ፤
እሱም እንድትዘጋው ነገራት፤ እንዴት እንዲህ ደከሞኝ
እያየህ ታዘኛለህ? ተነስተህ ዝጋው! ትለዋለች። እሱም ገና
አንድ ቀን እንኳ ሳይሞላን አልታዘዝም ትይኛለሽ?
በማለት ይቆጣል። በዚ እልህ ተያያዙ። እሷም መፍትሄ
ያለችውን ሀሳብ ሰነዘረች። ቀድሞ የተናገረ ተነስቶ ይዝጋ
በማለት። እሱም ተስማማ። እኩለ ለሊትም አልፎ ስለ
ነበር፤ ሌቦች ሲዘዋወሩ፤ ክፍት በር በማግኘታቸው
እየተደሰቱ ወደ ውስጥ በመግባት፤ ያገኙትን ሁሉ ዘረፉ።
አዲሶቹ ጥንዶች ግን የሚሆነውን ሁሉ ይመለከቱ ነበር።
እሷም በውስጧ እንዴት ሄዶ አያስቆማቸውም? ብላ
ትጠይቃለች። እሱም ቃል ካወጣ እንደ ሚሸነፍ እያሰበ
በዝምታ ይመለከታቸዋል። ዘራፊዎቹም ዘረፋውን
አጠናቀው ይወጣሉ። ነጋ። አንድ ተረኛ ፖሊስ በመንደሩ
ሲዘዋወር በሩ ክፍት ሆኖ በማየቱ፤ ለማረጋገጥ ተጠግቶ
ቢያንኳኳ የሚመልስለት አላገኘም። ቤቱም ዝብርቅርቅ
ብሎ በማየቱ ሽጉጡን መዞ ወደ ውስጥ ገባ። ጥንዶቹ
ቁጭ ብለው በማየቱ ጥያቄ ማቅረብ ጀመረ፤ አሁንም
የሚመልስለት አላገኘም። በቁጣ የባሏን ፊት በጥፊ
ቢመታው። ብድግ ብላ በመነሳት ባለ ቤቴን
እንድትመታው ማን ፍቃድ ሰጠህ? በማለት
አንባረቀችበት። ይህን ጊዜ ባለ ቤቷ አሸነፍኩሽ እያለ

ከተቀመጠበት በመነሳት በደስታ መዝለል ጀመረ። ዐዩ? አባባ እንዲ ያሉ ድርጊቶቻችን ከጥላቻ የመነጩ አይደሉም፤ ለእራሳችን ከምንሰጣቸው የተዛቡ አመለካከቶች እንጂ። መታዘዝ የበታችነት የሚመስላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ይሄን ስተት ሲሳሳቱ ይገኛሉ። ቀና ልብ መያዝ የብዙ ጥሎቻችን እና አለመግባባቶቻችን መንስሄ ነው።

የኔ ልጅ ጋብቻችሁን የተቃወምኩት በአደግንበት ልጅ ከሌላ ስፍራ ስለማይዳር ነው። ይህ ባህልም ወግም አይደለም፤ ልጅ የሚዳረው በቤተ ሰብ አስተዳደጓ ተጠንቶ የማን ልጅ እንደሆነች ተጣርቶ ነው ልጅ የሚዳረው፤ የሷም ወገኖች እንደዚያው። በዚያ መልኩ የተመሰረተ ትዳር ጥበቅ እና ጥልቅ ይሆናል። ፍቺም የማይታሰብ ነው። ያው መጋጨቱ ባይቀርም መፋታት ግን እንብዛም አይኖርም። የሚለያቸው ሞት ነው፤ ልጆቻቸውን ያለ አሳዳጊ አያስቀሩም። ልጆቹም ግማሽ ሰው ሆነው አያድጉም።

የኔ ልጅ ፍቺ ክፉ ነው ጎዶሎ ያደርጋል። ስብራቱም ሊጠገን የማይችል የእድሜ ልክ ነው። ግማሽ ማንነትሽን፣ አንቺነትሽን፣ ትዝታሽን፣ ድካምሽን፣ የልጅነት ወዝሽን፣ እድሜሽን፣ ተስፋሽን እንዲሁም የልጆቻሽን ተስፋ፣ ሳቃቸውን፣ ቤታቸውን፣ ህልማቸውን፣ በድምሩ ያንቺንም የባለቤትሽንም የልጆቻሽንም ሕይወት ነው ከወረቀቱ ጋር የምትቀጂው። ተዋወቅን፣ ተጠናናን፣ ተፈቃቀድን፣ ተዋደድን እናም ተጋባን ትላላችሁ። የድሮው ወግ ጎጂ ነው፤ እንዴት ሰው ከማያውቀው፣ ከማያፈቅረው ሰው ተጋብቶ ይኖራል? ትላላችሁ። እውነታው ያ አይደለም የኔ ልጅ በአንድ አይነት ባህል፣ ወግ፣ ሥርዐት፣ ሃይማኖትና ማኅበረሰብ ውስጥ ከማደግ እና ከመኖር በላይ ትውውቅ ያለ አይምሰልሽ። በዚህ መርኩ ተጋብተን ይኸው እኔ እና የቴራስ እናት ድፍን አርባ ዓመት በትዳር ኖርን። ፍቅር ደግሞ አብሮ የመኖር ቁልፍ የሚከፍተው

የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ነው። መተሳሰብ እና መከባበር የወለደው፤ በጊዜ ሂደት የመጣ ፍቅር ከአለት ይጠነክራል፤ ደራሽ ስሜት ነፋስ ሆኖ አይንደውም። ለዚህም ነው፤ ከእኛ ዘመን ይልቅ አዋቂ ነን በምትሉት፤ በእናንተ ዘመን የፍቺ ቁጥር በሚያስፈራ መጠን የበዛው። ማወቅ አስተውሎት ከሌለው ቅጠል ነው! የስሜት እሳት አርግፎ አመድ የሚያደርገው። ይህን ስልሽ የናንተ ዘመኑ የትዳር መንገድ ፉርሽ ነው ማለቴ አይደለም፤ እጅን በአፍ የሚያስጭኑ እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ድረስ የተጓዙ ትዳሮችን አይተናል፤ ግን አንዱን ጥሎ አንዱን አንስቶ አይዘለቅምና…

ድንገት አቋረጠቻቸውና ከዐይኗ ወደ ጉንጯ በዝግታ የሚፈሰውን እንባ እየጠረገች አባባ እንዲህ አልመሰለኝም ነበር! የሚሉት ሁሉ ገብቶኛል። እኔ ልጅን የምወደው እኮ ገና ልቤ ለፍቅር እንግዳ ከነበረበት እድሜ ጀምሮ ነው። የልቤ በር በእሱ ፍቅር ነው የተከፈተው፤ ዘግቶት ይኸው እስከ ዛሬ በውስጥ እንዳለ ነው። አባባ ላይወጣ ነው ልቤ ውስጥ ተደላድሎ የተቀመጠው። ከእሱ ውጭ ሌላ የምወድበት ሁለተኛ ልብ አይኖረኝም። የአባቴን ቁጭት በእሱ ነው የምከሰው። ልቡ ላይ አንግሶኛል አውቃለሁ። እንደዛ ባይሆን እንኳ ለአንዳች ደቂቃ ሳላመነታ፤ እየታዘዝኩ በልቤ አንግሼ ላኖረው፤ ለሁለታችን የሚተርፍ የዘለዓለም ፍቅር እኔ ጋር አለ። ይህ ጤዛ የሆነ የማለዳ ፍቅር እንዳይመስሎት፤ በብዙ የተፈተነ፤ በዓመታት የበሰለ እንጂ ብላ ስሜቷ የወለደው የእንባዋ ሳግ ከመናገር ከለከላት። እሳቸውም እያዩ ያሉትን ሕያው ፍቅር ከዚህ በላይ መካድ ስላቃታቸው ልባቸው ላይመለስ ተሸነፈ።

እየሆነ ያለውን በእንባ በመታጀብ ይከታተሉ የነበሩት እናት የሀዘንና የደስታ ድብልቅ በሆነ ስሜት ሲዋልሉ፤ ልባቸው በፍጥነት መምታት ጀምሮ በቆሙበት ተጥመልምለው ወደቁ። ተረባርበው ወደ ቀጣዩ ክፍል

ወሰደቸው። ክስተቱ የአኪያን ልብ በጸጸት ስለ ፋቀው፤ እንዳትነሳ የተሰጣትን ማስጠንቀቂያ ጥሳ፤ እጇ ላይ ያለውን የግሉኮስ ትቦ ነቃቅላ መሮጥ ጀመረች። ወደ ኮሪደሩ እንደታጠፈች ወለሉ አንሸራቶአት ወደቀች። በተሰማት ከባድ ህመም አብዝታ ጮኸች። እሷንም እንዲሁ ተረባርበው ሊያነሷት ሲሞክሩ አንድኛው ነርስ በመከልከል፤ በመጀመሪያ እግሮቿን አስተካክላላት፤ ከኋላዋ ሆና ወደ እሷ ጋደል በማድረግ እጆቿ መሃል ይዛ አነሳቻት። ከማዕጸኗ ደም መፍሰስ ጀመረ።

ህመሙም እየጠናባት በመምጣቱ ለተጨማሪ ህክምና ወደ ነፍሰ ጡሮች መከታተያ ወሰዷት። በሚገባ ከመረመሯት በኋላ፤ Placental Abruption አልያም Fetal Distress አለመከሰቱን አረጋግጠው፤ እሷንም ማረጋጋት ጀመሩ። አኪያ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም አይዞሽ። አላት ሲመረምራት የነበረው ዶክተር። ነፍሰ ጡር ሴቶች የመውደቅ አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ፤ የተለመዱ ሦስት አይነት አደጋዎች አሉ። ለእኔ ከሶስቱ ከባድ የምለው Fetal distress የምንለው ነው። ጽንሱ በቂ አክሲጅን አልያም አልሚ ምግቦችን እያገኘ እንዳልሆነ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው። የጽንሱ ልብ ምት መቀየር እና እንቅስቃሴ መቀነስ ዋናዎቹ ምልክቶች ናቸው። በብዙ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፤ የእንብርት ገመድ መጥበብን ጨምሮ። ይህ ሲሆን ደግሞ ጽንሱ ሕይወት አይኖረውም ማለት ነው። ሌላኛው ህጻኑ ከመወለዱ በፊት፤ የእንግዴ ልጁ ከእንብርት ሲለይ ሊከሰት የሚችል ከባድ ሁኔታ ነው። በልጁ ላይ የደም ፍሰትን ሊገድብና Placental abruption ሊያስከትል ይችላል። ሶስተኛው ጽንሱ ከ37ኛው ሳምንት አስቀድሞ እንዲወለድ የሚሆንበት ክስተት ነው። እንዳንቺ ያለን ኢጋጣሚ ጨምሮ፤ ምንም እንኳን አንቺ ሪላቲቭሊ ወደ መውለጃሽ የቀረብሽ ጽንሱ በሙሉ ጤንነት ላይ የሚገኝ ቢሆንም፤ የተለያዩ

ምክንያቶችን ልናነሳ እንችላለን። ኢንፌክሽኖች፣ Preeclampsia የደም ግፊትን እና ኩላሊትን አፈክት የሚያደርግ ክስተት ነው፣ Cervical insufficiency የማዕጸን በር ቀድሞ መከፈት፣ ተደጋጋሚ እርግዝና፣ ማጨስ፣ አልኮሆልና ከመጠን ያለፈ እንዲሁም የተከለከሉ መድኃኒቶችን መውሰድ፣ የስኳርና የልብ ህመም ጨምሮ..

ህመም ያሰቃያት ጀመር ከዚህ በፊት ተሰምቶአት የማያውቅ ቁርጠት አስጨነቃት። አጠገቧ የነበረችውን ነርስ በጥፍሯ እጇ እስኪደማ ቧጨረቻት። አይዞሽ ምን ይሰማሻል? ጠየቃት ከጩኸት በስተቀር አልመለሰችለትም። በዚህ ሁኔታ ቆይታ ረገብ አለላት። ዶክተሩ ህመምሽ ለ60 ሰከንዶች እንደቆየ ተረድቻለሁ። በዚህ መልኩ በየአስር ደቂቃው ወይም ቅርበት ባለው ልዩነት፤ በተደጋጋሚ ከቀጠለና ዳሌሽ አከባቢ ቁርጠት ከተሰማሽ፤ ሶስተኛ ላይ የገለጽኩልሽ መሆኑ ነው።

በዚህ ሁኔታ ቆይታ አመሻሽ ላይ ተገላገለች። ህመሙ ጸንቶባት ስለነበር ከአሸለበችበት ስትነቃ፤ ቴራስ ከሙሉ ቤተ ሰቡና እናቷ እንዲሁም ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር የነበረችበትን ክፍሉ አጥብበውት ነበር። እናቱ በእልልታ ክፍሉን ሞሉት፤ እናቷንና እህቱን ጨምሮ ሌሎች የማታውቃቸው ሦስት ሴቶችም እልልታውን ተቀላቀሉ። አኪያ የማፈር ስሜት ስለ ተሰማት ፊቷን መለስ አደረገች።

ሁሉም በተራ እየቀረቡ ማርያም በሽልም ታውጣሽ ሲሏት፤ በምላሹ ማርያም ታኑርልኝ እያለች ምላሽ መስጠት ጀመረች። ስለ መሸ ልጆቼ ጋር መሄድ ይኖርብኛ፤ እየመጣሁ እጠይቅሻለሁ ብላ ተሰናብታት ወጣች አይከል። አኪያ ከእናቷ በቀር ሁሉም የቴራስ ወገኖች መሆናቸው አሁን ግልጽ ሆኖላታል። ግቢ ግቢ ሲሉ ወደ ሰማችበት አቅጣጫ ስትዞር ሕልቃን አየቻት፤

እንዴት ነሽ አሁን? እኔንጃ አለች አኪያ፤ ሁሉም ሳቁ። አይዞሽ ለሁሉም ነገር አዲስ ስለሆንሽ ነው ትበረቻለሽ። ወደ ጆሮዋ ተጠግታ እድለኛ ሆነሽ እንጂ እራስሽንም ልጁንም ገድለሽ፤ ለእኔም የማይድን ጠባሳ አሳርፈሽብኝ ነበር።

ቴራስ አይከልን ለመሸኘት ከወጣበት ተመለሰ። ሕልቃን በማየቱ እየተገረመ እንዴት? የሚል ጥያቄ ሰነዘረ። አኪያ ደነገጠች፤ ሕልቃ ግን ፈጠን ብላ፤ ጓደኛዋ አይደለሁ እንዴ ከኔ ውጭ ማን እንዲያከማት ጠብቀህ ነበር? አለች። ይፈቀዳል እንዴ? እኔስ የገረመኝ አንቺን እዚህ ማየቴ ነበር። ልከ ነህ ላስት ታይም የተገናኘን ጊዜ ስለ ፕሮፌሽናችን ለማውራት ጊዜ ስላልነበረን ይሆናል። አረፍ በል ብላ በእጇ የያዘችውን ጣፋጭ አቀበለችው። አመስግኖ እንደማይፈልግ ነገራት። ለምን? ጣፋጭ ነገሮች የቴስቴስትሮን ሌቭልን እንደሚቀንሱ ለአንቺ አልነግርሽም። እናትቱ በመሃል ገብተው ምንድነው እሱ? በማለት ጠየቁት። እማ ቴስቴስትሮን በዋነኝነት የሚመረተው በወንድ የዘር ፍሬ ውስጥ ሲሆን በትንሽ መጠን ደግሞ በሴቶች እንቁላል ውስጥ የሚገኝ ሆርሞን ነው። ይሄ ነው ወንድን የወንድ መገለጫ የሆኑ ባህሪያትን እንዲላበስ የሚያደርገው። ይሄ ሆርሞን በሰውነቱ ውስጥ ያነሰው ወንድ እኚህን ባህሪያቱን እየለቀቀ ሴተኛ ባህሪያትን መያዝ ይጀምራል። እኔ ደግሞ ሴት እንደ ሴትነቷ ሴተኛ ባህሪ መያዝ፤ ወንድም እንደ ወንድነቱ ወንደኛ ባህሪ መያዝ እንዳለበት በጽኑ አምናለሁ! ማን ብላችሁ ልትሰይሙት አሰባችሁ? ብላ ርዕሱን ቀየረችው እራሷ ሕልቃ። አኪያ ቀልጠፍ ብላ፤ ስጠራው ደስ ይለኛል ሱር የሚለውን ሥም። አጋር ከሳራ ቤት ኩብልላ በዚያ በድካሟ፣ በመንገዷ ላይ አረፍ ብላ የነበረበትን ወንዝ ዳር ያስታውሰኛል። ልጇን እንደዛ እሰይመዋለሁ። ቴራስም፤ እኛ የሳራ ልጆች ነን! ከአጋር አይደለንም። ከባርያም አልተወለድንም፤ ባርነትም እጣ ፈንታችን

አይደለም። አዎ ምን አልባት በልባችን ጥመት፤ በግብጽ የፀሀይ ሀሩር ቀቅሎን ሽንኩርት ልጠን ይሆናል። ግን እግዚአብሔር ቁጣው እስኪበርድ፣ እስኪራራልን ለአራት መቶ ዓመት በግዞት ቆየን እንጂ፤ የእስራኤል አምላክ ለዘላለም አልተወንም። ስለዚህ ለልጇ ከይስሀቅ ወገን ምረጪለት አላት።

ሶስታችሁም ትተዋወቃላችሁ? አሉ የቴራስ አባት። አዎ ጋሼ ሕልቃ አብራን ነው የተማረችው። ከአኪያ ጋር ካልሆነ በምንም ተአምር ከሌላ ሰው ጋር ስትሳሳቅ አትገኝም፤ ለረጅም ጊዜ እንኳን አታወራም። ከፍል ውስጥ የጥያቄዎቹን መልስ ታውቃቸዋለች ግን መምህሮቹ ካልጠየቋት አትመልስም ነበር። ይሄን ስለሚያውቁ እነሱም ሌሎች ተማሪዎችን ጠይቀው ምላሽ ሲያጡ፤ ሕልቃ እስኪ መልሱን ንገሪያቸው ይሏት ነበር። አንድ ጊዜ እንደውም ምን ሆነ መሰላችሁ አዲስ መምህር ይመደብልንና እያስተማረ ጥያቄ ይጠይቃል፤ እጅ ያወጡ ነበሩ ግን ልክ አልነበሩም እንደ አጋጣሚ እሷን ይጠይቃታል መለሰችው። እያወቅሽ እንዴት ዝም ትያለሽ ብሎ ተቆጣት፤ ቁጡም ስለነበር። ይህ ነገር ተደጋገመ በሶስተኛው ወላጅ ካላመጣሽ እንዳትገቢ ብሎ ከክፍል አሶጣት። እንዲህ ተብላ ስለማታውቅ ደንግጣ ስታለቅስ ያዩ መምህራን ናቸው ባሕሪዋ እንደሆነ ነግረው ያስታረቋት።

ታስታውሳለህ አንድ ቀን ስልክ ሲፈተሽ ጓደኛህ የኔ ቦርሳ ውስጥ ደብቆ፤ እሷ እንዲ ስለማታደርግ ተብሎ የኔ ስለ ተዘለለ የተረፈለት? አንደኛዋ ጓደኛችን ደግሞ የደበቀችበት ቦታ? ከቤተሰብ ተደብቀው day party የሚሄዱ ልጆች እየመጡ ቦታው ላይ የተገኘን እስኪመስለን ይተርኩልናል፤ እኛም አንድ አንዴ እንሄዳለን። የምንሰማቸው የቢልቦርድ ሙዚቃዎች፣ ፊልሞች፤ ኢንተርኔት የተጀመረ ጊዜ ዳውንሎድ ለማድረግ እንበላ የነበረው ስቃይ፤ ወንዶቹ እየተደበቁ

ፑል ይጫወቱ ስለ ነበር ገንዘብ አይበረክትላቸውም! እኛ ነበርን ዳውንሎድ እንዲያደርጉ ካርድ የምንሞላላቸው የነበረው። ቴራስ ደግም under 17 ኳስ ቡድን ውስጥ ስለ ነበር ከተማዋን እየወከለ ይዞር ነበር። high school? Jesus! Those were the best years of my life! ኮካ ልንገዛ ወጥተን፤ መምህሩ ቀድሞን ገብቶ ያለቀሺበትን ቀንስ? እንዴ ትምህርት አመለጠኝ ብላ? አለች ሰዓር፤ አይደለም ስለማያስገባን እዚሁ እንሁን ብለን ከክላስ ጀርባ በተቀመጥንበት ዩኒት ሊደሩ ይመጣል፤ እኛም ተሯሩጠን ወደ ሽንት ቤት ገብተን ተደበቅን። የገባንበት የወንዶች እንደሆነ ስታውቅ አለቀሰች። ሁሉም ሳቁባት።

ቴራስ ምን አይነት ልጅ ነበረ? ብላ ጠየቀቻት ኤፍሮን። ከኔ ይልቅ አኪያ ትመልሰው ይሄን ጥያቄ አለች። እሷማ በቀለጠ ልቧ ነው የምትነግረን። እውነታው ያለው አንቺ ጋር ነው። እ... ቴራስ ግራ ያጋባኝ ነበር፤ ዝምተኛ ነው ስትዪው ከልጆች ሲደባደብ ታይዋለሽ። ኃይለኛ ነው ብለሽ ስትሸሺው፤ እርዳታ በሚያስፈልግሽ ጊዜ ሲረዳሽ ታገኚዋለሽ። የሆነ ቀን ከልጆች ተጣልቶ፤ ሊያባብሉት የሄዱትን ሁሉ በድንጋይ አሯሯጣቸውና ቦታ ቀየረ። በዚያው ደቂቃ ከእኛ ክፍል አጠገብ የነበረች ልጅ የወር ግዴታዋ መጥቶ ቀሚሷ ተበላሸ። በቦታው የነበሩ አምስት የሚሆኑ ልጆች ሲስቁባት፤ እሱ ሹራቡን አውልቆ አሰረላት። ቴራስ እንዲ አይነት ልጅ ነበረ። በጊዜው ምን አይነት ልጅ እንደሆነ ማወቅ ይከብደኝ ነበር። አሁን ግን ግልጽ ነው።

ሙዚቃ በጣም ይወድ ነበር። ሰዓር የጂንራ ቴስትህ? ብላ ጥያቄ አቀረበች። Hip Hop ሞስትልይ RnB አላት። ኢስት ኮስት ወይስ ዌስት ኮስት? ደገመች። ሳቀ። ያባል ኢስት ነው እንጂ አለ። ምን? አለች። አዎ ኢስት

ኮስት ሁሌም የሂፕ ፖፕ ውልደት ስፍራ እንደሆነ ይኖራል። ወደ ፊት ዘንበል ብሎ፤ ከግራንድ ማስተር ፍላሽ እስከ ናስ፤ በጄንራው እውቅና ምርጥ አርቲስቶችን አፍርተናል። ሰዓር፤ don't get me wrong ኢስት ኮስት በእርግጥም የራሱን አሻራ አሳርፎአል፤ ግን ዌስት ልዩ የሆነ ድምጻትና ኢነርጂ ወደ ሲኑ አምጥቶአል አለች። ልዩ? ያባል ሳቀ፤ more like derivative ዌስቶች የኢስትን ስታይል ኮፒ ለማድረግ ነው የሚሞክሩት።

ሰዓር ሳቀችና፤ what about the G-funk sound? The gangsta rap that came out of Compton? That was a revolutionary and original contribution to the genre. ልክ ነሽ ግን እኮ እሱ የአከባቢው ውጤት ነበረ ሲል ያባል መለሰ። ዌስት የጋንግ ባህል ላይ እና ማቴሪያሊዝም ላይ ያተኩራል። its a far cry ስቶሪቴሊንግ እና ላይሪክሲዝም ላይ ለሚያተኩረው ኢስት። ሰዓር ዐይኗ እየተንበለበለ ወደ ፊት ጠጋ ብላ፤ ምናልባት እንደዛ ይሆናል። ያ ማለት ግን ያነሰ ስፍራ አያሰጠውም። ሂፕ ፖፕ እራስን ስለ መግለጽና ታሪክን ስለ መናገር ነው። ዌስት ደግሞ የሚነገር ታሪክ አለው። ያባል እራሱን ነቀነቀ፤ የተናገርሺው እውነት ነው። ምናልባትም የትኛው ይበልጣል የሚለው አይደለም ዋናው ሁለቱ በልዩነታቸው ውስጥ በቅንጅት ያመጡት ተጽዕኖና ለውጥ ነው።

ሰዓርም ፈገግ ብላ Hip-hop is a melting pot of cultures and influences. It's perpetually evolving, and there's always space for groundbreaking innovations አለች። ኬንድሪክ ለማርን ተመልከተው he is a lyrical genius. His storytelling is

unmatched. ይሄን ለማረጋገጥ good kid, m.A.A.d city የሚለውን ማዳመጥ በቂ ነው። It's a masterpiece of storytelling.

ያባል ራሱን ነቀነቀ፣ ነገር ግን አገላለጹ የጥርጣሬ ነበር። አውቃለሁ ኬንድሪክ ትልቅ ራፐር ነው። ግን የጀ ዚ የግጥም ችሎታ ወደር የለሽ ነው። በቃላቱ ግልጽ ምስሎችን የመሳል ችሎታው በቀላሉ የማይታመን ነው። ሰዓርም አዎ፣ ግን የጀ ዚ flow ትንሽ ተደጋጋሚ ነው። የኬንድሪክ የበለጠ ተለዋዋጭ እና ሊተነበይ የማይችል ነው። አለች።

ኤፍሮን እና ሕልቃ በመሃል ገብተው ረገብ ለማድረግ ሞከሩ። ሕልቃ መሃል ላይ ወደ መግባባቱ ደርሳችሁ ነበር በድጋሚ መለያየቱን ጀመራችሁ። እኔ የኢስትም ሆነ ዌስት ኮስት የጥበብ እንጂ የስፍራ ተገዢ አይደለሁም። ስለዚህ ከየትም አከባቢ ይምጣ ስልቱ፣ ፍሎው፣ እንዲሁም ግጥሙ ለጆሮዬ ከተስማማኝ አደምጠዋለሁ። ይሄም በሙዚቃ እንድዝናና ይረዳኝ ነበር። ያው አሁን ሙዚቃ ሳይሆን መዝሙር ነው መዝናኛዬ። በኢስት እና በኮስት ይሄ የኔ ያ የእነሱ የሚል ስሜት ውስጣችን ካለ አርቱን እንረሳዋለን። አሁን dr. dre የሚያመርታቸውን ያኚን የመሰሉ ሙዚቃዎች ላላዳምጥ ነው የአንደኛው ደጋፊ ከሆንኩ? መሃል የገባሁበት አንደኛው ጉዳይ ይሄ ነው። ቦታው ሳይሆን ጥበቡ ይጥራን። አሁን ይሄን ውይይት ማድረጋችን ግትርነታችንን ያሳየኛል። የስፍራው ተወላጆች ብንሆን ምን ልንሆን እንደምንችል አስቡት። አንቺ እንደውም አክሰንትሽ የእነሱን ይመስላል። እዛው ተወላጅ መስለሺኛል።

ይሄ ውስጣችን ምን ያህል መቧደንን እንደለመደ፤ የእኛና የእነሱ የሚል ካንሰር እንደያዘን ያመለክታል። በሀገር በቀል ጥበባትና ባህሎቻችንም ውስጥ

ልናንጸባርቀው ነው ማለት ነው? ልዩነትን ማክበርና መከባበር ይልመድብን። ሀገሪቷ በዚህ አይነት እሳቤ ነው እዚህ የደረሰችው። ይቅርታ ከረበሽኩ። አንገታቸውን ደፉ።

የአኪያስ ሲሉ ጠየቋት የቴራስ አባት። ብዙ ሴቶች ይጠሏት ነበር። ለምን አለ ጋይዳድ። እጅግ ሲበዛ ቆንጆ ነበረች አለች። አሁን አትበልጥም? አሉ እናቱ። ጊዜው ለመግለጽ ያህል እንጂ አሁንም ያው ናት። በእሷ ምክንያት እኛ ክፍል የማይመጣ ተማሪ አልነበረም። ብቻ ብዙ ሴቶች አይወዷትም ነበር። አምስት ነበርን በአጠቃላይ ጓደኛሞች፤ ሁለታችን ግን በጣም እንቀራረብ ነበር። ቤተ ሰቦቻችንም እያደረሱ እየመለሱን፤ አብረን እንድናድር ሁላ ይፈቀድልን ነበር። እኔ ግን አባቴን እና እናቴን አብዝቼ እወዳቸው ስለ ነበርና፤ ትምህርት ቤት እንኳን ሆኜ ይናፍቁኝ ስለ ነበር ሌላ ቤት ማደር አልፈልግም ነበር። ግን ይሄን ጸባይ የአኪያ ጓደኝነት አስቀየረኝ። አይደል እንዴ? ስትል የአኪያን እናት ጠየቀች፤ እውነት ነው አሉ። አባቷ ይወዱኝ ስለነበር፤ እኛ ቤት ቅዳሜ ቅዳሜ እሳቸው ነበሩ የሚያመጧት፤ በዚህም ከአባቴ ጋር ጓደኛ ሁነው ነበር።

አኪያ ቀልድ እና ትረካ መተረክ ጎበዝ ነበረች። በውበቷ ምክንያት ይጠሏታል እንጂ እሷ ከማንም ጋር ተጣልታ አታውቅም። ሲናገሯት ሌሎቹ ጓደኞቻችን እንምታቸው ሲሉ እሷ እርሷቸው ባካችሁ ነበር የምትለው። አንድ ቀን ግን አንድ ልጅ አባቷን ሰደበችባት፤ ልጅቷን እንዳልነበረች አደረገቻት አስተኛታ ቀጠቀጠቻት። እነ ቴራስ ናቸው መተው ከላይዋ ያነሷት። ህጻኑ ማልቀስ ስለጀመረ ጨዋታውን አቋርጠው ትኩረታቸውን ወደ እሱ መለሱት። ነርሷ መጥታ ዶክተር ቆየሽ እየጠበቅንሽ ነው ስላለቻት ተጫወቱ ጊዜ ከአገኘሁ እመለሳለሁ ብላ ወጣች።

“የሰላሜ ሰው የታመንሁበት
እንጀራዬን የበላ፤

በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ”

ቴራስ ከደህንነት መሥሪያ ቤት አስቸኳይ የስልክ ጥሪ በመቀበሉ ያባልን እና ጋይዳድን በማስከተል፤ ስልኩ የሰላም እንዳልመሰለው በመንገር ኤፍሮን፣ ሰዓር እና ሶዲያር ወደ ዞዓር በመሄድ እንዲዘጋጁ አሳስቦአቸው ተያይዘው ወጡ።

መሥሪያ ቤት እንደደረሱ የሀገሪቷ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ሰፊውን ሞላላ ጠረጴዛ ከበው በሳተላይት መስመር መልዕክት ሲቀባበሉ በማየቱ፤ ያባልን፤ ለኤፍሮን ደግመህ እንድትዘጋጅ አሳውቃት ልክ ያልሆነ ነገር አለ! ብሎት ወደ መሰብሰቢያ ክፍል ዘለቀ። አቶ ፊንሐስ አጠገቡ የነበረን ወንበር እየጠቆመ፤ እንዲቀመጥ ጋበዘው።

ተቋርጦ የነበረው የሬዲኦ ሞገድ ወደ መስመር እንደገባ፤ ኢታማዦር ሹሙ ኦ92 ያላችሁበትን ሁኔታ አሳውቁኝ አለ። ኦ1..3 ሳ..ናስ..በ.. ከበባ ውስ.. ገብተና... የደ..ሰን መረጃ የተሳሳ... ነው። ቁጥ...ው ..ፍተኛ ነው። ኦ92 ምንም ያህል በቁጥር ቢበዙ በትጥቅ ትበልጧቸኋላችሁ። ሳትጨርሷቸው እንዳታፈገፍጉ! ምሽግ ይዛችሁ አዘግዩአቸው ሲነጋ ድሮን እንጠቀማለን። ኦ13 አቅማች.. አይፈ...ድም ..ዙ አባላ..ቻች.. እያለቁ ነው! የከባድ መሳሪያ ድምጽ መሰማት ጀመረ። ደርሰውብናል! ሊጨ... ኦ92... ኦ92... ኦ92 ምን ተከሰተ? 92 አብቅቶለታል! በቅርቡ እናንተም ያበቃላችኋል! የሚል ቃል ተሰምቶ ግንኙነቱ ተቋረጠ።

ሁለት ሻለቃ ሙሉ ጦር አለቀ ማለት ነው? አለ አንደኛ ጄነራል። ይሄ እኮ የመጀመሪያችን አይደለም፤ የመጨረሻችንም አይሆንም በዚሁ ከቀጠልን። በሚገባ እያስታጠቅናቸው ነው። ቆም ብለን ማሰብ ይኖርብናል። ይህ ጦርነት ከተጀመረ ቁጥራችን እጅግ መንምኖአል አባላቶቻችንን በሽምቅ ውጊያ ጨርሰውብናል። አሉ

ሌላኛው። ኢታማዦር ሹሙ ዝም ብላችሁ ከምትለፈልፉ አንድ መፍትሄ አምጡ እያለቅን መሆናችንን ለእኔ ነው የምትነግሩኝ? ወሬውን አቁማችሁ መፍትሄ አምጡ። ቴራስ መደራደር! መደራደር ነው መፍትሄው አለ። ከማን? ከማን ጋር እንደራደር? የልብ ምታቸውን ለመለካት እንዲ አለ እንጂ መልሱን ያውቀው ነበር። የታሉ? የት እናግኛቸው? የመረጃና ደህንነት ባለሞያዎች ተብላችሁ የተቀመጣቹ እናንተ እንኳን አንድ ጠብ የሚል መረጃ እጃቹ ላይ የለም። ይገኙበታል ከሚባለው ስፍራ ቀድመው ያጡቁናል። እዚ ስንላቸው እዛ ይሆናሉ አሉ ሲባሉ የሉም።

አምስት ናቸው አስር ናቸው ስንል ከርመን አሁን እንዴት እናድርጋቸው? ይሄን ዜና ሳያዳርሱት በቶሎ ሌላ አጀንዳ ስጧቸው። ምን አይነት? በአከባቢው ያለ ባንክ እንዲዘረፍ አድርጉ፤ ወይም አንድ አስር ሰዎች ይረሽኑ። ይሄን በተደጋጋሚ አድርገነዋል! በቃ ሌላ ዘዴ ዘይዱ። ሴት አርቲስቶች እንዲደውሉላቸው እንድታደርጉ የተሰጣቹ ትዕዛዝ ከምን ደረሰ አቶ ፊንሐስ? የተቻለንን እየሞከርን ነው፤ ቀድሞ መረጃው በአክቲቪስቶች በኩል ስለተበተነ፤ መራመድ አልቻልንም። ሁሉም መረጃዎች አስቀድሞ ስለሚደርሷቸው፤ ምንም አይነት መንገድ ብንጠቀም ማግኘት አልቻልንም። እሱን ለኛ ተወው አለ። እሱን ለኛ ተወው በቅርቡ ሁላችንም እንበጠራለን። ከእነሱ ጋር ሲሰራ የተገኘ የማያዳግም እርምጃ ይወሰድበታል። ከእነሱ በላይ የፈጀን ጉያችን ውስጥ የታቀፍነው እሳት ነው።

ቀይ ቦኔት ለብሰው ዐይናቸው ሲቀር ፊታቸውን ተከናንበው M4 carbine መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮች በሩን በርግደው በመግባት ወደ ተሰብሳቢዎቹ አነጣጥረው ተደርድረው ቆሙ። ኢታማዦር ሹሙም እስካሁን ስትጫወቱብን ከርማችኋል የመንግሥትን

ሚስጥር ሁሉ የምንለብሰውን ሳይቀር የምንበላውን ጭምር አደባባይ ስፀሩት ከርማችኋል። አሁን የመጨረሻ ስትንፋሳችሁን የምትተነፍሱበት ሰዓት ደርሶአል! ከማለቱ፤ አቶ ፊንሐስ፤ ቴራስ እኔ የማስተዳድረውን የደህንነት ቤሮ በኃላፊነት ሰጥቼህ ዝም ብዬ የምተውህ ይመስልሃል? ሁሉን እናውቃለን። ጀነራል ሠሀረ ሲመለምላቸው፣ ድርጅቱን ሲያቋቁም እቅድ ሲወጣ ሁሉ ሲከናወን አባል ነበርኩ።

አሁን ልዩ ወታደሮች ዞዓርን ከበው፤ የኛን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ከደቂቃዎች በኋላ ዞዓር ወደ አመድነት አባሎቹም ወደ አፈርነት ይቀየራሉ። ወንበርህ ላይ ጓደኛህ ያባል ይቀመጥበታል። ቴራስ የእጅ ስልኩን ማብሪያና ማጥፊያ ሦስት ጊዜ በፍጥነት ተጫነው። ደጋግሞም ጆሮውን ሦስት ጊዜ በክብ ቅርጽ ያሽ ነበር። ቀጠለ አቶ ፊንሐስ፤ የአንተ ነገር ነበር አልገለጽ ያለኝ ከውህደቱ በኋላ አንገትህን ነክስኩህ! ዛሬ ትደማለህ። ሌሎቹንም ስምንቱን ወታደራዊ መኮንኖች አፈራርቆ እየተመለከተ የእናንተም እንዲሁ ብሎ ወንበሩን ወደ ኋላ ተደግፎ ድምጹን ከፍ በማድረግ መሳቅ ጀመረ።

ቴራስ እነዚህ ስምንቱ መኮንኖች እነማን እንደሆኑ ቢያውቅም ከዚህ ጋር ምን እንዳገናኛቸው ማወቅ ተሳነው። አንደኛው ሦስት ጊዜ ሲያጨበጭብ ሰባቱም ተንሸራተው ጠረጴዛ ውስጥ በመግባት ገለበጡት። እሱ በቀኝ እጁ መዳፍ ጠረጴዛውን በመደገፍ፤ ሁለቱንም እግሮቹን ብድግ አድርጎ ከፊት የነበረውን በመምታት ጠረጴዛውን ዘሎ ወደ ኢታማዦር ሹሙ ሲንደረደር አጠገባቸው የነበረው ወታደር ደረቱ ላይ በተደጋጋሚ ተኮሰበት። ከስር ከነበሩት አንደኛው ተመቺውን ተከልሎ ኢታማዦር ሹሙን አንገቱን በማነቅ መሳሪያቸውን እንዲጥሉ አዘዛቸው።

ኢታማዦሩ እንዳታወርዱ አናቱን በርቅሱት ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈ። እሱም አንገቱን እንዳነቀው ወደ ግርግዳው ጠርዝ በመሸሽ ተደገፈው። ሁለመናውን በኢታማዦሩ ሸፈነው። ሁሉ ነገር ፍጥነት ስለነበረው የገለበጡትን ጠረጴዛ ተሸክመው በመከለል ወንበር እየወረወሩ፤ ቆመው ወደ ሚተኩሱባቸው ወታደሮች መጠጋት ጀመሩ። ሶስቱ ጥይት ጨርሰው በማቀባበል ላይ ባሉበት ጠልፈው በመጣል ተናንቀው ተቀበሏቸው። በዚህ ሁኔታ ሁለቱ መሳሪያውን መቀበል ቻሉ። አንደኛውን መኮንን አንገቱ ላይ ስለተኮሰበት በወደቀበት ቀረ፤ ሁለቱ የወደቁትን ወታደሮች አንስተው ከእነሱ ጀርባ በመከለል ወደ ቀሪዎቹ መተኮስ ጀመሩ። አቶ ፊንሐስ ለቀሪዎቹ ዞሯርን ከበዋል ላላቸው ትዕዛዝ አስተላልፎ በሩን ከፍቶ በመሮጡ፤ የመጀመሪያው መኮንን ኢታማዦሩን እንዳነቀው ግርግዳውን እየታሸ ወደ በሩ በመጠጋት እግሩን ጠልፎ በአፍጥሙ እንዲወድቅ በመገፍተር አመለጠ። እነቴራስም በአገኙት ሁሉ እየተከላከሉ፤ አንድ በአንድ በበሩ በመውጣት አመለጡ። የተረፉት ግን አራቱ ብቻ ነበሩ።

ቴራስ ትከሻውን መመታቱን ያወቀው ከተረጋጉ በኋላ ነበር። ለምን እዚህ ውስጥ ተካተታችሁ? ቴራስ ጠየቀ። ለታጋዮቹ እንዲሁም ለሕዝቡ እንዲበትኑት፤ ለአክቲቪስቶቹ የሚደርሳቸውን አብዛኛውን መረጃ ማን ይመስልሃል የሚያቀብላቸው? አሁንም ውስጥ ብዙ አሉ በፍጹም አይደርሱባቸውም። እኛም በወሰድነው ተገቢ ባልሆነ ሪስክ ነው የተደረሰብን እንጂ እነሱ ጥረው አይደለም። ከጥቂቶች በቀር አብዛኛዎቻችን በአካል ትግሉን መቀላቀል እንፈልጋለን፤ በእኛ ቦታ የሚቀመጡት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ስለምናውቅ፤ እዚሁ መሆንን መርጠናል።

አሁን ሠራዊቱ በትጥቅም፣ በሞራልም፣ በቁጥርም ተዳከሞአል። መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ እጅግ

ቀላሉ ጊዜ አሁን ነበር። ነገር ግን የምንከለከልበት ምክንያት የሀገሬቷ አሁናዊ ሁኔታ ለዚህ ስለማይጋብዝ እንጂ፤ ስለማይቻል አልያም ስላልፈለግን አይደለም።

ዞዓር

ሰዓር ከቴራስ የእጅ ስልክ በደረሳት የአደጋ ጊዜ ልዩ ጥሪ መሰረት የሚያስፈልጓትን ሃርድ ዲስኮች ሰብስባ ከሰነዶቹ ጋር በአንድ ቦርሳ ውስጥ ከከተተቻቸው በኋላ፤ እየዞረች ጋዝ በማርከፍከት ክብሪት ጭራ ወረወረች። ኤፍሮን የመረጋጋት ሁኔታ ስለ ታየባት ሰዓር ግራ እየተጋባች ነው። ኤፍሮን ካሜራዎቹን ተመልከቺ ተከበናል ምንድነው የምናደርጋቸው? አይዞሽ የሚሆነው ይሆናል ታገሺ! አለቻት። ሶዲያር ሽንጡ ስር የሸጎጣትን ፒስትል አውጥቶ እንዳትንቀሳቀሱ ብሎ ደቀነባቸው። ሰዓር ቀልዱን ትተህ በል አሁን አግዘን ስትለው፤ ተንበርከኩ! ብሎ አንባረቀባት።

ሶዲያር አውቀው ነበር አለች ኤፍሮን፤ አውቄው ነበር፤ ማመን ስላልፈለኩ እንጂ በሚገባ አውቀው ነበር። ለዚያም ነው ልጆቹን ሁሉ አስቀድሜ ወደ ሌላ ስፍራ የላኳቸው። እኔ እና አንተ ብቻ የምናውቀውን እውነት ለጂነራል ሠሀረ ስትነግራቸው፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእኔንም የእሳቸውንም እምነት በልተሃል። አንተ ለመወደድ ያደረከው፤ ማንነትህን ገልጾልናል።

በሕይወትህ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እምነትህን የምትሰጣቸው ግን ጥቂቶቹ ናቸው። እምነት በጊዜ ተፈትኖ በመከራ የሚገለጽ እንቁ ነው። አንተ በጊዜም በመከራም ወድቀሃል። ሰው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ይወድቃል፣ ይነሳል፤ እምነትም ይሰበራል ደግሞ ይጠገናል። ሁኔታዎቹ ግን የአጠጋገን መልክ ይወስኑታል። መጥረቢያ ወደ ጫካ ሲገባ አይተው ዛፎቹ፤ እጀታው የኛው አካል ነው አለ። የሚሉት ተረት አቸው ቱርኮች። ቀኑ መች እንደሚሆን እንጂ የማላውቀው፤ ይሄ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር አልነበረኝም። ያ ሁሉ ማስመሰል ለምን? ለምን ይሄን ማድረግ አስፈለገ?

አፍሽን ዝጊ! ለምን? ሀ...ሀ...ሀ ለምን አይሆንም? እኔን እንደ ተራ አባል እንጂ መች የሚገባኝን አድርጋችሁልኝ ታውቃላችሁ? ምንድነው እሱ የሚገባህ? ለኛ ያለን ለአንተ የተነፈገህ ምን ነበር? ዝም በይ አልኩሽ! እሺ ተናገር። ምንም ከእኔ የምትሰሚው አይኖርም። እስኪገቡ አፍሽን ዘግተሽ ተንበርከኪ። በፍጹም አላደርገውም ንገረኝ ምክንያትህን! ብናገርም አይገባሽም። ሞክረኝ!

ሰው ወዳጁን በምንስ ቢሆን እንዴት ይከዳል? አለች፤ እምነት የሰጠህን ሰው እንዴት በክህደት ትከፍለዋለህ? በሌላ መልክ እዚህ ተገኝተን ቢሆን አታለውህ አልያም አስገድደውህ ይመስለኝና ሶዲያር እባክህ እንዲ አታድርግ እያልኩ እማጸንህ ነበር። እንደዚያ አይደለም። የማመዛዘን ጉለት፣ የጤና እክል ኑሮብህም አይደለም። በሙሉ ፍቃደኝነት ነው እንዲ የምታደርገው። ምንድነው ምክንያትህ ሶዲያር? በቀል ነው? ምን አድርገንህ? ማንን?

ኢትዮጵያን! አለ። ኢትዮጵያን እቺን ሀገር አምርሬ እጠላታለሁ። አካል ለብሳ ባገኛት ግንባሯ ላይ ጥይት

አልቆጥርም እሱ ስለማያረካኝ። ባዶ ቤት ውስጥ ለዘመናት እቆልፍባታለሁ። መጀመሪያ ሀያውንም ጥፍሮቿን በጉጠት እነቅለውና ሚጥሚጣ እነሰንስባቸዋለሁ፤ ቀጥዬ የፈላ ዘይት ውስጥ በቁሟ እከታታለሁ ግን ከአንገቷ በታች ነው። ቶሎ ነፍሷ እንዲወጣ አልፈቅድላትም። ምን አድርጋህ? ለምን ሞቷን እንኳን የክብር አታደርግላትም? በጭራሽ ያን አልፈቅድላትም! ለእኔ ያሳየችኝን የበዛ ፍቅር እማ መልሼ አላሳያትም፤ በማዕረግ እንዳኖረችኝ እማ በማዕረግ አልቀብራትም። ሀ..ሀ...ሀ መራብ፣ መጠማት፣ መራቆት፣ መጠላት፣ መዋረድ፣ አንገት መድፋት ምን ማለት እንደሆነ እንድታየው እፈልጋለሁ። አባት በግፍ ሲደፋ፣ እናት በሀዘን ተቆራምታ ቤት ውስጥ ሚላስ፣ ሚቀመስ ሲጠፋ የመንደርተኛው አፍ ማሟሺያ ስትሆን፤ ልጅ በጨቅላ እድሜው ምን እንደሚሰማው እንድታውቅ እፈልጋለሁ። ይሄ ሀዘን፣ ይሄ ቁስል ሁሉም ቤት እንዲገባ ሁሉንም እንዲነካው እፈልጋለሁ! ለዚህ ነው ስምንት አባላቱን ጨምሮ፤ መቶ አርባ ዘጠኝ ተሳፋሪዎችን ጭኖ ደብረ ዘይት ላይ ከተከሰከሰው ቦይንግ 737፤ ሰዓት አርፍጄ ሳልሳፈር የቀረሁት!

እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ ነኝ ብሎ እጁን የሚታጠብ ማንም የለም። ሁሉም የእዝቸ ሀገር ሰዎች እንባዬ እጃቸው ላይ አለ። መሳሪያ ይዤ ወጥቼ ያገኘሁትን ሰው መግደል ያስኘኛል ግን እንደማልረካ አውቀዋለሁ። ምክንያቱም የማላዳርሳቸው ሰዎች ስለሚበዙ። ያለኝ ትክክለኛ አማራጭ ከጠላቶቿ ጋር በመሆን ሀዘኗን፣ ስቃዩአን ማብዛት። ቀስ እያለች በስቃይ ከእነ ልጆቿ ስትሞት እሱ ደስታን ይሰጠኛል። እንደናንተ አይነት ድርጅቶችን ሳጠፋ የመጀመሪያዬ እንዳይመስልሽ ከዚህም በኋላም ይቀጥላል። የመጥፊያችሁንም ጊዜ ያረዘምኩት ቺፑ እጃቹ እስኪገባ ነበር። በዚህ ሰዓት ቴራስ ደረቱ ላይ ጥይት እየተርከፈከፈበት እንደሆነ ስነግራችሁ በደስታ

ነው። አሁን ቺፑን ቀስ ብለሽ ወደ እግሬ ስር ወርውሪው! ሰዓርን አዘዛት። ገድለኽኝ ትወስደዋለህ! ለመሞት አትጣደፊ ይደርሳል። በዚህ ቺፕ ከዓለም ባለ ሀብቶች ተርታ አይደለም የምሰለፈው፤ እነሱን አስከትዬ በሀብት ማማ ሰቅለው ያነግሡኛል እንጂ። አይዞአችሁ ለእናንተም ቢሆን እኔ ንፉግ አይደለሁም፤ የተዋበ መቃብር አስገነባላቹኻለው። ሀገር ሀገር ትላላችሁ ያልታደላችሁ! ይህቺን ደሃ ምኗን እንደምትወዱላት አይገባኝም።

ሶዲያር ላለፍክባቸው መንገዶች በጣም አዝናለሁ። የእውነት ከልቤ። አን...ሳይጨርስ አስጨርሰኝ!። እንደምታየው ሁሉም ነገር እየነደደ ነው መፍጠን ይኖርብናል! እንዳድንህ እድል ስጠኝ! እነዚህ መንገዶች ያንተ ብቻ ነበሩ ያለህ ማን ነው? አንተ እናትህ አጠገብህ ነበረች ቢያንስ። የእናትም የአባትም ፍቅር ተነፍጎት በማደጎ ያደገ ስንት ሰው አለ፤ እንደዚህ ስልህ ያንተን ህመም ማሳነሴ አይደለም። ግን አንተ ስታለቅስ እንባህን የምትጠርግልህ፣ ገላህን የምታጥብህ፣ ልብስህን የምትቀይርልህ እናት ነበረህ። ዞር ዞር በል እስኪ አንድ ፍሬ ልጆችን በረንዳ ተኝተው ታገኛለህ። ይሄ የሕይወት አንዱ አካል ነው። አንዱ ደልቶት የሚበላውን ይመርጣል ተርፎትም ይደፋል፤ ሌላው የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በርሃብ ይሞታል። የለበሰው ገላው ላይ ነትቦ እላዩ ላይ የሚያልቅበት እንዳለ ሁሉ፤ የሚለብሰውን አጥቶ ሳይሆን ምርጫ ቸግሮት የሚጨነቅ አለ። ይሄ ደግሞ በርትቶ በመሥራት ይለወጣል። ጥፋት አላጠፋንም አይደለም፤ ግን እንደ ማኅበረሰብ ስትፈርጅ እራስህንም በዛው ተመልከት፤ አንተም የዚያው ውጤት ስለሆንክ። ይሄን ለመቀየር መስሎኝ የምንታገለው። የተመረዘውን አስተሳሰብ በማጠብ አዲስ የሚያመዛዝን፣ ለእኔ ብቻ የማይል፣ የሌሎችን ህመም የሚታመም፣ በልዩነት ውስጥ የተጋመደ ማኅበረሰብ ለመፍጠር መስሎኝ እዚህ የተገኘነው።

የምታውቀው ዶክተር እናቱም አባቱም በጥይት በፊቱ አይደለም የተገደሉበት? መች ሀገሩን ሕዝቡን ጠላ? ይልቁንም ለሀገራችን እድገትና መከበር፤ ለሕዝባችን የተሻለ ሕይወትን ልንሰጥ እኔነትን ጥለን ቢጋራ ቆመናል። ማጣትና መጠላትን በአንድም በሌላ ሁሉም ያውቀዋል። ይህቺ ሀገር unconditional love ስትሰጥህ ነበር! ሶዲያር ስለ ራስህ ያለህ አመለካከት ነው በዙሪያህ ያለውን ገዐድ ዓለም የሚፈጥርልህ! እኔን የሚወደኝ የለም! መልከጥፉ ነኝ! ለእኔ የሚያስብልኝ የለም! እድለ ቢስ ነኝ! ብለህ እያመንክ፤ እንዴት ብሩህ ዓለም እንዲኖርህ ትጠብቃለህ? መንገድህ ሁሉ ጨለማ ነው የሚሆነው! መጀመሪያ እራስህን ውደድ! አክብረውም! ሌሎችም ይከተሉሃል። ሶዲያር ይሄ ከሚሰማህ ወቀሳና ሽሽገህ ከያዝከው የውስጥ ህመም ለማምለጥ በምናብህ የፈጠርከው ቅዠት ነው ንቃ!።

ነቅቻለሁ ብሎ ግንባሯን ለመምታት ተኮሰ። በፍጥነት ጭንቅላቷን ወደ ቀኝ በማሸሽ ተንከባላ እግሩ ስር በመግባት ጠልፋ ጣለችው። በጀርባው ከወደቀበት በጉልበቶቹ ጀርባዋን እንዳይመታት እንዳይገለብጣትም፤ አቅሙን እንዳይጠቀም፤ የኃይሉ ምንጭ በሆነው ጭኑ ላይ ቁጭ ብላ በቦክስ አፍንጫውን ደጋግማ መታችው። አንደኛውን እጁን በጉልበቷ ከመሬት ጋር አጣብቃ መሳሪያ የያዘበትን እጁን በአንደኛው እጇ ይዛ ስትታገለው ታፋዋ ላይ ተኩሶ መታት። እንደ ምንም ብላ በሁለቱም እጆቿ መሳሪያውን ከነ እጁ በማዞር አፉ ውስጥ ከተተችውና ሶዲያር እኔ በዝምታ ሳፈቅርህ ኖሬአለሁ። አንተም ታፈቅረኛለህ ብዬ አስብ ስለ ነበር፤ ብቻችንን በሆንን እና እራት ይዘኸኝ በወጣህ ቁጥር ከመች መች ፍቅርህን ትገልጽልኛለህ ስል እጓጓ ነበር። ከዚያች ቀን ጀምሮ ግን ማንነትህን ባውቅም በመንታ ልብ ስዋልል እዚህ ደርሻለሁ። mathematics እወዳለሁ ትል የለ? በዚያው እንለያይ negative quadratics ከፍታቸው

እንደ ማማ ነው፤ ነገር ግን እጣ ፈንታቸው መፈጥፈጥ ይሆናል! Positive quadratics ግን የፈለገ ዝቅ ብለው አንገት ቢደፉ፣ ቢፈጠፈጡ ማማው ላይ ለመድረስ መንገድ ይፈልጋሉ ያገኙትማል! እንደ exponential functions ከባዶ አንስተን ከብር ሰጥተን ከፍ አደረግንህ፤ እራስህን የት እንዳስቀመጥክ ተመልከት! ለአህያ ማር አይጥማትም። ስለዚህ እኔ እና አንተ perpendicular lines እንመስላለን ሕይወት አንድ ጊዜ አገናኝታናለች ከንግዲህ ደግመን አንተያይም! ለሀገርህ ያልተመለስክ ለእኔ ልትጠቅመኝ አትችልም። አሁን የዘመናት ፍቅሬን በፍቃዴ እገለዋለሁ ብላው፤ በራሱ ጣት ቃታውን ሳበችው።

እሳቱ ኃይሉ እየጨመረ በመምጣቱ ሙቀቱ ስለ ጨመረ ሰዓር የደረበችውን ጥቁር ሌዘር አውልቃ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን አምጥታ ከጥይቱ በላይ አጥብቃ ከአሰረችላት በኋላ፤ እግሯን ሰቅላላት በመቀስ ሱሪዋን ቀደደችው። ጥጥ በአልከሆል በማርጠብ ዙሪያውን ጠርጋ፤ በጥርሷ ብረት አስነክሳት፤ በክላምፕ ጥይቱን አወጣችላት። ልታስርላት እየተዘጋጀች፤ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምጽ ተሰምቶ የክፍሉ መብራቶች በሙሉ ጠፉ። ወዲያው ባትሪ እያበሩ በቁጥር ብዙ የሆኑ ወታደሮች ወደ ውስጥ መግባት ጀመሩ። ኤፍሮን፤ ከኋላሽ ያለውን በተን ተጫኚው አለቻት። ዞራ በዳበሳ ስትጫነው እነሱ ያሉበት ወለል ወደ ውስጥ መግባትና ሁለቱ ግርግዳዎች ለመግጠም መንሸራተት ጀመሩ።

⁘⁘⁘

በናቡከደነጾር ቤተ መንግሥት ውስጥ በሚገኝ፤ ከዚህ ቀደም ተገኝተው በማያውቁበት ቢሮ ተሰብስበዋል። ሁሉም ምንም አይነት የቴክኖሎጂ ቁስ እንዳይዙ ተደርገዋል። ብዕርም ቢሆን መነድርም ጭምር። ይህ ስብሰባ በዚህ ጉዳይ የመጨረሻቸን እንዲሆን እፈጋለሁ! ትዕግስቴ ተሟጦ አልቆአል! በማለት ወንበሩን ደበደበ ናቡከደነጾር። ቀጠለ፤ አማጽያኑ ላይ ፉል ፍሌጅ ጦርነት መክፈት ይኖርብናል። እስካሁን የተጠቀምናቸው ስትራቴጂዎች ምንም እንኳን በቁጥር ብዙ ቢሆኑም፤ አንዳቸውም ውጤት ሲያመጡ አልታዩም። ይበልጥ መሸቶ በነጋ ቁጥር ወደ እኔ እየቀረቡ እንዲመጡ አደረጋቸው እንጂ። ስለዚህ መሳሪያ የያዙትንም ሆነ ሲቪሉን አንድ ላይ ማርገፍ አለብን። ከአንዳችሁም የርህራሄ ቃል እንዲወጣ አልፈልግም! ሊወጣም አይችልም። ሁላችሁንም በሚገባ አውቃችኋለሁ፤ ይህቺን ቀን ስትናፍቁ ከርማችኋል። ይኸው ከፊታችሁ ቆማለች ተጠቀሙባት።

ይሄን አምርራችሁ የምትጠሉትን ሕዝብ በምትፈልጉት መንገድ ተበቀሉት! ይሄኛው ተልዕኮ ግን በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ እፈልጋለሁ! ሀገሪቷ ውስጥ ወንድ፤ በቀን በማትሪ እስኪፈለግ ድረስ እንድታጭዷቸው እፈልጋለሁ። ሰገነት ላይ ወጥቼ የማየው ሁሉ እንዲሰግድልኝ መሆን አለበት! እኔን ሲያዩኝ አይደለም፤ ገና ሥሜ ሲጠራ መንቀጥቀጥ በግንባራቸው መሬት ላይ መደፋት መጀመር አለባቸው። የማይሸሩኝ፣ የማይደፍሩኝ መሆኔን ማወቅ ይህንም ማክበር አለባቸው! ይህ ዙፋን የእኔ ብ...ቻ ነው!!! ሞትን በሁሉም ቤት አስገቡት ጩኸት የሌለበትን ቤት ማየት አልሻም! ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ኦና አድርጓት!! ምድሪቷን በደም እጠቧት!

የከተማዋ ዐይን በሆነ ስፍራ ላይ የአማጽያኑ አባል የሆኑ ሁለት ወጣቶች ለዚያ ሁሉ ሰዓት መንገድ እስኪዘጋ ድረስ ሲታኮሱ ምን አንደረጋችሁ? እንዴት ያ ሁሉ ቀንስ በከተማዋ ሲዘዋወሩ ልትደርሱባቸው አቃታችሁ? ይህ ሁሉ ከተከሰተ በኋላ ምን አልከኝ? አቶ ፊንሐስን ጠየቀው፤ አንገቱን አቀረቀረ። እሱንም የራሳቸው የሆነ ሰው መረጃ ባያቀብላችሁ አትደርሱባቸውም አታውቋቸውም ነበር? ምን ሲሰሩ እንደከረሙ የተበጣጠሰ እንጂ ሙሉ መረጃ የላችሁም! አሁንስ ምን ያህል አባሎቻቸው በከተማዋ ውስጥ አሉ? ውስጣችንስ? ቴራስ እንኳን የት እንዳለ አታውቁም። ጭራሽ ባዶ እጃቸውን ከታጠቁ ኮማንዶውች ገጥመው አመለጧችሁ!

ትክክለኛ የሆነውን ድርጊት ለመፈጸም ወኔው የላችሁም! ሀሞታችሁ ፈሶአል! ምንም አይነት የስልክም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት በመላው ሀገሪቷ እንዳይኖር። ሳተላይቱ ሙሉ በሙሉ ይቋረጥ። በእኛ መዋቅር ውስጥ ሆኖ መረጃ የሚያቀብል ሁሉ ነጻ እርምጃ ይወሰድበት ረሽኗቸው! ምንም አይነት የሎጀስቲክ መስመር እንዳይኖራቸው። እርስ በእርስ እንዳይተማመኑ አድርጓቸው። መረጃ የሚለዋወጡባቸውንም መንገዶች በሙሉ ዝጉት። ልብ በሉ፤ ይሄ የመጨረሻ አፕሬሽናችን ነው! እኔም ወደ ጎረቤት ሀገራት አቻዎቼ በመሄድ የጀመርኩትን ሥራ አጠናክሬ እቀጥላለሁ፤ ተጠናክረው የሚመጡ ከሆነ ኢትዮጵያ በግብጽ እና ሱዳን እንድትወረር ፍቃድ ሰጥቼ የፈለጉትን ያህል መሬት መውሰድ እንደሚችሉ በመንገር አስወርራታሉሁ። ሁሉም ሀገሩን ለማዳን በሙሉ ትኩረቱ በሚዘምትበት ጊዜ እንዳያንሰራሩ አድርጌ መቃብራቸውን አርቄ ቆፍሬ እቀብራቸዋለሁ። ዛሬ ማታ ወደ ተግባር ይገባ! ጨርሻለሁ። በተቀመጡበት ጥሎአቸው ወጣ።

።።።

፧ ያለሁበት ቦታ ጨለማ ነው።

፧ ችግር የለውም እሱን ካየኸው ይበቃል።

ቴራስ ቪዲዮ ኮል አደረገው። ሕጻኑን ሲያየው ስሜቱ ተረበሸበት። አኪያ አሁን ታስፈልጊኛለሽ! ሁኔታዎቹ ግልጽ አልሆን ስላሏት መጠየቁም ሰልችቶአት ዝም አለች። መረጋጋት ስለ ፈለገ እንደ ልጅነቱ ዐይኖቹን እንደ ጨፈነ ነገራት። ምን ማለቱ እንደሆነ አኪያ ታውቃለች።

ስትተርክ የሚያምርባትን ደግሞም የምትችለውን ትረካ ጀመረች። አጠር ላድርግልህ። ሰፊ ግዛት እና የተከበረ ሀገር ይመራ የነበረ ንጉሥ፤ ከተለያዩ ሀገራት ግዛቶች ነገሥታት፤ ይመጡለት የነበሩትን የልጅህን ዳረን ጥያቄዎች ውድቅ ሲያደርግ ቆይቶ፤ ለሀገሩ ዜጎች ያለውን ክብር እና ፍቅር ይገልጽልኛል ብሎ ስላሰበ የሀገሩን ወጣቶች ሰብስቦ አንድ ፈተና አዘጋጅቻለሁ፤ ያንን ፈተና በድል የተወጣ ልጄን እድርለታለሁ በማለት ቃል ይገባል። ይህንም እድል ብዙዎች መሞከር ጀመሩ፤ ፈተናውን ግን ማለፍ የተቻለው አልነበረም።

በመጨረሻ አንድ እረኛ ወጣት ይመጣና፣ ፈተናውን ለመፈተን እንደሚፈልግ ይናገራል። ፈገግ በማለት ይፈቅዱለታል። ንጉሡም ሁለት ቁልፎችን ይሰጠዋል። አንደኛው የወርቅ አንድኛው የብር። የወርቁ ቁልፍ የደስታን፤ የብሩ ደግሞ የእምነትን በር እንደሚከፍት አሳውቆ፤ ወደ ልጁ ልብ ለመድረስ ሁለቱንም በብልሃት መጠቀም እንደሚኖርበት ይነግረዋል። ያ እረኛ ግር ቢለውም፤ ለመፈጸም ግን ቁርጠኛ ነበር። ቁልፉንም ተቀብሎ ጉዞውን ጀመረ። በመንገዱ ላይም አንድ ጠቢብ ያገኛል፤ እሱም ብዙዎች ደስታን አጥብቀው ይሿታል፤ ያለ እምነት ግን ደስታ ዘለቄታ የለውም ብሎት ያልፋል። እረኛውም ልባም ስለ ነበር የብሩን ቁልፍ ቀድሞ ተጠቀመው፤ ያም ቁልፍ ታማኝነትን እና ግልጸኝነትን

በሚጠይቁ ፈተናዎች የተሞላን መንገድ ከፈተለት። ይሄንም መንገድ ለመጨረስ ፍላጎቱን እና ሀሳቦቹን በግልጽ መናገር ይጠበቅበት ነበር። በመጨረሻ ወደ ቤተ መንግሥት ደረሰ፤ የወርቁን በር ከፈተው፤ ልዕልቷንም በደጃፍ ቆማ አገኛት። በፈገግታ ተሞልታ እውነተኛውን መንገድ መርጠሃል፤ እምነትን እና ግልጸኝነትን የሚያስቀድሙ ብቻ እውነተኛውን ደስታ ያገኙታል! ከአሁን ጀምሮ የአንተ ነኝ አለችው።

አኪያ ነገ ማልጀ ያለሽበት መጥቼ ሁሉን እነግርሻለሁ። ሌላም ድገሚልኝ!

በዚሁ ንጉሥ ግዛት ውስጥ የሚኖር እጅግ ብልሃተኛ እና ጎበዝ የእንጨት ቅርጻ ቅርጽ ባለ ሞያ ነበር። አንድ ቀን ይሄ ባለሞያ የልጁን በጸና መታመም በመስማቱ፤ ፕላስቲክ ለማቅለጥ የጫረውን እሳት ሳያጠፋው በሩን ዘግቶ ስለ ሄደ፤ እሳቱ በመያያዝ በትንሹ፤ ሱቁ መንደድ ይጀምራል። እባቦች በተፈጥሮ ደመ ቀዝቃዛ ectothermic ስለ ሆኑ፤ ውጫዊ ሙቀትን ይፈልጋሉ። በዚህም ምክንያት አንድ እባብ ውስጡ ወደ ሚነደው ሱቅ በማምራት ወደ ውስጥ ይገባል። ለመዘዋወርም በሚያደርገው ጥረት በሱቁ የነበሩ ቁሶች በቾኮላ በአግባቡ ስላልተደረደሩ ይናዳሉ። መጥረቢያም ወድቆ ጭራውን ይጭረዋል። በዚህ የተናደደው እባብም ይነድፈውና ይጠመጠምበታል። ይበልጥ እየሸረከተው ሲመጣ፤ እሱም እልሁ እየጨመረ ይበልጥ ይጠመጠምበታል። በመጨረሻ እባቡ ተበጣጥሶ አረፈው። አንድ አንድ ጊዜ ሁኔታዎች ወይም ሌላ አካል ሳይሆን ሌላውን የጎዳን መስሎን በምናደርጋቸው ድርጊቶች የራሳችን አጥፊ እራሳችን ሆነን እንገኛለን።

ይህን እየተናገረች ያለችበት አፓርታማ በሩ ሲከፈት ሳይሰማት የታጠቁ ወታደሮች ወደ ነበረችበት መኝታ

በመግባት ስልኩን ከእጇ ነጥቀው፤ ብትለምናቸውም ጆሮ ሳይሰጧት መሬት ላይ እየጎተቱ ወደ ሳሎን ይዘዋት ገቡ። አንደኛውም የቴራስንም እህት በተመሳሳይ እየጎተተ ከሌላኛው ክፍል ይዞአት በመምጣት ሁለቱንም እጆቻቸውን ወደ ኋላ አሰራቸው አኪያ እየጮኸች ስለ ነበር ልብሷን ቀዶ አፏን አፈነበት። የቴራስ እህትም ደጋግማ አራስ ናት እባካችሁ እሷን ተዎት እያለች ስታለቅስ፤ በሩን ከፍቶ የገባው አቶ ፊንሐስ በእርግጫ ልቧን ሲመታት ተዘረረች። አኪያን ጸጉሯን ይዞ ያ ውሻ የት እንዳለ ንገሪኝ? ብሎ በጥፊ መታት። አላውቅም! ደገማት። ሕጻኑ ከመኝታ ቤት ድምጹን አሰምቶ ማልቀስ ጀመረ። አቶ ፊንሐስ አጠገቡ ቆሞ የነበረውን ሂዶ እንዲያመጣው አዘዘው። ሄዶ እንዳመጣው ፊንሐስ ስልኩን ተቀብሎ ይታይሃል? ቴራስ ትታይሃለች? ሚስትህን እቆራርጣታለሁ! ያላችሁበትን ጠቁመኝ እያለ ሆዷን ይረግጣት ጀመረ።

ፊንሐስ እባክህ እሷን ተዋት፤ እባክህ እኔ ያላችሁበት ድረስ እመጣለሁ። አሁን እመጣለሁ እያለ ተማጸነ ቴራስ። አቶ ፊንሐስ ካሜራውን ወደ ሕጻኑ አዙሮ፤ ብቻህን አልፈልግህም! ሁላችሁም ያላችሁበትን ቦታ ጠቁመኝ! እያለ ደጋግሞ ቢጠይቀውም፤ እሱን በፍጹም አላደርግም! እኔ ግን ያላችሁበት አሁኑኑ እመጣለሁ! እያለ ይጮህ ነበር። ካሜራውን ሲያንቀሳቅሰው እህቱ ወድቃ በማየቱ፤ እህቴን ምን አደረካት ፊንሐስ እገልሃለሁ ሲል፤ እስካሁን ምንም አላደረኳትም አሁን አደርጋታሉሁ በማለት ደጋግሞ ተኮሰባት። ቴራስ እና አኪያ አምርረው አለቀሱ። አሁንም አትናገርም? አቶ ፊንሐስ ጠየቀ።

በፍጹም የሀገሬን ተስፋ አሳልፌ አልሰጥህም! አንተ ወራዳ! ባንዳ! ቃል ኪዳኔን አልበላም! በፍጹም እኔን እንደፈለክ አድርገኝ አለ።

ልጅህን ከመግደሌ በፊት የመጨረሻ እድል እሰጥሃለሁ። ያላችሁበትን ጠቁመኝ ይሄን ቅዠታችሁን ልቋጨው! 1...2...3

እንዳታደርገው አንተ...

የሕጻኑን እግር ይዞ ከግርግዳው ጋር ጭንቅላቱን ደጋግሞ አጋጨው። አኪያ ድምጿ እስኪ ጠፋ አምርራ ጮኸች። ቴራስ ድምጹ ጠፋ የቆመበት መሬት የከዳው መሰለው፤ ጨለመበትና አዙሮት ወደቀ። ስልኩን ግን ከእጁ አልጣለውም ነበር። መናገር ፈልጓል ቃል ማውጣት አቃተው። አትናገርም? አሁን ወደ ሚስትህ እዞራለሁ! ይህቺን የመሰለች ጽጌሬዳ እቀጥፋታለሁ ካሜራውን ወደ አኪያ አዞረው። አኪያ እንደ ተንበረከከች ሁለቱንም እጆቿን መሬት ላይ ዘርግታ በግንባሯ ተደፍታ ትጮኻለች ድምጿ አይሰማም። አንተ የተረገምህ የስካሁኑ አይበቃህም? አትናገርም? ቴራስ አሁንም መናገር እንዳቃተው ነው። ያባል እና ኤፍሮን እንደ ገቡ ምንም ሳይናገሩ ጥይቱን ግንባር ግንባራቸው ላይ እያነጣጠሩ ለቀቁባቸው። አቶ ፊንሐስ እሱ ጋር ሳይደርሱ የአጸፋ እየተኮሰ ወደ ሶፋው ተወርውሮ በመግባት ተመሸገ። እያዘናጋ እጁን እያወጣ በመተኮስ እየተከለለ ወደ በሩ በመጠጋት እንደለመደው በበሩ በኩል አመለጠ። ያባል ተከታትሎ ሊመታው ቢሞክርም አልቻለም።

⁜⁜⁜

ቡድኖቹን ሲያዘጋጅ ሰንብቶአል። ዛሬ ማታ ይህ ኃይል አለበት በተባለበት ሁሉ ስፍራ እኩል በሆነ ሰዓት ኦፐሬሽን ለመጀመር ሁሉም በያለበት የመጨረሻዋን የነጋሪት ድምጽ በተጠንቀቅ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ዝግጅት ኦፐሬሽኑ በሚደረግባቸው አከባቢዎች የሚገኙ ወጣቶች መንገድ እንዲዘጉ በቀረበላቸው ጥሪ መሰረት የትኛውም አይነት የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ላልተወሰነ ጊዜ ገድበዋል።

ሂሶጵ የቀጠሮው ሰዓት እንደ ደረሰ ወደ ተራራ በመውጣት፤ በሰዓር አማካኝነት የተላከለትን ሩሲያ ሰራሽ ሳተላይት ፋይንደር በማብራት፤ አንቴናውን ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በማዞር ተከለው። ፋይንደሩ አረንጓዴ ሲያበራለት፤ በጀርባው የተሸከመውን ቦርሳ አውርዶ ሚሊተሪ ስታንዳርድ የሆነውን Getac X600 በመባል የሚጠራ በብዛት በአሜሪካን እና በሩሲያ ስፔሻል ፎርስ ወታደሮች ለውጊያ ጥቅም የሚውል ኮምፒውተር በመክፈት ከሳተላይት ጋር አገናኝቶ መጠበቅ ጀመረ።

ስክሪኑ ውስጥ፤ ተደርድረው የተቀመጡ በቁጥር በዛ ያሉ ሰዎች መታየት ጀመሩ። ሂሶጵ እያያቸው ያሉ ሁሉ በአንድነት በመነሳት ማጨብጨብ ጀመሩ። ቀኝ እጁን የግራ ደረቱ ላይ በማድረግ በተቀመጠበት አንገቱን ደጋግሞ ዝቅ በማድረግ ምስጋናውን ገለጸላቸው። ተቀመጡ። ኤፍሮን አሁን ወሳኝ የሆነውን ስብሰባ መጀመር እንችላለን በማለት የጉባኤውን መጀመር አበሰረች።

ጄነራል ሂሶጵ የዞዓር ኦፐሬሽን ማዕከል በደረሰበት አደጋ የተሰማውን ሀዘን በመግለጽ ጀመረ። እንደምታውቁት ትግላችን የተለያዩ መሰናክሎችን በማለፍ፤ አሁን የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሶአል። በውጊያው አውድማ ከምንገጥመው ጦር ይልቅ፤ ወጣቶቹ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት እራሳቸውን በራሳቸው ይምሩ፤

የሚፈልጉትን መሪ ራሳቸው በሚፈልጉት መስፈርት ይምረጡ ተብሎ መወሰኑ፤ ብዙ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ነበር። ነገር ግን ወጣቶቹ ያላቸው የጦርም ይሁን የአስተዳደር ዕውቀት ከተጠበቀው በላይ በመሆኑ፤ ለዓላማቸውም ጽኑአን በመሆናቸውም ሊደርስ ከነበረው የእርስ በእርስ እልቂት በጥበብ አልፈዋል። የበላይ ጠባቂ ሽማግሌዎቹም ጥበብ ተጨምሮበት።

ውስጣቸው የተለያዩ የግል እና የማኅበር ፍላጎቶችን አንግበው ትግሉን የተቀላቀሉትን፤ ከተለያየ የማኅበረሰቡ ክፍል የተውጣጡ ግለሰቦች በጥበብም በኃይልም እንዴት እንዳስወገዷቸው ስታዩ ትደመማላችሁ። ይህ ማለት ጥፋት አላደረሱም ማለት አይደለም ነገር ግን ሊደርስ ከነበረው አንጻር፤ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

አንድ የጦርነት ሜዳ ላይ ያጋጠመን ክስተት ላጋራችሁ። እግዚአብሔር ከነሱ ጋር ይዋጋ ነበር፤ ውግያ ሲጀምሩ የማያውቁትን ኃይል ይላበሳሉ። ኃያላን ይሆናሉ ተኩሰው አይስቱም ምሽጋቸው በጠላት አይደፈርም። የላይኛውን መንገድ የሚያስቡ ነበሩና። እስኪገረሙም ድረስ ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዱ ነበር። ግን መጠንቀል ጀመሩ፤ አንድ አውድማ ላይ እልቂት ደረሰባቸው፤ ይህን ያደረጉት ቡድኖች ፈጽሞም ወደሙ። የእግዚአብሔርን ኃይል በመካዳቸው። ሌላኛው ደግሞ አንደኛው ቡድን ያለበት ስፍራ ቁጥራቸው ከፍ ባለ ሞርታሮችን፣ ዲሽቃዎችን እና በቁጥር የበዙ የነፍስ ወከፍ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ከእነተተኳሻቸው በታጠቁ የአርባ ስምንተኛ ክፍለ ጦር የስድስተኛ ሺ አለቃ የናቡከደነጾር ወታደሮች ይከበባል። በዚህም መሰረት ሌላ ስፍራ የነበሩ የአብዮቱ አባላት እንዲያግዟቸው በደረሳቸው ጥሪ መሰረት ይደርሱና፤ በተቃራኒው በማለቅ ላይ የነበረውን የናቡከደነጾር ሠራዊት አግዘው ወንድሞቻቸውን መውጋት ይጀምራሉ። የመጀመሪያዎቹ በመደናገጥ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ይጀምራሉ። ይከተሏቸዋል። እነዚህም ምንም አማራጭ

ስላልነበራቸው ውጊያውን ይቀጥሉታል ይደመሰሷቸዋልም። የተረፉትንም ማርከው ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው፤ ታዘው እንደሆነ ይነግሯቸውላል። በማን? በማለት ይጠይቃሉ፤ ሁሉንም አደረጃጀቶች ጠቅልለው መምራት የሚፈልጉ ኃይሎች እንዳሉ ይደርሱበታል።

ታድያ እነዚህ ኃይሎች የሕዝቡን ትግል ጠርንፈው ሥልጣን መያዝ እንጂ፤ የከረፋውን ይሄን ሥርዐት ለሕዝቡ በሚጠቅም አዲስ መንገድ መገንባት አይደለም ፍላጎታቸው። በመሆኑም ይህን የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። ብዙም ጥፋት አድርሰዋል። አሁንም በመሃል የሉም ማለት ባይቻልም፤ በወጣቶቹ ብልሃት ግን ቁጥራቸው እዚህ ግባ በማይባል መልኩ መንምኖ ከአመራር ስፍራም ተወግደዋል። አሁን አመራር ላይ ያሉት በሙሉ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። አንድ አዛዥ ከድቶ ወደ መንግሥት እንደኮበለለ በዜና ሰምታችኋል። እውነታው ግን እንደዚያ አይደለም! ውስጣቸው መጥራት ስላለበት ከአዛዦች አንዱ እንደከዳ እና ከመንግሥት ጎን መሆን እንደሚፈልግ በማሳወቅ ከነሱ አንድ አንድ ጠቃሚ የሆኑ ግን የሚለወጡ መረጃዎችን በመስጠት ማን ከመንግሥት ጋር እንደ ሚሠራ ለማወቅ እና ቆርጦ ለመጣል ውስጣቸውንም ለማጥራት የተጠቀሙበት መላ ነበር ተሳክቶላቸዋልም። የድል አጥቢያ አርበኞች እንዳይበረክቱ የሚቻላቸውን በማድረግ ላይ ናቸው። ሌንጊዎስ የጌታን ጎን ሲወጋው እሱ መጉዳቱ ነበር ግን ከጎኑ የወጣው የድህነታችን ደም እና ውሀ ነበር። ለክፋት ያደረጉት ለበጎ ሆነልን።

በሄሊኮፕተር እና በአንቶኖቭ ጭምር እየላከ ከሚያሳጭዳቸው ወታደሮች እና በድሮን ለማድረስ ከሚሞክረው ጥቃት በተጨማሪ፤ ናቡከደነጾርም ይከፍተው የነበረው የሴራ ዘመቻ ቀላል የሚባል

አልነበረም። ማኅበረሰቡ ቀድሞ ስለ ነቃ የተፈለገውን ያህል ውጤት ሳያመጣ ቀርቶአል። አሁን ሁለንተናዊ ቁመናችን የተሟላ ነው። ቁጥራችንም ለመቁጠር የሚያዳግት ደረጃ ደርሶአል። በዚህ ምሽት ከሰዓታት በኋላ የምንጀምረው ኦፕሬሽን የናቡከደነጾርን አገዛዝ ሥርዓተ ቀብር የምንፈጽምበት ይሆናል። ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲው ሥራም አመርቂ ውጤት ማሳየት እየጀመረ ነው። ተልኮ ሞርያም! በዚህች ምሽት ይጀምራል። አብርሃም የሚወደውን ልጁን በፍቃዱ ሊሰዋ እንደ ተዘጋጀ እንዲሁ እኛም እንደ ዐይናችን ብሌን የምንሳሳላቸውን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች፤ ከምን ጊዜውም በበለጠ፤ ባሩድ እንዲያሸቱ፤ ሞትን ፊት ለፊት እንዲያዩት ወደ ሲኦል በዚህች ሰዓት እንልካቸዋለን። እነሱ ወድቀው ሀገር እንዲያቆሙ። አብርሃም የሚወደው ልጁን ለእግዚአብሔር ሲል ለመሰዋት ተዘጋጀ። እኛስ? የምንወደውን ለእግዚአብሔር ወይም ለትዳር አጋር ወይም ለቤተሰብ ከፍ ሲልም ለሀገር ምናችንን ለመሰዋት ዝግጁ ነን? አጥብቀን የምንወደው ምንድነው? እኔ ነፍሴን ለመሰዋት! በማለት ንግግሩን ቋጨ።

በድጋሚ ሁሉም በአንድነት በመነሳት በጭብጨባ አድናቆታቸውን እና መልካም ምኞታቸውን ገለጹለት። ኤፍሮንም ተነስታ፤ ለወደመው ስፍራ አትዘን አሁን ያለንበትን ጨምሮ ብዙ በረቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተሞሉ ስፍራዎች አሉን አለችውና፤ አሁን ወጣቶቹ በእሳት የተፈተነ ወርቅን እንደሚመስሉ አረጋግጠናል። ሁሉን በድል ተወጥተው እዚህ ሲደርሱ፤ እጆቻችን ላይ ያሉትን ሰነዶች በሙሉ እናስረክባቸዋለን! ሀገሪቷን ፍትሕ፣ ርትህ አዋቂ፤ የተከበረች፣ የተፈራች፣ የታፈረች፣ ታላቅ እና ገናና ያደርጓታል! ለዜጎቿ ብቻ ሳይሆን ለዓለም የምትተርፍ የበረከት፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የመከባበር ምልክት ያደርጓታል! የፍትሕ ሰንደቅ ትሆናለች ኢትዮጵያ! የሕግ መፍለቂያ ትሆናለች! በማለት

ድምጿን ከፍ አድራ ስትናገር፤ ሁሉም እንባዎቻቸው መንታ መንታ እየሆኑ በጉንጮቻቸው መውረድ ጀመሩ። ፕሮፌሰር ጢሞቴዎስ እና ቴራስ በእኩል ጊዜ በደሜ ሀገሬ ቀና ትበል! አሉ፤ በነፍሴ ትለምልም በማለት ቀኝ እጆቻቸውን ጨብጠው ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ተቀበሏቸው።

ጄነራል ሂሶጵ ከዚህ በኋላ ከተራራው ወረደ። አጭር እንቅልፍም ተኝቶ ተነሣ። የታቀደው ሰዓት በመድረሱ ሁሉም የጦሩ አባላት በየስፍራው ተዘጋጅተው ነበር። የመጨረሻዋ ነጋሪት ተጎሰመች! ሁሉም አደረጃጀቶች በየስፍራቸው በእኩል ጊዜ የናቡከደነጾር ሠራዊት ላይ ከምሽቱ በሶስተኛው ክፍል ዘመቱባቸው።

ሌሊቱ ፀጥ ብሎአል፣ ብቸኛው ድምፅ የሣሩ ውስጥ የነፋስ ሹክሹክታ ነበር። በተራራ፣ በቁጥቋጦና ዛፍ ውስጥ ተደብቀው፣ የነጄነራል ሂሶጵ ቡድን ሸምቀዋል፣ ዓይኖቻቸው ከበታቻቸው ባለው ሸለቆ የሚገኘው ካምፕ ላይ አተኩረዋል። ጨረቃ በሰማይ ላይ ተንጠልጥላ፣ የስፍራውን ጠርዞች የሚያበራ ደማቅ ብርሃን ትረጫለች። የነጻነት ታጋዮቹ፤ የጠባቂዎቹን እንቅስቃሴ፣ የወታደሮቹን አሠራር እና በካምፑ ውስጥ ያሉ ተጋላጭ ስፍራዎችን በመሰለል ለሳምንታት ሲከታተሉ ቆይተዋል።

ሂሶጵ በመስቀል ቅርጽ አማትቦ የጠራኸኝ አንተ አበርታኝ አደራ ብሎ፤ እጁን በማንሳት፤ የመጀመሪያው ቡድን እንዲንቀሳቀስ ምልክት ሰጠ። በፍፁም ፀጥታ፣ ጨለማው ውስጥ እንደ ጥላ በምድር እየተንሸራተቱ ተጓዙ። በነዳጅ የተነከሩ ጎማዎችን በጥንቃቄ በአጥሩ ዙሪያ በማስቀመጥ ወደ ሥራ ገቡ። እያንዳንዱ እርምጃ፣ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የተጠና ነው። ዛሬ ማታ ምንም ስህተቶች ሊኖሩ እንደማይገባ ሁሉም ያውቃሉ።

በዚሁ ጊዜ ሌላ ቡድን ወደ ካምፑ ዳርቻ ዘልቆ ገባ። ተግባራቸው ግልጽ ነበር፣ የኃይል አቅርቦቱን ማቋረጥ። ሽቦዎቹን ሲቆርጧቸው፣ የብርሃን ብልጭታ በመፍጠር ድርግም ብለው፣ ካምፑ ከውጭው ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት አቋረጡት። ከዚያም ሰፈሩ በሙሉ ጨለማ ውስጥ ገባ። አባላቱ ምልክቱን እየጠበቁ በተጠንቀቅ ቆመዋል። ውጥረት በአየር ላይ ሰፍኖአል። ጄነራል ሂሶጵ፣ ዓይኖቹ በእልህ እየተንበለበሉ፣ አጭር ትዕዛዝ ሰጠ። በቅጽበት ሌሊቱ በእሳት ነበልባል ውስጥ ገባ። ጎማዎቹ በነበልባል ውስጥ ይጮኻሉ፤ በካምፑም ዙሪያ የእሳት ቀለበት ይነድዳል፤ ነበልባሉ ወታደሮቹን እንደ ጥበቅ ቋጠሮ ከበባቸው። ጥቅጥቅ ያለዉ ደረቅ ጭስ በሌሊት ወደ ሰማይ እየነፈሰ በመንገዱ ላይ ያገኘውን ሁሉ በላ።

ድንጋጤ በናቡከደነጾር ሠራዊት ላይ ወደቀ። በጭሱ በመታፈን፣ ዓይኖቻቸው እየተቃጠሉ፣ ወታደሮቹ ከድንኳኖቻቸው ወጡ። ጥላዎች በጨለማ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፤ እነሂሶጵ ቦታ ያዙ ፣ ከተራራው ከፍታ ላይ አልሞ ተኳሾች ተሰይመዋል። የጥይት ድምጾች አስተጋቡና በካምፑ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ሰዎች አንድ በአንድ ወደቁ። ቀደም ብለው ያቀዱትን እቅድ በመተግበር፣ የጦር ትጥቅ ግምጃ ቤቶችን እና የነዳጅ ማደያዎችን በማንደድ ፍንዳታዎችን ፈጠሩ። ውዥንብር ሰፈሩን ሲበላው ሌሊቱን እሳት አበራው። ወታደሮቹ ግራ ተጋብተውና ተቆርጠው ይደናበራሉ። ዞሮዎች፣ እየተቀናጁ እና እየተናበቡ፤ ከየአቅጣጫው እየገፉ፣ ፈጣን እና የማያቋርጥ ጥቃት መሰንዘር ጀመሩ።

እየነመራ ባለው እሳት፤ ድምፅ ማጉያዎች፣ የእምቢተኝነት እና የአሸናፊነት መልዕክቶችን አሰራጩ። ድምጾቹ በየጦር ሜዳው ተስተጋብተዋል፣ ይህም የአምባገነኑ ወታደሮች በቁጥር እንደሚበልጡና እንደተከበቡ ማሳሰቢያ ነበር። "መሳሪያዎቻችሁን በመጣል፣ እጆቻችሁን ስጡ !" ድምፁ ጮኸ።

"የምታመልጡበት ቦታ የለህም" የዞሳር አባላት ግን እየሆነ ያለውን ያውቁታልና ይሄ ድምጽ አላሸበራቸውም። ስፍራውን እያበራ፣ ሌሊቱን ወደ ቀን እየለወጠ፣ የእሳቱ ቃጠሎ ወደ ላይ መውጣቱን ቀጠለ። ለዞሳር አልሞ ተኳሾች፣ ብርሃኑ ኢላማቸውን የሚያጎላ ኢጋዥ ሆነ። ለአምባገነኑ ወታደሮች፣ እያንዳንዱን እንቅስቃሴያቸውን የሚያጋልጥ ቅዠት ነበር። አልሞ ተኳሾቹ በጫዋታው ሜዳ፤ ተጫዋቾች መሸፈኛ ለማግኘት ሲሯሯጡ እየለቀሙ ጣሏቸው።

⁘⁘⁘

ተመዘንህ፣ ቀለህም ተገኘህ። መንግሥትህ ተከፈለ። ማለት እንደሆነ ነገረቻት። ይህን ጽሁፍ ከፊት ላይ ያሉት በስክሪኑ ላይ የሚታዩት ወጣቶች ሁሉም ይዘውታል። ከሁሉም አቅጣጫ የተሰባሰቡት ወጣቶች ወደ መስቀል አደባባይ ማምራት ጀመሩ። ይህን ጊዜ ከታች የሚመጡትን ለም ሆቴል አከባቢ ጀምሮ እንዳያልፉ ጎን ለጎን በመሰለፍ የከተማው ፖሊሶች መንገዱን አጠሩት። በብሄራዊ ቴአትር ለሚመጡት ደግሞ ቴዎድሮስ አደባባይ፤ ከቦሌ አቅጣጫ ወደ መስቀል አደባባይ ለሚያቀኑት ኦሎምፒያ አደባባይ ላይ እና ታች እንዲሁም ግራና ቀኝ፤ ከመስቀል ፍላወር ወደ ኦሎምፒያ የሚወስደው መንገድ ጋዜቦ አደባባይ፤ ከጎተራ ለሚመጡ አጎና ሲኒማ፤ ከቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን የተነሱትን ለገሀር መብራት፤ ከሜክሲኮ ለሚመጡ ለገሀር መብራት፤ ከጌጃ ሰፈር አቅጣጫ ለሚመጡ ሰንጋተራ ትራፊክ መብራት ላይ፤ ከአምባሳደር ሲኒማ ለሚመጡ ሃራምቤ መብራት ላይ፤ የቤተ መንግሥት መንገድ፤ ከካዛንቺስ ወደ ባምቢስ የሚወስደው መንገድ፤ ከጆፒተር ሆቴል ወደ ECA ሚወስደው መንገድ በተመሳሳይ ታጠረ። ወጣቶቹ ግን ይህ አላገዳቸውም፤ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

እየተቀራረቡ በመምጣታቸው አድማ በታኞች ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ አስለቃሽ ጪስ ወደ ወጣቶቹ መተኮስ ጀመሩ። ወጣቶቹም ወደ እነሱ የሚተኮሰውን ጋስ መልሰው በመወርወር አጸፋውን መለሱ። ይህን ጊዜ ስፍራው በጪሱ ደመና ተከለለ። ወጣቱን አስቆጣው፤ የወጣቱም የተቃውሞ መንገድ ወደ ኃይል ተዘዋወረ፤ ፊት ለፊት በመሄድ ተጋፈጧቸው። የያዙትን ዱላ ሰነዘሩ፤ እየተቀበሉ እነሱኑ መቷቸው። መሳሪያ የያዙትም መተኮስ ጀመሩ። ከጪሱ ክብደት የተነሣ አርቆ ለመተያየት አዳጋች ነበር፤ በዚህም መሃል ወደ ወጣቱ በኃይል በሁለቱ አቅጣጫ ውሃ እየረጩ የመጡትን ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ጎንበስ ብለው በጪሱ ተከልለው የመጡ አምስት ወጣቶች ከላይ ወጥተው በብረት በመቀጥቀጥ

በሩን ለመክፈት ትግል ሲያደርጉ፤ ያም ሰው ከውስጥ ሆኖ በእልህ በሩን ከፍቶ አከታትሎ ተኮሰ። አንደኛው በያዘው ብረት እጁን መታው፤ መሳሪያውንም እንደጣለ ሲያረጋግጡ ጎትተው በማስወጣት፤ አቅጣጫውን አዙረው ወደ እነሱ መርጨትና መንገዱን ማስከፈት ጀመሩ።

በቁጥር ባለ መመጣጠናቸው የኃይል ሚዛኑ ወደ ወጣቶቹ በማድላቱ፤ ወታደሮቹም መተኮስ ጀመሩ። ከስፍራው የነበረ ወታደራዊ አዛዥ ኃይል እንዲጨመር ጥያቄ አቀረበ። የሚበዙቱ አልሞ ተኳሾች እንዲሆኑ ተደርጎ ኃይል ተጨመረ። ይህ መረጃ የደረሰው ዞሳርም እዚያው መሃል ባሉ ወታደራዊ አባላቶቹ ምክንያት አስለቃሽ ጪስ አብዝቶ እንዲተኮስ ተደረገ። ጪሱም አብዝቶ ስፍራውን አፈነው። ወጣቶቹ በውሃ በረጠበው ማስካቸው ምክንያትነት እንብዛም ጉዳት አልደረሰባቸውም ነበር። በዚህም ምክንያት አልሞ ተኳሾቹ ወደ ሕዝቡ መተኮስ ተሳናቸው። ወጣቶቹም በጠርሙስ የያዟቸውን ተቀጣጣይ ፈሳሾች እየለኮሱ ወረወሩ። አድማ በታኞችም መሸሽ ጀመሩ። በዚህ መልክ ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጡት ወጣቶች ወደ ፊት በመጠጋት ወረሯቸው። ለሁለተኛ ጊዜ የተላከው ተጨማሪ ኃይል በአብዮቱ አመራሮች ስለ ነበር የሚመራው ወደ ላይ ከመተኮስ ውጪ እንብዛም ጉዳት አላደረሰም ነበር። በዚህ መልኩ የቀጠለው ተቃውሞ ከሰዓታት ቆይታ በኋላ፤ መልኩን እና ይዘቱን እየቀየረ በመምጣቱ ጥይትም በመጨረሳቸውም፤ ማምለጫም እንደሌላቸው በማወቃቸው፤ እጅ ለመስጠት ተገደዱ። በዚህ መሃል የነበሩትን ወታደሮች ቦታ እያስለቀቁ፤ ቀይ ቦኔት ለባሽ የሆኑ ሠራዊቶች በአስር ፓትሮል ከነሙሉ ትጥቃቸው ወደ ቤተ መንግሥት አቅጣጫ ሲመጡ፤ ወጣቱ በከፍተኛ ፉጨት እና ጩኸት ተቀበላቸው። ሁሉንም በአከባቢው የነበሩ ወታደሮችን ትጥቅ

አስፈቷቸው። ሕዝብ ላይ እንዴት ትተኩሳላችሁ ብለው አንበረከኳቸው።

በቁጥር የሚበዛው ወጣት ግን አስቀድሞ ወደ ቤተ መንግሥት በማምራት ቤተ መንግሥቱን ከበው ነበር። ጠባቂዎቹም መሳሪያዎቻቸውን አቀባብለው በማነጣጠር ማስጠንቀቂያ መስጠት ጀመሩ። ጥቂቶች ፈርተው ቢያፈገፍጉም፤ ወጣቱ በሞቱ ሀገሩን ሊያቀና ቆርጦ ነበርና ወደ ፊት በአንድነት ሆነው ተጠጉ። መተኮስ ቢጀምሩም የሚበዙት እንደማያዋጣና ይሄን ሁሉ ወጣት ገድሎ መጨረስ እንደማይቻል ስለገባቸው መሸሽ እና እጅ መስጠት ጀመሩ። የተቀሩትን በመውረር እየደረሱባቸው መሳሪያዎቻቸውን በመቀበል አጥሩንም እየዘለሉ ገቡ።

ቤተ መንግሥት ጊቢ ውስጥ ከገቡም በኋላ፤ ለመነሳት እያኮበኮበ የነበረውን የአሜሪካን ስሪት Marine One, Sikorsky VH-3D Sea King helicopter ከማህላቸው አንደኛው የያዘውን ብረት በመወርወር ሮውተሩን ስለመታው ተሰባበረ፤ አንደኛው ፍንጣሪም ግንቡ ላይ ተሰካ። ናቡከደነጾር ክብ በሰሩ ዐሥራ ሁለት ቀይ ቦኔት ለባሾች መሃል ሆኖ ለዚህ ሁሉ የዳረጋችሁኝ እናንተው ናችሁ! አስቀድሜ ልውጣ ስላችሁ እዚሁ መሆን ይሻላል ያላችሁኝ፤ በሏቸው! እያለ በቁጣ ይወራጭ ነበር። እንደ ቀድሞዎቹ ይሄን ሁሉ ወጣት ገድለው መጨረስ እንደማይችሉ ተረድተዋልና የታጠቁትን መሳሪያ በማስቀመጥ እጆቻቸውን ወደ ላይ ሰቀሉ። ናቡከደነጾር መሳሪያ ከመሬት አንስቶ መጀመሪያ እጅ የሰጠው ወታደር ላይ አርከፈከፈበት።

ወጣቱም ወደ እሱ መሮጥ ጀመረ። እየተኮሰ ወደ ውስጥ ገብቶ ግዙፉን በር ቆለፈው። በሩንም ለመክፈት ቢታገሉ በእግራቸውም በትከሻቸውም ቢደበድቡት አልከፈት ስላለ፤ አንድ ልጆች በቅርብ የነበረን Humvee

በማስነሳት እየነዳ በሩን ሰብሮ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ናቡከደነጾርም እየተኮሰ በኮሊደሩ ወደ ውስጥ ቢሮጥም፤ ጥይት ግን አለቀበት።

‘’እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለ ሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኀጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና”

የፍጻሜው መጀመሪያ